አሌክሳንደር ፑሽኪን

# የኢቫን ፡ ቤልኪን ፡ ታሪኮች ።



አሌክሳንደር ፡ ፑሽኪን ። ከኪፕሬንስኪይ
የተሣለ ። (፲፰፻፳፯ ዓ. ም.)

# አሌክሳንደር፡ ፑሽኪን።

## ቅጽ፡አንድ።

## የኢቫን፡ቤልኪን፡ ታሪኮች።

## ዱብሮቭስኪይ።

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡
ማሳተሚያ ፡ ቤት ።
ሞስኮ ።

А. С. Пушкин

*Проза. Том I*

**Повести Белкина**

**Дубровский**

ተርጓሚው ፤ ዮሐንስ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ።

አንደኛው ፡ እትም ፤ ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. እ. ኤ. አ.

ሁለተኛው ፡ እትም ፤ ፲፱፻፸፰ ዓ. ም. እ. ኤ. አ.

© የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡
ቤት ፡ የአማርኛ ፡ ትርጉም ፡ እ. ኤ. አ. ፲፱፻፸፰ ዓ. ም.

በሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ታተመ ።

П $\frac{70301—829}{014(01)—78}$ 590—78

## ማውጫ ።


| | ገጽ ፡ |
| --- | --- |
| ያረፈው ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤልኪን ፡ የጻፋቸው ፡ ታሪኮች ። . . . . . . . . . . . | ፭ |
| ታሪኮቹን ፡ ከአዘጋጀውና ፡ ከአሳተመው ። . . | ፯ |
| ተኩስ ። . . . . . . . . . . . . . | ፲፫ |
| የበረዶ ፡ ውሽንፍር ። . . . . . . . . . | ፴፫ |
| የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪ ። . . . . . . . . . | ፶፬ |
| የማመላለሻ ፡ ጣቢያ ፡ ሹም ። . . . . . . | ፷፯ |
| ባላገር ፡ መሳይ ፡ እመቤት ። . . . . . . | ፹፯ |
| ዱብሮቭስኪይ ። . . . . . . . . . . . . . | ፻፲፯ |
| መግለጫ ። . . . . . . . . . . . . . . | ፪፻፴፯ |

# የሩሲው፡
# ኢቫን፡ፔትሮቪች፡
# ቤልኪን፡
# የጻፋቸው፡
# ታሪኮች።

## ታሪኰቹን ፡ ከአዘጋጀውና ፡ ከአሳተመው ።

ወይዘሮ ፡ ፕሮስታኰቫ ፤
— ውድ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ! ልጄ ፡ ከሕፃንነቱ ፡
ጀምሮ ፡ ታሪክ ፡ መስማት ፡ ይወድ ፡ ነበር ።

ስኰቲኒን ፤
— ሚትሮፋን ፡ እኔን ፡ ይመስላል ።

ጥራዝ ፡ ነጠቅ ።

የኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤልኪንን ፡ ታሪኰች ፡ አሳትመን ፡ ለአንባቢዎች ፡ ከአቀረብን ፡ በኋላ ፡ ስለሟቹ ፡ ደራሲ ፡ አጭር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ መቅድም ፡ በመጻፍ ፡ የሃገራችንን ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ለማወቅ ፡ ያላቸውን ፡ ተገቢ ፡ ፍላጐት ፡ በከፊል ፡ እናረካለን ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤልኪን ፡ ቅርብ ፡ ዘመድና ፡ ወራሽ ፡ የሆነችውን ፡ ማሪያ ፡ አሌክሲየቭና ፡ ትራፊሊናን ፡ ጠየቅናት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሟቹን ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ አታውቀውም ፡ ነበርና ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መረጃ ፡ ልትሰጠን ፡ አልቻለችም ። ሆኖም ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ወዳጅ ፡ የሆነን ፡ አንድ ፡ የተከበረ ፡ ሰው ፡ እንድንጠይቅ ፡ መከረችን ። ምክሯን ፡ ተቀብለን ፡ ብንጠይቅም ፡ ለደብዳቤአችን ፡ ጥያቄ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ተስማሚ ፡ መልስ ፡ አገኘን ። ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ለረቀቀ ፡ አስተዋይነትና ፡ ለልባዊ ፡ ወዳጅነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሐውልት ፡ ስለሆነና ፡ ወዲያውም ፡

ፍጹም ፡ አጥጋቢ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ መግለጫ ፡ ስለሆነ ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ሳንለውጥ ፡ እንዳለ ፡ እናትመዋለን ።

ክቡር ፡ ሆይ ፤

በዚህ ፡ ወር ፡ በአስራምስተኛው ፡ ቀን ፡ የጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ በዚሁ ፡ ወር ፡ በሃያ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ደርሶኛል ። በዚሁ ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ እንደገለጹልኝ ፡ የልብ ፡ ወዳጄና ፡ የባላገር ፡ ጐረቤቴ ፡ ስለነበረው ፡ ስለኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ትውልድና ፡ ሞት ፤ ስለአገልግሎቱና ፡ ስለሕይወቱ ፤ ስለ ፡ ሥራውና ፡ ስለጠባዩ ፡ ዝርዝር ፡ መረጃ ፡ እንድሰጥዎት ፡ ያለዎትን ፡ ፍላጐት ፡ ገልጸውልኛል ። ክቡር ፡ ሆይ ፤ ይህን ፡ ፍላጐትዎን ፡ ለማርካት ፡ ጥልቅ ፡ ደስታ ፡ እየተሰማኝ ፡ የማስታውሰውን ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያደረግነውን ፡ ጨዋታ ፡ ሁሉና ፡ የራሴንም ፡ የግል ፡ አስተያየት ፡ ጨምሬ ፡ እልክልዎታለሁ ።

ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ከአንድ ፡ የተከበረ ፡ ቤተሰብ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፯፻፺፰ ዓ ፡ ም ፡ በጐሪውኺኖ ፡ መንደር ፡ ተወለደ ። ሟቹ ፡ አባቱም ፡ ምክትል ፡ የሺ ፡ አለቃ ፡ ፒዮትር ፡ ኢቫኖቪች ፡ ቤልኪን ፡ ከትራፊሊን ፡ ቤተሰብ ፡ የምትወለድ ፡ ፔላጌያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ አገባ ። ሃብታም ፡ አልነበረም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ ቆጣቢና ፡ የዕለት ፡ ተግባሩን ፡ ማስተዳደር ፡ አሳምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ልጁ ፡ በሕጻንነቱ ፡ ትምህርት ፡ የተቀበለው ፡ ከደብር ፡ አለቃው ፡ ጸሐፊ ፡ ነበር ። ይህ ፡ መምህሩ ፡ ንባብ ፡ እንዲወድና ፡ በሃገሩ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲጽፍ ፡ አደረገው ። እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፰፻፲፭ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ የምድር ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍል ፡ (ቁጥሩን ፡ እረሳሁት ፡) ገብቶ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፳፫ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ቆየ ። ቤተዘመዶቹ ፡ ተከታትለው ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ስለሞቱበት ፡ የስንብት ፡ ደብዳቤ ፡ አስገብቶ ፡ በጐሪውኺኖ ፡ የትውልድ ፡ መንደሩ ፡ በሚገኘው ፡ የወረሰው ፡ እርስት ፡ ላይ ፡ ሄዶ ፡ መኖር ፡ ግድ ፡ ሆነበት ።

ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ እርስቱን ፡ ማስተዳደር ፡ ሲጀምር ፡ ልማድ ፡ ስላልነበረውና ፡ ገራገር ፡ ስለነበር ፤ ንብረቱ ፡ እንዲወድቅ ፡ አደረገ ፤ ሟቹ ፡ አባቱ ፡ ይከተለው ፡ የነበረውን ፡ ጥብቅ ፡ ስርዓትም ፡ አላላው ። ገበሬዎቹ ፡ የማይወዱትን ፡ (ልማዳቸው ፡ ነው ፡) ብልሁንና ፡ ቀልጣፋውን ፡ የመንደር ፡ ሽማግሌ ፡ አሰናብቶ ፡ ታሪክ ፡ በመተረክ ፡ ብልህነቷ ፡ ታማኝ ፡ ለመሆን ፡ የቻለችውን ፡ የቀድሞ ፡ የቤት ፡ ጠባቂውን ፡ የመንደሩ ፡ አስተዳዳሪ ፡ አደረጋት ። ይህች ፡ በቀላሉ ፡ የምትታለል ፡ አሮጊት ፡ የሃያ ፡ አምስት ፡ ሩብል ፡ ወረቀት ፡ ከአምሳ ፡ ሩብል ፡ ወረቀት ፡ ለመለየት ፡ አትችልም ፡ ነበር ። የአብዛኞቹ ፡ ገበሬዎች ፡ ልጆች ፡ የክርስትና ፡ እናት ፡ በመሆንዋም ፡ ገበሬዎቹ ፡ አይፈሯትም ፡ ነበር ። ገበሬዎቹ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ተባብራ ፡ ጌታቸውን ፡ እንድታታልልና ፡ እንደልብ ፡ እንድትይዛቸው ፡ ይህቺን ፡ አሮጊት ፡ ሴት ፡ መረጡ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ጥንት ፡ ሲሰራበት ፡ የቆየውን ፡ ልማድ ፡ ትቶ ፡ አዲስ ፡ ደንብ ፡ አወጣ ። ይሄውም ፡ ሆኖ ፡ ገበሬዎቹ ፡ በጌታቸው ፡ ደካማነት ፡ በመጠቀም ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆነ ፡ ውለታ ፡ በዘዴ ፡ ለማግኘት ፡ ቻሉ ። በሚቀጥለው ፡ ዓመትም ፡ ግብራቸውን ፡ ከሦስት ፡ እጅ ፡ ሁለቱን ፡ በኖቼሊንና ፡ በእንጆሪ ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ ነገር ፡ ከፈሉ ። እዚህም ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ አጭበርብረዋል ።

የኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ አባት ፡ የቀድሞ ፡ ወዳጅ ፡ እንደመሆኔ ፡ መጠን ፡ ለልጁ ፡ ምክር ፡ መስጠት ፡ ተግባሬ ፡ ሆኖ ፡ ተሰማኝ ። ልጁ ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ለማቋቋም ፡ ያልቻለውን ፡ የቀድሞውን ፡ ደንብና ፡ ስርዓት ፡ እንደወትሮው ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኔን ፡ ገልጬ ፡ ነበር ። ለዚሁ ፡ ስል ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ልጠይቀው ፡ ሄድኩና ፡ የሂሳብ ፡ መዝገቡን ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ጠየቅሁ ፤ አሮጊትዋን ፡ ወስላታም ፡ አስጠራሁና ፡ በኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ፊት ፡ መመርመር ፡ ጀመርኩ ።

ወጣቱ ፡ ባለቤት ፡ መጀመሪያ ፡ ምርመራዬን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጥን
ቃቄና ፡ በትጉህነት ፡ ተከተለ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ባለፉት ፡ ሁለት ፡
ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የገበሬዎቹ ፡ ቁጥር ፡ መበርከቱንና ፡ የዶሮ
ዎችና ፡ የከብቶች ፡ ቁጥር ፡ ግን ፡ ማነሱን ፡ ሂሳቡ ፡ ሲያሳይ ፤
ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ በዚህ ፡ በመጀመሪያው ፡ ምርመራ ፡ ብቻ ፡
በቃኝ ፡ ብሎ ፡ ሌላውን ፡ ለመስማት ፡ ሳይፈልግ ፡ ቀረ ። ቀጣሬ
ዋን ፡ አሮጊት ፡ በምርመራዬና ፡ በጥብቅ ፡ ጥያቄዬ ፡ ፍጹም ፡
ግራ ፡ ሳገባትና ፡ ጭጭ ፡ ሳሰኛት ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ እወን
በሩ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ሲያኰርፍ ፡ በሰማሁት ፡ ጊዜ ፡ አለቅ
ጥ ፡ ነደደኝ ። ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮም ፡ በርስቱ ፡ አስተዳደር ፡
ውስጥ ፡ ጣልቃ ፡ መግባቱን ፡ ትቼ ፡ ጉዳዩን ፡ (እርሱ ፡ እራሱ ፡
እንደሚያደርገው ፡ ) ለእግዜር ፡ ተውኩለት ።

ሆኖም ፡ ወዳጅነታችን ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከቶ ፡ አልተና
ካም ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ በወጣት ፡ ጨዋዎች ፡ ላይ ፡
የሚታየውን ፡ ደካማነትና ፡ አደገኛ ፡ ቸልተኝነት ፡ ብነቅፍም ፡
ኢቫን ፡ ፔትሮቪችን ፡ ከልብ ፡ እወደው ፡ ነበር ። በውነቱ ፡ እን
ደዚህ ፡ ያለ ፡ ደግና ፡ ተከባሪ ፡ ወጣት ፡ የሚወደድ ፡ ነው ። ኢቫን ፡
ፔትሮቪችም ፡ ለዕድሜዬ ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ክብር ፡ ሰጠ
ኝ ፤ ይወደኝም ፡ ነበር ። እስከመጨረሻው ፡ ድረስም ፡ በየቀኑ ፡
እንገናኝ ፡ ነበር ፤ ምክንያቱም ፡ አስደሳች ፡ ጨዋታዬን ፡ ይናፍ
ቅ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ነው ። ሆኖም ፡ በልማዳችንና ፡ በአስተሳሰባችን ፡
እንዲሁም ፡ በጠባያችን ፡ እምብዛም ፡ አንመሳሰልም ፡ ነበር ።

ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ የሚወደው ፡
በመጠኑ ፡ ነበር ፤ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ከሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይርቅ ፡
ነበር ። ብዙ ፡ ሲጠጣ ፡ አይቼው ፡ አላውቅም ፡ (ለእኛ ፡ ይሄ ፡
ተአምር ፡ ነው ፡ ) ። ነገር ፡ ግን ፡ የሴት ፡ ነገር ፡ አይሆንለትም ፡
ነበር ። ሆኖም ፡ እርሱም ፡ እራሱ ፡ እንደልጃገረድ ፡ አፋር ፡ ነ
በር ። *

---

* ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ አንድ ፡ ቀልድ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ትርፍ ፡ ነ

በደብዳቤው ፡ ላይ ፡ ከጠቀሱት ፡ ታሪክ ፡ ሌላ ፡ ኢቫን ፡ ፔ ትሮቪች ፡ አያሌ ፡ እረቂቅ ፡ ጽሑፎች ፡ ትቷል ፤ አንዳንዶቹም ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡ ይገኛሉ ፤ ሌሎቹንም ፡ ቤት ፡ ጠባቂዋ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የቤት ፡ አገልግሎት ፡ አውላዋለች ። ለምሳሌ ፡ ባለፈው ፡ ክረምት ፡ መስኮቶቹ ፡ ሁሉ ፡ የተለጠፉት ፡ ገና ፡ ባልጨረሰው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ ነበር ። ባልሳሳት ፡ እላይ ፡ የጠቀስኳቸው ፡ ታሪኮች ፡ የሟቹ ፡ የመጀመሪያ ፡ የድ ርሰት ፡ ሙከራዎቹ ፡ ናቸው ። ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ እንደሚለ ው ፡ አብዛኞቹ ፡ ዕውነት ፡ ናቸው ፤ የነገሩትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎ ች ፡ ናቸው ። * የሰዎቹ ፡ ስሞች ፡ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ ልብ ፡ ወለ ድ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። የመንደሮቹ ፡ ስም ፡ ግን ፡ ከ እኛ ፡ ቀበሌ ፡ የተቀዳ ፡ ነው ። የኔም ፡ መንደር ፡ ከሌሎቹ ፡ ጋ ር ፡ አብሮ ፡ ተጠቅሷል ። ይሄውም ፡ ለክፋት ፡ ሳይሆን ፡ በየዋ ኸነት ፡ ነው ።

እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፯፻፺፯ ዓ ፡ ም ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮቪችን ፡ ከ

---

ው ፡ በማለት ፡ ዘለነዋል ። ሆኖም ፡ የኢቫን ፡ ፔትሮቪችን ፡ ስ ም ፡ የማያጠፋ ፡ መሆኑን ፡ ለአንባቢዎች ፡ እናረጋግጣለን ።

* በኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤልኪን ፡ እረቂቅ ፡ ጽሑፍ ፡ በያን ዳንዱ ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ደራሲው ፡ እራሱ ፡ የጻፈው ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ነበር ፤ «የነገረኝ ፡ እገሌ ፡ ነው ፡ (ማዕርግ ፡ ወ ይም ፡ ሹመት ፡ እንዲሁም ፡ የስም ፡ መጀመሪያ ፡ ) ። ለምሳሌ ፡ ያሀል ፤ የማወቅ ፡ ፍላጎት ፡ ላላቸው ፡ የሚቀጥለውን ፡ እንጠቅ ሳለን ። «የማመላለሻ ፡ ጣቢያ ፡ ሹምን ፡» ታሪክ ፡ የነገረኝ ፡ አማካሪው ፡ አ. ገ. ነ. ፡ ነው ። «ተኩስን ፡» የነገረኝ ፡ ኰሎኔ ል ፡ አ. ኤል. ፒ. ፡ ነው ። «የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪን ፡» የነገረኝ ፡ በ. ቨ. ፡ የተባለ ፡ የሱቅ ፡ እረዳት ፡ ነው ። «የበረዶ ፡ ውሽንፍ ር ፡» ና ፡ «ባላገር ፡ መሳይ ፡ እመቤትን ፡» የነገረችኝ ፡ ከ. ኢ. ተ. ፡ የተባለች ፡ ወጣት ፡ ሴት ፡ ናት ።

ባድ ፡ ጉንፋን ፡ ያዘው ፤ ወደ ፡ ኃይለኛ ፡ ትኩሳትም ፡ ተለወጠ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሰፈሩ ፡ ሐኪም ፡ ሊያድነው ፡ ከልብ ፡ ቢጣጣርም ፤ ሞተ ። ሐኪሙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበር ። በተለይም ፡ እንደ ፡ የግር ፡ ጣት ፡ ቁስል ፡ ያለና ፡ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቆየ ፡ ሕመም ፡ አክሞ ፡ የሚያድን ፡ ነበር ። ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ በሰላሳ ፡ ዓመቱ ፤ እኔ ፡ እንዳቀፍኩት ፡ ሞቶ ፡ በጐሪውኺኖ ፡ ቤተክርስትያን ፡ የመቃብር ፡ ቦታ ፡ ከቤተሰቦቹ ፡ ጐን ፡ ተቀበረ ።

ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ቁመቱ ፡ መጠነኛ ፤ ዓይኖቹ ፡ ግራጫ ፤ ጸጉሩ ፡ ነጣ ፡ ያለ ፤ አፍንጫው ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ቆዳውም ፡ ነጣ ፡ ያለና ፡ ሰውነቱም ፡ ቀጠን ፡ ያለ ፡ ነበር ።

ክቡር ፡ ሆይ! ስለሚቹ ፡ ወዳጄና ፡ ጐረቤቴ ፡ ሥራና ፡ ጠባይ ፤ እንዲሁም ፡ መልክ ፡ የማስታውሰው ፡ ይሄው ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ደብዳቤዬ ፡ የሚጠቅም ፡ ሆኖ ፡ ቢያገኙት ፡ ስሜን ፡ እንዳይጠቅሱ ፡ እለምንዎታለሁ ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ለደራሲዎች ፡ ታላቅ ፡ አክብሮትና ፡ ፍቅር ፡ ቢኖረኝም ፡ እኔ ፡ እራሴ ፡ እነሱን ፡ መስዬ ፡ ለመታየት ፡ ፍላጐት ፡ የለኝም ። ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ ዕድሜዬን ፡ ሲገመቱት ፡ ለዚህ ፡ ተገቢ ፡ ሆኜ ፡ አልገኝም ።

ፍጹም ፡ አክባሪዎ …

ኅዳር ፡ ፲፮ ፡ ፲፰፻፴ ።
የኔናራዶቮ ፡ መንደር ።

የደራሲያችንን ፡ ወዳጅ ፡ ፍላጐት ፡ ማክበር ፡ ግዴታችን ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፤ ለሰጠን ፡ መረጃ ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጋናችንን ፡ እናቀርባለን ፤ አንባቢዎቻችንም ፡ በቅንነትና ፡ በግልጽ ፡ ያበረከተውን ፡ መግለጫ ፡ እንደሚወዱልን ፡ እናምናለን ።

አ ፡ ፑ ።

# ተ ኩ ስ ።

ዱዌል ፡ ተታኩሰን ።

ባራቲንስኪይ ።

በዱዌል ፡ ተኩስ ፡ እገድለዋለሁ ፡
ብዬ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባሁ ።

ምሽት ፡ በጦር ፡ ሰፈር ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

የሰፈርነው ፡ ስሟ ፡ በማይነሳ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። የጦር ፡ ሠራዊት ፡ መኰንን ፡ ኑሮ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሆነ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የሚያውቀው ፡ ነው ። ጧት ፡ የሰውነት ፡ ማጠንከሪያ ፡ ልምምድና ፡ የፈረስ ፡ ግልቢያ ፡ እናደርጋለን ፤ ምሳችንን ፡ በክፍለ ፡ ጦር ፡ አዛዦችን ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ የአይሁድ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ እንበላለን ፤ ማታ ፡ አረቂ ፡ እየጠጣን ፡ ካርታ ፡ እንጫወታለን ። በከተማዋ ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ እቤቱ ፡ የሚያስገባን ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፤ ለጋብቻ ፡ የምትሆን ፡ ልጃገረድም ፡ ከቶ ፡ አትገኝም ፡ ነበር ። በየሠፈራችን ፡ አንድነት ፡ እንሰበሰብ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ ከያንዳንዳችን ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የምናየው ፡ ነገር ፡ አልነበረም ።

ከእኛ ፡ ውስጥ ፡ ወታደር ፡ ያልሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ዕድሜው ፡ ወደ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ነበር ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ እንቆጥረው ፡ ነበር ። የኑሮ ፡ ልማድ ፡ ስለነበረውም ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ብልጫነትን ፡ ለመያዝ ፡ ቻለ ፤ ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ፊቱ ፡ ዘወትር ፡ ጨፍጋ

ጋና ፡ ጠባዩም ፡ ኰስታራ ፤ ምላሱም ፡ ምላጭ ፡ ስለነበር ፡ የወ
ጣት ፡ አዕምሮአችንን ፡ ማርኰት ፡ ነበር ። ሰውየው ፡ በምስጢ
ር ፡ ብልኰ ፡ የተሸፋፈነ ፡ ነው ። መስኰባዊ ፡ ይመስላል ፡ ዳሩ ፡
ግን ፡ ስሙ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ስም ፡ ነው ። ካሁን ፡ በፊት ፡ በፈ
ረስ ፡ ዘበኛነት ፡ አገልግሎ ፡ ነበር ፤ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ለመሆን
ም ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ ነበረው ። ከመኰንንነቱ ፡ ለምን ፡
እንደተሰናበተና ፡ በአንድ ፡ ትንሽ ፡ ችጋራም ፡ ከተማ ፡ ውስ
ጥ ፡ ለመኖር ፡ እንዴት ፡ እንደወሰነ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አያውቅ
ም ። ኑሮው ፡ የድህነት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ለጋስ ፡ ነበር ።
ያለቀ ፡ ጥቁር ፡ ኰት ፡ ለብሶ ፡ በእግሩ ፡ ይሄዳል ፤ ሆኖም ፡
ቤቱ ፡ ዘወትር ፡ ለመኰንኖች ፡ ክፍት ፡ ነው ። እርግ
ጥ ፡ ነው ፡ ምሳው ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ ምግብ ፡
ነበር ፤ የሚያዘጋጅለትም ፡ አንድ ፡ የዱሮ ፡ ወታደር ፡ ነበር ፤
ሆኖም ፡ ሻምፓኝ ፡ ሳያቋርጥ ፡ በገበታው ፡ ላይ ፡ ይፈስ ፡ ነበ
ር ። ሀብቱ ፡ ወይም ፡ ገቢው ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ማንም ፡
ሰው ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለመጠየቅም ፡
አንድም ፡ የደፈረ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። አያሌ ፡ መጻሕፍትም ፡
ነበሩት ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ ወታደር ፡ ነክና ፡
ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪኮች ፡ ነበሩ ። መጽሐፎቹን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡
ለማዋስም ፡ ዘወትር ፡ ዝግጁ ፡ ነበር ። ከአዋሰም ፡ እንዲመለ
ስለት ፡ ከቶ ፡ አይጠይቅም ፡ ነበር ። እሱም ፡ በበኩሉ ፡ መጽሐ
ፍ ፡ ከተዋሰ ፡ ለባለቤቱ ፡ ከቶ ፡ መልሶ ፡ አይሰጥም ፡ ነበር ። ዋና ፡
ተግባሩም ፡ ሽጉጥ ፡ መተኰስ ፡ ነበር ። የክፍሉ ፡ ግድግዳዎች ፡
በጥይት ፡ ከመበሳሳታቸው ፡ የተነሳ ፡ የማር ፡ እንጀራ ፡ ይመስ
ሉ ፡ ነበር ። በሚኖርበት ፡ ቆርማዳ ፡ የሸክላ ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡
የሚታየው ፡ የከበረ ፡ ዕቃ ፡ ያከማቸው ፡ ሽጉጥ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።
በተኩስ ፡ ረገድ ፡ የነበረውም ፡ ችሎታ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር ።
በአንድ ፡ ሰው ፡ ቆብ ፡ ላይ ፡ ፖም ፡ አስቀምጦ ፡ ለይቶ ፡ ለመ
ምታት ፡ ባሳሰበ ፡ ጊዜ ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ እራሱን ፡ የማያቀር

ብለት ፡ ከክፍለ ፡ ጦራችን ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አልነበ ረም ። ጨዋታችን ፡ ዘወትር ፡ ስለ ፡ ዱዌል ፡ ነበር ፤ ሲልቪዎ ፡ ግን ፡ (ሲልቪዎ ፡ ልበለው ፡) በጨዋታው ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ዱዌል ፡ ተታኩሶ ፡ ያውቅ ፡ እንደሆ ን ፡ በተጠየቀም ፡ ጊዜ ፡ ተታኩሻለሁ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ ዝርዝር ፡ ሳይገባ ፡ በአጭሩ ፡ ይመልሳል ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጥያቄ ፡ እን ደማያስደስተውም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። እኛም ፡ በዚህ ፡ በሚያስደንቅ ፡ የተኩስ ፡ ችሎታው ፡ የጠፋ ፡ ሕሊናውን ፡ የሚ ከነክነው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ብለን ፡ ቆረጥን ። በልቡም ፡ አንዳችም ፡ ፍርሃት ፡ አለ ፡ ብለን ፡ አልጠረጠርንም ፡ ነበር ። መልካቸው ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ጥርጣሬ ፡ የሚያስወግ ድ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሁላችንንም ፡ በድን ገት ፡ ያስደነቀ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ተፈጠረ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አስር ፡ መኰንኖች ፡ ሆነን ፡ በሲልቪዎ ፡ ቤት ፡ ምሳ ፡ እንበላ ፡ ነበር ። የተለመደውን ፡ ያ ህልም ፡ ጠጣን ፤ ማለት ፡ ብዙ ፡ ጠጣን ። ከምሳ ፡ በኋላም ፡ ጋባ ዣቻችን ፡ ገንዘብ ፡ ያዥ ፡ እንዲሆን ፡ ጠየቅነው ። ካርታ ፡ አዘው ትሮ ፡ ስለማይጫወትም ፡ መጀመሪያ ፡ እምቢ ፡ አለ ። በመጨ ረሻ ፡ ግን ፡ ካርታ ፡ እንዲቀርብ ፡ አዘዘ ፤ ሃምሳ ፡ የባለ ፡ አስር ፡ ሩብል ፡ ወረቀትም ፡ እጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ በተነና ፡ ካርታ ፡ ማደ ል ፡ ጀመረ ። ሁላችንም ፡ ከበብነው ፤ ጨዋታውም ፡ ተጀመረ ። ሲልቪዎ ፡ ካርታ ፡ በሚጫወትበት ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ጸጥ ፡ ማለ ት ፡ ልማዱ ፡ ነው ፤ አይከራከርም ፡ ማስረጃም ፡ አይሰጥም ። ተጫዋቹ ፡ ስህተት ፡ ያደረገ ፡ እንደሆን ፡ ሲልቪዎ ፡ ወዲያው ፡ ያስከፍላል ፡ ወይም ፡ ሂሳቡን ፡ ይጽፋል ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ አጥርተን ፡ እናውቅ ፡ ስለነበር ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ እንዲፈጽም ፡ ፈቀድንለት ። ነገር ፡ ግን ፡ ከእኛ ፡ መካከል ፡ በቅ ርብ ፡ ጊዜ ፡ የተዛወረ ፡ አንድ ፡ መኰንን ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰው ፡ ካርታ ፡ ሲጫወት ፡ ሳለ ፡ ሳያውቀው ፡ ክርክር ፡ አነሳ ። ሲል

ቪዎ ፡ ጠመኔ ፡ አንስቶ ፡ ድምሩን ፡ እርሱ ፡ እንደመሰለው ፡ ጻ
ፈ ። መኰንኑም ፡ ሲልቪዎ ፡ ስህተት ፡ ያደረገ ፡ ስለመሰለው ፡
ማስረዳት ፡ ጀመረ ። ሲልቪዎ ፡ ግን ፡ ጨዋታውን ፡ በጸጥታ ፡
ቀጠለ ። መኰንኑም ፡ ትዕግሥቱ ፡ ስላለቀ ፡ ብሩሹን ፡ አንስቶ ፡
በስህተት ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የገመተውን ፡ አጠፋው ።
ሲልቪዎም ፡ ጠመኔውን ፡ አንስቶ ፡ እንደገና ፡ ቁጥሩን ፡ ጻፈ ።
መኰንኑም ፡ ከወይኑና ፡ ከቊማሩ ፡ ጨዋታ ፡ ሞቅታና ፡ እን
ዲሁም ፡ ከጓደኞቹ ፡ ሳቅ ፡ የተነሳ ፡ ውርደቱን ፡ የሞት ፡ ሞት ፡
ያህል ፡ ስለቆጠረው ፡ የነሐስ ፡ የሻማ ፡ መስኪያ ፡ ከጠረጴዛ
ው ፡ ላይ ፡ አንስቶ ፡ ወደ ፡ ሲልቪዎ ፡ አውዘገዘገው ። ሲልቪዎ ፡
ግን ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ሊድን ፡ ቻለ ። በነገሩ ፡ እጅግ ፡ በ
ጣም ፡ ደነገጥን ። ሲልቪዎም ፡ በንዴት ፡ ደሙ ፡ ምጥጥ ፡ ብ
ሎ ፡ ዓይኖቹም ፡ እየተንቀለቀሉ ፡ ብድግ ፡ አለና ፤ «ሰማህ ፡
ጌታዬ ፤ በል ፡ ቀስ ፡ ብለህ ፡ ውጣ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ እኔ ፡ ቤት ፡
በመደረጉም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግን ፡ » አለው ።

የጠቡ ፡ ውጤት ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ስላወቅን ፡ አዲሱ
ን ፡ ጓደኛችንን ፡ እንደሞተ ፡ ሰው ፡ ያህል ፡ ቆጠርነው ። መኰ
ንኑም ፡ ገንዘብ ፡ ያዡ ፡ ሰውዬ ፡ በተመቸው ፡ ሰዓት ፡ ውር
ደቱን ፡ ለመበቀል ፡ ዝግጁ ፡ መሆኑን ፡ አስታውቆ ፡ ወጣ ።
ለጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ቀጠለ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ጋባዦችን ፡ በሙ
ሉ ፡ ልቡ ፡ የካርታ ፡ ጨዋታውን ፡ እንደማይከተል ፡ ሁላችን
ም ፡ ስለተሰማን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየተነሳን ፡ ወደየሠፈራች
ን ፡ ሄድን ፤ እግረ ፡ መንገዳችንንም ፡ ስለወደፊቱ ፡ አዲስ ፡ ክፍ
ት ፡ ቦታ ፡ ተጨዋወትን ።

በማግሥቱ ፡ በፈረስ ፡ ግልቢያ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ምስኪ
ኑ ፡ የሙቶ ፡ አለቃ ፡ በሕይወት ፡ ለመኖሩ ፡ ስንጠያየቅ ፡ ሳለ ፡
በድንገት ፡ መጥቶ ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ተቀላቀለ ። ይህንኑ ፡ ጥያቄ
ም ፡ አቀረብንለት ። ከሲልቪዎ ፡ ዘንድ ፡ ገና ፡ መልስ ፡ እንዳላ
ገኘም ፡ ገለጸልን ። ነገሩ ፡ አስደነቀን ። ወደ ፡ ሲልቪዎ ፡ ቤት ፡



ፑሽኪን ፡ በ፲፫ ዓመት ፡ ዕድሜው ።





ሰርጌይ ፡ ፑሽኪን ፡ የባለቅኔው ፡ አባት
( ፲፯፻፷፪ — ፲፰፻፵ ዓ ም ) ።



የባለቅኔው ፡ እናት ፡ ናደዥዳ ፡ ጋኒባል
( ፲፯፻፷፯ — ፲፰፻፳፰ ዓ. ም. )

ስንሄድም ፡ ባጥር ፡ ግቢው ፡ በር ፡ ላይ ፡ በተሰካ ፡ የባለ ፡ አንድ ፡ ቁጥር ፡ ካርታ ፡ እምብርት ፡ ላይ ፡ እያከታተለ ፡ ሲተኩስ ፡ አገኘነው ። በተለመደው ፡ ጠባዩ ፡ ስለ ፡ አለፈው ፡ ቀን ፡ ሁናቴ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ሳያነሳ ፡ ተቀበለን ። ሦስት ፡ ቀኖች ፡ አለፉ ፤ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ላይ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። ምና ልባት ፡ ሲልቪዎ ፡ መታኰስ ፡ አልፈለገ ፡ ይሆን? ስንል ፡ በመደነቅ ፡ ተጠያየቅን ። ሲልቪዎ ፡ ሳይታኰስ ፡ ቀረ ። አነስተኛ ፡ ይቅርታ ፡ ተቀብሎም ፡ ከመቶ ፡ አለቃው ፡ ጋር ፡ ታረቀ ።

ይህ ፡ ሁናቴ ፡ በወጣቶቹ ፡ መኰንኖች ፡ ዘንድ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ባስገመተው ፡ ነበር ። ጉብዝና ፡ የማያሳይ ፡ ሰው ፡ በወጣቶች ፡ ዘንድ ፡ ምህረት ፡ የማይደረግለት ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ወጣቶች ፡ ጉብዝናን ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ሙያ ፡ ይቆጥሩታል ፤ ምክንያቱም ፡ ብዙውን ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ስለሚያስተሰርይላቸው ፡ ነው ። የሆን ፡ ሆኖ ፡ ነገሩ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ጨርሶ ፡ ተረሳ ፤ ሲልቪዎም ፡ የቀድሞ ፡ የተከባሪነት ፡ ቦታውን ፡ ያዘ ።

እኔ ፡ ብቻ ፡ ግን ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ያለኝ ፡ ስሜት ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ ሊሆን ፡ አልቻለም ። በተፈጥሮዬ ፡ የጀግንነት ፡ ዓይነ ፡ ሕሊና ፡ ስለነበረኝ ፡ ሕይወቱ ፡ እረቂቅ ፡ ለሆነው ፡ ለዚህ ፡ ሰውዬ ፡ የነበረኝ ፡ አድንቆት ፡ ከሌሎቹ ፡ የበለጠ ፡ ነበር ፤ ያንድ ፡ ምሥጢራዊ ፡ ታሪክ ፡ ጀግና ፡ አድርጌም ፡ እመለከተው ፡ ነበር ። እሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ለእኔ ፡ አፍቅሮት ፡ ነበረው ። የሆን ፡ ሆኖ ፡ በተለመደው ፡ የሽሙጥ ፡ ቃሉ ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ ስለማይነካኝ ፡ ስለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ በቅንነትና ፡ በሚያስደስት ፡ ለዛ ፡ እንጨዋወት ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ በዚያን ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ያየሁት ፡ የሚያሳዝን ፡ ሁናቴ ፡ ትዝታና ፡ እሱም ፡ በክብሩ ፡ ላይ ፡ የተላከከበትን ፡ ዕድፍ ፡ በፈቃዱ ፡ አጥቦ ፡ ባለማስለቀቁ ፡ ነገሩን ፡ ልረሳው ፡ አልቻልኩም ፤ ለርሱ ፡ ያለኝ ፡ ስሜትም ፡ እንደወትሮው ፡ ሊሆን ፡ አልቻለም ። ዓይኑን ፡ ለማየትም ፡ አፍር ፡

ነበር ። ሲልቪዎም ፡ በጣም ፡ ብልጥና ፡ ሕይወትንም ፡ ያየ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ የኔን ፡ ስሜት ፡ መለወጥ ፡ ለመመልከትና ፡ ምክንያቱንም ፡ ለማወቅ ፡ ቻለ ። ነገሩ ፡ አሳዘነው ፤ ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ከአንድ ፡ ጊዜም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ የልቡን ፡ ሊያጫውተኝ ፡ ሲቃጣ ፡ ተመለከትኩ ። እኔ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ስለራቅሁ ፡ ሲልቪዎም ፡ ተወኝ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ከሲልቪዎ ፡ ጋር ፡ የምንገናኘው ፡ ከጓደኞቼ ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ ሆነን ፡ ነበር ፤ የቀድሞ ፡ የልብ ፡ ጭውውታችንም ፡ ቆመ ።

የተቀማጠሉ ፡ የታላላቅ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪዎች ፡ የገጠርን ፡ ወይም ፡ የታናናሽ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪዎችን ፡ አንዳንድ ፡ ደስታ ፡ ሊገነዘቡ ፡ አይችሉም ፤ ለምሳሌ ፡ ፖስታ ፡ የሚመጣበትን ፡ ቀን ፡ ሲጠብቁ ። ለምሳሌ ፡ ዘወትር ፡ ማክሰኞና ፡ አርብ ፡ በክፍለ ፡ ጦር ፡ ዋና ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በብዙ ፡ የሚቆጠሩ ፡ መኰንኖች ፡ ይሰበሰባሉ ። አንዳንዶቹ ፡ የሚላክላቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመቀበል ፡ ነው ፤ አንዳንዶቹም ፡ ደብዳቤ ፤ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ ጋዜጣ ። እንደ ፡ ደንቡ ፡ ባለ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ወዲያውኑ ፡ እዚያው ፡ ይከፍቱና ፡ ወሬ ፡ ይከፋፈላሉ ፤ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ የሚታየው ፡ ትርኢት ፡ እጅግ ፡ የሚያስደስት ፡ ነበር ። ሲልቪዎም ፡ ደብዳቤውን ፡ የሚቀበለው ፡ በክፍለ ፡ ጦሩ ፡ በኩል ፡ ስለነበር ፡ እሱም ፡ እንደዚሁ ፡ አብሮ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰውና ፡ በታላቅ ፡ የችኰላ ፡ ስሜት ፡ ከፈተው ። ዓይኖቹም ፡ ጽሑፉን ፡ በፍጥነት ፡ ሲያነቡ ፡ አበሩ ። መኰንኖች ፡ የየራሳቸውን ፡ ደብዳቤ ፡ ያነቡ ፡ ስለነበር ፡ ልብም ፡ አላኩት ፡ ነበር ። « ክቡራን ፡ » ሲል ፡ ጮኸ ፡ ሲልቪዎ ፤ « በፍጥነት ፡ እንድጓዝ ፡ ሁናቴው ፡ ያስገድደኛል ። ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ መሄድ ፡ አለብኝ ። ለመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ እራት ፡ ለመብላት ፡ እምቢ ፡ እንደማትሉ ፡ አምናለሁ ። እጠብቃችኋለሁ ፡ » አለ ፡ ወደኔ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡

እየተናገረ ። « መምጣት ፡ አለባችሁ! » ይህን ፡ ቃል ፡ ተና ግሮ ፡ ከክፍለ ፡ ጦሩ ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ። የቀረነውም ፡ በሲልቪ ዎ ፡ ቤት ፡ ለመገናኘት ፡ ተስማምተን ፡ ወደየፊናችን ፡ ሄድን ።

በቀጠሮው ፡ ሰዓት ፡ እሲልቪዎ ፡ ቤት ፡ በደረስኩ ፡ ጊዜ ፡ መላ ፡ የክፍለ ፡ ጦሩ ፡ መኰንኖች ፡ እዚያው ፡ ተሰብስበው ፡ አገኘኋቸው ። ዕቃዎቹም ፡ ተጠፍረው ፡ ነበር ። በጥይት ፡ ከተ በሳሱት ፡ ግድግዳዎች ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የቀረ ፡ ነገር ፡ አልነ በረም ። ለምግብ ፡ ቀረብን ፤ ጋባዣችንም ፡ በደስታ ፡ ተመልቶ ፡ ነበር ፤ የደስታ ፡ ስሜቱንም ፡ ወዲያው ፡ ለእንግዶቹ ፡ አካፈ ለ ። ቡሾች ፡ ያለማቋረጥ ፡ እድው ፡ እያሉ ፡ ተከፈቱ ፤ የወይን ፡ ጠጅም ፡ በብርጭቆ ፡ ውስጥ ፡ ሲንሿሿ ፡ ሊያጁን ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡ ያድርግልህ ፡ እያልን ፡ በመደጋገም ፡ ምኞታችን ፡ ገለጽንለት ። ከጠረጴዛ ፡ ስንነሳ ፡ እጅግ ፡ መሽቶ ፡ ነበር ። ለመ ሄድ ፡ ቆባችንን ፡ ስንደፋም ፡ ሲልቪዎ ፡ እያንዳንዳችንን ፡ ተሰ ናበተን ። ልወጣ ፡ ስል ፡ እጄን ፡ ይዞ ፡ አስቀረኝና ፤ « ላነጋግርህ ፡ እፈልጋለሁ ፡ » አለኝ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ። እኔም ፡ ቀረሁ ።

እንግዶቹ ፡ ሄዱ ፤ እኔና ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እየ ተያየንና ፡ በጸጥታ ፡ ፒፓችንን ፡ እያቀጣጠልን ፡ ቀረን ። ሲልቪ ዎ ፡ በሐሳብ ፡ ተመሰጠ ፤ ያ ፡ የደስታ ፡ ስሜቱም ፡ ጨርሶ ፡ ጠፋ ። ጨፍጋጋ ፡ ፊቱና ፡ የሚያበሩት ፡ ዓይኖቹ ፡ እንዲሁም ፡ ከአፉ ፡ የሚቡለቀለቀው ፡ ወፍራም ፡ ጭስ ፡ ዕውነተኛ ፡ ሰይጣን ፡ አስመ ሰሉት ። ጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ አለፉ ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሲልቪዎ ፡ ጸጥታውን ፡ በማቋረጥ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

« ምናልባት ፡ ዳግመኛ ፡ አንገናኝ ፡ ይሆናል ። ከመለያየ ታችን ፡ በፊት ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ እፈቅዳለሁ ። ሌሎ ች ፡ ሰዎች ፡ ስለኔ ፡ ምን ፡ እንደሚያስቡ ፡ ግድ ፡ እንደሌለኝ ፡ ሳትገነዘብ ፡ አልቀረህም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንተን ፡ ስለምወድህ ፡ ስለኔ ፡ የተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ይዘህ ፡ እንድትቀር ፡ አልፈል ግም ። »

አረፍ ፡ አለና ፡ ፒፓውን ፡ በትምባሆ ፡ መሙላት ፡ ጀመረ ። አንድም ፡ ቃል ፡ ሳልናገር ፡ ወደታች ፡ አጐንብሼ ፡ እመለከት ፡ ነበር ።

ነገሩንም ፡ በመቀጠል ፤ « ያ ፡ ስካሩም ፡ አንትና ፡ አዋርዶኝ ፡ ብድሬን ፡ ባለመክፈሌ ፡ ነገሩ ፡ ግራ ፡ ሳይሆንብህ ፡ አልቀረም ። የፈለግሁትን ፡ መሣሪያ ፡ ለመምረጥ ፡ መብቱ ፡ የኔ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ሕይወቱን ፡ በእጄ ፡ እንደያዝኳትና ፡ የኔ ፡ ሕይወት ፡ ግን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ እንዳልነበረ ፡ ሳትስማማ ፡ አትቀርም ። ትዕግሥቴን ፡ በደግነት ፡ እንድትተረጉመው ፡ እፈቅድልሃለሁ ፤ ሆኖም ፡ አንተን ፡ ለማታለል ፡ ፍላጐት ፡ የለኝም ። ሕይወቴን ፡ ፈጽሞ ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ሳልጥል ፡ እንትናን ፡ ልቀጣው ፡ ብችል ፡ ኖሮ ፡ ጨርሶ ፡ ምሕረት ፡ አላደርግለትም ፡ ነበር ።»

በመደነቅ ፡ ተመለከትኩት ። ዕውነቱን ፡ በመናገሩ ፡ ተገረምኩ ። ሲልቪዮ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ቀጠለ ፤

« እርግጥ ፡ ነው ፡ ሕይወቴን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ የለብኝም ። የዛሬ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በጥፊ ፡ መትቶኝ ፡ ነበር ፤ ያ ፡ ጠላቴ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ አለ ። »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ ለማወቅ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ጓጓሁ ። « ታዲያስ ፡ ተኩስ ፡ ሳትገጥመው ፡ ቀረህ? » ስል ፡ ጠየቅሁት ። « ሁናቴው ፡ ሳይፈቅድ ፡ ቀርቶ ፡ የተለያያችሁ ፡ ይመስለኛል ።»

« ተታኩሰን ፡ ነበር ፡ » አለ ፡ ሲልቪዮ ፡ « የተኩሳችንም ፡ ማስታወሻ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ አለ ።»

ብድግ ፡ ብሎም ፡ ከወረቀት ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ የተጠለፈና ፡ የወርቅ ፡ ቾብቾቦ ፡ ያለው ፡ ቀይ ፡ ቆብ ፡ አወጣ ።( ፈረንሳዊዎች ፡ bonnet de police የሚሉት ፡ ዓይነት ፡ ) ባጠለቀውም ፡ ጊዜ ፡ ከግንባሩ ፡ ሁለት ፡ ሴንቲሜትር ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የጥይት ፡ ቀዳዳ ፡ አየሁ ።

ሲልቪዮ ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፤ « ካሁን ፡ በፊት ፡ በእንትና ፡ የፈረሰኛ ፡ ክፍል ፡ አገለግል ፡ እንደነበር ፡ ሳታውቅ ፡

አትቀርም ፡ » አለ ። « ጠባዬንም ፡ ታውቃለህ ። በሁሉ ፡ ነገር ፡ በልጦ ፡ መገኘት ፡ ልማዴ ፡ ነው ። በወጣትነቴ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ውን ፡ ነገር ፡ አጥብቄ ፡ እወድ ፡ ነበር ። በኛ ፡ ጊዜ ፡ ድፍረትና ፡ ጨካኝነት ፡ ይወደድ ፡ ነበር ፤ በጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ውስጥ ፡ በጨካኝ ነትና ፡ በድፍረት ፡ አንደኛ ፡ ነበርኩ ። በሰከርንም ፡ ጊዜ ፡ ኩ ራት ፡ ይሰማን ፡ ነበር ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቡርትሶቭ ፡ ከ ተባለው ፡ የታወቀ ፡ ጠጪ ፡ ይበልጥ ፡ ጠጣሁ ። ስመ ፡ ጥሩው ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ ዴኒስ ፡ ዳቪዶቭ ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ የሆ ነ ፡ ግጥም ፡ ጽፏል ።[3] በኛ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ በየደቂቃ ው ፡ የዱዌል ፡ ግጥሚያ ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ ወይም ፡ ረዳት ፡ ወይም ፡ ዋና ፡ ተታኳሽ ፡ ያልሆንኩበት ፡ ጊዜ ፡ አይገኝም ። ጓደኞቼ ፡ በ ጣም ፡ ያደንቁኝ ፡ ነበር ። በየጊዜው ፡ የሚለዋወጡት ፡ የክፍለ ፡ ጦሩ ፡ አዛዦች ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሰይጣን ፡ ይቆጥሩኝ ፡ ነበር ።

እኔም ፡ በጸጥታ ፡ ( ምናልባት ፡ በጸጥታ ፡ ላይሆን ፡ ይችላ ል! ) ዝናዬን ፡ ይገፍ ፡ ተቀምጬ ፡ ሳለሁ ፡ አንድ ፡ ዘሩ ፡ የታወ ቀና ፡ ስሙን ፡ ልጠራው ፡ የማልፈቅድ ፡ ባለጸጋ ፡ ወጣት ፡ በክ ፍለ ፡ ጦራችን ፡ ተመደበ ። እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ብልህና ፡ ዕድለኛ ፡ ሰው ፡ መቸውንም ፡ አይቼ ፡ አላውቅም ። ከወጣትነቱ ፡ የብል ህነቱ ፤ ከደም ፡ ግባቱ ፡ የንቁነቱ ፤ ከጀግንነቱ ፡ የዝነኛነቱ ፤ ከዚህ ፡ በተረፈ ፡ ደግሞ ፡ እንደልቡ ፡ የሚያወጣው ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ባለ ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ስ ሜት ፡ እንዳሳደረብን ፡ ለመገመት ፡ ይቻላል ። ያኔ ፡ የበላይነት ፡ ማዕርግ ፡ ተናጋ ። ባለ ፡ ዝና ፡ መሆኔን ፡ በማወቅ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ለመጐዳኘት ፡ መጀመሪያ ፡ ሞከረ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ የሱን ፡ አቀራረ ብ ፡ ችላ ፡ ስላልኩት ፡ ያላንዳች ፡ ቅሬታ ፡ ሸሸኝ ። አጥብቄ ፡ ጠ ላሁት ። በክፍለ ፡ ጦራችን ፡ ውስጥና ፡ በሴቶች ፡ መካከል ፡ ተወ ዳጅ ፡ መሆኑም ፡ ተስፋ ፡ እስከ ፡ መቁረጥ ፡ አደረሰኝ ። ልጣላ ውም ፡ ሞከርኩ ፤ የማቀርበውን ፡ ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ በአዲስ ና ፡ ይበልጥ ፡ በረቀቀ ፡ እንዲሁም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አስቂኝ ፡

በሆን ፡ በራሱ ፡ ምሳሌ ፡ ይመልስልኛል ። ዝም ፡ ብሎ ፡ ይቀልዳል ፤ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እርር ፡ ብግን ፡ ያደርገኛል ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ አንድ ፡ የፖላንድ ፡ ባለ ፡ እርስት ፡ የዳንስ ፡ ግብዣ ፡ አድርጐ ፡ የሴት ፡ ወይዛዝርቱ ፡ ሁሉ ፡ ዓይን ፡ በዚህ ፡ ወጣት ፡ ላይ ፡ ስላረፈና ፡ በተለይም ፡ ደግሞ ፡ ወዳጄ ፡ የሆነችው ፡ የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ዓይኗን ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ ስለጣለችበት ፡ በጆሮው ፡ የብልግና ፡ ቃል ፡ ተናገርሁት ። ደሙ ፡ ፈላና ፡ በጥፊ ፡ አጮለኝ ። እጆቻችንም ፡ ወደየሰይፋችን ፡ ሰገባ ፡ ፈጥነው ፡ ተሰማሩ ። ሴት ፡ ወይዛዝርቱ ፡ ተደናገጡ ፤ እኛም ፡ በገላጋይ ፡ በግድ ፡ ተለያየንና ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ሌሊት ፡ ዱዌል ፡ ለመታኰስ ፡ ተስማማን ።

ጐህ ፡ ቀደደ ። በተቃጠርንበት ፡ ቦታም ፡ ከሶስት ፡ ተከታዮቼ ፡ ጋር ፡ ሆኜ ፡ ጠላቴን ፡ በታላቅ ፡ ጉጉት ፡ ቆሜ ፡ ጠበቅሁ ። የፀደይ ፡ ወር ፡ ስለነበረም ፡ ጸሐይ ፡ ቀድም ፡ ብላ ፡ ወጣች ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሙቀት ፡ ሆነ ። ከሩቁ ፡ አየሁት ። የመጣው ፡ በእግሩ ፡ ነው ፤ ኰቱንም ፡ እሰይፉ ፡ ላይ ፡ ሰቅሎ ፡ ይዟል ፤ ያስከተለውም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ልንቀበለው ፡ ሄድን ፤ በቆቡ ፡ ሙሉም ፡ የቸሪ ፡ ፍሬ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። ተከታዮቻችን ፡ በመካከላችን ፡ አስራሁለት ፡ እርምጃ ፡ ቆጠሩ ። መጀመሪያ ፡ መተኰስ ፡ የነበረብኝ ፡ እኔ ፡ ነበርኩ ። ነገር ፡ ግን ፡ በንዴት ፡ ተቃጥዬ ፡ ስለነበር ፡ እጄ ፡ ይንቀጠቀጥብኛል ፡ በማለት ፡ የመጀመሪያውን ፡ ተኩስ ፡ ለርሱ ፡ ለቀቅሁለት ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠላቴ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሊስማማ ፡ አልቻለም ። ስለዚህ ፡ እጣ ፡ እንዲጣል ፡ ተወሰነ ፤ መቸም ፡ እርሱ ፡ ምንጊዜም ፡ ዕድለኛ ፡ ነውና ፡ እጣው ፡ ለርሱ ፡ ደረሰ ። አነጣጥሮም ፡ ቆቤን ፡ ነደለው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የኔ ፡ ተራ ፡ ሆነ ። እነሆ ፡ በመጨረሻ ፡ ሕይወቱ ፡ በእጄ ፡ ገባችልኝ ። ምናልባት ፡ ተጨንቆ ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ አተኩሬ ፡ ተመለከትኩት ። እሱ ፡ ግን ፡ ሽጉጤን ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ ሳይቆጥር ፡ ከቆቡ ፡ ውስጥ ፡ የበሰለ ፡

የበሰለውን ፤ የቾሪ ፡ ፍሬ ፡ መርጦ ፡ እየበላ ፡ ጠጠሩን ፡ እኔ ፡ እቆምኩበት ፡ ቦታ ፡ ገደማ ፡ ድረስ ፡ ተፍቶ ፣ ይወረውረው ፡ ጀመር ። እርጋታውና ፡ ጸጥታው ፡ አናደደኝ ። እርሱ ፣ እራሱ ፡ ለሕይወቱ ፣ ዋጋ ፡ ካልሰጠው ፡ ሕይወቱን ፡ ባጠፋበት ፡ ምን ፡ ይጠቅማል? ስል ፡ አሰብኩ ። አንድ ፡ ክፉ ፡ ሐሳብ ፣ በአዕምሮ ዬ ፡ ውስጥ ፡ ሽው ፡ አለብኝ ፤ ሽጉጤን ፡ የያዝኩበትን ፡ እጄን ፡ ወደታች ፡ አወረድኩት ።

« ሞትን ፡ የማያሳስብ ፡ ሥራ ፡ ይዘዋል ። ቁርስ ፡ በመብላ ት ፡ ላይ ፡ ስለሆኑ ፡ ላስቸግርዎት ፡ አልፈልግም ፡ » አልኩት ። « ፈጽሞ ፡ አላስቸገሩኝም ፡ » ሲል ፡ መለሰና ፤ « ይልቁንስ ፡ ይ ተኩሱ ። ካልፈለጉም ፡ ይተው ። እርስዎ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ተኩስ ፡ ስላለዎት ፡ ምንጊዜም ፡ ልቀበልዎት ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ፡ » አለ ። ወደ ፡ ተከታዮቼ ፡ ዘወር ፡ ብዬ ፡ ለጊዜው ፡ ለመተኰስ ፡ አለመፈለጌን ፡ ገልጬላቸው ፡ ዱዌሉ ፡ በዚህ ፡ ተፈጸመ ።

ከጦር ፡ ሠራዊትም ፡ ተሰናበትኩና ፡ ወደዚች ፡ ትንሽ ፡ ቦታ ፡ ለመኖር ፡ መጣሁ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ብድሬን ፡ የምወጣበትን ፡ ሰዓት ፡ ሳላስብ ፡ ያለፍኩት ፡ ቀን ፡ የለም ። ሰዓ ቱ ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ደረሰ … »

ሲልቪዎ ፡ ጢት ፡ የደረሰውን ፡ ደብዳቤ ፡ ከኪሱ ፡ አውጥቶ ፡ እንዳነበው ፡ ሰጠኝ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ( ምናልባት ፡ ጠበቃው ፡ ሳይ ሆን ፡ አይቀርም ፡ ) ደብዳቤ ፡ ከሞስኮ ፡ በመጻፍ ፡ እገሌ ፡ የሚ ባል ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ የተዋበች ፡ ወጣት ፡ ሴት ፡ ሊያገባ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ገልጾለታል ።

« ይህ ፡ እገሌ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ በመላ ፡ ሳታውቅ ፡ አትቀርም ፡ » አለ ፡ ሲልቪዎ ። « እነሆ ፡ ወደ ፡ ሞስ ኮ ፡ መሄዴ ፡ ነው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ የቾሪ ፡ ፍሬ ፡ ከቆቡ ፡ ውስጥ ፡ አውጥቶ ፡ እየበላ ፡ የሞቱን ፡ ሰዓት ፡ በግዴለሽነት ፡ እንደተጋ ጠመ ፡ አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ሚስት ፡ በሚያገባበት ፡ አጥቢያ ፡ እንደዚሁ ፡ በግዴለሽነት ፡ ይጋጠመው ፡ እንደሆን ፡ እና ያለን ። »

ሲልቪዎ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ብድግ ፡ አለና ፡ ቆቡን ፡
ወደ ፡ መሬት ፡ ጥሎ ፡ በሽቦ ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ነብር ፡ ወ
ደላይና ፡ ወደታች ፡ ይንጐራደድ ፡ ጀመር ። እኔም ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡
ቆሜ ፡ ሰማሁት ፤ እንግዳ ፡ በሆነና ፡ በተመሳቀለ ፡ ሐሳብ ፡ ተበ
ሳጭቼ ፡ ነበር ።

ፈረሶች ፡ መዘጋጀታቸውን ፡ ለማስታወቅ ፡ አሽከሩ ፡ ገባ ።
ሲልቪዎ ፡ እጁን ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ ጨበጠው ፤ ተቃቀፍን ።
ሁለት ፡ ሣጥኖች ፡ ወዳሉበት ፡ ሠረገላ ፡ ላይም ፡ ወጣ ። በአን
ደኛው ፡ ሣጥን ፡ ውስጥ ፡ ሽጉጦቹ ፤ በሌላው ፡ ውስጥ ፡ የግል ፡
ዕቃዎቹ ፡ ነበሩ ። እንደገና ፡ ደግሞ ፡ ተሰነባበትንና ፡ ፈረሶቹ ፡
ጋልበው ፡ ሄዱ ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ከአለፉ ፡ በኋላ ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ አስገ
ድዶኝ ፡ እገሌ ፡ በምትባለው ፡ ድህነት ፡ ባጠቃት ፡ መንደር ፡
ውስጥ ፡ መኖር ፡ ጀመርኩ ። የርስቴን ፡ ጉዳይ ፡ በማስተዳደር ፡
ላይ ፡ ብገኝም ፡ ቅሉ ፡ የዱሮው ፡ የልጅነትና ፡ የጭፈራ ፡ ሕይወ
ቴ ፡ ይናፍቀኝ ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ ልለምደው ፡ ያል
ቻልኩት ፡ በመጸውና ፡ በክረምት ፡ ወራት ፡ ሀወትር ፡ ማታ ፡ ፍ
ጹም ፡ ብቸኛ ፡ መሆኔን ፡ ነበር ። እስከ ፡ እራት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡
አንድም ፡ ከመንደሩ ፡ የጭቃ ፡ ሹም ፡ ጋር ፡ በመጨዋወት ፤
ወይም ፡ ደግሞ ፡ እርስቴን ፡ በሠረገላ ፡ እየተዘዋወርኩ ፡ ሥራ
ው ፡ እንዴት ፡ እንደሚካሄድ ፡ በማየት ፤ አለበለዚያም ፡ አዲስ ፡
የተቋቋሙትን ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ በመጐብኘት ፡ ጊዜውን ፡
እንደምንም ፡ ብዬ ፡ አሳልፍ ፡ ነበር ። ሲጨልም ፡ ግን ፡ የማደር
ገው ፡ ነገር ፡ ቅጡ ፡ ይጠፋኛል ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቁም ፡ ሣጥን ፡
ውስጥና ፡ በዕቃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያገኘኋቸውን ፡ ጥቂት ፡ መጻ

ሕፍት ፡ በቃሌ ፡ አጥንቻቸዋለሁ ። ቤት ፡ ጠባቂዋ ፡ ኪሪሎብና ም ፡ የምታውቀውን ፡ ተረት ፡ ሁሉ ፡ ደጋግማ ፡ ደጋግማ ፡ ነግ ራኛለች ። የሴቶቹም ፡ ዘፈን ፡ ማስደሰቱ ፡ ቀርቶ ፡ ያሳዝነኝ ፡ ጀመር ። እራሴን ፡ ባያሳምመኝ ፡ ኖሮ ፡ አረቂ ፡ መጠጣት ፡ በወ ደድኩ ፡ ነበር ። በውነቱ ፡ ግን ፡ ከመሰልቸት ፡ የተነሣ ፡ መጠጥ ፡ ብጀምር ፡ ሰካራም ፡ እሆናለሁ ፡ በማለት ፡ ፍርሃት ፡ አድሮብኝ ፡ እንደነበር ፡ ገልጬ ፡ ለመናገር ፡ እፈቅዳለሁ ። ይህን ፡ ማለቴ ፡ በሰፈራችን ፡ ከአየኋቸው ፡ ቁጥር ፡ ስፍር ፡ ከሌላቸው ፡ ሰካራ ሞች ፡ የባሰኩ ፡ እንዳልሆን ፡ ማለቴ ፡ ነው ። የነበሩኝ ፡ ጐረቤቶ ች ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሶስት ፡ ምስኪኖች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ጨዋታቸውም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ስቅታና ፡ ቁና ፡ ቁና ፡ መተንፈስ ፡ ነው ። ከነዚህስ ፡ ጋር ፡ ከመጐዳኘት ፡ ያው ፡ ብቸኝነቱ ፡ ይሻላል ።

አራት ፡ ቬርስታዎች ፡* እራቅ ፡ ብሎ ፡ የልዕልት ፡ እገሌ ፡ ሰፌ ፡ እርስት ፡ ይገኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ ከጠባቂው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይኖርም ። ልዕልቲቱ ፡ እርስቷን ፡ ባገ ባች ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓመት ፡ መጥታ ፡ ጐብኝታው ፡ አን ድ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ተቀምጣ ፡ ተመልሳ ፡ ሄደች ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁለተኛው ፡ የብቸኝነቴ ፡ ዓመት ፡ ሲገባ ፡ ልዕልቲቱና ፡ ባልዋ ፡ እርስታቸውን ፡ በበጋ ፡ ወር ፡ መጥተው ፡ ይጐበኛ ሉ ፡ እየተባለ፡ ተወራ ። በሰኔ ፡ ወር ፡ መጀመሪያ ፡ ላይም ፡ መጡ።

በገጠር ፡ ነዋሪዎች ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ባለጸጋ ፡ ጐረቤት ፡ ሲመጣ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ይቆጠራል ። ባለርስቶችና ፡ አገልጋዮቻቸው ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ቀድም ፡ ብለው ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ ሲያወሩ ፡ ይከርማሉ ፤ ሰዎቹ ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ወሬው ፡ ለሶስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ይቀጥላል ። እኔ ፡ በበ ኩሌ ፡ ወጣትና ፡ ቆንጆ ፡ ሴት ፡ ጐረቤታችን ፡ ሊሆኑ ፡ ይመጣሉ ፡

---

* ቬርስታ ፡ የጥንት ፡ ሩሲያ ፡ የርዝመት ፡ መለኪያ ፡ ነው ። አንድ ፡ ቬርስታ ፡ 3500 ጫማ ፡ ነው ።

እየተባለ ፡ የሚወራው ፡ ወሬ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ስሜቴን ፡ ለወ ጠው ። እርሷን ፡ የማየት ፡ ጉጉትም ፡ ሆዴን ፡ ስላቃጠለው ፡ በመ ጣች ፡ በመጀመሪያው ፡ ዕሁድ ፡ ቀን ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ክብርት ና ፡ ክቡርነታቸውን ፡ እጅ ፡ ለመንሳትና ፡ እንዲሁም ፡ ታዛዥ ፡ የቅርብ ፡ ጐረቤታቸው ፡ መሆኔን ፡ ለማስታወቅ ፡ ወደ ፡ እንት ና ፡ መንደር ፡ ሄድኩ ።

የዕልፍኝ ፡ አስከልካዩ ፡ ወደ ፡ ክቡርነታቸው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መራኝና ፡ መምጣቴን ፡ ለማስታወቅ ፡ ሄደ ። ሰፊው ፡ የጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የተሽቆጠቆጠ ፡ ነበር ። በግርግዳው ፡ አኳያ ም ፡ በመጻሕፍት ፡ የተመሉ ፡ የመጻሕፍት ፡ መደርደሪያ ዎች ፡ አሉ ። በያንዳንዱም ፡ ላይ ፡ የነሐስ ፡ ጭንቅላት ፡ ተቀ ምጦበታል ። ከዕምነ ፡ በረድ ፡ ከተሰራው ፡ የእሳት ፡ መሞ ቂያ ፡ ምድጃ ፡ በላይ ፡ ትልቅ ፡ መስታዋት ፡ አለ ። ወለሉ ፡ በአረንጓዴ ፡ ጨርቅ ፡ ተሸፍኖ ፡ እላው ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ትናንሽ ፡ ምንጣፎች ፡ ተዘርግተዋል ። በታናሽ ፡ ቤቴ ፡ ውስ ጥ ፡ ያደግሁት ፡ ምቾትን ፡ ሳላይ ፡ በመሆኑ ፡ የሌሎችንም ፡ ሀብት ፡ ከአየሁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜዬ ፡ ስለሆነ ፡ ሐፍረት ፡ ያዘኝ ፤ ለእ ቤቱታ ፡ የመጣ ፡ የገጠር ፡ ሰው ፡ ሚኒስትሩን ፡ በፍርሃትና ፡ በመ ጨነቅ ፡ እንደሚጠብቅ ፡ ሁሉ ፡ እኔም ፡ ክቡርነታቸውን ፡ በፍ ርሃትና ፡ በመጨነቅ ፡ ጠበቅኋቸው ። በሩ ፡ ተከፈተ ፤ መልኩ ፡ እጅግ ፡ የተዋበና ፡ ዕድሜውም ፡ ወደ ፡ ሰላሳ ፡ ሁለት ፡ የሚ ሆን ፡ ሰው ፡ ገባ ። ክቡርነታቸው ፡ በአክብሮትና ፡ በወዳጅ ነት ፡ ስሜት ፡ ተቀበሉኝ ። ነቃ ፡ ብየ ፡ እራሴን ፡ ለማስተዋወ ቅ ፡ ስሞክር ፡ እርሳቸው ፡ ቀደሙኝ ። ተቀመጥን ። ትህትናና ፡ ለ ዛብታ ፡ ያለበት ፡ ጨዋታቸው ፡ ከረጅም ፡ ጊዜ ፡ ብቸኝነት ፡ የ ተነሣ ፡ የወረረኝን ፡ ሐፍረት ፡ ወዲያው ፡ አስወገደልኝ ። መዝና ናት ፡ ስጀምርም ፡ ክብርትነታቸው ፡ ገቡ ፤ ከበፊት ፡ የበለጠ ፡ ሐ ፍረትም ፡ ያዘኝ ። በውነቱ ፡ ክብርትነታቸው ፡ እጅግ ፡ የተዋቡ ፡ ሴት ፡ ነበሩ ። የተገዘናናሁ ፡ ለመምሰል ፡ ሞከርኩ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡

እረጋ ፡ ያልኩ ፡ ለመምሰል ፡ በሞከርኩ ፡ ቁጥር ፡ ሐፍረቴ ፡ እየ ባሰብኝ ፡ ሄደ ። አዕምሮዬ ፡ እስኪረጋጋና ፡ ከእንግዳ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ መቀላቀል ፡ እስክለምድ ፡ ድረስ ፡ ያላንዳች ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ጐረቤት ፡ በመቁጠር ፡ እርስ ፡ በርሳ ቸው ፡ ያወሩ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተን ጐራደድኩ ፡ መጽሐፎቹንና ፡ ሥዕሎቹን ፡ እመለከት ፡ ጀ መር ። ስለ ፡ ሥዕል ፡ እምብዛም ፡ አላውቅም ፤ ሆኖም ፡ ዓይኔን ፡ የማረከው ፡ አንድ ፡ ሥዕል ፡ ነበር ። በሥዕሉ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ አንድ ፡ የስዊዝ ፡ አገር ፡ መስክ ፡ ነው ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ የማረ ከኝ ፡ ሥዕሉ ፡ ሳይሆን ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የተደራረበ ፡ የጥ ይት ፡ ቀዳዳ ፡ ምልክት ፡ ነበር ።

« ማለፊያ ፡ አተኳኳስ ፡ ነው ፡ » አልኩኝ ፡ ዘወር ፡ ብየ ፡ ወደ ፡ ክቡርነታቸው ።

« አዎን ፤ ድንቅ ፡ አተኳኳስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ » ሲሉ ፡ መለሱ ልኝ ። ቀጥሎም ፤ « እርስዎስ ፡ ደህና ፡ ተኳሽ ፡ ነዎት? » ሲ ሉ ፡ ጠየቁኝ ።

« እንዴታ ፤ ተኩስ ፡ መራኸ ፡ ነኝ ፡ » ስል ፡ መለስኩ ፤ ጨ ዋታው ፡ እጅግ ፡ የምወደውን ፡ ነገር ፡ በመንካቱ ፡ ልቤ ፡ እየተ ደሰተ ። ቀጥየም ፡ « አንድ ፡ ካርታ ፡ ሰላሣ ፡ ጫማ ፡ እርቄ ፡ አል ስትም ፤ በማውቀው ፡ ሽጉጥ ፡ ነው ፡ ታዲያ ፡ » አልኩ ።

« ዕውነት? » አሉ ፡ ክብርትነታቸው ፡ እጅግ ፡ በመደነቅ ። « ፍቅሬ ፤ አንተስ ፡ ካርታ ፡ ሰላሣ ፡ ጫማ ፡ እርቀህ ፡ ትመ ታለህ? »

« እስቲ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንሞክራለን ፡ » አሉ ፡ ክቡርነታ ቸው ። ቀጥለውም ፤ « እኔም ፡ በጊዜዬ ፡ ደህና ፡ ተኳሽ ፡ ነበር ኩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ባለፉት ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሽጉጥ ፡ በእጄ ፡ አልነካሁም ፡ » አሉ ።

« እንግዲያውስ ፡ ከክቡርነትዎ ፡ ጋር ፡ እወራረዳለሁ ፡ ሃያ ፡ ጫማም ፡ እርቀው ፡ ካርታ ፡ አይመቱ ፡ » አልኩኝ ። « የሽጉ

ጥ ፡ ተኵስ ፡ በየቀኑ ፡ ልማድ ፡ ያስፈልገዋል ። እኔ ፡ ልማድ ፡ ስላ ለኝ ፡ አውቀዋለሁ ። በክፍለ ፡ ጦራችን ፡ ዋና ፡ ተኳሾች ፡ ከሚባ ሉት ፡ ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ ነበርኩ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሽጉ ጦቼ ፡ ሲታደሱ ፡ ሳለ ፡ ሽጉጥ ፡ ሳልነካ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ አለፈ ። ምን ፡ እንደሆነ ፡ ያውቃሉ ፡ ክቡርነትዎ? ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ጠርሙስ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ እርምጃ ፡ እርቄ ፡ ለመምታት ፡ አራ ት ፡ ጊዜ ፡ ብተኵስ ፡ አራት ፡ ጊዜም ፡ ሳትኩኝ ። ቀልደኛና ፡ ነገረኛ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሻምበላችን ፡ እዚያው ፡ ስለነበር ፡ እን ዲህ ፡ አለኝ ፤ « ወዳጄ ፤ ጠርሙስ ፡ ጨክነህ ፡ ለመምታት ፡ የማትችል ፡ መሆንህን ፡ አየንልህ ። » ስለዚህ ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ልምምድ ፡ ማድረግን ፡ ችላ ፡ ማለት ፡ የለብዎትም ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡ በፍጥነት ፡ ጨርሶ ፡ ይረሱታል ። እኔ ፡ የማ ውቀው ፡ አንድ ፡ ጥሩ ፡ ተኳሽ ፡ ነበር ፤ በየቀኑም ፡ ልምምድ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ ከምሳ ፡ በፊት ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ሶስት ፡ ጊ ዜ ፡ ይተኵስ ፡ ነበር ። ከምግብ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ አረቂ ፡ የመጠጣት ፡ ልማድ ፡ እንዳለበት ፡ ሰው ፡ እርሱም ፡ እንደዚሁ ፡ የተኵስ ፡ ልማድ ፡ ነበረበት ። »

ክቡርነታቸውና ፡ ክብርትነታቸው ፡ እንደበኑ ፡ ስለተ ፈታልኝ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

« እስቲ ፡ ጨመር ፡ አድርገው ፡ ይንገሩን ፡ ስለአተኳኰ ሱ ፡ » ሲሉ ፡ ክቡርነታቸው ፡ ጠየቁ ። « አዬ ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዝንብ ፡ እግርግዳ ፡ ላይ ፡ ስታርፍ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፤ ምን ፡ ያስቀዎታል ፡ እሜትዬ ፤ የምናገረው ፡ እኰ ፡ ዕውነት ፡ ነው ፤ እምላለሁ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ዝንብ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፤ « ኩዝካ ፤ ሽጉጤን ፡ አምጣ! » ብሎ ፡ ይጮኻል ። ኩዝካም ፡ የተቀባበለ ውን ፡ ሽጉጡን ፡ ይሰጠዋል ። እድው ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ዝንቧ ፡ እግ ርግዳው ፡ ላይ ፡ ትጨፈለቃለች ። »

« ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው! » አሉ ፡ ክቡርነታቸው ፤ « ስሙ ስ ፡ ማን ፡ ይባል ፡ ነበር? »

« ሲልቪዎ ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ።»

« ሲልቪዎ! » ሲሉ ፡ ጮኹ ፡ ክቡርነታቸው ፡ ከመቀመጫ ቸው ፡ ብድግ ፡ ብለው ። « ሲልቪዎን ፡ ያውቁት ፡ ነበር?»

« እንዴታ ፡ ጌታዬ ። የልብ ፡ ወዳጆች ፡ ነበርን ። በክፍለ ፡ ጦራችንም ፡ እንደኛው ፡ ነበር ፡ የሚታየው ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ርሱ ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ሳልሰማ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሆነኝ ። ስለ ዚህ ፡ ክቡርነትዎም ፡ ያውቀው ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነዋ?»

« እንዴታ ። በደንብ ፡ አውቀው ፡ ነበር ፡ እንጂ ። አንድ ፡ ታ ሪክ ፡ አላጫወተዎትም ፡ ሳያጫውትዎ ፡ አልቀረም ። በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ ስለደረሰበት ፡ አንድ ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ አላጫወተ ዎትም?»

« ክቡርነትዎ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ባለጌ ፡ በጥፊ ፡ የመታው ፡ ጊዜ ፡ ነው? »

« የዚያንስ ፡ የወጣት ፡ ባለጌ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ አልነገረዎት ም?»

« የለም ፡ ክቡር ፡ ሆይ ፤ አልነገረኝም ፡ » አልኩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዕውነተኛው ፡ ነገር ፡ ድንገት ፡ ተገለጸልኝ ። « ይቅር ታ ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፤ እርስዎ ፡ አልመሰሉኝም ፡ ነበር ፤ ሰውየው ፡ እርስዎ ፡ ነዎት ፡ እንዴ?»

« አዎን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ » ሲሉ ፡ መለሱ ፡ ፊታቸው ፡ ሐዘን ፡ ለብሶ ። « ይህ ፡ ጥይት ፡ የበሳው ፡ ሥዕል ፡ የመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ግንኙነታችን ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ... »

« እባክህ ፡ ፍቅሬ ፡ ሆይ ፤ ስለሱ ፡ ነገር ፡ አታውራ ፤ እለምን ሃለሁ ፤ ዘወትር ፡ እንደሚያስፈራራኝ ፡ ታውቃለህ ፡» አሉ ፡ ክብርትነታቸው ።

« የለም ፡ መናገር ፡ አለብኝ ፤ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ መናገር ፡ አለብኝ ፡ » አሉ ፡ ጌቶች ። « ወዳጄን ፡ እንዴት ፡ እንዳዋረድ ኩት ፡ ያውቃልና ፡ ሲልቪዎ ፡ ብድሩን ፡ እንዴት ፡ እንደመለሰ ፡ እነግረዋለሁ ። »

ክቡርነታቸው ፡ ምቹ ፡ ወንበር ፡ አቀረቡልኝና ፡ የሚቀጥለውን ፡ ታሪክ ፡ በታላቅ ፡ ጉጉት ፡ ሰማሁ ፤

« የዛሬ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሚስት ፡ አገባሁ ። የመጀመሪያውን ፡ የሙሽርነቴን ፡ ወርም ፡ በዚህ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ አሳለፍኩ ። በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ ጥልቅ ፡ የሆነ ፡ ደስታ ፡ ያገኘሁት ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሲሆን ፤ እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ትዝታ ፡ የተቀበልኩትም ፡ በዚሁ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ከሚስቴ ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ ሆነን ፡ ፈረስ ፡ እንጋልብ ፡ ነበር ። የባለቤቴ ፡ ፈረስ ፡ ተቁነጠነጠ ። ነገሩ ፡ ስላስፈራት ፡ ልጓሙን ፡ ለኔ ፡ ሰጠችና ፡ በእግሯ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ተመለሰች ። እኔም ፡ ቀድሜ ፡ ሄድኩ ። በአጥር ፡ ግቢአችን ፡ ውስጥ ፡ የመንገደኛ ፡ ሠረገላ ፡ ቆሞ ፡ አየሁ ። አንድ ፡ ሰው ፡ በጽሕፈት ፡ ቤቴ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚጠብቀኝ ፡ ነገሩኝ ። ስሙን ፡ ግን ፡ አልተናገረም ፤ እንዲያው ፡ ብቻ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ጉዳይ ፡ እንዳለው ፡ ተናግሮ ፡ ዝም ፡ አለ ። ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ስገባ ፡ በምሽቱ ፡ ብርሃን ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አቧራ ፡ የለበሰና ፡ ጢሙን ፡ ያልተላጨ ፡ ሰው ፡ በእሳት ፡ መሞቂያው ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ አየሁ ። ወደርሱ ፡ ቀረብ ፡ ብዬ ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ ለማስታወስ ፡ ሞከርኩ ፡ « አያውቁኝም ፡ እንዴ ፡ ክቡር?» አለ ፡ በሚርገበገብ ፡ ድምጽ ። « ሲልቪዎ! » አልኩ ፡ በጩኸት ፡ ቃል ። ዕውነቱን ፡ ለመናገር ፡ ሰውነቴንም ፡ ወረረኝ ። « አዎን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ » አለ ። « መተኰስ ፡ የኔ ፡ ተራ ፡ ነው! ሽጉጤን ፡ ለማራገፍ ፡ መጥቻለሁ ። ታዲያስ ፡ ዝግጁ ፡ ነዎት? » አንድ ፡ ሽጉጥ ፡ ከደረት ፡ ኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። አስራ ፡ ሁለት ፡ እርምጃ ፡ ለክቼ ፡ በማዕዘኑ ፡ ላይ ፡ ቆምኩ ፤ ሚስቴ ፡ ከመምጣቷ ፡ በፊት ፡ ቶሎ ፡ እንዲተኩስም ፡ ለመንኩት ፤ ብርሃን ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ ነገሩን ፡ አዘገየው ። ሻማ ፡ አስመጣሁ ። በሩን ፡ ቆልፌም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፡ ትዕዛዝ ፡ ሰጠሁ ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ እንዲተኩስ ፡ ጠየ

ቅሁት ። ሽጉጡን ፡ አወጣና ፡ አነጣጠረ ። ደቂቃዎቹን ፡ ቆጠ
ርኩ ። ስለርሷም ፡ አሰብኩ … አንድ ፡ ደቂቃ ፡ የሚሆን ፡ የ
ጭንቅ ፡ ጊዜ ፡ አለፈ ። ሲልቪዎ ፡ እጁን ፡ አወረደ ። « ሽጉጤ ፡
የቸረ ፡ ጠጠር ፡ ስላልጐረሰ ፡ አዝናለሁ ፤ ጥይት ፡ ከባድ ፡ ነው ፡»
አለ ። « ይህ ፡ ነፍስ ፡ ማጥፋት ፡ እንጂ ፡ ዱዌል ፡ እንዳልሆነ ፡
ይሰማኛል ። መሣሪያ ፡ በሌለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የማነጣጠር ፡
ልማድ ፡ የለኝም ። ለመጀመሪያ ፡ ተኩስ ፡ እጣ ፡ እንጣጣልና ፡
እንደገና ፡ እንጀምር ፡ » አለ ። እራሴን ፡ አዞረኝ … እንደማስ
ታውሰው ፡ በሐሳቡ ፡ የተስማማሁ ፡ አይመስለኝም … በመጨረ
ሻ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ሽጉጥ ፡ አጐረስንና ፡ ሁለት ፡ ዕጣዎች ፡ ጠቅ
ልለን ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ እኔ ፡ በጥይት ፡ በበሳሁት ፡ ቆብ ፡ ውስ
ጥ ፡ አስገባን ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ እጣው ፡ ለኔ ፡ ደረሰ ። « ክ
ቡር ፤ ዕድልዎ ፡ የሚደንቅ ፡ ነው ፡ » አለ ፡ ምንጊዜም ፡ ከ
ማልረሳው ፡ ፈገግታ ፡ ጋር ። ምን ፡ እንደነካኝ ፡ አላውቅም … ፤
እንዴት ፡ እንዳስገደደኝም ፡ አይገባኝም … የሆነ ፡ ሆኖ ፡
ተኰስኩ ፤ ያን ፡ ሥዕልም ፡ መታሁ ።» ( ክቡርነታቸው ፡ የጥ
ይት ፡ ቀዳዳ ፡ ያለበትን ፡ ሥዕል ፡ በጣታቸው ፡ አመለከቱ ። ጉ
ንጫቸው ፡ ቀላ ፤ የክብርትነታቸውም ፡ ፊት ፡ ከደረቡት ፡ ነ
ጭ ፡ ሻሽ ፡ ነጣ ፤ እኔም ፡ የመደነቅ ፡ ስሜቴን ፡ ላፍነው ፡ አልቻ
ልኩም ።)

« ተኰስኩ ፤ ደግነቱ ፡ ሳትኩ ፡ » አሉ ፡ ክቡርነታቸው ፡
ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ። « ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሲልቪዎ … በዚ
ያን ፡ ሰዓት ፡ እጅግ ፡ ያስፈራ ፡ ነበር … ወደኔ ፡ ማነጣጠር ፡ ጀ
መረ ። በድንገት ፡ በሩ ፡ ተከፈተና ፡ ማሻ ፡ ኡ- ኡ ፡ እያለች ፡
ተንደርድራ ፡ ገብታ ፡ እትከሻዬ ፡ ላይ ፡ ወደቀች ። እሷን ፡ ሳይ ፡
ነፍስ ፡ ዘራሁ ። « ፍቅሬ ፡ ሆይ ፡ ጨዋታ ፡ እኮ ፡ ነው ፡ የያዝነ
ው ፡ አታይም ፡ እንዴ? » አልኳት ። « እንዴት ፡ ደንግጠሻል ፤
ሂጂ ፡ ውኃ ፡ ጠጭና ፡ ተመልሰሽ ፡ ነይ ። የጥንት ፡ ጓደኛዬን
ና ፡ ወዳጄን ፡ ላስተዋውቅሽ ፡ እፈልጋለሁ ። » ማሻ ፡ አላመነ

ችም ። «ባሌ ፡ የሚለው ፡ ዕውነት ፡ ነው?» ስትል ፡ ወደሚያ ስፈራው ፡ ሲልቪዎ ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ ጠየቀችው ። « አሁን ፡ ይ ሄ ፡ የምትሠሩት ፡ ሥራ ፡ ዕውነት ፡ የቀልድ ፡ ነው? » « እመቤ ቴ ፡ ሆይ ፤ እርሳቸው ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደቀለዱ ፡ ናቸው ፡ » ሲል ፡ መለሰ ፡ ሲልቪዎ ። « አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለቀልድ ፡ ሲሉ ፡ በጥፊ ፡ መቱኝ ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ለቀልድ ፡ ሲሉ ፡ ቆቤን ፡ በጥይት ፡ ነደሉት ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ለቀልድ ፡ ሲሉ ፡ አነጣጥረው ፡ ሳቱ ኝ ። እኔም ፡ በፈንታዬ ፡ ለመቀለድ ፡ እፈልጋለሁ ።» ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ በርሷ ፡ ፊት ፡ ወደኔ ፡ ማነጣጠር ፡ ጀመረ! ማ ሻም ፡ እግሩ ፡ ላይ ፡ ወደቀች ። « ማሻ ፡ ተነሺ ፤ አታዋርጂ ኝ! » ብዬ ፡ በታላቅ ፡ ቁጣ ፡ ጮኽኩ ። « አንተም ፡ ወንድ ሜ ፡ ሆይ ፤ በምስኪኗ ፡ ሴት ፡ መቀለድህን ፡ አቁም ። ትተኩሳ ለህ ፡ ወይስ ፡ አትተኩስም? » « የለም ፡ አልተኩስም ፡ » ሲል ፡ መለሰ ፡ ሲልቪዎ ። « የልቤን ፡ አድርሻለሁ ። ስትጨነቅና ፡ ስትጠበብ ፡ አየሁህ ። በኔ ፡ ላይ ፡ እንድትተኩስም ፡ አድርጌሃ ለሁ ፤ ካሁን ፡ ወዲያ ፡ በቃኝ ። ታስታውሰኛለህ ። ሕሊናህ ፡ ይውቀስህ ። » እዚህ ፡ ላይ ፡ እንደመሄድ ፡ አለና ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ እኔ ፡ የመታሁትን ፡ ሥዕል ፡ ተመለከተ ፤ ሳያነጣጥር ፡ ተኩሶም ፡ እልም ፡ ብሎ ፡ ጠፋ ። ባለቤቴ ፡ ነፍሷን ፡ ሳተች ። አ ሽከሮቼም ፡ እርሱን ፡ ለመያዝ ፡ ስለፈሩ ፡ በአድንቆት ፡ ተመለ ከቱት ። ወደ ፡ በረንዳው ፡ ወጣ ፡ አለና ፡ ሠረገላ ፡ ነጂውን ፡ ጠራ ፤ የሆነውን ፡ ነገር ፡ በደንብ ፡ ከማስታወሴ ፡ በፊት ፡ እርሱ ፡ ቀድሞ ፡ ሄደ ። »

ክቡርነታቸው ፡ከዚህ ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ አልተናገሩም ። እነሆ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መጀመሪያው ፡ ያስደነቀኝን ፡ ታሪክ ፡ መጨረሻውን ፡ ለመስማት ፡ ቻልኩ ። የታሪኩን ፡ ጀግና ፡ ዳ ግመኛ ፡ አላገኘሁትም ። እንደሚባለው ፡ ሲልቪዎ ፡ በአሌ ክሳንደር ፡ ኢፕሲላንቲ[4] ፡ ሁከት ፡ ጊዜ ፡ የአንድ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ በስኩላኒ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ሞተ ።



[illegible]



ከዋሽቢን ፡ ወዳጆች ፡ በብዙም ፡ ቅርብ
የሆነ ፡ ኢሳን ፡ ጉደሺን ፡ [illegible]



[illegible] ፡ [illegible] ፡ ፑሽኪን
[illegible]
[illegible] ፡ ፑሽኪን
[illegible] ፡ [illegible] ።



የፑሽኪን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጓደኛ ፡ እህት ፡ የነበረችው ፡ ኤካቴሪና ፡ ባኩኒና ( ፲፯፻፺፭ — ፲፰፻፷፱ ዓ ም ) ። በትምህርት ፡ ጊዜው ፡ ብዙ ፡ ግጥሞች ፡ ጽፎላት ፡ ነበር ።



ከፒተርበርግ ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ ጻርስኮዬ ፡ ሴሎ ፡ በሚባለው ፡ መንደር ፡ ፑሽኪን ፡ ይማርበት ፡ የነበረ ፡ ዬሊቴሬችንስኪይ ፡ ቤት ፡ መንግሥት ።



ታላቁ ሩሲያዊ ባለቅኔ ገብሪኤል፣
ዴርዣቪን [illegible] ዓ.ም.
የሚቆው ማስቀደ ላይ ተሸበርቆ በማየንት
«የሩሲያ ሥነ ጽሑፍ ክብብ ነው» ብሎ ጠራው።

# የበረዶ፡ውሽንፍር።

ፈረሶቹ ፡ በአባጣ ፡ ጐርባጣው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡
ፈጥነው ፡ ይሮጣሉ ።
በኰቴአቸውም ፡ በረዶውን ፡ ይሰረጉዱታል ፡
እነሆ ፡ አንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ከመንገዱ ፡ ዳር ፡
ብቻውን ፡ ቆሞ ፡ ይታያል ።

. . . . . . . . . . . . . . . .

ድንገተኛ ፡ የበረዶ ፡ ውሽንፍር ፡ በአካባቢው ፡ ወረደ፤
በረዶውም ፡ እንደ ፡ ንድፍ ፡ እየተጠማዘዘ ፡ ወደቀ ፡
አንድ ፡ መተተኛ ፡ ቁራ ፡ ክንፉን ፡ እያራገበ ፡
በበረዶው ፡ ጋሪ ፡ ላይ ፡ ሽው ፡ ብሎ ፡ አለፈ ።
ድምጹ ፡ የደግ ፡ ነገር ፡ ትንቢት ፡ አይደለም !
ፈረሶቹ ፡ ፈጥነው ፡ ይሮጣሉ ፡
ጋማቸውን ፡ በጥንቃቄና ፡ በፍርሃት ፡ ቀጥ ፡
አድርገውም ፡
ወደሩቁ ፡ ጨለማ ፡ ይመለከታሉ ።

ዡኮቭስኪይ ።

በታሪካችን ፡ ውስጥ ፡ በማይረሳው ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፰፻
፲፩ ዓ ፡ ም ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ጋቭሪላ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ የሚባ
ል ፡ የተከበረ ፡ ሰው ፡ ኔናራዶቮ ፡ በተባለው ፡ እርስቱ ፡ ላይ ፡
ይኖር ፡ ነበር ። በእንግዳ ፡ አስተናጋጅነቱና ፡ በደግነቱም ፡
በመላው ፡ ቀበሌ ፡ የታወቀ ፡ ነበር ። ጐረቤቶቹም ፡ ለመብላት
ና ፡ ለመጠጣት ፡ እንዲሁም ፡ ከባለቤቱ ፡ ጋር ፡ ቦስተን ፡ የተ
ባለውን ፡ የካርታ ፡ ጨዋታ ፡ በአምስት ፡ ኰፔክ ፡ እየተወራረ
ዱ ፡ ለመጫወት ፡ ያለማቋረጥ ፡ ይጐበኙት ፡ ነበር ። አንዳንዶ
ቹም ፡ የሚመጡት ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭናን ፡
ለማየት ፡ ነበር ። ይህች ፡ ልጅ ፡ መልኳ ፡ ነጣ ፡ ያለና ፡ ቀጠን ፡
ያለች ፡ ናት ፤ ዕድሜዋም ፡ አስራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ ለ

አቅሙ ፡ ሄዋን ፡ የደረሰች ፡ በመሆንዋ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ለራሳቸው ፡ ወይም ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይመኝዋት ፡ ነበር ።

ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ የፈረንሳዊ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪኰች ፡ ስታነብ ፡ ያደገች ፡ በመሆንዋ ፡ ፍቅር ፡ ይዟት ፡ ነበር ። የመረጠችውም ፡ ድኃ ፡ ዝቅተኛ ፡ መኰንን ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ መንደሩ ፡ ለእረፍት ፡ ሄዶ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ። እሱም ፡ በበኩሉ ፡ ለርሷ ፡ ባለው ፡ ፍቅር ፡ ይቃጠል ፡ እንደነበር ፡ ግልጽ ፡ ነው ። የሚወዳት ፡ ልጅ ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ የሁለቱን ፡ መፋቀር ፡ አይተው ፡ እርሷ ፡ ስለርሱ ፡ እንዳታስብ ፡ ከለከሏት ፤ ልጁን ፡ የሚቀበሉትም ፡ ከሥራው ፡ እንደተሰናበተ ፡ ዳኛ ፡ ቅዝቅዝ ፡ ባለ ፡ ስሜት ፡ ነበር ።

ሁለቱ ፡ ተፋቃሪዎች ፡ ደብዳቤ ፡ መጻጻፋቸውን ፡ ቀጠሉ ፤ በየቀኑም ፡ በአንድ ፡ የጥድ ፡ ዛፍ ፡ ስር ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ የጥንት ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ውስጥ ፡ ይገናኙ ፡ ጀመር ። እዚያም ፡ ሆነው ፡ ለዘላለሙ ፡ እንደሚፋቀሩ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገቡ ። በደረሰባቸው ፡ መጥፎ ፡ እጣም ፡ አዘኑ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴም ፡ ያቅዱ ፡ ጀመር ። ደብዳቤአቸውና ፡ ጭውውታቸው ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ በመሆኑ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ውሳኔ ፡ አደረጉ ፡ ( ሌላ ፡ ምን ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ) ። አንዳችን ፡ ያለአንዳችን ፡ ለመኖር ፡ ስለማንችል ፡ ጨካኝ ፡ ዘመዶቻችንም ፡ የደስታ ፡ በራችንን ፡ ከዘጉብን ፡ ለምን ፡ ፈቃዳቸውን ፡ አንጥስና ፡ አናርፍም? እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አስደሳች ፡ ሐሳብ ፡ ያመነጨው ፡ ወጣቱ ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡ መቸም ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ሐሳቡም ፡ በፍቅር ፡ የተነደፈውን ፡ የማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭናን ፡ ልብ ፡ እጅግ ፡ አድርጐ ፡ አስደሰተው ።

ክረምት ፡ ገባና ፡ መገናኘታቸውን ፡ አቋረጠው ። ሆኖም ፡ የሚጻጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ ይበልጥ ፡ ናፍቆት ፡ የተመላበት ፡ እንዲሆን ፡ አደረገው ። ቭላዲሚር ፡ ኒኮላየቪች ፡ በሚጽፈው ፡ በያንዳንዱ ፡ ደብዳቤው ፡ ላይ ፡ ፍቅሩ ፡ የእርሱ ፡ እንድትሆንና ፡

በምሥጢርም ፡ እንድታገባው ፤ ተደብቃም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አብራው ፡ እንድትኖር ፡ አጥብቆ ፡ ለመናት ፤ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ እዘመዶቿ ፡ ጫማ ፡ ላይ ፡ እንደሚወድቁና ፡ ቤተሰቦቿም ፡ በሁለቱ ፡ ተፋቃሪዎች ፡ ታላቅ ፡ መስዋዕትነትና ፡ ሥቃይ ፡ ልባቸው ፡ ተነክቶ ፡ « ልጆቻችን ፡ ሆይ ፤ ኑ ፡ ወደ ፡ እኛ! » ሳይሉ ፡ እንደማይቀሩ ፡ ገለጸላት ።

ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ሐሳቧን ፡ ከመቁረጧ ፡ በፊት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደባት ። አያሌ ፡ የማምለጫ ፡ ዘዴዎችንም ፡ ሳትቀበል ፡ ቀረች ። በመጨረሻ ፡ ግን ፡ ተስማማች ። በቀጠሮው ፡ ቀንም ፡ እራሴን ፡ አሞኛል ፡ በማለት ፡ ከገበታ ፡ ላይ ፡ ተነስታ ፡ ወደመኝታ ፡ ቤቷ ፡ እንድትሄድ ፡ ታቀደ ። ደንገጡርዋም ፡ የምሥጢሩ ፡ ተካፋይ ፡ ሆነች ። በታቀደው ፡ ዘዴ ፡ መሠረት ፡ ማሪያና ፡ ደንገጡርዋ ፡ በጓዳ ፡ በር ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ሲሄዱ ፡ አንድ ፡ የሚጠብቃቸው ፡ ሠረገላ ፡ ያገኛሉ ። እሱ ፡ ላይ ፡ ተሳፍረውም ፡ ከኔናራዶቮ ፡ እስከ ፡ ዣድሪኖ ፡ መንደር ፡ ድረስ ፡ አምስት ፡ ቬርስታዎች ፡ ከተጓዙ ፡ በኋላ ፡ በቀጥታ ፡ ቭላዲሚር ፡ እነርሱን ፡ ወደሚጠብቅበት ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ይደርሳሉ ።

በቁርጠኛው ፡ ቀን ፡ አጥቢያ ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ አልተኛችም ። ቁም ፡ ሳጥኗን ፡ እየበረበረች ፡ ልብሶቿን ፡ ሁሉ ፡ ጠቀለለች ። ለአንድ ፡ ሆደ ፡ ባሻ ፡ ወጣት ፡ ሴት ፡ ወዳጅዋና ፡ ለዘመዶቿ ፡ እረጂም ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈች ። ልብ ፡ በሚነካ ፡ አኳኋንም ፡ ዘመዶቿን ፡ ተሰናበተቻቸው ፤ ይህን ፡ እርምጃ ፡ የወሰደችውም ፡ በፍቅር ፡ ኃይል ፡ ተሸንፋ ፡ መሆንዋን ፡ በማስረዳት ፤ እንደገና ፡ ተመልሳ ፡ መጥታ ፡ እተወደዱት ፡ ዘመዶቿ ፡ ጫማ ፡ ላይ ፡ መውደቅ ፡ ጥልቅ ፡ ደስታ ፡ የሚሰጣት ፡ መሆኑን ፡ በደብዳቤው ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ ገለጸችላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለቱንም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ሁለት ፡ ልቦች ፡ በሚንበለበሉበትና ፡ እስሩም ፡ ላይ ፡ ተገቢው ፡ መግለጫ ፡ በተ

ጻፈበት ፡ የቴላ ፡ ማሽጊያ ፡ ከዘጋች ፡ በኋላ ፡ ጕህ ፡ ከመቅደዱ ፡ በፊት ፡ አልጋዋ ፡ ላይ ፡ ተዘረረች ፤ እንቅልፍ ፡ ሸለብ ፡ አደረጋት ። ሆኖም ፡ አስጨናቂ ፡ ሕልም ፡ በየደቂቃው ፡ ይቀሰቅሳት ፡ ጀመር ። መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ለመሄድ ፡ ወደ ፡ በረዶው ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ልትወጣ ፡ ስትል ፡ አባቷ ፡ ይዞ ፡ ሲያቆማትና ፡ በሚያሰቃይ ፡ ፍጥነትም ፡ በበረዶው ፡ ላይ ፡ እየጐተተ ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ጨለማ ፡ አዘቅት ፡ ውስጥ ፡ ሲወረውራት ... እርሷም ፡ ፈጥና ፡ ቁልቁል ፡ ስትወርድና ፡ ልቧም ፡ ሊቆም ፡ ጥቂት ፡ ሲቀረው ፡ በሕልሟ ፡ ታያት ። ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ቭላዲሚር ፡ ፊቱ ፡ ምጥጥ ፡ ብሎ ፡ ደም ፡ እየወረደው ፡ እሳር ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ አየችው ። እሞት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ሆኖም ፡ ልብ ፡ በሚሰነጥቅ ፡ ድምጽ ፡ ጋብቻቸው ፡ እንዲፋጠን ፡ ሲለምናት ፡ ሰማችው ... እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ የሚያስፈሩና ፡ የሚያሰቅቁ ፡ የተመሳቀሉ ፡ ሕልሞች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ በአዕምሮዋ ፡ ውስጥ ፡ እየታይዋት ፡ አለፉ ። በመጨረሻም ፡ ከምንጊዜውም ፡ ፊቷ ፡ ምጥጥ ፡ ብሎና ፡ እውነተኛ ፡ የራስ ፡ ምታትም ፡ ይዟት ፡ ተነሳች ። እናትና ፡ አባቷም ፡ መታወኳን ፡ ተመለከቱ ። « ምን ፡ ሆንሽ ፡ ማሻ? አመመሽ ፡ እንዴ? » እያሉ ፡ የሚያቀርቡላት ፡ የማያቋርጥ ፡ የደግነትና ፡ የማስተዛዘን ፡ ጥያቄ ፡ ልቧን ፡ ነካው ። ስጋታቸውን ፡ ለመቀነስና ፡ ደስ ፡ ያላት ፡ ለመምሰልም ፡ ሞከረች ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሆንላትም ። መምሸት ፡ ጀመረ ። በዘመዶቿ ፡ ጉያ ፡ ውስጥ ፡ የምትቆይበት ፡ የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ መሆኑን ፡ በማሰብ ፡ ልቧ ፡ ተሰቃየ ። መተንፈስም ፡ አቃታት ፤ በልቧ ፡ የቤቱን ፡ ሰው ፡ ሁሉና ፡ ዕቃውንም ፡ ተሰናበተች ። እራት ፡ ቀረበ ፤ ልቧም ፡ በኃይል ፡ ይመታ ፡ ጀመር ። በሚርገበገብ ፡ ድምጽ ፡ እራት ፡ አለመፈለጓን ፡ አስታውቃ ፡ እናትና ፡ አባቷን ፡ ደህና ፡ እደሩ ፡ አለች ። እንደተለመደው ፡ ስመው ፡ መረቋት ። ልታለቅስ ፡ ጥቂት ፡ ነበር ፡ የቀራት ። እመኝታ ፡ ቤቷ ፡ ከገባች ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እባለመደገፊያ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ወድ

ቃ ፡ ታለቅስ ፡ ጀመር ። ልቅሶዋን ፡ እንድታቆምና ፡ እንደበፊ
ቱ ፡ የደስታ ፡ መልኳን ፡ እንድትይዝ ፡ ገረዷ ፡ ለመነቻት ። ሁ
ሉ ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ። እንግዲህ ፡ ከግማሽ ፡
ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ማሻ ፡ የቤተ ፡ ዘመዶቿን ፡ ቤትና ፡ የራሷን ፡
የመኝታ ፡ ክፍል ፡ ጸጥታ ፡ የተመላበትንም ፡ የልጃገረድነት ፡
ሕይወቷን ፡ ጥሳ ፡ ልትሄድ ፡ ነው ፡ ... ከውጭ ፡ በኩል ፡
የበረዶው ፡ ውሽንፍር ፡ እንደ ፡ መዓት ፡ ነው ። ነፋሱ ፡ ያፏጫ
ል ፤ የመስኮቶቹ ፡ መዝጊያዎችም ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፤ ይንኳኳሉ
ም ። ማንኛውም ፡ ነገር ፡ የሚያስፈራና ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የሚያስ
ከትል ፡ ሆኖ ፡ ተሰማት ። ወዲያው ፡ የቤቱን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እ
ንቅልፍ ፡ ወሰደው ። ማሻ ፡ ትከሻዋን ፡ ከላይ ፡ በሚደረብ ፡
ጨርቅ ፡ ሸፈነችና ፡ ሞቃት ፡ ካፖርት ፡ አጠለቀች ። የጌጥ ፡
ሙዳይዋንም ፡ ብድግ ፡ አድርጋ ፡ በጓሮ ፡ በር ፡ ወጥታ ፡ ሄደች ።
ደንገጡርዋም ፡ ሁለት ፡ ጥቅል ፡ ዕቃ ፡ ይዛ ፡ ተከተለቻት ። ወ
ደ ፡ አትክልቱም ፡ ቦታ ፡ ሄዱ ። የበረዶው ፡ ውሽንፍርም ፡ አላ
ባራም ፡ ነበር ። ነፋሱም ፡ ወጣቷን ፡ ኰብላይ ፡ ለማቆም ፡ የፈ
ለገ ፡ ይመስል ፡ ፊት ፡ ፊታቸውን ፡ ይመታቸው ፡ ጀመር ። ወ
ደ ፡ አትክልቱ ፡ መጨረሻ ፡ ጋ ፡ በጣም ፡ ደክሟቸው ፡ ደረሱ ።
በመንገዱም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የበረዶ ፡ ጋሪ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ነ
በር ። ፈረሶቹም ፡ ብርድ ፡ ስለገባቸው ፡ መቆም ፡ አቅቷቸው ፡
ነበር ። የቭላዲሚር ፡ የበረዶ ፡ ጋሪ ፡ ነጂ ፡ የሚቁነጠነጡትን ፡
ፈረሶች ፡ ለማስታገስ ፡ በጋሪው ፡ አጠገብ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡
ይንጐራደድ ፡ ነበር ። ወጣቷን ፡ ልጃገረድና ፡ ደንገጡርዋን ፡
እሠረገላው ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ እንዲቀመጡ ፡ ሠረገላ ፡ ነጂው ፡
ረዳቸው ፤ የተጠቀለለውንም ፡ ዕቃና ፡ የጌጡንም ፡ ሙዳይ ፡ እ
ሠረገላው ፡ ላይ ፡ ጫነ ፤ ቀጥሎም ፡ ልጓሙን ፡ ሳብ ፡ ሲያደርግ ፡ ፈ
ረሶቹ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ወደፊት ፡ ዘለሉ ። እንግዲህ ፡ የታሪካች
ን ፡ እመቤት ፡ የሆነችውን ፡ ለዕድሏና ፡ ለሠረገላ ፡ ነጂው ፡ ለቴ
ሬሽካ ፡ ጥበብ ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ወጣቱ ፡ አፍቃሪዋ ፡ እንመለስ ።

ቭላዲሚር ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ከቦታ ፡ ወደቦታ ፡ ሲዘዋወር ፡ ዋለ ። በኖርድሪኖ ፡ ወደሚገኘው ፡ ቄስ ፡ ጋ ፡ ሄዶ ፡ ጥያቄውን ፡ እንዲፈጽምለት ፡ እንደምንም ፡ ሊያግባባው ፡ ቻለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምስክር ፡ ለመፈለግ ፡ ወደሠፈሩ ፡ ባለርስቶች ፡ ዘንድ ፡ ሄደ ። መጀመሪያ ፡ የጐበኘው ፡ ድራቪን ፡ የተባለው ፡ ከሥራ ፡ የተሰናበተ ፡ የአርባ ፡ ዓመት ፡ መኰንን ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የዱሮው ን ፡ ጊዜ ፡ የፈረስ ፡ ዘበኞች ፡ ጉብዝና ፡ ያስታውሰኛል ፡ ሲል ፡ በሐሳቡ ፡ የሚስማማ ፡ መሆኑን ፡ ወዲያው ፡ ገለጸለት ። ሌሎ ቹን ፡ ሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ለማግኘት ፡ የሚያስቸግር ፡ አለመሆ ኑን ፡ በማረጋገጥም ፡ ቭላዲሚር ፡ ቆይቶ ፡ ምሣ ፡ እንዲበላ ፡ ጠየ ቀው ። እንዳለውም ፡ ከምሣ ፡ በኋላ ፡ እሪዙ ፡ እንደ ፡ ጦር ፡ የቆ መው ፡ ምስለኔ ፡ ሽሚት ፡ ከሰፈሩ ፡ የፖሊስ ፡ ሹም ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ብቅ ፡ አለ ። ይህ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ዕድሜው ፡ አሥራ ፡ስ ድስት ፡ ሲሆን ፡ ወደፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ የገባውም ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በቭላዲሚር ፡ ሐሳብ ፡ ከመስማማታ ቸውም ፡ በላይ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለርሱ ፡ ሲሉ ፡ መስዋዕት ፡ ለማድረግ ፡ ዝግጁ ፡ መሆናቸውን ፡ ገለጹለት ። ቭላዲሚርም ፡ በጋለ ፡ ስሜት ፡ አቀፋቸውና ፡ ዝግጅቱን ፡ ለመቀጠል ፡ ወ ደቤቱ ፡ ሄደ ።

ከጨለመ ፡ ቆይቶ ፡ ነበር ። ቭላዲሚር ፡ ለታማኙ ፡ ለቴሬ ሽካ ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ካስጠናው ፡ በኋላ ፡ ባለሶ ስት ፡ ፈረስ ፡ ሠረገላውን ፡ ሰጥቶት ፡ ወደ ፡ ኔናራዶቮ ፡ ላከ ው ፤ ለራሱም ፡ ትንሹን ፡ ባለአንድ ፡ ፈረስ ፡ ሠረገላ ፡ አስጭ ኖ ፡ በሁለት ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ወደምት ገኝበት ፡ ወደ ፡ ዣድሪኖ ፡ ሄደ ። መንገዱን ፡ ያወቀው ፡ ስለነ በርም ፡ ጉዞው ፡ ከሃያ ፡ ደቂቃ ፡ ይበልጥ ፡ የሚወስድ ፡ አልነ በረም ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ቭላዲሚር ፡ ወዲያው ፡ ከመንደሩ ፡ ተነሥቶ ፡ እንደሄደ ፡ ግልጥ ፡ ወደሆነ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ደረሰ ፤ ነፋስም ፡ ስለ ተነሣና ፡ የበረዶውም ፡ ውሽንፍር ፡ ስላየለ ፡ ማየት ፡ ቸገረው ።

መንገዱም ፡ በአንድ ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ በበረዶ ፡ ተሸፈነ ። እካ ባቢውንም ፡ ድብዝዝ ፡ ያለና ፡ ቢጫ ፡ የመሰለ ፡ የበረዶ ፡ ጭጋ ግ ፡ አልብሶት ፡ ሳለ ፡ በመካከሉ ፡ ነጭ ፡ የበረዶ ፡ ቅርፊቶች ፡ እየተጠመዛዘዙ ፡ ይወርዱ ፡ ነበር ። ሰማዩም ፡ ከመሬቱ ፡ ጋር ፡ ተጋጠመ ። ቭላዲሚር ፡ በድንገት ፡ አንድ ፡ ሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። ከዚያ ፡ ለመውጣትና ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡ ለመግባት ፡ ቢሞክር ም ፡ ከንቱ ፡ ድካም ፡ ሆነበት ። ፈረሱም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እበረ ዶው ፡ ክምር ፡ ላይ ፡ ተሳስቶ ፡ እየወጣ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ደግ ሞ ፡ ጉርጓድ ፡ አደናቅፎት ፡ እየወደቀ ፡ አቅጣጫው ፡ ወደአል ታወቀ ፡ ቦታ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቀጠለ ። ሠረገላውም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይገለበጥ ፡ ነበር ። ቭላዲሚር ፡ አጥብቆ ፡ ያስብ ፡ የ ነበረው ፡ መንገዱ ፡ እንዳይሳሳተው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ለርሱ ፡ እንደመሰለው ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፡ ወደ ዣድሪኖ ፡ ጫካ ፡ ሳይደርስ ፡ ቀረ ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ አስር ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ አለፈ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የዣድሪኖ ፡ ጫካ ፡ የት ፡ እን ዳለ ፡ አልታየም ። ቭላዲሚር ፡ ብዙ ፡ የበረዶ ፡ ክምር ፡ ባለበት ፡ ግልጥ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ መጓዝ ፡ ጀመረ ። የበረዶው ፡ ውሽንፍር ፡ ገና ፡ አላባራም ፡ ነበር ፤ ሰማዩም ፡ ገና ፡ ደመና ፡ እንደለበሰ ፡ ነ በር ። ፈረሱ ፡ መድከም ፡ ጀመረ ፤ ቭላዲሚር ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ያለማቋረጥ ፡ እስከ ፡ ወገቡ ፡ ድረስ ፡ እበረዶ ፡ ውስጥ ፡ እየገባ ፡ ቢወጣም ፡ ላብ ፡ አጠመቀው ።

በመጨረሻ ፡ አቅጣጫውን ፡ ስቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ እን ደሚጓዝ ፡ ተገነዘበ ። ፈረሱን ፡ ገታና ፡ የመንገዱን ፡ አቅጣጫ ፡ ለማስታወስና ፡ ለማጣራት ፡ በሐሳብ ፡ ባህር ፡ ሰመጠ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደቀኝ ፡ መዞር ፡ እንደነበረበት ፡ ተረዳ ። ወደቀኝም ፡ ዞረ ። ፈረሱ ፡ ግን ፡ መላወስ ፡ እንኳ ፡ አቃተው ። መጓዝ ፡ ከጀ መረ ፡ ከአንድ ፡ ሰዓት ፡ በላይ ፡ ሆኖታል ። እንግዲህ ፡ ዣድሪ ኖ ፡ ሩቅ ፡ መሆን ፡ የለበትም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢጓዝ ፡ ቢጓዝ ፡ ሜ ዳው ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ሆነበት ፤ የሚታየው ፡ የበረዶ ፡ ክ

ምርና ፡ መሿለኪያ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ሥረገላውም ፡ በየጊዜው ፡ ሲገለበጥ ፡ ቭላዲሚር ፡ ያቀናው ፡ ነበር ። ጊዜው ፡ አለፈ ። ቭ ላዲሚር ፡ ከባድ ፡ ጭንቅ ፡ ያዘው ።

በመጨረሻ ፡ አንድ ፡ ጥቁር ፡ ነገር ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ታየ ። ቭላዲሚር ፡ ፈረሱን ፡ ወደዚህ ፡ አቅጣጫ ፡ መራው ። ቀረብ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጫካ ፡ እፊት ፡ ለፊቱ ፡ አየ ። ተመስገን ፡ አ ምላኬ ፡ ልደርስ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ አሰበ ። ያንን ፡ ዱሮ ፡ የሚያው ቀውን ፡ መንገድ ፡ ቶሎ ፡ አገኘዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ በማድ ረግና ፡ ዣድሪኖም ፡ ከጫካው ፡ ማዶ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ በማ ለት ፡ በጫካው ፡ በኩል ፡ አልፎ ፡ ሄደ ። መንገዱንም ፡ ወዲያ ው ፡ አገኘውና ፡ ቅጠላቸውን ፡ ከረምት ፡ በአረገፈው ፡ ዛፎች ፡ ጥላ ፡ ስር ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ቦታ ፡ ነፋሱ ፡ ኃይለኛ ፡ አ ልነበረም ፡ መንገዱም ፡ ለስላሳ ፡ ነበር ። ፈረሱም ፡ አዲስ ፡ ብር ታት ፡ አገኘ ፡ ቭላዲሚርም ፡ ነቃ ፡ አለ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢሄድ ፡ ቢሄድ ፡ ዣድሪኖን ፡ አላይ ፡ አለ ። ጫካውም ፡ ማለቂያ ፡ የሌለው ፡ ሆነ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚጓ ዝበት ፡ ጫካ ፡ የማያውቀው ፡ ጫካ ፡ መሆኑን ፡ በሚያስቅቅ ፡ ስሜት ፡ ተገነዘበው ። ተስፋ ፡ ስለቆረጠም ፡ ፈረሱን ፡ ገረፈው ። ምስኪኑ ፡ እንስሳም ፡ መጋለብ ፡ ጀመረ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ ደከመ ። ዕድለ ፡ ቢሱ ፡ ቭላዲሚር ፡ ሊያበረታው ፡ ቢሞክርም ፡ ከአስራምስት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ፈረሱ ፡ ድክምክም ፡ ብሎ ፡ ይ ጎተት ፡ ጀመረ ።

ጫካውም ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ዘርዘር ፡ እያለ ፡ ሄደ ። በመጨ ረሻም ፡ ቭላዲሚር ፡ ከጫካው ፡ ውስጥ ፡ ጨርሶ ፡ ወጣ ። ዣድሪ ኖን ፡ ግን ፡ ለማየት ፡ አልቻለም ። ዕኩለ ፡ ሌሊት ፡ ገደማ ፡ የ ሆነም ፡ መሰለው ። እንባውም ፡ በጉንጩ ፡ ላይ ፡ ወረደ ፤ አቅጣ ጫውን ፡ ሳያውቅም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ይሄድ ፡ ጀመር ። የበረዶው ፡ ዶፍም ፡ አባራ ፤ ደመናዎቹም ፡ ተበተኑ ፤ በፊትለፊቱም ፡ የጐ በረ ፡ ነጭ ፡ የበረዶ ፡ ምንጣፍ ፡ ያለበሰው ፡ ሜዳ ፡ አገኘ ። ሌሊ

ቱ ፡ ጠራ ፡ ያለ ፡ ነበር ። ትንሽ ፡ እራቅ ፡ ብሎ ፡ እጅብ ፡ ያሉ ፡ ቤቶች ፡ ያሉበት ፡ መንደር ፡ አየ ። ቭላዲሚር ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ አመራ ። ከሠረገላው ፡ ላይ ፡ ዱብ ፡ ብሎ ፡ ወርዶ ፡ ወደመጀመሪያው ፡ ጐጆ ፡ ሮጠ ፡ ሄደና ፡ መስኰቱን ፡ አንኳኳ ። ከጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላም ፡ የመስኰቱ ፡ የእንጨት ፡ መዝጊያ ፡ ተከፈተና ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ግራጫ ፡ ጢሙን ፡ ብቅ ፡ አድርጐ ፤ « ምን ፡ ይፈልጋሉ? » አለ ። « ዣድሪኖ ፡ ከዚህ ፡ እሩቅ ፡ ነውን?» «ዣድሪኖ ፤ እሩቅ ፡ ነወይ? » « አዎን ፤ አዎን ፤ እሩቅ ፡ ነው ፡ ወይ ፡ የምለው?» «እሩቅ ፡ አይደለም ፤ አስር ፡ ቬርስታ ፡ ያህል ፡ ቢሆን ፡ ነው ።» ይህን ፡ መልስ ፡ ሲሰማ ፡ ቭላዲሚር ፡ ጸጉሩን ፡ ነጨ ፤ የሞቱን ፡ ፍርድ ፡ እንደሰማ ፡ ሰውም ፡ ድርቅ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

«ለነገሩ ፡ ከየት ፡ ነው ፡ የመጡት? » ሲል ፡ ሽማግሌው ፡ ሰውየ ፡ ጠየቀ ። ቭላዲሚር ፡ ጥያቄውን ፡ ለመመለስ ፡ ብርታት ፡ አልነበረውም ። «ወደ ፡ ዣድሪኖ ፡ የሚወስደኝ ፡ ፈረስ ፡ ያገኙልኛል ፡ ወይ?» ሲል ፡ ጠየቀ ፡ ቭላዲሚር ። «አየ ፡ ጉድ ፤ ፈረስ ፡ እንዳለን ፡ ሰው ፡ ሁሉ! » ሲል ፡ መለሰ ፡ ባላገሩ ፡ ሰውየ ። «ይኸስ ፡ ይቅር ፤ መንገዱን ፡ የሚያሳየኝ ፡ ሰው ፡ ያገኙልኛል ? የጠየቀውን ፡ እከፍላለሁ ።» «ጥቂት ፡ ይቆዩ ፡ » አለ ፡ ሽማግሌው ፡ ሰውየ ፡ መስኰቱን ፡ ለመዝጋት ፡ ወደታች ፡ ሳብ ፡ እያደረገ ። «ልጄን ፡ እልከውና ፡ መንገዱን ፡ ያሳይዎታል ።» ቭላዲሚር ፡ ጠበቀ ። ገና ፡ አንድ ፡ ደቂቃ ፡ እንኳ ፡ ሳያልፍ ፡ እንደገና ፡ መስኰቱን ፡ መቆርቆር ፡ ጀመረ ። መዝጊያው ፡ ወደ ላይ ፡ ተነሳና ፡ ያው ፡ የቅድሙ ፡ ጢም ፡ ብቅ ፡ አለ ። « ምን ፡ ይፈልጋሉ?» «ልጅዎ ፡ የት ፡ አለ ።» «ይመጣል ፤ ጫማውን ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ነው ። በርዶዎት ፡ እንደሆን ፡ ይግቡና ፡ ሞቅ ፡ ይበልዎት ።» «የለም ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ። ይልቅ ፡ ልጅዎን ፡ ቶሎ ፡ ይላኩልኝ ። »

በሩ ፡ ሲጢጥ ፡ አለ ። ዱላ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡

ከቤት ፡ ወጣና ፡ ወደፊት ፡ ቀድሞ ፡ እየሄደ ፡ መንገዱን ፡ ያሳይ ፡ ጀመር ። ብዙ ፡ የበረዶ ፡ ቁልል ፡ ስለነበር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆም ፡ ይልና ፡ መንገዱን ፡ ይፈልጋል ። «ስንት ፡ ሰዓት ፡ ነው? » ሲል ፡ ቭላዲሚር ፡ ጠየቀው ። « እንግዲህ ፡ ሊነጋ ፡ ምንም ፡ አልቀረው ፡ » ሲል ፡ መለሰ ፡ ወጣቱ ፡ ልጅ ። ቭላዲሚር ፡ ዳግመኛ ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ አልተናገረም ።

ዣድሪኖ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፡ ይጮህ ፡ ነበር ፤ ገሀም ፡ ቀዶ ፡ ነበር ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ተዘግቶ ፡ ነበር ። ቭላዲሚር ፡ መንገድ ፡ ለመራው ፡ ልጅ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጠውና ፡ ወደ ፡ ቄሱ ፡ ቤት ፡ ሄደ ። በአጥር ፡ ግቢው ፡ ውስጥ ፡ ባለሶስት ፡ ፈረስ ፡ ሠረገላ ፡ አልነበረም ። እንዴት ፡ ያለ ፡ ወሬ ፡ የጠበቀው ፡ ይመስላችኋል!

እስቲ ፡ ደግሞ ፡ ወደተከበሩት ፡ የኔናራዶቮ ፡ መንደር ፡ ባለቤቶች ፡ ዘንድ ፡ እንመለስና ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ እንመልከት ።

ምንም ፡ አልሆኑ!

ጨዋዎቹ ፡ ባልና ፡ ሚስቶች ፡ ጧት ፡ ተነስተው ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። ጋቭሪላ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ የሌሊት ፡ ቆቡንና ፡ ስስ ፡ ኰቱን ፡ ለብሷል ፤ ፕራስኰቭያ ፡ ፔትሮቭናም ፡ ወፍራም ፡ የጧት ፡ ልብስ ፡ ለብሳለች ። የሻዩ ፡ ጀበና ፡ ቀረበ ፤ ጋቭሪላ ፡ ጋቭሪሎቪችም ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ እንዴት ፡ እንዳደረች ፡ ለማስጠየቅ ፡ አንዷን ፡ ገረድ ፡ ላካት ። ገረድዮዋም ፡ ተመልሳ ፡ መጥታ ፡ ወይዘሪት ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ደህና ፡ አለማደሯንና ፡ ሆኖም ፡ አሁን ፡ የተሻላት ፡ መሆኗን ፤ ወደ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊያ ፡ ቤትም ፡ በፍጥነት ፡ እንደምትመጣ ፡ አስታወቀች ። ያነየውንም ፡ በሩ ፡ ተከፈተና ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ገባች ፤ አባትና ፡ እናቷንም ፡ እጅ ፡ ነሳች ።

« እራስ ፡ ምታትሽ ፡ ተሻለሽ ፡ ወይ ፡ ማሻ? » ሲል ፡ ጋቭሪላ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ ጠየቃት ። « ተሽሎኛል ፡ አባብዬ ፡ » ስት

ል ፡ መለሰች ፡ ማሻ ። «እራስሽን ፡ ያሳመመሽ ፡ ምድጃው ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ ማሻዬ ፡» አለች ፡ ፕራስኮቭያ ፡ ፔትሮቭና ። «ምናልባት ፡ እሱ ፡ ይሆናል ፡» ስትል ፡ መለሰች ፡ ማሻም ።

ቀኑ ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ ሳይሆን ፡ አለፈ ። ያንኑ ፡ ሌሊት ፡ ግን ፡ ማሻ ፡ ታመመች ። ከአቅራቢያው ፡ ከተማም ፡ ሐኪም ፡ ተጠርቶ ፡ እንዲመጣ ፡ ሰው ፡ ተላከ ። ሐኪሙ ፡ በማግሥቱ ፡ ማታ ፡ ሲመጣ ፡ ልጂቱ ፡ ቅዠት ፡ ይዟት ፡ አገኛት ። ኃይለኛ ፡ ትኩሳት ፡ ስላደረባትም ፡ ምስኪኗ ፡ ልጃገረድ ፡ ሁለት ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ በሞትና ፡ በሕይወት ፡ መካከል ፡ ቆየች ።

ስለመኰብለሏ ፡ ጉዳይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ያን ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ የጻፈቻቸውም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ተቃጥለው ፡ ነበር ። የማሻ ፡ ደንገጡርም ፡ የጌታዋን ፡ ቁጣ ፡ በመፍራት ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ አልተናገረችም ፡ ነበር ። ቄሱና ፡ ከሥራ ፡ የተሰናበተው ፡ መኰንን ፤ እረዛሙ ፡ ምስለኔና ፡ ወጣቱ ፡ ልጅ ፡ በየበኩላቸው ፡ ዝም ፡ አሉ ። ሠረገላ ፡ ነጂው ፡ ቴሬሽካም ፡ እንኳንስ ፡ በጤናውና ፡ ሲሰክር ፡ እንኳ ፡ ቃል ፡ አይስትም ፡ ነበር ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ምስጢሩን ፡ የሚያውቁት ፡ ከስድስት ፡ በላይ ፡ የሚሆኑት ፡ አድመኞች ፡ ነገሩን ፡ ደብቀው ፡ ዝም ፡ አሉ ። ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ግን ፡ በማያቋርጠው ፡ ቅዠቷ ፡ ምስጢሯን ፡ አወጣችው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የምትለፈልፈው ፡ ቃል ፡ የሚጨበጥና ፡ የተጣራ ፡ ባለመሆኑ ፡ ከአልጋዋ ፡ አጠገብ ፡ ያልተለየቻት ፡ እናቷ ፡ ከማሻ ፡ ቅዠት ፡ ለመረዳት ፡ የቻለችውን ፡ ያህል ፡ ልጅዋ ፡ ከቭላዲሚር ፡ ኒኰላየቪች ፡ ጋር ፡ ከፉኛ ፡ ፍቅር ፡ እንደያዛትና ፡ የሕመሟም ፡ ምክንያት ፡ ይሄው ፡ ፍቅር ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አሰበች ። ባልዋንና ፡ ጥቂቶች ፡ ጐረቤቶቿን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አማከረች ። በመጨረሻም ፡ የማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ዕድል ፡ ጥንቱኑ ፡ የተወሰነ ፡ ለመሆኑና ፤ ሰው ፡ ከታሰበለት ፡ ዕድሉ ፡ የማያመልጥ ፡ መሆኑንም ፤

ድህነትም ፡ ቢሆን ፡ ኃጢአት ፡ እንዳልሆነ ፤ ሰው ፡ መኖር ፡ ያለ በትም ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ እንጂ ፡ ከገንዘብ ፡ ከረጢት ፡ ጋር ፡ እን ዳልሆነ ፤ ሁሉም ፡ ተስማሙ ። ሰው ፡ ለፈጸመው ፡ ተግባር ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሲያጣ ፡ መጽናኛ ፡ መንገድ ፡ መፈለጉ ፡ የተ ለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ።

የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ልጂቱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ እየተሻላት ፡ ሄደ ። ቭላዲሚርም ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጋቭሪላ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ ቤ ት ፡ ሳይመጣ ፡ ቀረ ። የቀረበት ፡ ምክንያት ፡ የአቀባበላቸውን ፡ ቀዝቃዛነት ፡ በመፍራት ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ ወደርሱ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ መልእክተኛ ፡ ሄዶ ፡ ልጂቱን ፡ እንዲያገባ ፡ ዘመዶቿ ፡ የሚፈቅዱለት ፡ መሆናቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ያልታሰበ ፡ ደስታ ፡ አመጣለት ። የኔናራዶቮ ፡ ጌታዎች ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልመና ፡ ሲያቀርቡለት ፡ እሱ ፡ ግን ፡ እብድ ፡ የጻፈው ፡ የመሰለ ፡ ደብ ዳቤ ፡ ስለላከላቸው ፡ በጣም ፡ ሳይገርማቸው ፡ አልቀረም ። በደ ብዳቤው ፡ ላይ ፡ ዳግመኛ ፡ እበራቸው ፡ እንደማይደርስና ፡ እን ደርሱ ፡ ያለውን ፡ ምስኪን ፡ ፍጡር ፡ መርሳት ፡ እንዳለባቸው ም ፤ ካሁን ፡ ወዲያ ፡ የቀረው ፡ ተስፋም ፡ ሞት ፡ ብቻ ፡ እንደሆ ነ ፡ ገለጸላቸው ። ከጥቂት ፡ ቀናት ፡ በኋላም ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ እንደገባ ፡ ተረዱ ። ይህ ፡ የሆነው ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፰፻፲፪ ዓ ፡ ም ፡ ነበር ።

ይህን ፡ ወሬ ፡ ለምታገግመው ፡ ማሪያ ፡ ደፍረው ፡ ሳይነ ግሯት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆዩ ። እሷ ፡ እራሷ ፡ ስለቭላዲሚር ፡ አን ስታ ፡ አታውቅም ፡ ነበር ። ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ የቭላዲ ሚርን ፡ ስም ፡ በቦሮዲኖ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ በጀግንነት ፡ ከተሸ ለሙትና ፡ በጠና ፡ ከቆሰሉት ፡ ሰዎች ፡ የስም ፡ ዝርዝር ፡ ው ስጥ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ በድንጋጤ ፡ ነፍሷን ፡ ሳተች ፤ በዚህ ፡ ምክ ንያት ፡ ህመሟ ፡ ያገረሽባታል ፡ ተብሎም ፡ ተፈርቶ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ምሥጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይድረሰውና ፡ ድንጋጤ

ዋ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሳያስከትል ፡ ቀረ ።

ወዲያውኑ ፡ ግን ፡ አዲስ ፡ ሐዘን ፡ ወደቀባት ፤ አባትዋ ፡ እርስታቸውን ፡ ሁሉ ፡ ትተውላት ፡ ሞቱ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የወረሰችው ፡ ሐብት ፡ ሊያጽናናት ፡ አልቻለም ። የምስኪን ፡ እናቷ ፡ የፕራስኮቭያ ፡ ፔትሮቭና ፡ ሐዘን ፡ ሙሉ ፡ ተካፋይ ፡ ከመሆኗ ፡ በስተቀር ፡ እንደማይለያዩም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባችላት ። የሐዘን ፡ ትዝታ ፡ የተመላበትን ፡ የኔናራዶቮን ፡ መንደር ፡ ለቀው ፡ በእንትና ፡ መንደር ፡ ባለው ፡ እርስታቸው ፡ ላይ ፡ ለመኖር ፡ ሄዱ ።

እዚህም ፡ እንደዚሁ ፡ ውቢቱንና ፡ ሐብታሟን ፡ ልጃገረድ ፡ ለማግባት ፡ የሚፈልጉ ፡ ወንዶች ፡ ያንዣብቡ ፡ ነበር ፤ እርሷ ፡ ግን ፡ አንዳቸውንም ፡ ትንሽ ፡ እንኳ ፡ አላደፋፈረቻቸውም ፡ ነበር ። እናትዮዋ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሕይወት ፡ ጓደኛ ፡ እንድትመርጥ ፡ ታግባባት ፡ ነበር ፤ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ግን ፡ እራሷን ፡ ትነቀንቅና ፡ ሐሳብ ፡ ይይዛታል ። ቭላዲሚር ፡ በሕይወት ፡ የለም ፤ ፈረንሳዮች ፡ ወደ ፡ ሞስኮ ፡ ከተማ ፡ በገቡበት ፡ እጥቢያ ፡ እዚያው ፡ ሞተ ። ማሻ ፡ የርሱን ፡ ትዝታ ፡ የተቀደሰ ፡ አድርጋ ፡ ያዘችው ፤ እርሱን ፡ የሚያስታውሳትንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በጥንቃቄ ፡ አስቀመጠች ፤ ለምሳሌ ፡ ያነበበውን ፡ መጽሐፍ ፤ የሳላቸውን ፡ ሥዕሎች ፤ ከመጽሐፍ ፡ ለርሷ ፡ የገለበጠውን ፡ የሙዚቃና ፡ የግጥም ፡ ስልት ፡ ጠብቃ ፡ አኖረች ። የጐረቤት ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምተው ፡ በርሷ ፡ ጽኑነት ፡ ታማኝነት ፡ አለቅጥ ፡ ተደነቁ ፤ አርቴሚዛ[6] ፡ ሐዘኗን ፡ አስወግዶ ፡ ልቧን ፡ ለመማረክ ፡ የሚችለውን ፡ ዕድለኛ ፡ ሰው ፡ ለማየትም ፡ ጓጉተው ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ ጦርነቱን ፡ ድል ፡ አደረግንና ፡ ወታደሮቻችንም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ተመልሰው ፡ መጡ ። ሕዝቡም ፡ ከየቤቱ ፡ ሮጦ ፡ እየወጣ ፡ ሊቀበላቸው ፡ ሄደ ። ሙዚቀኞችም ፡ ከጠላት ፡ የነጠቁትን ፡ ዜማ ፡ ይጫወቱ ፡ ጀመር ፤

ለምሳሌ ፡ Vive Henri-Quatre * ፤ ቲሮሌዝ ፡ ቫልስ ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከ « ላ - ገርኮንድ ፡ » የተቀዳ ፡ የኦፔራ ፡ ዜማ ፡[8] ተጫወቱ ። በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ እግር ፡ ሆነው ፡ የዘመቱት ፡ የጦር ፡ መኰንኖች ፡ አሁን ፡ ጉልምሰውና ፡ በስለው ፤ ሜዳይም ፡ አንጠልጥለው ፡ ተመለሱ ። ወታደሮችም ፡ በወሬአቸው ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ የፈረንሳይና ፡ የጀርመን ፡ ቃል ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ እያደረጉ ፡ በደስታ ፡ ይጫዋወቱ ፡ ነበር ። የማይረሳ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ! የደስታና ፡ የኩራት ፡ ጊዜ ፡ ነበር! እናት ፡ አገሬ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ የመስኰባውያን ፡ ልብ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ይመታ ፡ ነበር! እንደገና ፡ የመገናኘት ፡ እንባ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ልብ ፡ ይነካ ፡ ነበር! ለሃገራችንና ፡ ለቄሣሩ ፡ የነበረን ፡ የተዋሃደ ፡ የኩራትና ፡ የፍቅር ፡ ስሜት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ የተባበረ ፡ ነበር! ለቄሣሩስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰዓት ፡ ነበር!

የሩሲያ ፡ ሴቶች ፡ ሁናቴ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ የሚደነቅ ፡ ነበር ። የተለመደው ፡ የመሽኰርመም ፡ ስሜታቸው ፡ ጥሏቸው ፡ ጠፋ ፤ ድል ፡ አድራጊዎቹን ፡ በተቀበሉ ፡ ጊዜ ፡ የነበራቸው ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ በውነቱ ፡ የሚያሰክር ፡ ነበር ።

ሴቶች ፡ ሁራ! ብለው ፡ እየጮሁ ፡
ቫቫቸውን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወረወሩ ።[9]

መስኰባዊ ፡ ሴት ፡ ልቡን ፡ በደስታ ፡ ያልመላችው ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ የት ፡ ይገኝ ፡ ነበር?

በዚህ ፡ ዕፁብ ፡ ድንቅ ፡ በሆነ ፡ ሰዓት ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ከእናቷ ፡ ጋር ፡ በእንትና ፡ አውራጃ ፡ ትኖር ፡ ነበር ። ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ሁለቱ ፡ ዋና ፡ ከተማዎች ፡ ሲመለሱ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ እንደተቀበሏቸውም ፡ አላየችም ። ሆኖም ፡ የደስ

---

* Vive Henri-Quatre — አንሪ ፡ አራተኛው ፡ ለዘላለም ፡ ይኑር ። ( በፈረንሳይኛ ። )[7]

ታው ፡ ስሜት ፡ በመንደር ፡ ውስጥ ፡ የበለጠ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ብቅ ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ ዘወትር ፡ ሰውን ፡ ይማርክ ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ አፍቃሪ ፡ ነኝ ፡ ባይ ፡ ባለ ፡ ጥቁር ፡ ልብስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ነበረበት ።

ቀደም ፡ ብለን ፡ እንደተናገርነው ፡ ሁሉ ፤ ማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ ለወንዶች ፡ ፊት ፡ ባትሰጥም ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ቡርሚን ፡ የተባለ ፡ ቊስለኛ ፡ የፈረስ ፡ ዘበኛ ፡ ኰሎኔል ፡ ወደርሷ ፡ ዘንድ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ማፈግፈግ ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ። እርሱ ፡ በደረቱ ፡ ላይ ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ሜዳይ ፡ ከማን ጠልጠሉ ፡ ሌላ ፡ የሰፈሩ ፡ ሴቶች ፡ እንደሚሉት ፡ « ደማም ፡ ነበር ። » ዕድሜውም ፡ ወደ ፡ ሃያ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ገደማ ፡ ነበር ። በማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ እርስት ፡ አጠገብ ፡ በሚገኝ ፡ እርስቱ ፡ ላይ ፡ ለእረፍት ፡ መጥቶ ፡ ይቀመጣል ። ማሪያ ፡ ጋብሪሎቭናም ፡ ከሌሎቹ ፡ ይልቅ ፡ እርሱን ፡ መረጠች ። እሱ ፡ አጠገቧ ፡ ሲኖር ፡ የሐዘን ፡ ስሜቷ ፡ ተወግዶ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ያድርባታል ። በሁናቴዋም ፡ አንዳችም ፡ የቅናትና ፡ የፍቅር ፡ ስሜት ፡ አታሳይም ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ የተመለከታት ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ነበር ፤

Se amor non è, che dunque?...*

ቡርሚን ፡ በውነቱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚማርክ ፡ ወጣት ፡ ነበር ። ሴቶች ፡ የሚወዱት ፡ ጠባይም ፡ ነበረው — ሥልጡን ፤ ትሁትና ፡ የማይግደረደር ፡ ከመሆኑ ፡ በስተቀር ፡ ቀልደኛም ፡ ነበር ። በማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ ፊት ፡ የተራ ፡ ሰውነትና ፡ የነፃ ነት ፡ ስሜት ፡ ያሳይ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የምትናገረውንና ፡ የምታደርገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሐሳቡም ፡ በዓይኑም ፡ እጥ

---

*ይህ ፡ ፍቅር ፡ ካልሆነ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ሊሆን ፡ ነው? ... (በኢጣልያንኛ ።)

ብቆ ፡ ይከታተል ፡ ነበር ። ዝምተኛና ፡ ጨዋ ፡ ይመስላል ፤ ሰዎች ፡ እንደሚያወሩት ፡ ግን ፡ ዱሮ ፡ ጨዋታ ፡ ወዳድ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ በማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ ዘንድ ፡ የዱሮ ፡ ጠባዩ ፡ ጉዳትን ፡ አላስከተለበትም ፤ ምክንያቱም ፡ እሷ ፡ ( እንደቀሩት ፡ ወጣት ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ) ደፋሮችንና ፡ ባለጌዎችን ፡ ያላንዳች ፡ ቅሬታ ፡ ይቅርታ ፡ ስለምታደርግላቸው ፡ ነው ።

ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ስሜቷን ፡ የቀሰቀሰውና ፡ ያስገረማት ፡ ነገር ፡ የዚህ ፡ የወጣት ፡ ፈረሰኛ ፡ መልካም ፡ ጠባዩና ፡ አስደሳች ፡ ጨዋታው ፡ ወይም ፡ መልከ ፡ ቀናነቱና ፡ በሻሽ ፡ የተጠመጠመው ፡ እጁ ፡ ሳይሆን ፤ እርጋታው ፡ ነበር ። መልካም ፡ ስሜት ፡ እንዳሳደረችበት ፡ ገብቷታል ፤ እሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ብልህና ፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ ልማድ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ እሷ ፡ ለርሱ ፡ ያላት ፡ ስሜት ፡ ከአንገት ፡ በላይ ፡ እንዳልሆነ ፡ ያውቃል ፤ ታዲያ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ እግሯ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ወደድኩሽ ፡ በማለት ፡ ፍቅሩን ፡ ያልገለጸላት? ምንድን ፡ ነው ፡ ያገደው? ከዕውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ ጋር ፡ የማይላቀቀው ፡ ሐፍረት ፡ ይሆን? ወይስ ፡ ኩራት ፡ ይሆን? ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ሴቶችን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ የብልጠት ፡ ዘዴ ፡ ነው? ሰውየውን ፡ ለማወቅ ፡ ቸገራት ። በነገሩ ፡ ብዙ ፡ ካሰበችበት ፡ በኋላ ፡ ዝም ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ከሐፍረት ፡ የተነሳ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ቆረጠች ፤ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ በማድረግም ፡ ወደፊት ፡ ልታደፋፍረውና ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ሲኖርም ፡ ደርባባነትዋን ፡ ልታሳየው ፡ አሰበች ። አንድ ፡ ያልታሰበ ፡ ዘዴ ፡ ፈጥራም ፡ ፍቅሩን ፡ የሚገልጽበትን ፡ ሰዓት ፡ ጓጉታ ፡ ጠበቀች ። ምስጢራዊ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መቸም ፡ የሴቶችን ፡ ልብ ፡ ይበላዋል ። ያቀደችው ፡ ዘዴ ፡ ያዘላት ፤ የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ቡርሚንን ፡ አፈዘዘችው ፤ ጥቋቁር ፡ ዓይኖቹም ፡ የማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭናን ፡ ፊት ፡ አተኩረው ፡ ይመለከቱ ፡ ስለነበር ፡ ፍቅሩን ፡ የሚገልጽበት ፡ ሰዓት ፡ የተቃረበ ፡ መሰለ ። የጐረቤቱም ፡ ሰዎች ፡ ጉዳ



ባለቅኔው ፡ ኮንስታንቲን ፡ ባቲዩሽኮቭ ( ፲፯፻፹፯ — [illegible] ) ።
ፑሽኪን ፡ በወጣትነቱ ፡ ዘመን ፡ ግጥሞቹን ፡ በትልቅ ፡ አድናቆት ፡ ይመለ
ከታቸው ፡ ነበር ።



ፔትር ፡ ቻአዳዬቭ ( ፲፯፻፺፬ — ፲፰፻፶፮ ዓ. ም. ) ። በፑሽኪን ፡ ር
ዕዮተ ፡ ዓለም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተፅዕኖ ፡ ያለው ፡ ደራሲና ፡ ፈላስፋ ።



ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሩሲያ ፡ ባለቅኔ ፡ ቫሲሊይ ፡ዡኮቭስኪይ ( ፲፯፻፸፭ — ፲፰፻፵፬ ዓ. ም. ) ። በ ፲፰፻፲፪ ዓ. ም. ራሱን ፡ የሚያሳየውን ፡ ሥዕል ፡ ለፑሽኪን ፡ በገጸ ፡ በረከት ፡ መልክ ፡ ሰጠው ። ሥዕሉ ፡ « ለአሸነፈው ፡ ተማሪ ፡ ከተሸነፈው ፡ አስተማሪ ፡ የተሰጠ ፡ መታሰቢያ » የሚል ፡ ነበር ።



በ ፲፰፻፳፰ ዓ. ም. ፑሽኪን ፡ ይኖር ፡ የነበረበት ፡ የተርዞፍ ፡ መንደር ።



በባህቺሳራይ ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ፑሽኪን ፡
በግጥሞቹ ፡ ያሞገሠው ፡ « የዕንባ ፡ ፏፏቴ » ።

ዩን ፡ እንዳለቀ ፡ ነገር ፡ ቆጥረውት ፡ ስለጋብቻው ፡ ቀን ፡ ያወ
ሩ ፡ ነበር ። ደጊቱ ፡ ፕራስኮቭያ ፡ ፔትሮቭናም ፡ እነሆ ፡ ልጅ
ቋ ፡ በመጨረሻ ፡ ተገቢ ፡ ባል ፡ ስላገኘች ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላት ።
ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አሮጊቷ ፡ የማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡
እናት ፡ ከእንግዳ ፡ ቤት ፡ ሆነው ፡ ካርታ ፡ ሲደረድሩ ፡ ሳለ ፡ ቡር
ሚን ፡ ገባና ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭናን ፡ ጠየቀ ። አሮጊቷም ፤ « በ
አትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ያለችው ፤ ሂድ ፡ ወደርሷ ፡ ጋ ፤ እኔ ፡ እ
ዚህ ፡ እጠብቃችኋለሁ ፡» አሉት ። ቡርሚን ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ፤ አ
ሮጊቷም ፡ አማትበው ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ አሰቡ ፤ « ምናልባት ፡
ዛሬ ፡ ጉዳዩ ፡ ፍጻሜ ፡ ያገኝ ፡ ይሆናል ።»
ቡርሚን ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭናን ፡ በአንድ ፡ የኩሬ ፡ ውኃ ፡
አጠገብ ፡ በዛፍ ፡ ስር ፡ ተቀምጣና ፡ መጽሐፍ ፡ በእጅዋ ፡ ይዛ ፡
አገኛት ። የለበሰችው ፡ ቀሚስ ፡ ነጭ ፡ ከመሆኑ ፡ ጋር ፡ ልክ ፡
የአንድ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ እመቤት ፡ ትመስል ፡ ነበር ።
የተለመደውን ፡ የሰላምታ ፡ ቃል ፡ ካቀረበችለት ፡ በኋላ ፡ ሆን ፡
ብላ ፡ ጭውውቱን ፡ አቋረጠችው ፤ ይሄውም ፡ ሐፍረታቸውን ፡
ለማጋነንና ፡ ይህ ፡ ሐፍረት ፡ እንዲወግድም ፡ ቁርጠኛውን ፡ የፍ
ቅር ፡ ቃል ፡ በድንገት ፡ አፍርጦ ፡ እንዲነግራት ፡ ስትል ፡ ነው ።
እንዳሰበችውም ፡ ሆነ ። ቡርሚን ፡ የገጠመው ፡ ሁናቴ ፡ መው
ጫ ፡ በር ፡ የሌለበት ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀ
ምሮ ፡ ፍቅሩን ፡ የሚገልጽበት ፡ አጋጣሚ ፡ ሰዓት ፡ ይጠብቅ ፡
እንደነበር ፡ በማስረዳት ፡ አሁን ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ትሰጠው ፡ ዘን
ድ ፡ ጠየቃት ። ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭናም ፡ መጽሐፏን ፡ አጥፋ ፡
በጥያቄው ፡ የተስማማች ፡ መሆንዋን ፡ ለማሳየት ፡ ያይኗን ፡ ቆ
ብ ፡ ደፋ ፡ አደረገች ።
« እወድሻለሁ ፤ ከልቤ ፡ አፈቅርሻለሁ ፡ » አለ ፡ ቡርሚን ።
( ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭና ፡ በሐፍረት ፡ ፊቷ ፡ ስለቀላ ፡ እራሷን ፡
ወደታች ፡ ደፋ ፡ አደረገች ። ) ንግግሩንም ፡ በመቀጠል ፤ « አ
ንቺን ፡ በየቀኑ ፡ በማየትና ፡ ድምጽሽን ፡ በመስማት ፡ የደስታ ፡

4—1747

ልማድ ፡ በመፍጠሬ ፡ አጥፍቻለሁ ፡ ...» ( እዚህ ፡ ላይ ፡ ማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ የሴን-ፕሬን ፡ የመጀመሪያ ፡ ደብዳቤ ፡ አስታወሰች ... ። ) « አሁን ፡ ዕድሌን ፡ ለማሸነፍ ፡ ጊዜው ፡ ዘግይቷል ። ከአሁን ፡ ወዲያ ፡ ያንቺና ፡ ወደር ፡ የሌለው ፡ የተዋበው ፡ መልክሽ ፡ ትዝታ ፤ ሙሉ ፡ ደስታም ፤ ስቃይም ፡ ሆኖብኝ ፡ ይኖራል ። ሆኖም ፡ አንድ ፡ የሚያሳዝን ፡ ግዴታ ፡ ስላለብኝ ፡ በኔና ፡ ባንቺ ፡ መካከል ፡ የማይፈርስ ፡ ግድግዳ ፡ ለመፍጠር ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ ምስጢር ፡ ልገልጽልሽ ፡ ግዴታ ፡ ይሆንብኛል ።» ማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ ነገሩን ፡ አቋረጠችና ፡ «በኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ ምንጊዜም ፡ የማይፈርስ ፡ ግድግዳ ፡ አለ ፡ ... ሚስትህ ፡ ለመሆንም ፡ አልችልም ፡ ...» «አውቃለሁ ፡» አለ ፡ እሱም ፡ ለስለስ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ። «ከአሁን ፡ በፊት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ወደሽ ፡ እንደነበር ፡ አውቃለሁ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ ሞተ ፤ በሐዘን ፡ ላይ ፡ ሳለሽም ፡ ይሄው ፡ ሶስት ፡ ዓመት ፡ ሆነ ፡ ... ውድ ፡ ማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ ሆይ! ይህቺኑ ፡ ያለችኝን ፡ አንድ ፡ ደስታ ፡ አትንፈጊኝ! ምናልባት ፡ እሺ ፡ ብለሽ ፡ ታስደስቺኝ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ... ዝም ፡ በይ ፡ እባክሽ! ታስቃይኛለሽ ። የኔ ፡ ለመሆን ፡ ትችዪ ፡ እንደነበረ ፡ አውቃለሁ ፤ ይሰማኛልም ። ግን ፡ እኔ ፡ ዕድለ ፡ ቢስ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፤ አግብቻለሁ!»

ማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ በመደነቅ ፡ አተኩራ ፡ ተመለከተችው ።

« አግብቻለሁ ፡» ሲል ፡ ቡርሚን ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ። «እነሆ ፡ ከአገባሁ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ሆነኝ ፤ ባለቤቴም ፡ ማን ፡ እንደሆነች ፤ የት ፡ ቦታስ ፡ እንዳለች ፤ ከቶ ፡ ላገኛት ፡ እችል ፡ እንደሆንስ ፡ አላውቅም ።»

«ምን!» አለች ፡ ማሪያ ፡ ጋብሪሎቭና ፡ በመደነቅ ። « እንዴት ፡ የሚደንቅ ፡ ነገር ፡ ነው! ቀጥል ። ኋላ ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አጫውትሃለሁ ፡ ... ቀጥል ፡ እባክህ! »

« በ ፲፱፻፲፪ ዓ ፡ ም ፡ ገደማ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የ
ጦር ፡ ሠፈራችን ፡ ወደአለበት ፡ ወደ ፡ ቪልና ፡ ፈጥኜ ፡ እጓዝ ፡
ነበር ። ወደ ፡ አንድ ፡ ጣቢያ ፡ በደረስኩ ፡ ጊዜም ፡ እጅግ ፡ በጣ
ም ፡ መሽቶ ፡ ስለነበር ፡ አዲስ ፡ ፈረሶች ፡ ቶሎ ፡ እንዲጫኑልኝ ፡
ጠየቅሁ ፤ ወዲያው ፡ ግን ፡ ኃይለኛ ፡ የበረዶ ፡ ውሽንፍር ፡ መጣ
ል ፡ ስለጀመረ ፡ የጣቢያው ፡ ኃላፊና ፡ ሠረገላ ፡ ነጂዎቹ ፡ እስ
ኪያባራ ፡ ድረስ ፡ እንድጠብቅ ፡ መከሩኝ ። ምክራቸውን ፡ ሰማ
ሁ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ያልታወቀ ፡ ነገር ፡ ስሜቴን ፡ አሸነፈ
ው ። ና ፡ ቶሎ ፡ ተብየ ፡ የተጠራሁም ፡ መሰለኝ ። የበረዶው ፡ ው
ሽንፍርም ፡ አልታገስ ፡ አለ ። ትዕግሥቴ ፡ ስላለቀም ፡ አዲስ ፡
ፈረሶች ፡ እንዲጫኑ ፡ አዘዝኩና ፡ የበረዶ ፡ ዶፍ ፡ ሲወርድ ፡ ጉዞ
የን ፡ ጀመርኩ ። መንገዱን ፡ በሶስት ፡ ቬርስታ ፡ ለማሳጠር ፡
ሲል ፡ ሠረገላ ፡ ነጂው ፡ በወንዙ ፡ አኳያ ፡ ሄደ ። የወንዙ ፡ ዳር ፡
በበረዶ ፡ ተሸፍኖ ፡ ስለነበር ፡ ሠረገላ ፡ ነጂው ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡
የሚያገባውን ፡ አቅጣጫ ፡ ስቶ ፡ ስላለፈው ፡ ወዳልታወቀ ፡ ቦ
ታ ፡ ገባን ። በረዶውም ፡ የሚያባራ ፡ አይመስልም ፡ ነበር ። አን
ድ ፡ መብራት ፡ ስላየሁ ፡ ወደዚያ ፡ አቅጣጫ ፡ እንዲሄድ ፡ ሠረ
ገላ ፡ ነጂየን ፡ አዘዝኩት ። ወደ ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ ጋ ፡ ደረስን ።
ከእንጨት ፡ በተሠራው ፡ ቤተክርስትያንም ፡ ውስጥ ፡ መብ
ራት ፡ በርቶ ፡ ነበር ። በሩም ፡ ተከፍቶ ፡ ነበር ፤ በአጥሩ ፡ አ
ጠገብም ፡ ብዙ ፡ ጋሪዎች ፡ ቆመው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። ሰዎች
ም ፡ በቤተ ፡ ክርስትያኑ ፡ በረንዳ ፡ ላይ ፡ ይዘዋወሩ ፡ ነበር ።
«በዚህ ፡ በኩል! በዚህ ፡ በኩል!» የሚል ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡
ድምጽ ፡ ተሰማ ። ሠረገላ ፡ ነጂየን ፡ ወደ ፡ ቤተክርስትያኑ ፡
እንዲሄድ ፡ ነገርሁት ። «ምንድነው ፡ እንዲህ ፡ ያዘገየህ?»
ሲል ፡ ተናገረኝ ፡ አንድ ፡ ሰው ። «ሙሽራዋ ፡ ድክምክም ፡
ብላለች ፤ ቄሱም ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ ግራ ፡ ገብቶታል ፤
እኛም ፡ ወደየቤታችን ፡ ልንሄድ ፡ ነበር ። በል ፡ ቶሎ ፡ ግ
ባ! » ከሠረገላየ ፡ ላይ ፡ ዘልየ ፡ ወረድኩና ፡ አንድም ፡ ቃል ፡

ም

ሳልናገር ፡ ወደ ፡ ቤተክርስትያኑ ፡ ገባሁ ፤ ውስጡ ፡ በጥቂት ፡ ሻማዎች ፡ ላመል ፡ በርቷል ። አንድ ፡ ወጣት ፡ ልጃገረድ ፡ ጨለም ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ በሳንቃ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተቀምጣለች ። ሁለተኛዋ ፡ ልጃገረድ ፡ ደግሞ ፡ ግንባሯን ፡ ታሽላት ፡ ነበር ። «ተመስገን ፡ አምላኬ ፡» አለች ፡ ሁለተኛዋ ። «እንኳን ፡ አሁን ፡ መጣህ ። ወጣት ፡ እመቤቴን ፡ ለጥቂት ፡ ገድለሃት ፡ ነበር ። » አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ቄስ ፡ ወደእኔ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ እን ዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀኝ ፤ «እንጀምር?» «ይጀምሩ ፤ አባቴ ፤ ይ ጀምሩ ፡» ስል ፡ መለስኩ ፡ በጠቅላላው ። ልጂቱን ፡ ደግፈው ፡ አቆሟት ። ውብ ፡ መስላም ፡ ታየችኝ ። የሠራሁት ፡ ሥራ ፡ መ ችም ፡ ሊገለጽ ፡ የማይቻልና ፡ ምህረት ፡ የሌለው ፡ ቀልድ ፡ነ ው ፡ … በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አብሬያት ፡ ቆምሁ ። ቄሱ ፡ ቸኩሎ ፡ ነበር ። ሶስት ፡ ሰዎችና ፡ አንድ ፡ ደንገጡር ፡ ሙ ሽራዋን ፡ ደግፈው ፡ ያዟት ። ለሌላም ፡ ሰው ፡ ቁብም ፡ የላቸው ፡ ነበር ። ባልና ፡ ሚስት ፡ ተብለን ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ ተሣሠርን ። «በሉ ፡ ተሳሳሙ! » አሉን ። ሚስቴ ፡ ምጥጥ ፡ ያለ ፡ ፊቷን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ዘወር ፡ አደረገች ። ልስማት ፡ ስል ፡ ስቅቅ ፡ ብላ ፡ ጮኸችና ፤ «እርሱ ፡ አይደለም! እርሱ ፡ አይደለም!» ብላ ፡ ነፍሷን ፡ ስታ ፡ ወደቀች ። ምስክሮቹ ፡ በፍርሐት ፡ ዓይን ፡ ተመ ለከቱኝ ። እኔም ፡ ዘወር ፡ ብየ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያግደኝ ፡ ከቤ ተክርስትያኑ ፡ ወጥቼ ፡ እሠረገላዬ ፡ ላይ ፡ ሮጬ ፡ ወጣሁና ፡ ን ዳ ! ብዬ ፡ ጮህኩ ። »

«ወይ ፡ አምላክ!» ስትል ፡ ጮኸች ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭ ና ። «ያቺ ፡ ያልታደለች ፡ ሚስትህ ፡ ምን ፡ እንደሆነች ፡ እታው ቅም?»

«የለም ፡» አለ ፡ ቡርሚን ። «የተጋባሁበትንም ፡ መንደ ር ፡ አላውቅም ። ጣቢያውንም ፡ አላውቀውም ። ያንጊዜ ፡ ለሠ ራሁት ፡ የሚያስነቅፍ ፡ ሥራ ፡ ግድ ፡ ስላልነበረኝ ፡ ወዲያው ፡ ቤተክርስትያኑን ፡ ትተነው ፡ እንደሄድን ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደ

ኝ ። በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ እሶስተኛው ፡ ጣቢያ ፡ እስከደረስን
በት ፡ ሰዓትም ፡ ከእንቅልፌ ፡ አልነቃሁም ፡ ነበር ። ከእኔ ፡
ጋር ፡ የነበረውም ፡ አሽከር ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ስለሞተ ፡
እንደዚያ ፡ አድርጌ ፡ በጭካኔ ፡ የቀለድኩባትን ፡ ሴት ፡ ለማ
ግኘት ፡ ተስፋ ፡ የለኝም ። እሷን ፡ በጭካኔ ፡ እንደቀለድኩ
ባት ፡ ይሄው ፡ ብድሩ ፡ በኔም ፡ ላይ ፡ ደረሰብኝ ።»

«ወይ ፡ አንተ ፡ አምላክ! » አለች ፡ ማሪያ ፡ ጋቭሪሎቭ
ና ፡ እጅጌውን ፡ ይዛ ። « አንተ ፡ ኖረሃላ! አታስታውሰኝም ፡ እ
ኔን! »

ቡርሚን ፡ ፊቱ ፡ ምጥጥ ፡ አለ ፡ ... እጫማዋም ፡ ላይ ፡
ወደቀ ።

# የሬሳ፡ሣጥን፡ሠሪ።

የሬሳ ፡ ሣጥኖችን ፡ ስናይ ፡
እያረጀ ፡ የሚሄደውን ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ሽበት ፡
በየቀኑ ፡ እንመለከት ፡ የለምን ?

ዴርዣቪን ።

የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ የአድሪአን ፡ ፕሮኾሮቭ ፡ የመጨረሻ ፡ የቤት ፡ ዕቃ ፡ በሬሳ ፡ ማጓጓሮው ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ተጫነ ፤ ሁለቱ ፡ ቀጫጭን ፡ ፈረሶችም ፡ ለአራተኛ ፡ ጊዜ ፡ ከባስማኒያ ፡ መንገድ ፡ ተነስተው ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ከነቤተሰቡ ፡ ወደተዛወረበት ፡ ወደ ፡ ኒኪትስካያ ፡ መንገድ ፡ እየተጎተቱ ፡ አመሩ ። የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ሱቁን ፡ ከቆለፈ ፡ በኋላ ፡ ቤቱ ፡ የሚከራይና ፡ የሚሸጥም ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ማስታወቂያ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ በምስማር ፡ መትቶ ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ በእግሩ ፡ ሄደ ። ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይመኘው ፡ የነበረውንና ፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ዋጋ ፡ የገዛውን ፡ ቤት ፡ ቢጫ ፡ ግድግዳ ፡ ሲመለከት ፡ ሽማግሌው ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ደስታ ፡ እንዳልተሰማው ፡ ድንገት ፡ ተገነዘበ ። ያልለመደውን ፡ በር ፡ አልፎ ፡ ገና ፡ ምስቅልቅል ፡ ወደአለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሲገባም ፡ አስራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በደንብና ፡ በሥርዓት ፡ የኖረበትን ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆውን ፡ ናፈቀ ። ሁለቱን ፡

ሴት ፡ ልጆቹንና ፡ ገረዱን ፡ በዘገምተኛነታቸው ፡ ከሰደባቸው ፡ በኋላ ፡ ይረዳቸው ፡ ጀመር ። ቤቱ ፡ ወዲያውኑ ፡ መልክና ፡ ሥርዓት ፡ ያዘ ። ሥዕልና ፡ ምሳሌው ፤ የስሐን ፡ ማስቀመጫው ፤ ጠረጴዛው ፤ ሶፋውና ፡ አልጋው ፡ በስተኋላ ፡ በኩል ፡ በሚገኘው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ቦታ ፡ ቦታቸውን ፡ ያዙ ። የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ዕቃዎች ፡ የሆኑት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለምና ፡ መጠን ፡ ያላቸው ፡ የራሳ ፡ ሣጥኖች ፤ የሐዘን ፡ ባርኔጣዎችና ፡ ካባዎች ፡ እንዲሁም ፡ ችቦዎች ፡ የተመሉባቸው ፡ ቋም ፡ ሣጥኖች ፡ በወጥቤቱና ፡ በእንግዳ ፡ መቀበያ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቀጠቁ ። በአጥር ፡ ግቢው ፡ በር ፡ ላይም ፡ ችቦ ፡ ቁልቁል ፡ ደፍቶ ፡ የያዘ ፡ የግድንግድ ፡ ሰው ፡ ምልክት ፡ ተሰቅሏል ። በምልክቱ ፡ እግርጌም ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጽፏል ፤ « ሌጣና ፡ ቀለም ፡ የተቀቡ ፡ የሬሳ ፡ ሣጥኖች ፡ ይሸጣሉ ፤ ይለበዳሉም ፤ ይከራያሉ ፤ ይጠገናሉም ። » የሰውየው ፡ ልጆች ፡ ወደክፍላቸው ፡ ሄዱ ፤ አድሪአንም ፡ አዲሱን ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱን ፡ ከተመለካከተ ፡ በኋላ ፡ በመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠ ፤ የሻይ ፡ ጀበናው ፡ እንዲጣድም ፡ አዘዘ ።

ሼክስፒርና ፡ ሰር ፡ ወልተር ፡ስኮት ፡ በአዕምሮአችን ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜትን ፡ ለማሳደር ፡ ሲሉ ፡ መቃብር ፡ ቆፋሪዎችን ፡ በገራገርና ፡ በቀልደኛ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ ያቀርቡልናል ።[11] በዚህ ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ዕውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ለማሳየት ፡ ስለምንፈልግ ፡ የነርሱን ፡ ምሳሌ ፡ መከተላችንን ፡ ትተን ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ጠባይ ፡ ከሚቀፍ ፡ ሥራው ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ ተስማሚ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ አለብን ። አድሪአን ፡ ፕሮኾሮቭ ፡ ፊተ ፡ ጨፍጋጋና ፡ ግንባሩ ፡ የተቋጠረ ፡ ሰው ፡ ነው ። ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቃል ፡ ቢናገርም ፤ ሴት ፡ ልጆቹ ፡ በመስኮት ፡ ብቅ ፡ ብለው ፡ አላፊ ፡ አግዳሚውን ፡ ሲመለከቱ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ሲቆጣቸውና ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሊገዙ ፡ የመጡትን ፡ ያልታደሉ ፡ ( ወይም ፡ የታደ

ሉ ፡ ) ሰዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ሲጠይቃቸው ፡ ነው ። እነሆ ፡ አሁን ፡ አድሪአን ፡ በመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ እንደተለ መደው ፡ የሚያሳዝን ፡ ሐሳብ ፡ እያወጣና ፡ እያወረደ ፡ ሰባተኛ ውን ፡ ስኒ ፡ ሻይ ፡ ይጠጣል ። ከሥራ ፡ በተሰናበተው ፡ ወታደር ፡ ( የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካይ ፡ ) ሥርዓተ ፡ መቃብር ፡ ጊዜ ፡ እሬሳው ፡ የቀረጥ ፡ መቀበያውን ፡ በር ፡ ሲያልፍ ፡ ኃይለኛ ፡ ዝናብ ፡ እንዴት ፡ እንደተቀበለው ፡ አስታወሰ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ካባዎች ፡ ተበላሹ ፤ የባርኔጣ ፡ ክፈፎችም ፡ ተጨማደዱ ። ያሉት ፡ የሥርዓተ ፡ መቃብር ፡ ልብሶች ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ስለተበላሹበት ፡ ብዙ ፡ ወጭ ፡ ማድረግ ፡ እንዳለበ ት ፡ ተገነዘበ ። ይህን ፡ ወጭውን ፡ ለማጣጣትም ፡ ነጋዴ ፡ ባልዋ ፡ የሞተባት ፡ አሮጊቷ ፡ ትሪውኺና ፡ እስክትሞት ፡ ድረስ ፡ በተስፋ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ። ይህች ፡ ሴት ፡ በሞት ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ስትኖር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሆንዋታል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ትሪውኺና ፡ በራዝጉላይ ፡ ሠፈር ፡ የምትሞት ፡ ስለ ሆነ ፡ ምናልባት ፡ የእርሷ ፡ ወራሾች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ተስፋ ፡ ቢሰጡትም ፡ ወደርሱ ፡ ጋ ፡ ሰው ፡ ከመላክ ፡ ይ ልቅ ፡ በዚያው ፡ ሠፈር ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኝ ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪ ፡ ጋር ፡ ተስማምተው ፡ ሥርዓተ ፡ መቃብሩን ፡ ይፈጽሙታል ፡ በማለት ፡ ፍርሐት ፡ አደረበት ።

በዚህ ፡ ሐሳብ ፡ ተውጦ ፡ ሳለ ፡ ድንገት ፡ በሩ ፡ ላመል ፡ ሶስት ፡ ጊዜ ፡ ስለተቆረቆረ ፡ ሐሳቡን ፡ አቋረጠው ። « ማነው?» ሲል ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ጮኸ ። በሩ ፡ ተከፈተ ፤ የጀር መን ፡ የቀን ፡ ሙያተኛ ፡ መሆኑ ፡ ወዲያው ፡ የሚታወቅ ፡ ሰው ም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ገባና ፡ ደስታ ፡ በተመላበት ፡ መልክ ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪውን ፡ ተጠጋው ። በተወላገደና ፡ በሚያስ ቅ ፡ መስኮብኛም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ « ይቅርታ ፡ ያድርጉል ኝ ፡ ውድ ፡ ጐረቤቴ ፤ ይቅርታ ፡ ያድርጉልኝ ፡ ሥራዎን ፡ አቋር ጨ ፡ እንደሆን ፤ በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ልተዋወቅዎት ፡ እፈቅዳ

ለሁ ። ጫማ ፡ ሰፊ ፡ ነኝ ፤ ስሜም ፡ ጐትሊብ ፡ ሹልትስ ፡ ይባላ ል ፤ የምኖረውም ፡ በመስኰትዎ ፡ በኩል ፡ በመንገዱ ፡ ማዶ ፡ በምትታየው ፡ ትንሽ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ነገ ፡ የኢዮቤልዩ ፡ የጋብቻ ፡ በዓሌን ፡ ስለማከብር ፡ እርስዎ ፡ ከልጆችዎ ፡ ጋር ፡ መጥተው ፡ ምሳ ፡ እንዲጋበዙልኝ ፡ እፈልጋለሁ ።» አድሪአ ን ፡ ግብዣውን ፡ በደስታ ፡ ተቀበለ ። የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪውም ፡ ጫማ ፡ ሰፊውን ፡ እንዲቀመጥና ፡ ሻይ ፡ አብረው ፡ እንዲጠ ጡ ፡ ጠየቀው ። ጐትሊብ ፡ ሹልትስ ፡ በጠባዩ ፡ ግልጽ ፡ ሰው ፡ ስለነበር ፡ ልብ ፡ ለልብ ፡ መጨዋወት ፡ ጀመሩ ። «ሥራህ ፡ እንዴት ፡ ይካሄድልሃል?» ሲል ፡ ጠየቀ ፡ አድሪአን ። «እን ደነገሩ ፡ ነው ።» ሲል ፡ መለሰ ፡ ሹልትስ ፡ ቀጥሎም ፤ «አን ድ ፡ ጊዜም ፡ ወደላይ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ወደታች ፡ ነው ። ሆ ኖም ፡ አላማርርም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የምሸጠው ፡ ዕቃ ፡ አንተ ፡ እንደምትሸጠው ፡ ዕቃ ፡ ዓይነት ፡ አይደለም ። በሕይ ወት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ጫማ ፡ ሊሄድ ፡ ይችላል ፤ የሞተ ፡ ሰ ው ፡ ግን ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ በግድ ፡ ያስፈልገዋል ።» አለ ። «እርሱስ ፡ እውነት ፡ ነው» ሲል ፡ ተስማማ ፡ አድሪአን ። ቀጥሎ ም ፤ «ሆኖም ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ጫማ ፡ መግዣ ፡ ቢ ያጣ ፡ ባዶ ፡ እግሩን ፡ መሄድ ፡ ይችላል ። የሞተ ፡ ለማኝ ፡ ግን ፡ የሬሳ ፡ ሣጥኑን ፡ በነፃ ፡ ያገኛል ።» አለ ። ጭውውታቸው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ጥቂት ፡ ቀጠለ ፤ ኋላም ፡ ጫማ ፡ ሰፊው ፡ ብ ድግ ፡ አለና ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሻጩን ፡ ተሰናብቶ ፡ ወዲያውም ፡ ግብዣውን ፡ እንደገና ፡ አስታውቆ ፡ ሄደ ።

በማግሥቱ ፡ ልክ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠ ሪውና ፡ ሴት ፡ ልጆቹ ፡ አዲስ ፡ ከተገዛው ፡ ቤታቸው ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ በር ፡ ወጥተው ፡ ጐረቤታቸውን ፡ ለመጐብኘት ፡ ሄዱ ። አድሪአን ፡ ፕሮኮሮቭ ፡ የለበሰውን ፡ የሩሲያ ፡ ካፍታን ፡ ወይ ም ፡ አኩሊናና ፡ ዳርያ ፡ የለበሱትን ፡ የኤውሮፓ ፡ ቀሚስ ፡ ለ መግለጽ ፡ አልሞክርም ። ምክንያቱም ፡ ዘመናዊ ፡ ደራስያን ፡

የሚከተሉትን ፡ የድርሰት ፡ ሥርዓት ፡ መጣስ ፡ ስለሚሆንብኝ ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ሁለቱ ፡ ልጃገረዶች ፡ ቢጫ ፡ ባርኔጣና ፡ ቀይ ፡ ነጠላ ፡ ጫማ ፡ አድርገው ፡ ነበር ፡ ብየ ፡ ብጠቅስ ፡ ከትርፍ ፡ ንግግር ፡ አይቆጠርብኝ ፡ ይሆናል ።

የጫማ ፡ ሰፊው ፡ ትንሽ ፡ ክፍል ፡ በእንግዳ ፡ ተመልቶ ፡ ነበር ። አብዛኞቹም ፡ ከሚስቶቻቸውና ፡ ከረዳቶቻቸው ፡ ጋር ፡ የመጡ ፡ የጀርመን ፡ የተግባረ ፡ ዕድ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ መስኰባዊ ፡ ዩርኮ ፡ የተባለው ፡ ፖሊስ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ማዕርጉ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ቢሆንም ፡ የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ልዩ ፡ አክብሮት ፡ ያሳየው ፡ ነበር ። ሃያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ እንደታወቀው ፡ የፖጐሬልስኪይ ፡ ፖስተኛ ፡ ሳያቋርጥ ፡ በታማኝነት ፡ ሥራውን ፡ ይፈጽም ፡ ነበር ።[12] እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፰፻፲፪ ዓ ፡ ም ፡ የተነሳው ፡ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ጥንታዊቱን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ሲያጠፋት ፡ የእርሱንም ፡ ቢጫ ፡ የዘበኛ ፡ ቤት ፡ አብሮ ፡ አጠፋት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጠላት ፡ ወዲያው ፡ እንደ ተወገደ ፡ ግራጫ ፡ ቀለም ፡ የተቀባና ፡ በነጭ ፡ የዶሪክ ፡ ምሰሶ ፡ ያጌጠ ፡ የዘበኛ ፡ ቤት ፡ ስለተሠራለት ፡ ዩርኮ ፡ መሣሪያውን ፡ በደንብ ፡ ታጥቆ ፡ በዘበኛ ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ መንጐራደዱን ፡ እንደገና ፡ ቀጠለ ። በኒኪትስኪይ ፡ በር ፡ የሚኖሩትን ፡ አብዛኞቹን ፡ ጀርመኖች ፡ ያውቃቸው ፡ ስለነበር ፡ አንዳንዶቹ ፡ ዕሁድ ፡ ዕሁድ ፡ በርሱ ፡ ቤት ፡ ያድሩ ፡ ነበር ። አድሪአንም ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ ይረዳኛል ፡ በማለት ፡ ፈጥኖ ፡ ተዋወቀው ፤ እንግዶቹ ፡ ለምሳ ፡ ወደገበታ ፡ ቀርበው ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜም ፡ እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ተቀመጡ ። ሄር ፡ ሹልትስና ፡ ፍራው ፡ ሹልትስ ፡ እንዲሁም ፡ የአስራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሴት ፡ ልጃቸው ፡ ሎትኼን ፡ ከእንግዶቹ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ በምትጋበዝበት ፡ ጊዜ ፡ በገበታው ፡ ላይ ፡ ምግብ ፡ በማሳለፍ ፡ ወጥቤቱን ፡ ትረዳው ፡ ነበር ። ቢራ ፡ ሞልቶ ፡ ተርፎ ፡ ነበር ። ዩርኮ ፡ ሆዱ ፡ ነጋሪት ፡ እስኪያኽል ፡ ድረስ ፡ በላ ። አድ

ሪእንም ፡ ኰመኰመ ። ሴት ፡ ልጆቹም ፡ መልካም ፡ ጠባያቸው
ን ፡ ጠበቁ ። በጀርመንኛ ፡ ቋንቋ ፡ የሚያደርጉት ፡ ጭውውትም ፡
ጩኸቱ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ሄደ ። ጋባዡ ፡ ሰውየ ፡ ተጋባገሮቹ ፡
ወደእርሱ ፡ እንዲመለከቱ ፡ ጠርቶ ፡ በቅጥራን ፡ ከተደፈነ ፡ ጠ
ርሙስ ፡ ላይ ፡ ቡሹን ፡ ከፈተና ፡ በመስኰብኛ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ ጮኾ ፡ ተናገረ ፤ «ለሉዊዝዬ ፡ መልካም ፡ ጤና!» ሻም
ፔኙ ፡ ተንሿሿ ፤ ጋባዡም ፡ መካከለኛ ፡ ዕድሜ ፡ ያላትን ፡ የ
ባለቤቱን ፡ ለስላሳ ፡ ፊት ፡ ሳመ ፤ ተጋባገሮቹም ፡ ለደጓ ፡ ሉዊዛ ፡
መልካም ፡ ጤና ፡ በውካታ ፡ ጠጡ ። «ለተወደዳችሁ ፡ እንግ
ዶቼ ፡ ጤና!» ሲል ፡ አስታወቀ ፡ ጋባዡ ፡ ሌላ ፡ ጠርሙስ ፡
እየከፈተ ፤ እንግዶቹም ፡ መለኪያቸውን ፡ እንደገና ፡ እየጨለ
ጡ ፡ ምሥጋናቸውን ፡ ገለጹ ። ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ጽዋ ፡ ማንሳቱ ፡
ይበልጥ ፡ እየገነነ ፡ ሄደ ። ለእያንዳንዱ ፡ እንግዳ ፡ ጤና ፡ ተጠ
ጣ ፤ ለሞስኮ ፡ ከተማ ፡ ጽዋቸውን ፡ አነሱ ፤ እንዲሁም ፡ ለአያ
ሌ ፡ የጀርመን ፡ ከተማዎች ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ለተግባረ ፡ ዕድ ፡
ሥራ ፡ በጠቅላላው ፤ ቀጥሎም ፡ በዝርዝሩ ፤ እንዲሁም ፡ ለተ
ግባረ ፡ ዕድ ፡ ሠራተኞችና ፡ ለረዳቶቻቸው ። አድሪአን ፡ ተጠን
ቅቆ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ፤ ወደኋላ ፡ ግን ፡ ሞቅ ፡ ስላለው ፡ ጽዋው
ን ፡ አንስቶ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከእንግዶ
ቹ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ስውነቱ ፡ ሙሉ ፡ ዳቦ ፡ ጋጋሪ ፡ ሰውየ ፡
ጽዋውን ፡ አንስቶ ፤ «ለምናገለግላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጤና!» ሲ
ል ፡ አድምቆ ፡ ተናገረ ። ይህም ፡ ጽዋ ፡ እንደቀሩት ፡ ሁሉ ፡
በደስታና ፡ በኅብረት ፡ ተጠጣ ። እንግዶቹ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡
እጅ ፡ መነሳሳት ፡ ጀመሩ ። ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ጫማ ፡ ሰፊው
ን ፡ እጅ ፡ ነሳ ፤ ዳቦ ፡ ጋጋሪው ፡ ሁለቱንም ፡ እጅ ፡ ነሳ ። መ
ላው ፡ እንግዶች ፡ ደግሞ ፡ ዳቦ ፡ ጋጋሪውን ፤ እንዲህ ፡ እያለ ፡
ቀጠለ ። ሰላምታው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ሲቀጥል ፡ ዩርኮ ፡ ወደ
ሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ዘወር ፡ አለና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጮኾ ፡
ተናገረ ፤ «በላ ፡ ወዳጄ ፤ ለሙታን ፡ ጤና ፡ ጠጣ! » በዚህ ፡ ጊ

ዜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሳቀ ፤ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ግን ፡ ስለተቀ
የመ ፡ ፊቱን ፡ አኰሳተረ ። እንግዶቹ ፡ ግን ፡ ልብ ፡ ብለው ፡ ስላላ
ዩ ፡ መጠጣታቸውን ፡ ቀጠሉ ። ከጠረጴዛ ፡ ሲነሱም ፡ የቅዳሴ ፡
ደወል ፡ ተደወለ ።

እነሆ ፡ እንግዶቹ ፡ አምሽተውና ፡ አብዛኞቹም ፡ ሞቅ ፡ ብ
ሏቸው ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ። ሰውነተ ፡ ሙሉው ፡ ዳቦ ፡ ጋ
ጋሪና ፡ ፊቱ ፡ በርበሬ ፡ የመሰለው ፡ መጽሐፍ ፡ ጠራዥ ፡ በፖሊ
ሱ ፡ ብብቻ ፡ ውስጥ ፡ እጃቸውን ፡ አስገብተው ፤ «የብድር ፡ ቀ
ጋው ፡ የሚታወቀው ፡ ሲከፈል ፡ ነው ፡» የሚለውን ፡ የመስ
ኰብን ፡ ምሳሌ ፡ በመከተል ፡ ፖሊሱን ፡ ደግፈው ፡ ወደዘበኛ ፡
ቤቱ ፡ ወሰዱት ። የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ነዶትና ፡ ተበሳጭቶ ፡
እቤቱ ፡ ደረሰ ። እንዲህ ፡ ሲልም ፡ አሰበ ፤ «ምንስ ፡ ቢሆን ፡ የ
ኔ ፡ ሥራ ፡ ከሌሎቹ ፡ በምን ፡ ያንሳል? የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪ ፡ የሰ
ው ፡ ስቃይ ፡ ወንድም ፡ ነውን? እነዚህ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎ
ች ፡ የሚስቁበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው? የሬሳ ፡ ሣጥን ፡
ሠሪ ፡ ቂል ፡ መሰላቸው ፡ ይሆን? የቤት ፡ መመረቂያ ፡ ግብዣ ፡
ላደርግላቸው ፡ አስቤ ፡ ነበር ። የለም ፤ አላደርገውም! የለም ፤
የማገለግላቸውን ፡ ሰዎች ፡ እነዚያን ፡ ክርስትያኖቹን ፡ ሙታን ፡
እጋብዛለሁ ።» «ምነዋ ፡ ጌታዬ!» አለች ፡ ጫማውን ፡ የም
ታወልቅለት ፡ ገረዱ ። «ምን ፡ እንደተናገሩ ፡ ያውቃሉ! በስ
መ ፡ አብ ፡ ብለው ፡ ያማትቡ ። ቤት ፡ ለመመረቂያ ፡ ሙታንን ፡
ሊጋብዙ ፡ ነው! የሚያስቅቅ ፡ ነው!» «እግዚአብሔር ፡ በሚ
ያውቀው ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እጋብዛቸዋለሁ ፡ » ሲል ፡ ቀጠለ ፡
አድሪአን ። «ያውም ፡ ነገ ፡ ነው! እናንተም ፡ ዘመዶቼ ፡ ነገ ፡
ማታ ፡ አብራችሁኝ ፡ እንድትጋበዙ ፡ ይሁን ። ያለኝን ፡ ሁሉ ፡
ትካፈላላችሁ ።» ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡
ሠሪው ፡ አልጋው ፡ ውስጥ ፡ ገባና ፡ ወዲያው ፡ ያኰርፍ ፡ ጀመር ።

አድሪአን ፡ በተቀሰቀሰ ፡ ጊዜ ፡ በውጭ ፡ በኩል ፡ ገና ፡
ጨለማ ፡ ነበር ። የነጋዴው ፡ ሚስት ፡ ትሪውኺና ፡ ሌሊት ፡ ሰለ

ሞቶች ፡ ከአሽከሮቿ ፡ አንዱ ፡ ወሬውን ፡ ለአድሪአን ፡ ለመን ገር ፡ በፈረስ ፡ ጋልቦ ፡ ሄደ ። የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪውም ፡ ለሰው የው ፡ የቮድካ ፡ መጠጫ ፡ አስር ፡ ኰፔክ ፡ ሰጠውና ፡ በፍጥ ነት ፡ ለብሶ ፡ በሠረገላ ፡ ወደ ፡ ራዝጉላይ ፡ ሠፈር ፡ ሄደ ። ፖሊ ሶች ፡ በሟቿ ፡ ሴትዮ ፡ ቤት ፡ በር ፡ ላይ ፡ ቆመዋል ፤ ነጋዴዎ ችም ፡ ጥምብ ፡ እንዳየ ፡ አሞራ ፡ ወደላይና ፡ ወደታች ፡ ይን ጐራደዳሉ ። እሬሳዋ ፡ በአንድ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ተጋድሟል ፤ መልኳ ፡ ሰም ፡ ይመስላል ፤ ሆኖም ፡ ገና ፡ አልፈረሰም ፤ አልበሰ በሰም ። ዘመዶቿ ፤ ጐረቤቶቿና ፡ የቤት ፡ አገልጋዮቿ ፡ በዙሪ ያዋ ፡ ተሰበሰቡ ። መስኰቱ ፡ ሁሉ ፡ ተከፈተ ፤ ሻማም ፡ በራ ፤ ቀሳውስትም ፡ ለሟቿ ፡ ፍትሐት ፡ ያደርሱ ፡ ጀመር ።

አድሪአን ፡ ዘመናዊ ፡ ጥቁር ፡ ኰት ፡ ወደለበሰ ፡ ወጣት ፡ ነጋዴ ፡ ጋ ፡ ተጠጋ ። ይህ ፡ ሰው ፡ የሟቿ ፡ ሴትዮ ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ነው ። አድሪአን ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፤ ሻማ ፤ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ መሸፈኛና ፡ ሌላም ፡ የሥርዓተ ፡ መቃብር ፡ ቅራቅንቦ ፡ በደን ብ ፡ አዘጋጅቶ ፡ በፍጥነት ፡ የሚያቀርብ ፡ መሆኑን ፡ ለዚሁ ፡ ሰ ውየ ፡ አስታወቀው ። ወራሹም ፡ ልብ ፡ ሳይል ፡ አመሥግኖ ፡ በ ዋጋው ፡ የማይከራከር ፡ መሆኑንና ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ በሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ላይ ፡ በእምነት ፡ የሚተወው ፡ መሆኑን ፡ ገለ ጸለት ። የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪውም ፡ እንደልማዱ ፡ ከዋጋው ፡ በላይ ፡ አንድ ፡ ኰፔክ ፡ የማይጨምር ፡ መሆኑን ፡ ቃል ፡ ሰጥቶ ፡ ከአሽ ከርዮው ፡ ጋር ፡ በስርቆት ፡ ተያዩና ፡ አስፈላጊውን ፡ ዝግጅት ፡ ለማድረግ ፡ ወደቤቱ ፡ በሠረገላው ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ። ቀኑን ፡ ሙ ሉ ፡ በራዝጉላይና ፡ በኒኪትስኪይ ፡ በር ፡ ሲመላለስ ፡ ዋለ ። ወደማታ ፡ ጊዜ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ ተጠናቀቀለት ፤ ሠረገላ ፡ ነጂውን ፡ አሰናብቶም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ በእግሩ ፡ ሄደ ። ሌሊቱ ፡ ጨ ረቃ ፡ የደመቀችበት ፡ ሌሊት ፡ ነበር ። የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ኒኪትስኪይ ፡ በር ፡ ደረሰ ። የትንሳኤን ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ሲያልፍም ፡ ወዳጃችን ፡ ዩርኮ ፡ አቆመው ፤ ነገር ፡

ግን ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ መሆኑን ፡ ሲያይ ፡ ደህና ፡ እደር ፡ ብሎ ፡ አሳለፈው ። ሰዓቱ ፡ እጅግ ፡ ዘግይቶ ፡ ነበር ። የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሲደርስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የአጥር ፡ ግቢውን ፡ በር ፡ ከፍቶ ፡ ወደውስጥ ፡ እልም ፡ ብሎ ፡ ሲገባ ፡ ያየ ፡ መሰለው ። «ምን ፡ ይሆን?» ሲል ፡ አሰበ ፡ አድሪአን ። «ማን ፡ ይሆን ፡ የሚፈልገኝ ፡ ደግሞ? ሌባ ፡ ሰብሮ ፡ መግባቱ ፡ ይሆን? ወይስ ፡ ጐረምሳዎች ፡ ሴት ፡ ልጆቼን ፡ ሌሊት ፡ ይጐበኙአቸዋል ፡ ልበል? » ወዳጁ ፡ ዩርኮ ፡ እንዲረዳው ፡ ለመጣራትም ፡ አሰበ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ወደአጥር ፡ ግቢው ፡ በር ፡ ደርሶ ፡ ሊገባ ፡ ሲል ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ ወደቤቱ ፡ ለመግባት ፡ ሲጣደፍ ፡ ስላየው ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመና ፡ ሞላላ ፡ ባርኔጣውን ፡ ብድግ ፡ አደረገ ። አድሪአን ፡ ሰውየውን ፡ የሚያውቀው ፡ መሰለው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይጣደፍ ፡ ስለነበር ፡ አጥርቶም ፡ አላየው ። «ወደኔ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ የመጡት ፤ ይግቡ ፡ እንጂ ፡» ሲል ፡ አቃሰተ ። « ግድ ፡ የለም ፤ መሸኰርመም ፡ አያብዙ ። እርስዎ ፡ ቀድመው ፡ ይግቡና ፡ መንገዱን ፡ ለእንግዳዎችዎ ፡ ያሳዩ ፡ » አለ ፡ ያልታወቀው ፡ ሰውዬ ፡ በባዶ ፡ ድምጽ ። አድሪአን ፡ በጣም ፡ ቸኩሎ ፡ ስለነበር ፡ ግርግር ፡ አላበዛም ። የአጥር ፡ ግቢው ፡ በር ፡ ተከፈተ ፤ ሰውዬው ፡ እንደተከተለውም ፡ ደረጃውን ፡ ወጥቶ ፡ ወደቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አመራ ። አድሪአን ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሰዎች ፡ ያሉ ፡ መሰለው ። «ምንድነው ፡ ነገሩ?» አለ ፡ ሊገባ ፡ እየተጣደፈ ። ጉልበቱም ፡ ተንቀጠቀጠ ። ቤቱ ፡ በሙታን ፡ ተመልቶ ፡ ነበር ። በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ የሚገባው ፡ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ የሙታኖቹን ፡ ሰማያዊና ፡ ቢጫ ፡ ፊታቸውን ፤ የተንጠለጠለ ፡ አፋቸውን ፤ ድብዝዝ ፡ ያለና ፡ በግማሽ ፡ የተከደነ ፡ ዓይናቸውንና ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ የቆመ ፡ አፍንጫቸውን ፡ ያሳይ ፡ ነበር ። አድሪአን ፡ የእነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ሥርዓተ ፡ መቃብር ፡ የረዳ ፡ መሆኑን ፡ በመሰቀቅ ፡ ተገነዘበው ። አብሮት ፡ የገባውም ፡ የዝናብ ፡ ዶፍ ፡

ይወርድ ፤ በነበረ ፤ ጊዜ ፤ የተቀበረው ፤ ወታደር ፤ መሆኑን ፤ አስታወሰ ። ሴቶቹም ፤ ወንዶቹም ፤ ሁሉም ፤ በሬሳ ፤ ማጥን ፤ ሠሪው ፤ ዙሪያ ፤ ተሰብስበው ፤ እጅ ፤ እየነሱ ፤ ሰላምታ ፤ ሰ ጡት ። አንድ ፤ በቅርብ ፤ ጊዜ ፤ ሞቶ ፤ በነፃ ፤ የተቀበረ ፤ ሰው ፤ ብቻ ፤ ልብሱ ፤ የተቀዳደደ ፤ በመሆኑ ፤ አፍሮ ፤ ይሁን ፤ በክፍ ሉ ፤ ማዕዘን ፤ እራቅ ፤ ብሎ ፤ በትህትና ፤ ቆሟል ። ከእርሱ ፤ በስተ ቀር ፤ ሁሉም ፤ ቱር ፤ ብለው ፤ ለብሰዋል ። ሴቶቹ ፤ ሻሽ ፤ ያለ ው ፤ ባርኔጣ ፤ ደፍተዋል ፤ የሞቱት ፤ የመንግሥት ፤ ባለሥል ጣኖች ፤ የማዕርግ ፤ ልብሳቸውን ፤ ለብሰዋል ፤ ነገር ፤ ግን ፤ ጢማቸውን ፤ አልተላጩም ። ነጋዴዎችም ፤ የክት ፤ ካፖርታ ቸውን ፤ ለብሰዋል ። «ሰማህ ፤ ፕሮኾሮቭ ፤» አለ ፤ ወታደ ሩ ፤ በሁሉም ፤ ስም ፤ ሆኖ ፤ በመናገር ፤ «እኛ ፤ ሁላችንም ፤ ግብዣህን ፤ ለመቀበል ፤ ተነስተን ፤ መጣን ። ያልመጡት ፤ ፍጹም ፤ የፈረሱትና ፤ የበሰበሱት ፤ እንዲሁም ፤ አጥንታቸው ፤ ብቻ ፤ የቀረው ፤ ነው ። ሆኖም ፤ አጽማቸው ፤ ብቻ ፤ ከቀረው ፤ ውስጥ ፤ አንደኛው ፤ አንተን ፤ ለመጎብኘት ፤ በጣም ፤ ስለፈ ለገ ፤ ተነስቶ ፤ መጣ ።» በዚህ ፤ ጊዜ ፤ አንድ ፤ ትንሽ ፤ አጽም ፤ በሰዎቹ ፤ መካከል ፤ ፈልፍሎ ፤ ገባና ፤ ወደ ፤ አድሪአን ፤ ቀረበ ። ሥጋ ፤ የሌለው ፤ ፊቱ ፤ አድሪአንን ፤ በመናፈቅ ፤ ዓይን ፤ ተመ ለከተው ። የለበሰው ፤ አረንጓዴና ፤ ቀይ ፤ የተበጣጠሰ ፤ የሐር ፤ ጨርቅ ፤ ክሩ ፤ ዘልቆ ፤ ይታይ ፤ ነበር ። ልብሱ ፤ በእንጨት ፤ ላይ ፤ የተሰቀለ ፤ ቁርጥራጭ ፤ ጨርቅም ፤ ይመስል ፤ ነበር ። የቅልጥሙ ፤ አጥንትም ፤ በፈረስ ፤ መጋለቢያ ፤ ጫማው ፤ ውስ ጥ ፤ ሲንቋቋ ፤ ይሰማ ፤ ነበር ። «አታስታውሰኝም ፤ እንዴ ፤ ፕሮኾሮቭ?» ሲል ፤ ጠየቀው ፤ አጽሙ ። «እኔ ፤ እኮ ፤ የክብ ር ፤ ዘበኛ ፤ ሴርጀንት ፤ የነበርኩት ፤ ፒዮትር ፤ ፔትሮቪች ፤ ኩሪልኪን ፤ ነኝ ። ኤ ፤ ኤ ፤ አ ፤ በ ፲፯፻፺፱ ዓ ፤ ም ፤ የመጀመሪያ ፤ የሬሳ ፤ ሣጥንህን ፤ የሸጥክልኝም ፤ ለኔ ፤ ነው ። ከዋርካ ፤ እን ጨት ፤ ነው ፤ የተሠራው ፤ ብለህ ፤ ነበር ፤ ግን ፤ ወይራ ፤ ነበር ።»

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ አጽሙ ፡ በደስታ ፡ ስሜት ፡ ሊያቅፈ ው ፡ እጁን ፡ ሲዘረጋ ፡ አድሪአን ፡ ግን ፡ በድፍረት ፡ ጮኸና ፡ አሽቀንጥሮ ፡ ገፋው ። ፒዮትር ፡ ፔትሮቪችም ፡ ተንገደገደና ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ አጥንቱም ፡ ውልቅልቅ ፡ ብሎ ፡ ተከመ ረ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ የነበሩት ፡ ሙታን ፡ በቁጣ ፡ ገነፈሉ ። ሁሉም ፡ የወዳጃቸውን ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ለመበቀል ፡ ወደ ፡ አ ድሪአን ፡ ገሠገሡና ፡ የስድብና ፡ የቁጣ ፡ መዓት ፡ አወረዱ በት ። ምስኪኑ ፡ ጋባዥም ፡ ጩኸታቸው ፡ ስላደነቆረው ና ፡ ሊደቁሱት ፡ ስለተቃረቡ ፡ ነፍሱን ፡ ስቶ ፡ እሱም ፡ እንደዚ ሁ ፡ በክብር ፡ ዘበኛው ፡ ሴርጃንት ፡ አጽም ፡ ላይ ፡ ወደቀ ።

የፀሐይዋ ፡ ጨረር ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፡ የተኛበትን ፡ አ ልጋ ፡ አብርቶት ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ዓይኑን ፡ ሲገልጥ ፡ ገረ ዲ ፡ የሻይ ፡ ጀበናውን ፡ ለመጣድ ፡ ፍም ፡ ስታረግብ ፡ አያት ። አድሪአን ፡ በሕልሙ ፡ ያየውን ፡ በፍርሃት ፡ አስታወሰ ። ትሪው ኺና ፤ የእሳት ፡ አደጋ ፡ ተከላካዩና ፡ ሴርጃንት ፡ ኩሪልኪን ፡ ጥ ቂት ፡ ጥቂት ፡ ትዝ ፡ አሉት ። ገረድዮዋ ፡ እስክታናግረውና ፡ ሌሊት ፡ ያየው ፡ ነገር ፡ በምን ፡ የተነሳ ፡ እንደሆን ፡ እስክትነ ግረው ፡ ድረስ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ጠበቀ ።

«ጌታዬ ፡ አድሪአን ፡ ፕሮኾሮቪች ፤ እንዴት ፡ ነው ፡ አር ፍደው ፡ የተኙት ፡ ዛሬ ፡ » ስትል ፡ ተናገረች ፡ አክሲኒያ ፡ የጧት ፡ ልብሱን ፡ እየሰጠችው ። « ጐረቤታችን ፡ ልብስ ፡ ሰፊው ፡ ሊጠ ይቁዎት ፡ መጥተው ፡ ነበር ። ፖሊሱም ፡ እንደዚሁ ፡ ዛሬ ፡ የፖ ሊስ ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ የክርስትና ፡ ቀን ፡ መሆኑን ፡ ሊነግሩዎት ፡ መጥተው ፡ ነበር ፡ እርስዎ ፡ ግን ፡ ተኝተው ፡ ስለነበር ፡ ልን ቀሰቅስዎት ፡ አልፈለግንም ።»

«ባሏ ፡ ከሞተባት ፡ ከትሪውኺና ፡ ዘንድስ ፡ ሰው ፡ ተል ኮ ፡ አልመጣም?» ሲል ፡ ጠየቀ ።

«ከትሪውኺና ፡ ዘንድ? ለምን? ሞተች ፡ እንዴ?»

« ምን ፡ ቂሏ ፡ ነሽ! ለሥርዓተ ፡ መቃብሯ ፡ ዝግጅት ፡ ትላ ንት ፡ አልረዳሽኝም?»

«አበዱ ፡ እንዴ ፡ ጌታዬ? ወይስ ፡ የትላንቱ ፡ ስካር ፡ አላለ ፈልዎትም ፡ ልበል? ትላንት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሥርዓተ ፡ መቃብር ፡ አልነበረም! ወደ ፡ ጀርመኑ ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ሲጋበዙ ፡ ከዋሉ ፡ በኋላ ፡ ሰክረው ፡ ተመልሰው ፡ አልጋዎ ፡ ላይ ፡ ወደቁ ። እነሆ ፡ እስካሁን ፡ ድረስም ፡ ተኝተው ፡ አረፈዱ ፤ የቅዳሴ ፡ ደወል ፡ ከተደወለም ፡ ቆይቷል ። »

«እውነት ፡ ነው?» ሲል ፡ የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪው ፤ እፎይ ፡ በማለት ፡ ስሜት ፡ ተናገረ ።

«እንዴታ ፡» ስትል ፡ መለሰች ፡ ገረድዮዋ ።

«ይህ ፡ ከሆነስ ፡ ሻዩን ፡ ቶሎ ፡ አፍይና ፡ ልጆቼን ፡ ጥሪ ።»

# የማመሳለሻ፡ጣቢያ፡
# ሹም ።

የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ አማካሪና ፡
የማመላለሻ ፡ ጣቢያ ፡ ፈላጭ ፡ ቆራጭ ፡ ነው ።
ልዑል ፡ ቪያዜምስኪይ ።

የማመላለሻ ፡ ጣቢያን ፡ ሹም ፡ ያልረገመና ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ያልተጨቃጨቀ ፤ በቁጣ ፡ በገነፈለም ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ገምድልነትና ፡ በብልግና ፤ በገዛ ፡ ራሱም ፡ መዘግየት ፡ የማይረባ ፡ ክሱን ፡ በጥፋት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ለማስፈር ፡ መዝገቡን ፡ አቅርቡልኝ ፡ ያላለ ፡ ሰው ፡ የት ፡ ይገኛል? የማመላለሻ ፡ ሹሞችንስ ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ እንደለበሱ ፡ አውሬዎች ፤ ወይም ፡ በቁጣቸው ፡ እንደሞቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምንት ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሙሮም ፡ ወንበዴዎች ፡ የማይቆጥራቸው ፡ ማን ፡ አለ? ትክክለኛ ፡ ፍርድን ፡ ለመመርኰዝና ፡ እራሳችንን ፡ በነርሱ ፡ ቦታ ፡ ለመተካት ፡ ብንሞክር ፡ ምናልባት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትዕግሥት ፡ ፍርድ ፡ ልንሰጣቸው ፡ እንችላለን ። የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ ምንድን ፡ ነው? በተራ ፡ ሹማምንት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ዕውነተኛ ፡ ሰማዕት ፡ ነው ። ከዱላና ፡ ከእስራት ፡ የሚድነውም ፡ በዚሁ ፡ በማዕርጉ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ያውም ፡ ሆኖ ፡ ደግሞ ፡ ሁልጊዜ ፡ አያመልጥም ። ( ያንባቢዎቼን ፡ የህሊና ፡ ፍርድ ፡ እጠይቃለሁ ። ) ልዑል ፡ ቪያዜምስኪይ ፡

በቧልት ፡ በማፌዝ ፡ ፈላጭ ፡ ቆራጭ ፡ ብሎ ፡ የሚጠራው ፡ የዚ
ህ ፡ ሰው ፡ ሥራ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው? ተግባሩ ፡
በውነቱ ፡ ከባድ ፡ አይደለምን? ሌት ፡ ሆነ ፡ ቀን ፡ እረፍት ፡ የለ
ውም! መንገደኞች ፡ በአድካሚ ፡ ጉዞአቸው ፡ ላይ ፡ ያጠራቀ
ሙትን ፡ ብስጭት ፡ ሁሉ ፡ በማመላለሻ ፡ ሹም ፡ ላይ ፡ ያዘንቡ
በታል ። በአየር ፡ ጠባዩ ፡ አስመራሪነት ፤ በመንገዱ ፡ መጥፎ
ነት ፤ በሰረገላ ፡ ነጂው ፡ ችኰነት ፤ በፈረሶቹ ፡ ሰነፍነት ፤ በዚ
ህ ፡ ሁሉ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ እንደ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሰው ፡ ወቀ
ሳውን ፡ ይቀበላል ። ወደ ፡ ምስኪን ፡ ቤቱ ፡ የሚገባው ፡ መን
ገደኛም ፡ እንደ ፡ ጠላቱ ፡ ይቆጥረዋል ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡
ይህን ፡ ሳይጠሩት ፡ የመጣ ፡ እንግዳ ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ በ
ፍጥነት ፡ ለማስወገድ ፡ የቻለ ፡ እንደሆን ፡ ዕድለኛ ፡ ነው ።
የሚጫን ፡ ፈረስ ፡ ያልተገኘማ ፡ እንደሆን! አየ ፡ የሚወርድበ
ት ፡ ስድብና ፡ ዛቻ! በዝናብና ፡ በጭቃ ፡ ከቤት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡
መሮጥ ፡ ግድ ፡ ይሆንበታል ። በረዶ ፡ በኃይል ፡ እየወረደና ፡
ገና ፡ የጥር ፡ ወር ፡ ውርጭ ፡ እያለ ፡ ከተቆጣው ፡ መንገደኛ ፡
ጩኸትና ፡ ግልምጫ ፡ ትንሽ ፡ ለማረፍ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ በረንዳ
ው ፡ ወጣ ፡ ይላል ። አንድ ፡ ጀኔራል ፡ ሲመጣም ፡ ያሉትን ፡
የመጨረሻዎቹን ፡ ሁለት ፡ «ትሮይካዎች ፡» * ይሰጠዋል ።
ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ ለፖስታ ፡ ማመላለሻ ፡ የተቀ
መጠ ፡ ነበር ። ጀኔራሉም ፡ አንዳችም ፡ የምሥጋና ፡ ቃል ፡ ሳይ
ናገር ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ይሄዳል ። ካምስት ፡ ደቂቃም ፡ በኋላ ፡
የደወል ፡ ድምጽ ፡ ይሰማል ፤ አንድ ፡ የመንግሥት ፡ መልዕክ
ተኛ ፡ መጥቶም ፡ አዲስ ፡ ፈረሶች ፡ የመጠየቂያ ፡ ትዕዛዙን ፡ እ
ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ይወረውረዋል ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስናመዛዝ
ነው ፡ ልባችን ፡ ከቁጣ ፡ ይልቅ ፡ በርኅራኄና ፡ በሐዘን ፡ ይመላ
ል ። ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ጥቂት ፡ ቃል ፡ ጨምሬ ፡ ለመናገር ፡ እፈ

* «ትሮይካ» በሶስት ፡ ፈረሶች ፡ የሚሳብ ፡ ሠረገላ ፡ ነው ።

ሊጋለሁ ፤ ለሃያ ፡ ዓመታት ፡ ያህል ፡ በመላው ፡ ሩሲያ ፤ እየ ተዘዋወርኩ ፡ ጉቦ ፡ አድርጌአለሁ ። የማመላለሻ ፡ ጣቢያዎች ፡ የሚገኙባቸውንም ፡ መንገዶች ፡ ሁሉ ፡ አብዛኞቹን ፡ አውቃ ቸዋለሁ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕድሜ ፡ ያላቸውን ፡ የሠረገላ ፡ ነጂ ዎችም ፡ አውቃለሁ ። እኔ ፡ የማላውቀውና ፡ በጉዳይ ፡ ምክን ያት ፡ ያላጋጠመኝ ፡ አንድም ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ አይገኝ ም ። በጉዞዬ ፡ ላይ ፡ የተመለከትኩትንና ፡ ያጠራቀምኩትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ እንደማሳትመው ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ። ላሁኑ ፡ ግን ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሞች ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ የ ሚታዩት ፡ ፈጽሞ ፡ በተሳሳተ ፡ መንገድ ፡ መሆኑን ፡ ልገልጽ ፡ እወዳለሁ ። እንዚህ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ የተጠሉ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሞች ፡ በጠቅላላው ፡ ሰላማዊና ፡ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡ ሰውንም ፡ ለማስደሰት ፡ የሚጥሩ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ክብራቸውን ፡ የሚያ ጋንኑና ፡ የሰውንም ፡ ገንዘብ ፡ ለመንጠቅ ፡ የሚሞክሩ ፡ ሰዎች ፡ አይደሉም ። በንግግራቸው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ የማወቅና ፡ የመረ ዳት ፡ ፍላጎት ፡ ያሳያሉ ። አብዛኞቹ ፡ የተከበሩ ፡ መንገደኞች ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ሳይመለከቱ ፡ በማለፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስህተት ፡ ያደርጋሉ ። እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ግን ፡ አንዳንድ ፡ የማይረቡ ፡ የመ ንግሥት ፡ ሹማምንት ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ጉዳይ ፡ ሲዘዋ ወሩ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ንግግር ፡ ከመስማት ፡ የማመላለሻ ፡ ሹ ሞችን ፡ ጨዋታ ፡ መስማትን ፡ እመርጣለሁ ።

ከተከበሩ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሞች ፡ መካከል ፡ ወዳጆች ፡ እን ዳሉኝ ፡ በቀላሉ ፡ ለመረዳት ፡ የሚቻል ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ደግ ሞ ፡ ትዝታው ፡ ከልቤ ፡ ምንጊዜም ፡ የማይጠፋ ፡ አንድ ፡ የማ መላለሻ ፡ ሹም ፡ አለ ። ከሕይወቱ ፡ ባንደኛው ፡ ዘመን ፡ ውስ ጥ ፡ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ አገናኘን ፤ እነሆ ፡ አ ሁን ፡ ለትዕግሥተኛ ፡ አንባቢዬ ፡ ልነግር ፡ የምፈቅደው ፡ ይህ ንኑ ፡ ታሪክ ፡ ነው ።

እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፰፻፲፪ ዓ ፡ ም ፡ እንደአጋጣሚ ፡ ወደ ፡ እ

ንትና … አውራጃ ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡ ተጓዝኩ ። ያ ፡ መንገድ ፡ አሁን ፡ የለም ። በማዕርጌ ፡ ዝቅተኛነትና ፡ ያለኝም ፡ ገንዘብ ፡ ለሁለት ፡ ፈረስ ፡ ብቻ ፡ የሚበቃ ፡ ስለነበር ፡ የምጓዘው ፡ ከጣቢ ያ ፡ ወደ ፡ ጣቢያ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የማመላለሻ ፡ ሹ ማምንትም ፡ እምብዛም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አክብሮት ፡ አይቀበሉኝ ም ፡ ነበር ። ለኔ ፡ መብቴና ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታየኝንም ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኃይል ፡ አስገድጄ ፡ እወስድ ፡ ነበር ። ወጣትና ፡ ትዕግሥተ ፡ ቢስ ፡ በመሆኔም ፡ አንዳንድ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሞ ች ፡ ከፍርሃትና ፡ ከግብረ ፡ ገብ ፡ ማነስ ፡ የተነሳ ፡ ለኔ ፡ የተዘጋ ጀውን ፡ ፈረስ ፡ ለሌላ ፡ ከፍተኛ ፡ ሰው ፡ ሲሰጡ ፡ እናደድ ፡ ነ በር ። መታለፍን ፡ የለመድኩት ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ በሚሰጠው ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ተገኝቼ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ የማይረባ ፡ አሽከር ፡ እ ኔን ፡ እየተወ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሲያሳልፍ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። አሁን ፡ ግን ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ሁናቴዎች ፡ የተለመዱ ፡ ነገ ሮች ፡ ሆነው ፡ አገኘኋቸው ። ለነገሩ ፡ «ሰው ፡ እንደ ፡ ማዕር ጉ ፡» የተባለው ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ የጸደቀው ፡ ደንብ ፡ ቀርቶ ፡ «ሰው ፡ እንደ ፡ አዕምሮው ፡» የሚባል ፡ ደንብ ፡ ቢተካ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ ይውጠን ፡ ነበር? እንዴት ፡ ያለ ፡ ክርክርስ ፡ በተነሳ ፡ ነበር! አሽከሮችስ ፡ መጀመሪያ ፡ ማንን ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር? ዳ ሩ ፡ ግን ፡ ይሄ ፡ ይቅርና ፡ ወደ ፡ ጥንት ፡ ታሪኬ ፡ ልመለስ ።

ቀኑ ፡ ሞቃት ፡ ነበር ። ከእንትና ፡ ጣቢያ ፡ ሶስት ፡ ቬርስታ ዎች ፡ እራቅ ፡ ብሎ ፡ ካፊያ ፡ ጀመረ ፤ ካንድ ፡ ደቂቃ ፡ በኋላም ፡ ዶፍ ፡ ስለወረደ ፡ ከግር ፡ እስከራሴ ፡ በዝናብ ፡ በሰበስኩ ። ወደ ፡ ጣቢያው ፡ እንደደረስኩም ፡ መጀመሪያ ፡ የፈለግሁት ፡ በፍጥ ነት ፡ ልብሴን ፡ መለወጥና ፡ ሁለተኛም ፡ ሻይ ፡ መጠጣት ፡ ነ በር ። «ሰማሽ ፡ ወይ ፡ ዱኛ!» አለና ፡ ጮኸ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹ ሙ ። «የሻዩን ፡ ጀበና ፡ አዘጋጂና ፡ ሄደሽ ፡ ወተት ፡ አምጪ ።» ይህን ፡ ትዕዛዝ ፡ በመቀበል ፡ ያንድ ፡ ያስራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ልጃገረድ ፡ በመጋረጃ ፡ ከተከፈለ ፡ ግድግዳ ፡ በስተኋላ ፡ ብቅ ፡

አለችና ፡ ፈጥና ፡ ወደበረንዳው ፡ ወጣች ። ውብቷ ፡ አስደነቀኝ ። «ልጅዎ ፡ ናት? » ብዬ ፡ ጠየቅሁት ። «አዎን ፡ ልጄ ፡ ናት ፡» ሲል ፡ በኩራት ፡ ልብ ፡ መለሰልኝና ፡ «እንደ ፡ ቀድሞ ፡ እና ቷ ፡ ብልህና ፡ ቀልጣፋ ፡ ናት ፡» አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወዲያ ው ፡ ማዘገየዬን ፡ መገልበጥ ፡ ጀመረ ፤ እኔም ፡ መጠነኛና ፡ ን ጹህ ፡ በሆነው ፡ የመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ የተደረደሩትንና ፡ ቤቱን ፡ ያደመቁትን ፡ ሥዕሎች ፡ መመልከት ፡ ጀመርኩ ። ሥ ዕሎቹ ፡ የሚያስረዱት ፡ የኰበለለውን ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። በመጀመሪያው ፡ ሥዕል ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አዛውንት ፡ ሰውዬ ፡ የሌሊት ፡ ቆቡን ፡ እንዳደረገና ፡ የጧት ፡ ልብሱን ፡ እንደለበሰ ፡ አንድ ፡ ልቡ ፡ የሸፈተን ፡ ልጅ ፡ ሲሰናበትና ፡ ልጁም ፡ ያባቱ ን ፡ ምርቃንና ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ገንዘብ ፡ በችኰላ ፡ ሲቀበ ል ፡ ይታያል ። ሌላው ፡ ሥዕል ፡ ደግሞ ፡ የልጁን ፡ ያመንዝራ ፡ ጠባይ ፡ በከንቱ ፡ ወዳጆችና ፡ በሐፍረተ ፡ ቢስ ፡ ሴቶች ፡ እን ደተከበበ ፡ በዝርዝር ፡ ያሳያል ። ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ደግሞ ፡ ወ ጣቱ ፡ ልጅ ፡ ከተበላሸና ፡ ከደኸየ ፡ በኋላ ፡ የተቀዳደደና ፡ ያ ረጀ ፡ ካባ ፡ ለብሶና ፡ ሾጣጣ ፡ ባርኔጣ ፡ ደፍቶ ፡ አሳማዎች ፡ ሲጠብቅና ፡ ምግባቸውንም ፡ ሲካፈል ፡ ያመለክታል ። በልጁ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ጥልቅ ፡ የሐዘንና ፡ የመጸጸት ፡ ስሜት ፡ አለበት ። የመጨረሻው ፡ ሥዕል ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ጋ ፡ ሲመለስ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። ደግ ፡ አባቱ ፡ የሌሊት ፡ ቆቡን ፡ እንዳደረገ ና ፡ የጧት ፡ ልብሱን ፡ እንደለበሰ ፡ ሮጦ ፡ ወጥቶ ፡ ይቀበለዋ ል ። የኰበለለውም ፡ ልጅ ፡ ወዲያው ፡ አባቱ ፡ ጫማ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ። በስተጓሮ ፡ በኩልም ፡ የወጥ ፡ ቤቱ ፡ የሰባ ፡ ጥጃ ፡ ሲያርድና ፡ ታላቅ ፡ ወንድምየውም ፡ የደስታው ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ አገልጋዮቹን ፡ ሲጠይቅ ፡ ያሳያል ። በያንዳ ንዱ ፡ ሥዕል ፡ ስር ፡ ያለውን ፡ የጀርመንኛ ፡ የግጥም ፡ ቃልም ፡ አነበብኩ ። ይህ ፡ ሁሉና ፡ የሚጣፍጥ ፡ መአዛ ፡ ያለው ፡ በማሰ ሮ ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ የዛፍ ፡ ችግኝ ፤ አልጋውና ፡ በብሩህ ፡ የተ

ጠለፈው ፡ የመሰከኵት ፡ መጋረጃ ፤ እንዲሁም ፡ ባካባቢው ፡ የነበረው ፡ ሌላው ፡ ዕቃ ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ አዲስ ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ። ዕድሜው ፡ ወደ ፡ ሃምሳ ፡ የሚጠጋው ፡ ጤናማና ፡ ደስተኛ ፡ የሆነው ፡ የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ረጂም ፡ አረንጓዴ ፡ ካፖርቱን ፡ እንደለበሰና ፡ ባለቁ ፡ የጨርቅ ፡ ቁራጮች ፡ ላይ ፡ ሶስት ፡ ሜዳዩን ፡ እንዳንጠለጠለ ፡ አሁንም ፡ ይታየኛል ።

የሠረገላ ፡ ነጂዬን ፡ ወዲያው ፡ ከፍየው ፡ እንደሄደ ፡ ዱኛ ፡ የሻይ ፡ ጀበናውን ፡ ይዛ ፡ መጣች ። ይህች ፡ ትንሽ ፡ ፍቅር ፡ ወዳድ ፡ ልጃገረድ ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ያሳደረችው ፡ ስሜት ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ ለማወቅ ፡ አልዘገየችም ፤ ታላላቅና ፡ ሰማያዊ ፡ ዓይኖቿን ፡ ኵስተር ፡ አድርጋ ፡ ወደታች ፡ ጣል ፡ አደረገቻቸው ። ከርሷ ፡ ጋር ፡ ጨዋታ ፡ ጀመርኩ ፤ ዓለምን ፡ እንደሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያላንዳች ፡ ሐፍረት ፡ ጥያቄየን ፡ ትመልስ ፡ ነበር ። አባቷን ፡ አረቂ ፡ ጋበዝሁት ፤ ለርሷም ፡ አንድ ፡ ስኒ ፡ ሻይ ፡ ሰጠኋት ፤ ሶስታችንም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እንደምንተዋወቅ ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ እንጨዋወት ፡ ጀመር ።

ፈረሶቹ ፡ ተዘጋጁ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከማመላለሻ ፡ ሹሙና ፡ ከልጂቷ ፡ ጋር ፡ መለየት ፡ አልወደድኩም ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ተሰናበትኳቸው ፤ አባትየውም ፡ መልካም ፡ ጉዞ ፡ ተመኘልኝ ፤ ልጅቷም ፡ እሠረገላዬ ፡ ድረስ ፡ መጥታ ፡ ሸኘችኝ ። እበረንዳው ፡ ላይ ፡ ቆም ፡ አልኩና ፡ እንድስማት ፡ ትፈቅድልኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠየቅኋት ። ዱኛም ፡ ፈቀደችልኝ ፡ ... መሳምን ፡ እንደ ፡ ጊዜ ፡ ማሳለፊያ ፡ ያህል ፡ ቆጥሬ ፡ እራሴን ፡ ማስደሰት ፡ ከጀመርኩበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ የሳምኳቸውን ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ብቆጥር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አይባልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህችን ፡ ልጅ ፡ እንደመሳም ፡ ያህል ፡ የሚያስደስትና ፡ የዘላለም ፡ ትዝታ ፡ የሰጠኝ ፡ የለም ።

ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ እግር ፡

ጣለኝና ፡ በዚያው ፡ መንገድ ፡ መጥቼ ፡ እዚያው ፡ ቦታ ፡ ደረስ
ኩ ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ልጅ ፡ ትዝ ፡ አለችኝና ፡ እንደገና ፡
እያት ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ አደረብኝ ። ባ
ንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ምናልባት ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ተሽሮ ፡
ይሆናል ፤ ዱኛም ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ አግብታ ፡ ይሆናል ፡ ብየ ፡ አ
ሰብኩ ። ምናልባት ፡ ከሁለት ፡ አንዳቸው ፡ ሞተው ፡ ይሆናል ፡
የሚል ፡ ሐሳብም ፡ በአዕምሮዬ ፡ ላይ ፡ ብልጭ ፡ አለ ። ስለዚ
ህ ፡ ወደ ፡ እንትና ፡ ... የማመላለሻ ፡ ጣቢያ ፡ በሐዘን ፡ ስሜ
ት ፡ ተቃረብኩ ። ፈረሶቼ ፡ ወደ ፡ ማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ አነስተ
ኛ ፡ ቤት ፡ ተጠጉ ። ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ስገባም ፡ የኰበለ
ለውን ፡ ልጅ ፡ ታሪክ ፡ የሚገልጹትን ፡ ሥዕሎች ፡ ወዲያው ፡
አስታወስኳቸው ። ጠረጴዛውና ፡ አልጋው ፡ እዱሮ ፡ ቦታቸው ፡
እንዳሉ ፡ ናቸው ። በመስኰቱ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ አበባ ፡ የለም ። በ
ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉም ፡ የመበስበስና ፡ የመ
ወዳደቅ ፡ ምልክት ፡ ያሳያል ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ የበግ ፡
ቆዳ ፡ ኰት ፡ ለብሶ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ። እኔ ፡ በመምጣቴ ፡ ተነስ
ቶ ፡ ቁጭ ፡ አለ ። ... ዱሮ ፡ እንደማውቀው ፡ ሳምሶንን ፡ ይመ
ስል ፡ ነበር ፤ አሁን ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ አርጅቷል! ማዘግየቱን ፡
ሲገለብጥ ፡ የሸበተ ፡ ጸጉሩንና ፡ ባልተላጨ ፡ ጢሙ ፡ ላይ ፡
ያለውን ፡ ጐርጓዳ ፡ መስመር ፤ እንዲሁም ፡ የጐበጠ ፡ ትከሻ
ውን ፡ አየሁ ፤ በዚህ ፡ ጊዜም ፡ ያን ፡ የመሰለ ፡ ግድንግድ ፡ ሰ
ው ፡ በሶስትና ፡ በአራት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ኰሳሳና ፡ ያረጀ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ እጅግ ፡ ተደነቅኩ ።«አያ
ውቁኝም ፡ ወይ?» አልኩና ፡ ጠየቅሁት ። «እኔና ፡ እርስዎ ፡ እ
ኰ ፡ የጥንት ፡ ወዳጆች ፡ ነን ።» — «ሊሆን ፡ ይችላል ፡»
አለና ፡ በከፋው ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ መለሰልኝ ። «በዚህ ፡ መን
ገድ ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚተላለፉ ፡ ብዙዎቹ ፡ መንገደኞች ፡
ወደዚህ ፡ ይመጣሉ ።» — «ልጅዎ ፡ ዱኛስ ፡ እንደምን ፡ ና
ት?» አልኩና ፡ ቀጠልኩ ። ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ፊቱን ፡ ኰ

ስተር ፡ አደረገና ፡ «እግዜር ፡ ያውቃል ፡» አለ ። — « አገባ ችን? » ብዬ ፡ ጠየቅሁት ። ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ጥያቄዬን ፡ ያልሰማ ፡ በመምሰል ፡ ማዘጋዎዬን ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ማን በቡን ፡ ቀጠለ ። እኔም ፡ ጥያቄዬን ፡ ተውኩና ፡ ጀበና ፡ እንዲ ጣድ ፡ አሳሰብኩ ። ነገሩን ፡ የማወቅ ፡ ፍላጐት ፡ ሆዴን ፡ ስለ ቆረጠኝ ፡ ምናልባት ፡ አረቂ ፡ የጥንት ፡ ወዳጄን ፡ ምላስ ፡ ያፍ ታታው ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ አደረግሁ ።

አልተሳሳትኩም ፤ ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ የጋበዝኩትን ፡ አንድ ፡ ብርጭቆ ፡ አረቂ ፡ አልቀበልም ፡ አላለም ። ሩም ( አ ረቂ ፡ ) የከፋውን ፡ ፊቱን ፡ እንደሚያብራራለት ፡ ተረዳሁ ። ሁ ለተኛውን ፡ ብርጭቆ ፡ ሲጠጣ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደሆንኩ ፡ በማ ስታወስ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ያስታወሰኝ ፡ በመምሰል ፡ መለፍ ለፍ ፡ ጀመረ ። እኔም ፡ ከሰውዬው ፡ አንደበት ፡ ያስደነቀኝና ፡ ልቤን ፡ የነካው ፡ ታሪክ ፡ ሰማሁ ።

«ዱኛን ፡ ልጄን ፡ ያውቋት ፡ ነበር?» ሲል ፡ ጀመረ ። «ዋ ፡ እሷን ፡ የማያውቅ ፡ ማን ፡ አለ? አየ ፡ ዱኛ! አየ ፡ ዱኛ! እንዴ ት ፡ ያለች ፡ ልጃገረድ ፡ ነበረች! እዚህ ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያመ ስግናት ፡ ነበር ፤ በርሷ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ የሚናገር ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። ሴት ፡ ወይዛዝርቱም ፡ ለመታሰቢያ ፡ መ ሐረብና ፡ ጉትቻ ፡ ይሰጧት ፡ ነበር ። መኳንንትም ፡ ወደዚህ ፡ ጣቢያ ፡ ሲመጡ ፡ ምሳ ፡ ወይም ፡ እራት ፡ የሚጠብቁ ፡ በመም ሰል ፡ አውቀው ፡ ይቆዩ ፡ ነበር ። በውነቱ ፡ ግን ፡ እሷን ፡ እስቲ ጠግቧት ፡ ድረስ ፡ ለመመልከት ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ አን ድ ፡ ጨዋ ፡ መኰንን ፡ ቢናደድም ፡ ቅሉ ፡ እሷን ፡ ሲያይ ፡ ወዲ ያው ፡ ይቀዘቅዝና ፡ በጥሞና ፡ ቃል ፡ ያናግረኝ ፡ ነበር ። ብነግ ርዎት ፡ አያምኑኝም ፡ እንጂ ፡ የመንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልዕክተ ኞች ፡ እንኳ ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ያነጋግሯት ፡ ነበር ። ቤቴ ንም ፡ ደግፋ ፡ የያዘችልኝ ፡ እሷው ፡ ነበረች ፤ ቤት ፡ የምትጠር ገውና ፡ ወጥ ፡ የምትሰራው ፤ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ የምታደርገው ፡

እሷው ፡ ነበረች ። እኔም ፡ የዋሁ ፡ ዓይኔን ፡ ከርሷ ፡ ላይ ፡ ለማ ንሳትና ፡ አይቼ ፡ ልጠግባትም ፡ አልችልም ፡ ነበር ። ዱኛዬን ፡ እወዳት ፡ አልነበረምን? ልጄን ፡ አፈቅራት ፡ አልነበረምን? ደ ስ ፡ ብሏት ፡ ትኖር ፡ አልነበረምን? ነገር ፡ ግን ፡ አደጋን ፡ በጸሎ ት ፡ ለማስወገድ ፡ አይቻልም ፤ ሰው ፡ ከታሰበለት ፡ ዕድሉ ፡ ሊ ያመልጥ ፡ አይችልም ።» እዚህ ፡ ላይ ፡ የደረሰበትን ፡ አደጋ ፡ በዝርዝሩ ፡ ሊነግረኝ ፡ ጀመረ ።

ከሶስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ በአንድ ፡ የክረምት ፡ ምሽት ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ አንድ ፡ መዝገብ ፡ ይዞ ፡ ሲያሰምርና ፡ ል ጁም ፡ ከመጋረጃው ፡ በስተኋላ ፡ ተቀምጣ ፡ ልብስ ፡ ስትሰፋ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ትሮይካ ፡ ሠረገላ ፡ መጣ ፤ ዘርፋፋ ፡ ቆብ ፡ ያደረ ገና ፡ ትልቅ ፡ የወታደር ፡ ካፖርት ፡ የለበሰ ፤ ወፍራም ፡ ያንገት ፡ መጠምጠሚያ ፡ የጠመጠመ ፡ መንገደኛም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገባና ፡ ፈረሶች ፡ ጠየቀ ። ፈረሶቹ ፡ ግን ፡ በሙሉ ፡ ሄደው ፡ ነበር ። መን ገደኛው ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ድምጹን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ጮ ኸና ፡ አለንጋውን ፡ ቃጣ ። ዱኛ ፡ ይህን ፡ ዓይነት ፡ ትርኢት ፡ ለ ምዳ ፡ ስለነበር ፡ ከመጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ ሮጣ ፡ ወጣችና ፡ እንግ ዳውን ፡ በጥሞና ፡ ቃል ፡ በማናገር ፡ እህል ፡ መብላት ፡ ይፈልግ ፡ እንደሆን ፡ በትህትና ፡ ጠየቀችው ። የዱኛ ፡ ብቅ ፡ ማለት ፡ የ ተለመደውን ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አስገኘ ። መንገደኛውን ፡ ቁጣው ፡ ለቆት ፡ ሄደ ። ፈረሶች ፡ እስኪመጡም ፡ ለመጠበቅ ፡ ተስማማና ፡ እራት ፡ አዘዘ ። የራስ ፡ የለስላሳ ፡ ጸጉር ፡ ባርኔ ጣውን ፡ አውልቆ ፤ ያንገት ፡ መጠምጠሚያውንም ፡ ፈትቶ ፤ ት ልቅ ፡ ካፖርቱንም ፡ አውልቆ ፡ ጥሎ ፡ ሲታይ ፡ ጊዜ ፡ ትንሽ ፡ ጥቁር ፡ እሪዝ ፡ ያለው ፡ ወጣትና ፡ መለሎ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ። ሰውየው ፡ ወዲያውኑ ፡ ተዝናንቶ ፡ ከማመላለሻ ፡ ሹ ሙና ፡ ከልጁ ፡ ጋር ፡ በደስታ ፡ መጫወት ፡ ጀመረ ። እራትም ፡ ቀረበ ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ ፈረሶቹ ፡ ተመለሱ ፤ ሳር ፡ ሳይበሉ ም ፡ ወዲያው ፡ ለመንገደኛው ፡ ሰውየ ፡ እንዲጫኑለት ፡ የማመ

ላለሻ ፡ ሹሙ ፡ አዘዘ ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ተ
መልሶ ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡ መንገደኛው ፡ ሰውዬው ፡ በጠና ፡ ታሞ ፡
እሳንቃው ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ አገኘው ። ድካምና ፡ እ
ራስ ፡ ምታት ፡ ስለተሰማው ፡ መንገዱን ፡ ሊቀጥል ፡ አልቻለም ፡ ...
ምን ፡ ይደረግ! የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ አልጋውን ፡ ለቀቀለት ፤
ሕመምተኛው ፡ በማግሥቱ ፡ ሳይሻለው ፡ ቢቀርም ፡ ከእንትና ፡ ...
ቀበሌ ፡ ሐኪም ፡ እንዲመጣለት ፡ ተወሰነ ።

በማግሥቱ ፡ ፈረሰኛው ፡ ሕመሙ ፡ ባሰበት ። አሽከሩ ፡ ወጌ
ሻ ፡ ለመጥራት ፡ ወደ ፡ አቅራቢያው ፡ ከተማ ፡ ሄደ ። ዱኛም ፡
በኰምጣጤ ፡ የራስ ፡ መሐረብ ፡ እሕመምተኛው ፡ ሰውዬ ፡ እ
ራስ ፡ ላይ ፡ አድርጋ ፡ ስፌቷን ፡ እየሰፋች ፡ አልጋው ፡ አጠገብ ፡
ተቀመጠች ። ሕመምተኛው ፡ በማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ፊት ፡ ሲ
ሆን ፡ ያቃስታል ፤ አንዳችም ፡ ቃል ፡ ለመናገርም ፡ አይችልም ።
ሆኖም ፡ ሁለት ፡ ስኒ ፡ ቡና ፡ ጠጥቶ ፡ እራቱን ፡ ስጡኝ ፡ እያለ ፡
አቃሰተ ። ዱኛ ፡ ካልጋው ፡ አጠገብ ፡ ከቶ ፡ አልተለየችውም ፡
ነበር ። የሚጠጣ ፡ ነገር ፡ ስጡኝ ፡ እያለ ፡ ያለማቋረጥ ፡ ሲለም
ንም ፡ ዱኛ ፡ እርሷ ፡ እራሷ ፡ በእጅዋ ፡ ያዘጋጀችውን ፡ የሎ
ሚ ፡ ጭማቂ ፡ በኩባያ ፡ እያመጣች ፡ ትሰጠው ፡ ነበር ። ሕመ
ምተኛውም ፡ ከንፈሩን ፡ በሎሚው ፡ ጭማቂ ፡ እያራሰ ፡ ኩባ
ያውን ፡ በመለሰ ፡ ቁጥር ፡ የዱኛን ፡ እጅች ፡ በደካማ ፡ አያያዝ ፡
ጨበጥ ፡ እያደረገ ፡ ምሥጋናውን ፡ ይገልጽ ፡ ነበር ።

ሐኪሙ ፡ በራት ፡ ሰዓት ፡ ደረሰ ። የሕመምተኛውን ፡ ልብ ፡
ካዳመጠ ፡ በኋላ ፡ በጀርመንኛ ፡ አናገረው ፤ ቀጥሎም ፡ በመስ
ኰብኛ ፡ ቋንቋ ፡ በመናገር ፡ ሕመምተኛው ፡ የሚያስፈልገው ፡
እረፍት ፡ ማድረግ ፡ ብቻ ፡ እንደሆነና ፡ ከጥቂት ፡ ቀናት ፡ በኋ
ላም ፡ ጉዞውን ፡ ለመቀጠል ፡ እንደሚችል ፡ አስታወቀ ። ሐኪ
ሙ ፡ ስላደረገው ፡ ምርመራ ፡ ፈረሰኛው ፡ ሰውዬ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡
ሩብል ፡ ከፈለው ፤ እራትም ፡ ጋበዘው ። ሐኪሙም ፡ ግብዣው
ን ፡ ተቀበለና ፡ ሁለቱም ፡ እራታቸውን ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡

በሉ ፤ አንድ ፡ ጠርሙስ ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ ጨልጠው ፡ ጠ
ጡ ። እንዳቸው ፡ ላንዳቸው ፡ የነበራቸውም ፡ ስሜት ፡ በደስ
ታ ፡ የተሞላ ፡ ነበር ።

ካንድ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ፈረሰኛው ፡ ሰውዬ ፡ በሙሉ ፡ ዳነ ።
እጅግ ፡ ከመደሰቱም ፡ የተነሣ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከዱኛ ፡ ጋር ፡ አ
ንድ ፡ ጊዜም ፡ ከማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ጋር ፡ ያለ ፡ ማቋረጥ ፡ ይ
ቀልዳል ፤ እያፏጨም ፡ ያዜማል ፤ ከመንገደኞችም ፡ ጋር ፡ ይ
ጫወታል ፤ የፈረስ ፡ መጠየቂያ ፡ ደብዳቤአቸውንም ፡ ይመዘግ
ባል ፤ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ ለመሄድ ፡ ሲ
ነሣ ፡ ደጉ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ ከዚህ ፡ ከለመደው ፡ መልካም ፡
ሰው ፡ ጋር ፡ መለያየት ፡ ከባድ ፡ ቅሬታ ፡ አሳደረበት ። ቀኑ ፡
ዕሁድ ፡ ዕለት ፡ ስለነበር ፡ ዱኛ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡
ለመሔድ ፡ ተዘጋጀች ። የፈረሰኛው ፡ ሰውዬ ፡ ሠረገላ ፡ ቀ
ረበ ። በማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ቤት ፡ ለቆየበት ፡ ጊዜ ፡ ለማመ
ላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችሮታ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ተሰናበ
ተው ። ዱኛንም ፡ እንደዚሁ ፡ ተሰናበታትና ፡ ከመንደሩ ፡ በ
ንደኛው ፡ አንጻር ፡ ወደሚገኘው ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ድረ
ስ ፡ በሠረገላ ፡ ልውሰድሽ ፡ ብሎ ፡ ጋበዛት ። ዱኛ ፡ ግራ ፡
ገባት ... «ምን ፡ አስፈራሽ?» አላት ፡ አባቷ ። «ክቡርነታ
ቸው ፡ እንደሆኑ ፡ ተኩላ ፡ አይደሉም ፤ አይነክሱሽም ። እ
ስከ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያኑ ፡ ድረስ ፡ ይውሰዱሽ ።» ዱኛ ፡
እሠረገላው ፡ ላይ ፡ ወጣችና ፡ በፈረሰኛው ፡ ሰውዬ ፡ ጐን ፡
ተቀመጠች ፤ አሽከርየውም ፡ ዘሎ ፡ እፊት ፡ መቀመጫው ፡
ላይ ፡ ወጣ ፤ ሠረገላ ፡ ነጂውም ፡ አፏጨ ፤ ፈረሶቹም ፡
ጋልበው ፡ ሄዱ ።

ምስኪኑ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ ልጁን ፡ ዱኛን ፡ ከፈረስ
ኛው ፡ ሰውዬ ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ እንድትሄድ ፡ ለምን ፡ እንደፈቀ
ደና! አዕምሮውንስ ፡ ምን ፡ እንዳሳወረው! ምን ፡ እንደነካው
ስ! ከቶ ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም ። ገና ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ሳይሆን ፡

ልቡ ፡ መጨነቅ ፡ ጀመረ ፤ እጅግ ፡ ከመስጋቱም ፡ የተነሳ ፡ ሊታ
ገስ ፡ ስላልቻለ ፡ ልጁን ፡ ለመፈለግ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡
ሄደ ። እዚያ ፡ እንደደረሰም ፡ ሰዎች ፡ ተሳልመው ፡ ሲወጡ ፡
አየ ። ዱኛ ፡ ግን ፡ በቅጥሩም ፡ ውስጥ ፡ ሆነ ፡ በቤተ ፡ ክርስትያ
ኑ ፡ በር ፡ ላይ ፡ አልነበረችም ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስትያኑ ፡ ውስጥ ፡ ፈጥኖ ፡ ገባ ። ቄሱ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወጥ
ቷል ። ቄሰ ፡ ገበዙም ፡ ሻማዎቹን ፡ ያጠፋል ። ሁለት ፡ አሮጊ
ቶች ፡ ሴቶች ፡ ጥግ ፡ ይዘው ፡ ጸሎታቸውን ፡ ያደርሳሉ ። ዱኛ ፡
ግን ፡ የትም ፡ ቦታ ፡ አልነበረችም ። ምስኪን ፡ አባትዮው ፡ ቢ
ቸግረው ፡ «ልጄ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ መጥታ ፡ ነበር ፡
ወይ?» ብሎ ፡ ቄሰ ፡ ገበዙን ፡ ጠየቀው ። ቄሰ ፡ ገበዙም ፡ «አ
ልመጣችም ፡» ሲል ፡ መለሰለት ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ሙት
ት ፡ ድክም ፡ ብሎ ፡ ተመለሰ ። የቀረው ፡ አንድ ፡ ተስፋ ፡ ብ
ቻ ፡ ነበር ፤ ይሄውም ፡ ምናልባት ፡ ዱኛ ፡ የልጅነት ፡ ሐሳብ ፡
መርቷት ፡ የክርስትና ፡ እናቷ ፡ ወደምትኖርበት ፡ ቀጥሎ ፡ ወ
ዳለው ፡ ጣቢያ ፡ ሄዳ ፡ እንደሆን ፡ ነው ። ከሠረገላው ፡ ጋር ፡
የላካቸው ፡ ሰዎች ፡ ተመልሰው ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ በጭን
ቅ ፡ ጓግቶ ፡ ጠበቀ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቀኑ ፡ መሸ ፤ የሠረገላ ፡ ነጂ
ውም ፡ ሳይመለስ ፡ ቀረ ። በመጨረሻም ፡ ወደሌሊት ፡ ገደማ ፡
ሰክሮና ፡ ብቻውን ፡ ሆኖ ፡ ይህንን ፡ የሚያስቅቅ ፡ ወሬ ፡ ይዞ ፡
መጣ ። «ዱኛ ፡ ከሚቀጥለው ፡ ጣቢያ ፡ ከፈረሰኛው ፡ ጋ
ር ፡ አብራ ፡ ሄደች ።»

ሽማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ የደረሰበትን ፡ አደጋ ፡ ችሎ ፡ ሊቀበ
ለው ፡ አልቻለም ። ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ማታም ፡ ያ ፡ ቀጣፊ ፡ ወጣ
ት ፡ ሳይሄድ ፡ በፊት ፡ ተኝቶበት ፡ በነበረው ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ ሽ
ማግሌው ፡ ሰውዬ ፡ ተኛ ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ሲመለከተው ፡ ጊዜ ፡ ወጣቱ ፡ ሰውዬ ፡
ታመምኩ ፡ ያለው ፡ ሲያብል ፡ መሆኑን ፡ ተረዳው ። ምስኪኑ ፡
ሽማግሌ ፡ በትኩሳት ፡ ክፉኛ ፡ ስለታመመ ፡ ወደ ፡ እንትና ፡ ...

ቀበሌ ፡ ወሰዱት ። ሌላ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹምም ፡ በሱ ፡ እግር ፡ ለጊዜው ፡ ተተካ ። ሽማግሌውን ፡ የሚያክመው ፡ ሐኪም ፡ ያንን ፡ ፈረሰኛ ፡ የመረመረው ፡ ሐኪም ፡ ስለነበር ፤ ያ ፡ ታመምኩ ፡ ያለ ፡ ወጣት ፡ ፈረሰኛ ፡ ፍጹም ፡ ደህና ፡ እንደነበርና ፡ ተንኰል ፡ ማሰቡንም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያውቅ ፡ እንደነበር ፤ ያልተናገረበትም ፡ ምክንያት ፡ ፈረሰኛው ፡ ሰውዬ ፡ ይገርፈኛል ፡ ብሎ ፡ በመፍራት ፡ እንደነበር ፡ ለሽማግሌው ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ ገለጸለት ። ጀርመኑ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ዕውነቱን ፡ ይሁን ፡ ወይስ ፡ ዕውቀቱን ፡ ለማሳየት ፡ ያህል ፡ ይሁን ፡ ምስኪኑን ፡ ሕመምተኛ ፡ በምንም ፡ እረገድ ፡ ሊያጽናናው ፡ አልቻለም ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ከሕመሙ ፡ ገና ፡ በጐ ፡ ሳይሆን ፡ በእንትና ፡ ... ቀበሌ ፡ ካለው ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሁለት ፡ ወር ፡ ፈቃድ ፡ ጠይቆ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ እንዳሰበ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ሳይነግር ፡ ልጁን ፡ ለመፈለግ ፡ በግሩ ፡ ተነስቶ ፡ ሄደ ። ከመዝገቡ ፡ ላይ ፡ ሻምበል ፡ ሚንስኪይ ፡ (ፈረሰኛው ፡ ሰውዬ ፡) ከስሞሌንስክ ፡ ወደ ፡ ፔቴርቡርግ ፡ እንደተጓዘ ፡ አጣራ ። ሠረገላውን ፡ የነዳለት ፡ ሰውዬ ፡ እንደተናገረውም ፡ ዱኛ ፡ የሄደችው ፡ እያለቀሰች ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ በገዛ ፡ ፈቃዷ ፡ ይመስላል ። «የእግዜር ፡ ፈቃዱ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡» አለ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ «የጠፋች ፡ ጠቦቴን ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ መልሼ ፡ አመጣታለሁ ።» በዚህ ፡ ሐሳብ ፡ ተጽናንቶ ፡ ወደ ፡ ፔቴርቡርግ ፡ ደረሰ ፤ እዚያም ፡ ወደኢዝማይሎቭ ፡ የጦር ፡ ሠፈር ፡ ገብቶ ፡ በወታደርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጁ ፡ ወደነበረና ፡ አሁን ፡ ከሥራ ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደሚኖር ፡ መኰንን ፡ ቤት ፡ ገባ ። ከዚያም ፡ ፍለጋውን ፡ ጀመረ ። ሻምበል ፡ ሚንስኪይ ፡ በፔቴርቡርግ ፡ ውስጥ ፡ ዲሙቶቭ ፡ በተባለ ፡ ሆቴል ፡ ውስጥ ፡ እንደሚኖር ፡ ወዲያው ፡ ተረዳ ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ሰውየውን ፡ ለማየት ፡ ወሰነ ።

ማለዳ ፡ ጧትም ፡ ወደፈረሰኛው ፡ ቤት ፡ ደርሶና ፡ እበሩ ፡

ላይ ፡ ቁሞ ፡ «አንድ ፡ የዱሮ ፡ ወታደር ፡ ክቡርነትዎን ፡ ለማየ
ት ፡ ይፈልጋል ፡ » ብለህ ፡ ንገርልኝ ፡ ሲል ፡ አሽከርዮውን ፡
ጠየቀው ። አሽከርዮውም ፡ የፈረስ ፡ ጫማውን ፡ እግንድ ፡ ላ
ይ ፡ እየጠረገ ፡ ጌታው ፡ መተኛቱንና ፡ ከአምስት ፡ ሰዓት ፡
በፊትም ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ አለመቀበሉን ፡ ነገረው ። የማመ
ላለሻ ፡ ሹሙም ፡ ተመልሶ ፡ ሄደና ፡ በቀጠረው ፡ ሰዓት ፡ እን
ደገና ፡ ተመልሶ ፡ መጣ ። ሚንስኪይ ፡ እራሱ ፡ የጧት ፡ ልብ
ሱን ፡ ለብሶና ፡ ደማቅ ፡ ቀይ ፡ ቆብ ፡ አድርጎ ፡ ሊቀበለው ፡
ወጣ ። « ምንድን ፡ ነው ፡ ጉዳይህ ፡ ወንድሜ?» አለና ፡ ጠየ
ቀው ። የሽማግሌው ፡ ልብ ፡ በስሜት ፡ ገነፈለ ፤ ዓይኖቹም ፡
እንባ ፡ ቋጠሩ ፤ አንደበቱ ፡ ስለተሳሰረም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡
ብቻ ፡ ተናገረ ፤ «ክቡር ፡ ሆይ! ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው!
ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ! ...» ሚንስኪያ ፡ ሽማግሌውን ፡ በፍ
ጥነት ፡ ከግር ፡ እስከራሱ ፡ አየውና ፤ ፊቱ ፡ ቀላ ፤ እጁን ፡ ይ
ዞም ፡ ወደ ፡ ቢሮው ፡ ይዞት ፡ ገባና ፡ በሩን ፡ ከውስጡ ፡ በኩል ፡
ቆለፈው ። «ክቡር ፡ ሆይ ፡» ሲል ፡ ሽማግሌው ፡ ነገሩን ፡ ቀ
ጠል ፡ አድርጎ ፤ «መቸም ፡ የፈሰሰ ፡ ውኃ ፡ አይታፈስም ፤
ግን ፡ ምስኪን ፡ ልጄን ፡ ዱኛን ፡ መልሰው ፡ ይስጡኝ ። እስኪ
በቃዎት ፡ ድረስ ፡ ተደስተውባታል ፤ ግን ፡ ጨርሰው ፡ አያበላ
ሿት ። » «አንድዩ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ አይመለስም ፡» አለ ፡ ወ
ጣቱ ፡ ሰውዩ ፡ በመጸጸት ፡ መልክ ። «በድዩኃለሁ ፤ ይቅርታ ፡
ልጠይቅህም ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዱኛን ፡ ይከዳታል ፡
ብለህ ፡ አታስብ ። ከኔ ፡ ጋር ፡ በደስታ ፡ እንደምትኖር ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ እገባልሃለሁ ። ምን ፡ ታደርግልሃለች? እኔን ፡ ትወደኛ
ለች ፤ የጥንት ፡ ኑሮዋንም ፡ እረስታዋለች ። የሆነውን ፡ ነገር ፡
አንተም ፡ ሆንክ ፡ እርሷ ፡ ምንጊዜም ፡ አትረሱትም ።» ከ
ዚህ ፡ በኋላ ፡ ወጣቱ ፡ ሰውዩ ፡ በማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ እጅጌ ፡
ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሸጉጥ ፡ አደረገና ፡ በሩን ፡ ከፈተው ፤
ሽማግሌው ፡ ሰውዩም ፡ ሳያውቀው ፡ እመንገድ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

ለብዙ ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ እንጨት ፡ ደርቆ ፡ ቆመ ፤ በመጨ
ረሻም ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ ወረቀት ፡ በጅጌው ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡
አስታወሰ ። መዞ ፡ አውጥቶ ፡ በፊታውም ፡ ጊዜ ፡ የተጨባበ
ጡ ፡ አያሌ ፡ ያምስትና ፡ ያስር ፡ ሩብል ፡ ወረቀቶች ፡ አገኘ ።
እንደገና ፡ ዓይኖቹ ፡ እንባ ፡ ቋጠሩ ፤ እንባ ፡ ያቀረረውም ፡ እን
ዲህ ፡ ያለ ፡ ውርደት ፡ ስለደረሰበት ፡ ነው ። ወረቀቶቹን ፡ ጨ
ባብጦ ፡ እንደ ፡ ኳስ ፡ ጠቀለለና ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ጣላቸው ፤
በግሩ ፡ እረጋግጦም ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ። ... ጥቂት ፡ እርምጃ
ዎች ፡ ያህል ፡ ከሄደ ፡ በኋላም ፡ ተገትሮ ፡ ቆመ ፤ አሰበም ፤
በሄደበትም ፡ መንገድ ፡ ተመልሶ ፡ መጣ ። ነገር ፡ ግን ፡
የጣላቸውን ፡ የገንዘብ ፡ ወረቀቶች ፡ ሊያገኛቸው ፡ አልቻለም ።
አንድ ፡ ቁር ፡ ብሎ ፡ የለበሰ ፡ ወጣት ፡ ሽማግሌውን ፡ ሰውየ ፡
ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሮጦ ፡ እሠረገላ ፡ ላይ ፡ ወጣና ፡ ነጂውን ፡ በጩኸ
ት ፡ «ንዳ! ንዳ!» አለው ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ አባሮ ፡ ሊ
ይዘው ፡ አልሞከረም ። ወደገዛ ፡ ጣቢያው ፡ ለመሄድ ፡ ወሰነ ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ላንድ ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ምስኪን ፡ ልጁን ፡ ዱኛ
ን ፡ ለማየት ፡ ፈለገ ። ስለዚህ ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሚንስኪ
ይ ፡ ወደሚኖርበት ፡ ሰፈር ፡ እንደገና ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚ
ንስኪይ ፡ ወታደር ፡ አሽከር ፡ ጌታው ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ የማ
ይቀበል ፡ መሆኑን ፡ በቁርጥ ፡ ቃል ፡ ነገረውና ፡ ካዳራሹ ፡
ውስጥ ፡ ገፍቶ ፡ አስወጥቶ ፡ በሩን ፡ ወርውሮ ፡ ዘጋበት ። የማ
መላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ እውጭ ፡ ቆመና ፡
መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ሽማግሌው ፡ ሰውየ ፡ በሰማዕታት ፡
ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ጸሎት ፡ አድርሶ ፡ በሊቴይናያ ፡ መንገ
ድ ፡ ሲሄድ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ የተዋበ ፡ ሠረገላ ፡ ባጠገቡ ፡ አለፈ ፤
የማመላለሻ ፡ ሹሙም ፡ ባለሠረገላው ፡ ሚንስኪይ ፡ እንደሆ
ን ፡ አወቀ ። ሠረገላው ፡ እባለ ፡ ሶስት ፡ ፎቅ ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ለ
ፊት ፡ እበሩ ፡ አጠገብ ፡ ሲቆም ፡ የፈረሰኛው ፡ ክፍል ፡ ባልደ



ማሪያ ፡ ቮልኮንስካያ ( ፲፰፻፭ — ፲፰፻፷፫ ዓ. ም. ) ከነልጅዋ ። የመስፍን ፡ ሴር
ጌይ ፡ ቮልኮንስኪይ ፡ ባለቤት ። ባልዋ ፡ በታህሣሥ ፡ ፲፰፻፳፭ ዓ. ም. በቄሣሩ ፡
ተቃውሞ ፡ አድማ ፡ ስለተሳተፈ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ከተላከ ፡ በኋላ ፡ እሷም ፡ የመኳ

ንንትነት ፡ ማዕረግዋን ፡ በመጣል ፡ ባሌን ፡ አልተውም ፡ ብላ ፡ ባሏ ፡ ወደለበት ፡
ግዞት ፡ ሄደች ።



ኔቭስኪ ፡ ፕሮስፔክት ፡ የሚባለው ፡ የፒተርስበርግ ፡ ከተማ ፡ [illegible] ።



ዩሊዛቬታ ፡ ቮሮንጾቫ ( ፲፯፻፺፪ — ፲፰፻፹ ዓ. ም. ) ። ፑሽኪን ፡ በጣም ፡ ስለወ
ደዳት ፡ በ ፲፰፻፳ ዓ. ም. ብዙ ፡ የፍቅር ፡ ግጥሞች ፡ ጻፈላት ።

ረባ ፡ ዘሎ ፡ እበረንዳው ፡ ላይ ፡ ወረደ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ አደረበት ። ተመልሶ ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ቀረበና ፡ ነጂውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ፤ «ይህ ፡ የማን ፡ ሠረገላ ፡ ነው ፡ ወንድሜ? የሚንስኪይ ፡ ነው?» «አዎን ፡ ነው ፡» አለ ፡ ሠረገላ ፡ ነጂው ። «ምን ፡ አስጠየቅዎ?» «ምክንያቱን ፡ እነግርሃለሁ ። ጌታህ ፡ ለዱኛ ፡ መልዕክት ፡ እንዳደርስ ፡ ጽፎ ፡ ሰጥቶኝ ፡ ነበር ፤ ዱኛ ፡ የምትኖርበትን ፡ ቦታ ፡ ግን ፡ ዘነጋሁት ።» «እሷማ ፡ የምትኖረው ፡ እዚህ ፡ እፎቁ ፡ ላይ ፡ ነው ። ግን ፡ መልዕክቱን ፡ አዘግይተውታል ፡ ወዳጄ ። ጌታዬ ፡ እራሳቸው ፡ አሁን ፡ ከርሷ ፡ ጋር ፡ ናቸው ።» «ቢሆንም ፡ ግድ ፡ የለም ፡» አለ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ልቡ ፡ ድንገት ፡ ትር ፡ ትር ፡ እያለ ። «ቦታውን ፡ ስላሳየኸኝ ፡ አመሰግንሃለሁ ፤ ግን ፡ ቃሌን ፡ ማክበር ፡ አለብኝ ፡» ይህንን ፡ ተናግሮ ፡ ደረጃውን ፡ መውጣት ፡ ጀመረ ።

በሩ ፡ ተቆልፎ ፡ ነበር ። ደወሉን ፡ ደወለ ፤ ለጥቂት ፡ ሴኮንዶች ፡ ያህልም ፡ ጭንቅ ፡ ያዘው ። ቁልፉ ፡ ተንኳኳና ፡ በሩ ፡ ተከፈተ ። «አቭዶትያ ፡ ሳምሶኖቭና ፡ እዚህ ፡ ትኖራለችን? » ብሎ ፡ ጠየቀ ። «አዎን ፡ እዚህ ፡ ነው ፡ የምትኖረው ፡» ስትል ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ገረድ ፡ መለሰችለትና ፡ «ለምን ፡ ይፈልጓታል?» አለችው ። መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ እዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። «ክልክል ፡ ነው ፡ አይግቡ ። አቭዶትያ ፡ ሳምሶኖቭና ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ናት ፡ » ስትል ፡ ገረድየዋ ፡ እንዲመለስ ፡ ጠራችው ። የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ገባ ። መጀመሪያ ፡ ያለፋቸው ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ጨለማ ፡ ነበሩ ፤ በሶስተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ብርሃን ፡ ነበር ። ወደተከፈተው ፡ በር ፡ ጋ ፡ ሄዶ ፡ ቆመ ። እጅግ ፡ በተሽቆጠቆጠው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሚንስኪይ ፡ በሐሳብ ፡ ተውጦ ፡ ተቀምጧል ። ዱኛም ፡ እጅግ ፡ የተዋበ ፡ ዘመናዊ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ በጐን ፡ ተቀምጠው ፡ ፈረስ ፡ እንደሚጋልቡ ፡

የእንግሊዝ ፡ ሴቶች ፡ በወንበሩ ፡ የእጅ ፡ መደገፊያ ፡ ላይ ፡ ተቀ ምጣለች ። ሚንስኪይንም ፡ በፍቅር ፡ ዓይን ፡ እየተመለከተች ፡ የተጠቀለለ ፡ ጥቁር ፡ ጸጉሩን ፡ ባልማገዝ ፡ በተንቆጠቆጠው ፡ ጣቷ ፡ ትጠመዝዘዋለች ። ምስኪን ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም! ልጁ ን ፡ እንዲህም ፡ ተውባ ፡ አይቷት ፡ አያውቅ ፤ ሳይወድ ፡ በግድ ፡ በአድንቆት ፡ ዓይን ፡ ተመለከታት ። «ማነው?» ብላ ፡ እራ ሷን ፡ ቀና ፡ ሳታደርግ ፡ ተጣራች ። ሽማግሌው ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ። ዱኛም ፡ መልስ ፡ ስላላገኘች ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ ተመለከተ ች ፤ ... በድንጋጤ ፡ ጮኻም ፡ እሰጋጃው ፡ ላይ ፡ ወደቀች ። ሚንስኪይም ፡ ስለደነገጠ ፡ ከወደቀችበት ፡ ሊያነሳት ፡ አፈፍ ፡ ብሎ ፡ ተነሳ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሽማግሌውን ፡ የማመላለሻ ፡ ሹ ም ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ዱኛን ፡ ተወና ፡ ወደእ ርሱ ፡ ጋ ፡ በቁጣ ፡ እየነደደ ፡ ሄደ ። «ምን ፡ ትፈልጋለህ?» አለው ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ። «እንደ ፡ ሌባ ፡ የምታሳድደኝ ፡ ለምንድን ፡ ነው? ሕይወቴን ፡ ለማጥፋት ፡ ትፈልጋለህን? ሂድ ፡ ውጣ!» አለው ። የካፖርቱን ፡ ያንገት ፡ ክሳድ ፡ በጠን ካራ ፡ እጆቹ ፡ ይዞም ፡ ወደ ፡ ደረጃው ፡ ገፍትሮ ፡ አስወጣው ።

ሽማግሌው ፡ ሰውየ ፡ ወደ ፡ አረፈበት ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ሄደ ። የርሱ ፡ ወዳጅ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ያቤቱታ ፡ ደብዳቤ ፡ እንዲ ጽፍ ፡ መከረው ፤ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ግን ፡ ምክሩን ፡ ካሰበበት ፡ በኋላ ፡ እጁን ፡ አወዛውዞ ፡ ተወው ፤ ነገሩን ፡ እንዳለ ፡ ጨርሶ ፡ ለመተውም ፡ ወሰነ ። ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ ከፔቴርቡርግ ፡ ተነስቶ ፡ ወደ ፡ ማመላለሻ ፡ ጣቢያው ፡ ተመለሰና ፡ የጥንት ፡ ሥራውን ፡ ቀጠለ ። «እነሆ ፡ ከዱኛ ፡ ጋር ፡ ተለይቼ ፡ ስኖርና ፡ ከርሷም ፡ አንዳችም ፡ ቃል ፡ ሳልሰማ ፡ ሶስት ፡ ዓመት ፡ ሊሆ ን ፡ ነው ፡» አለ ፡ በንግግሩ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ። «በሕይወት ፡ ትኑር ፡ ወይስ ፡ ትሙት ፡ እግዜር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያውቀው ። በሰው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ። ወስላታ ፡ መን ገደኛ ፡ ጠልፎ ፡ ወስዶ ፡ ያስቀመጣትና ፡ የከዳት ፡ የመጀመሪ

ያዋ ፡ ልጃገረድ ፡ እርሷ ፡ አይደለችም ፤ የመጨረሻዋም ፡ ል ትሆን ፡ አትችልም ። በፔቴርቡርግ ፡ ከተማ ፡ እንደርሷ ፡ ያ ሉ ፡ ብዙ ፡ ተላላዎች ፡ አሉ ፤ መጀመሪያ ፡ ሐርና ፡ ከፈይ ፡ ለብ ሰው ፡ ይንቀባረሩና ፡ ኋላ ፡ ደግሞ ፡ የመንገድ ፡ ቆሻሻ ፡ ሲጠ ርጉ ፡ ይገኛሉ ። ዱኛም ፡ ምናልባት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስቃይ ፡ ደርሶባት ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳስብ ፡ ምነው ፡ ሞታ ፡ ተቀብራ ፡ ቢሆን ፡ የሚል ፡ የኃጢአት ፡ ምኞት ፡ መመኘ ቴ ፡ አልቀረም ፡ ... »

እነሆ ፡ ሽማግሌው ፡ ወዳጄ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ የተረ ከልኝ ፡ ታሪክ ፡ ይህ ፡ ነበር ፤ ሲተርክልኝም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እን ባ ፡ እያቋረጠውና ፡ ድሚትሪየቭ ፡ በጻፈው ፡ ግጥም ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገኘው ፡ እንደ ፡ ቴሬንቲች ፡[14] እንባውንም ፡ በካፖርቱ ፡ እጅጌ ፡ አበስ ፡ እያደረገ ፡ ነበር ። እንባውን ፡ ያስፈሰሰው ፡ አን ደኛው ፡ ምክንያት ፡ የጠጣው ፡ አምስት ፡ ብርጭቆ ፡ አረቂ ፡ ሳ ይሆን ፡ አይቀርም ፤ ሆኖም ፡ እጅግ ፡ አሳዘነኝ ፤ ልቤንም ፡ ነ ካው ። ከተሰናበትኩት ፡ በኋላ ፡ የዚህን ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ ሰውየ ፡ ነገር ፡ ለመርሳትና ፡ ስለምስኪኗ ፡ ስለዱኛ ፡ ማሰቤን ም ፡ ለማቆም ፡ ረጅም ፡ ጊዜ ፡ ወሰደብኝ ።

ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ በእንትና ፡ ... መንደር ፡ በኩል ፡ ሳ ልፍ ፡ ያን ፡ የጥንት ፡ ወዳጄን ፡ አስታወስኩት ። በርሱ ፡ አስተ ዳደር ፡ ስር ፡ የነበረው ፡ ጣቢያ ፡ ዛሬ ፡ አለመኖሩን ፡ ተረዳሁ ። « ያ ፡ የዱሮ ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ አሁንም ፡ አለን? » ብዬ ፡ ለማቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ የሚያጠግብ ፡ መልስ ፡ አጣሁ ። ያን ፡ የጥንቱን ፡ ቦታ ፡ ለመጎብኘት ፡ ስለፈለግሁ ፡ ፈረስ ፡ ተከራ የሁና ፡ ወደ ፡ እንትና ፡ ... መንደር ፡ ሄድሁ ።

ጊዜው ፡ መጸው ፡ ነበር ። ሰማዩም ፡ በግራጫ ፡ ደመና ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ። ከታጨደው ፡ የእህል ፡ ሜዳ ፡ የሚነፍሰው ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነፋስ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ከዛፎች ፡ ላይ ፡ ቀይና ፡ ቢጫ ፡ ቅጠሎች ፡ እያረገፈ ፡ ያልፋል ። ፀሐይ ፡ ከመጥለቋ ፡ በፊ

ት ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ ጋ ፡ ደረስኩ ፤ እማመላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ለፊትም ፡ ቆምኩ ። አንዲት ፡ ወፍራም ፡ ሴትዮ ፡ ወደ ፡ በረንዳው ፡ ወጣችና ፡ ( ምስኪኗ ፡ ዱኛ ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ እሳ መችኝ ፡ ቦታ ፡ ) ላቀረብኩት ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ስትሰጠኝ ፡ የማ መላለሻ ፡ ሹሙ ፡ ከሞተ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ እንደሆነውና ፡ ቤ ቱም ፡ አሁን ፡ ያንድ ፡ ጠላ ፡ ጠማቂ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ እንደሆነ ፡ እርሷም ፡ የሰውየው ፡ ሚስት ፡ እንደሆነች ፡ ገለጸችልኝ ። በከ ንቱ ፡ ያደረግሁት ፡ ጉዞና ፡ ያወጣሁት ፡ ሰባት ፡ ሩብል ፡ ቆጨ ኝ ። « ምን ፡ ሆኖ ፡ ሞተ? » ብየ ፡ ጠየቅኋት ፡ የጠላ ፡ ጠማቂ ውን ፡ ሚስት ። « ስካር ፡ ገደለው ፡ ጌታዬ ፡ » ስትል ፡ መለሰ ችልኝ ። « የት ፡ ተቀበረ? » — « ከመንደሩ ፡ ወዲያ ፡ ማዶ ፡ ከሚስቱ ፡ ጐን ። » « ወደ ፡ መቃብሩ ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መርቶ ፡ ሊወስደኝ ፡ ይችላልን? » — « እንዴታ ። ሰማህ ፡ ወ ይ ፡ ቫኝካ! ድመቷን ፡ ተዋት! እኚህን ፡ ሰውዬ ፡ ወደ ፡ መቃ ብሩ ፡ ቦታ ፡ ውሰዳቸውና ፡ የማመላለሻ ፡ ሹሙን ፡ መቃብር ፡ አሳያቸው ። »

የተቀደደ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፤ ጸጉረ ፡ ቀይና ፡ አንድ ፡ ዓይነ ፡ ተንኰልኛ ፡ ልጅ ፡ ሮጦ ፡ መጣና ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ ጫፍ ፡ መር ቶ ፡ ወሰደኝ ።

« የማመላለሻ ፡ ሹሙን ፡ ታውቀው ፡ ነበር? » ብየ ፡ ጠየቅ ሁት ።

« እንዴታ ፡ አውቀው ፡ ነበር ፡ እንጂ ። ፉጨት ፡ ያስተማ ረኝ ፡ እርሱ ፡ ነው ። ከመጠጥ ፡ ቤት ፡ ሲወጣ ፡ ( ነፍሱን ፡ ይማ ረውና! ) ከኋላ ፡ ከኋላው ፡ እየሮጥን ፡ አባባ! አባባ! ኖቾሊኒ ፡ ስጠ ን! እንለው ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ያለውን ፡ ኖቾሊኒ ፡ ሁሉ ፡ ይሰ ጠን ፡ ነበር ። ሁልጊዜም ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ይጫወት ፡ ነበር ። »

« መንገደኞች ፡ ስለርሱ ፡ ይጠይቃሉ? »

« ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እምብዛም ፡ መንገደኞች ፡ የሉ ። ዳኛም ፡ እንደሆን ፡ ለሞተ ፡ ሰው ፡ ቁብ ፡ የለውም ። ይልቁንስ ፡ በዚህ ፡

በጋ ፡ ወር ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ስለ ፡ ሽማግሌው ፡ የማመ ላለሻ ፡ ሹም ፡ ጠይቃ ፡ መቃብሩን ፡ ለማየት ፡ ሄደች ። »

« እንዴት ፡ ያለች ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ነበረች? » ብዬ ፡ በመ ጓጓት ፡ ጠየቅሁት ።

« የተዋበች ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ ነበረች ፡ » አለ ፡ ልጁ ። « የ መጣችው ፡ በስድስት ፡ ፈረስ ፡ በሚሳብ ፡ ሠረገላ ፡ ነበር ፤ ሶ ስት ፡ ልጆችና ፡ አንድ ፡ ሞግዚት ፤ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ጥቁር ፡ ው ሻም ፡ ነበራት ። ሽማግሌው ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ ሞትዋል ፡ ብለው ፡ በነገሯትም ፡ ጊዜ ፡ አለቀሰችና ፡ ልጆቿን ፡ እንዲህ ፡ አለቻቸው ፤ « እመቃብሩ ፡ ቦታ ፡ ደርሼ ፡ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ቁጭ ፡ ብላችሁ ፡ ጠብቁኝ ። » እኔም ፡ እመቃብሩ ፡ ቦታ ፡ ልው ሰድዎት ፡ ብየ ፡ ጠየቅኋት ። ሴት ፡ ወይዘሮዋ ፡ ግን ፤ « መንገ ዱን ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ አውቀዋለሁ ፡ » አለች ። የባለ ፡ አምስት ፡ ኮፔክ ፡ የብር ፡ መሐለቅም ፡ ሰጠችኝ ፤ እንዴት ፡ ያለች ፡ ደግ ፡ ሴትዮ ፡ ነበረች! »

እመቃብሩ ፡ ቦታ ፡ ደረስን ። ቦታው ፡ ገላጣና ፡ ያልታጠ ረ ፤ የንጨት ፡ መስቀሎች ፡ እዚህም ፡ እዚያም ፡ የተሰኩበት ና ፡ ከጸሐይ ፡ ጨረር ፡ ያልተጋረደ ፡ ነበር ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ የሚ ያሳዝን ፡ የመቃብር ፡ ቦታ ፡ በሕይወቴ ፡ ሙሉ ፡ አይቼም ፡ አላ ውቅ ።

« የሽማግሌው ፡ የማመላለሻ ፡ ሹም ፡ መቃብር ፡ እነሆ ፡ ይሄ ፡ ነው ፡ » አለ ፡ ትንሹ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ አሸዋ ፡ ክምር ፡ላ ይ ፡ ዘሎ ፡ ወጣና ። እመቃብሩም ፡ ላይ ፡ ከመዳብ ፡ የተሠራ ፡ የጻድቃን ፡ ሥዕል ፡ ያለበት ፡ ጥቁር ፡ መስቀል ፡ ተሰክቶበታል ።

« ሴት ፡ ወይዘሮዋ ፡ እዚህ ፡ ድረስ ፡ መጥታ ፡ ነበርን? » ብ የ ፡ ልጁን ፡ ጠየቅሁት ።

« አዎን ፡ » ሲል ፡ መለሰልኝ ፡ ቫኛ ። « ከሩቅ ፡ እመለከታ ት ፡ ነበር ። እዚህ ፡ ተደፍታ ፡ ብዙ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቆየች ። ከዚ ያ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ ሄደችና ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ ጠርታ ፡ ገን

ዘብ ፡ ሰጠችው ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ሄደች ፡ ለኔም ፡ የባለ ፡ አምስት ፡ ኰፔክ ፡ መሐለቅ ፡ ሰጠችኝ ። እንዴት ፡ ያለች ፡ ደግ ፡ ሴት ፡ ነበረች! »

እኔም ፡ እንደዚሁ ፡ ለትንሹ ፡ ልጅ ፡ የአምስት ፡ ኰፔክ ፡ መሐለቅ ፡ ሰጠሁት ። ባደረግሁት ፡ ጉዞና ፡ ባወጣሁትም ፡ ሰባት ፡ እሩብል ፡ አልተጸጸትኩም ።

# ባላገር ፡ መሳይ ፡ እመቤት ፡፡

ፍቅሬ ፡ ሆይ ! ማንኛውንም ፡
ዓይነት ፡ ቀሚስ ፡ ብትልብሺ ፡
ውብ ፡ ነሽ ።

ቦግዳኖቪች ።

የኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤሬስቶቭ ፡ እርስት ፡ የሚገኘው ፡ በጣም ፡ ርቀው ፡ ከሚገኙት ፡ አውራጃዎች ፡ ባንደኛው ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ በወጣትነቱ ፡ ዘመን ፡ በክብር ፡ ዘበኛ ፡ ውስጥ ፡ ከአገለገለ ፡ በኋላ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፰፻ ፺፯ ዓ ፡ ም ፡ ስንብት ፡ ተቀብሎ ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ ለመኖር ፡ ሄዶ ፤ ዳግመኛ ፡ ከመሬቱ ፡ ላይ ፡ እንዳይንቀሳቀስም ፡ ወሰነ ። አንድ ፡ ድኃ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ አግብቶ ፡ ሲኖር ፡ ለአደን ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ቦታ ፡ ሄዶ ፡ ሳለ ፡ በወሊድ ፡ ምክንያት ፡ ሞተችበት ። እርስቱን ፡ በማስተዳደርም ፡ ወዲያው ፡ ከሐዘኑ ፡ ለመጽናናት ፡ ቻለ ። የመኖሪያ ፡ ቤቱንም ፡ እርሱ ፡ እራሱ ፡ ባቀደው ፡ ፕላን ፡ መሠረት ፡ አሰራ ፤ የጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ፋብሪካም ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ አቋቋመ ፤ ገቢውንም ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፤ በወረዳው ፡ ከሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ብልህ ፡ ነኝ ፡ ብሎም ፡ እራሱን ፡ ገመተ ። ከቤተሰቦቻቸውና ፡ ከአዳኝ ፡ ውሾቻቸው ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ዘወትር ፡ ሊጠይቁት ፡ የሚመጡት ፡ ጐረቤቶቹም ፡ ብልህነቱን ፡ አመኑለት ። በአዘቦት ፡ ቀን ፡ ሐምራዊ ፡ ኰት ፡ ለብሶ ፡ ይታያል ፤ በበዓል ፡ ቀን ፡ ግን ፡ በእጅ ፡ ከተፈተለ ፡ ጨርቅ ፡ የተሠ

ራ ፡ ጥቁር ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል ። የሂሳብ ፡ መዝገቡን ፡ የሚይ
ዘውም ፡ እርሱ ፡ እራሱ ፡ ነው ፤ ከሕግ ፡ መወሰኛ ፡ መጽሔት ፡
በስተቀር ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አያነብም ። በጠቅላላው ፡ ም
ንም ፡ እንኳ ፡ ክፉ ፡ ቢሆንም ፡ ተወዳጅነትን ፡ አትርፎ ፡ ነበር ።
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የማይስማማው ፡ የቅርብ ፡ ጐረቤቱ ፡ ግሪጐሪ
ይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ሙሮምስኪይ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሰው ፡ በ
ጠባዩ ፡ የጥንት ፡ ሩሲያዊ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነው ። አብዛኛውን ፡
ሐብቱን ፡ በሞስኰ ፡ ከተማ ፡ ከአባከነ ፡ በኋላና ፡ ሚስቱም ፡
ከሞተችበት ፡ በኋላ ፡ ወደተረፈችው ፡ አንድ ፡ መንደር ፡ ሄዶ ፡
ተቀመጠ ። እዚያም ፡ ሐብቱን ፡ ማባከን ፡ ጀመረ ፤ በዚህ ፡ ጊ
ዜ ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ነበር ። በእንግሊዞች ፡ አቅድ ፡ የአ
ትክልት ፡ ቦታ ፡ በማሠራት ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ አወጣ ።
የፈረስ ፡ ጋጣ ፡ ጠባቂዎቹም ፡ ልብሳቸው ፡ እንደ ፡ እንግሊዝ ፡
የፈረስ ፡ ጠባቂዎች ፡ ልብስ ፡ ነበር ። ሴት ፡ ልጁም ፡ የእንግሊ
ዝ ፡ ሞግዚት ፡ ነበረቻት ። መሬቱን ፡ የሚያርሰውም ፡ እንደ ፡
እንግሊዞች ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዘዴ ፡
ለመስኰብ ፡ ማሽላ ፡ አይስማማውም ።[16]

ግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ወጭውን ፡ በብዙ ፡
ቢቀንስም ፡ ገቢው ፡ ከፍ ፡ ሊልለት ፡ አልቻለም ። በባላገር ፡ ው
ስጥ ፡ ሆኖ ፡ እንኳ ፡ ዕዳው ፡ እየበረከተበት ፡ ሄደ ። ይሄውም ፡
ሆኖ ፡ እርስቱን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አሲዞ ፡ ገንዘብ ፡ ለመበደር ፡
በማሰብ ፡ የመጀመሪያው ፡ ባለርስት ፡ በመሆኑ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡
ነው ፡ ተብሎ ፡ ተገመተ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ዘዴ ፡ በዚያን ፡ ዘመ
ን ፡ አስቸጋሪና ፡ የተወሳሰበ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመት ፡ ነበር ።
እርሱን ፡ ከሚነቅፉት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ ቤሬስቶ
ቭ ፡ ነበር ። ቤሬስቶቭ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚቃወምና ፡
የሚጠላ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ስለጐረቤቱ ፡ እንግሊዝ ፡ ልምስል ፡
ባይነት ፡ በጥላቻ ፡ ከመናገሩም ፡ ሌላ ፡ ዘወትር ፡ ነቀፌታ ፡

ለማግኘት ፡ እንደጣረ ፡ ነበር ። እርስቱን ፡ ለእንግዶች ፡ ባስጐበኘ ፡ ጊዜ ፡ ምስጋና ፡ ሲቀበል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በማሽሟጠጥ ፡ ይናገር ፡ ነበር ፤ « እያችሁ! እኛ ፡ እኮ ፡ ሥራችንን ፡ የምናካሄደው ፡ እንደ ፡ ጐረቤታችን ፡ እንደ ፡ ግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ አይደለም ። የእንግሊዞችን ፡ ዘዴ ፡ እንቀዳለን ፡ በማለት ፡ አንደክምም ። በኛው ፡ በሩሲያ ፡ ዘዴ ፡ ለሆዳችን ፡ ያህል ፡ ለማፍራት ፡ ከቻልን ፡ እግዜርን ፡ እናመሰግናቀለን! » ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ቃል ፡ በጐረቤቶቹ ፡ ብርታት ፡ ወደ ፡ ግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ጆሮ ፡ ለመድረስ ፡ ቻለ ። ይህ ፡ እንግሊዝ ፡ ልሁን ፡ ባይ ፡ ሰው ፡ እንደዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጋዜጠኞች ፡ ነቀፌታ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። በሰማው ፡ ነገር ፡ ስለተናደደ ፡ ጐረቤቱን ፡ ድብና ፡ ገልቱ ፡ ሲል ፡ ሰደበው ።

የቤሬስቶቭ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ ሊጠይቅ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ሁናቴ ፡ ይህ ፡ ነበር ። ልጁ ፡ በእንትና ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ትምህርቱን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ ለመግባት ፡ አሰበ ፤ አባቱ ፡ ግን ፡ ሳይፈቅድለት ፡ ቀረ ። ልጁ ፡ ለመንግሥት ፡ ሥራ ፡ በፍጹም ፡ ተስማሚ ፡ አለመሆኑ ፡ ተሰማው ። አባትየውም ፡ ልጁም ፡ በሐሳባቸው ፡ ስለጸኑ ፡ ለጊዜው ፡ ወጣቱ ፡ አሌክሴይ ፡ ለድንገትኛ ፡ ሁናቴ ፡ ዝግጁ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ አሪገዘ ፡ አበቀለና ፡[17] የጨዋ ፡ ሰው ፡ ኑሮ ፡ ጀመረ ።

አሉክሴይ ፡ በርግጥ ፡ መልካም ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ነበር ። በእውነቱ ፡ ሎጋ ፡ ሰውነቱ ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ ሳይለብስና ፡ እፈረስ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦም ፡ ሰይፍ ፡ መዘ ፡ እየጋለበ ፡ አንገት ፡በመቅላት ፡ ፈንታ ፤ የወጣትነቱን ፡ ጊዜ ፡ አጐንብሶ ፡ የመንግሥት ፡ መዝገብ ፡ በማገላበጥ ፡ ቢያባክነው ፡ እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ነው ። በአደን ፡ ጊዜ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ መሰናክልም ፡ ቢኖር ፡ ዘወትር ፡ እፊት ፡ ቀድሞ ፡ ሲጋልብ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ የቢሮ ፡ ሠራተኛ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፡ ሲሉ ፡ ጐረቤቶቹ ፡

በአንድነት ፡ ተስማሙ ። የመንደሩ ፡ ወጣት ፡ ሴቶችም ፡ ወደ ፡ አድንቆት ፡ በሚያደላ ፡ ዓይን ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ። አሌክሲ ይ ፡ ግን ፡ ልብ ፡ ብሎም ፡ አያያቸው ፡ ነበር ። እነርሱም ፡ የእር ሱን ፡ ቸልተኛነት ፡ ፍቅር ፡ ቢይዘው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ገመቱ ። ይህን ፡ ጥርጣሬ ፡ የሚያረጋግጥም ፡ ከእርሱ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ከአንደኛው ፡ ላይ ፡ የተቀዳ ፡ አድራሻ ፡ ያለበት ፡ ወረቀት ፡ ከ እጅ ፡ ወደ ፡ እጅ ፡ ይተላለፍ ፡ ነበር ። « አኩሊና ፡ ፔትሮቭና ፡ ኩሮችኪና ፤ ሞስኮ ፡ ባለው ፡ ብረት ፡ ሥሪ ፡ በሳቬሌቭ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ ለ እ.እን.ፒ ፡ እንዲያደርሱ ፡ ይለመናሉ ። »

ከአንባቢዎቼ ፡ መካከል ፡ በባላገር ፡ ውስጥ ፡ ያልኖሩ ፡ ሰ ዎች ፡ እንዳሉ ፡ የባላገር ፡ ወጣት ፡ ሴቶች ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ አስ ደሳች ፡ እንደሆኑ ፡ ሊገነዘቡ ፡ አይችሉም ። አስተዳደጋቸው ፡ በንጹህ ፡ አየር ፡ ውስጥና ፡ በፖም ፡ ጥላ ፡ ስር ፡ ሲሆን ፡ ስለሕ ይወትና ፡ ስለማህበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕውቀት ፡ ለማግኘት ፡ የሚች ሉትም ፡ መጽሐፍ ፡ በማንበብ ፡ ነው ። ፀጥታ ፤ ነፃነትና ፡ መጽሐ ፍ ፡ ማንበብ ፤ በከተማ ፡ የሚገኙት ፡ የተበላሹ ፡ ወይዛዝርት ፡ ከቶ ፡ የማያገኙትን ፡ ጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ገና ፡ በልጅነታቸው ፡ ያ ሳድርባቸዋል ። ለነዚህ ፡ የባላገር ፡ ወይዛዝርት ፡ ደወል ፡ ሲደ ወል ፡ መስማት ፡ እንኳ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፤ ወደ ፡ አቅራ ቢያው ፡ ከተማ ፡ ደርሶ ፡ መመለስም ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ቦታ ፡ የሚጐበኙ ፡ ሰዎችም ፡ በልጃገረዶቹ ፡ ላይ ፡ ለዘላለሙ ፡ የማይረሳ ፡ ትዝታ ፡ ይተዋሉ ። እርግጥ ፡ ነው ፡ እነ ዚህ ፡ ወጣት ፡ ወይዛዝርት ፡ አንዳንድ ፡ የሚያስቅ ፡ ጠባይ ፡ ይ ታይባቸዋል ። ሆኖም ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ የሚመለከት ፡ ሰው ፡ የሚያ ቀርበው ፡ አስቂኝ ፡ አስተያየት ፡ መልካም ፡ ጠባያቸውን ፡ ሊ ደመስሰው ፡ አይችልም ። ከዚህም ፡ ጠባያቸው ፡ ውስጥ ፡ ዋና ው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ የተለየ ፡ የግል ፡ ባህርይ ፡ ማሳየት ፡ ነው ። ዣን ፡ ፖል ፡ ሪኽተር ፡[18] እንደሚለው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የተለየ ፡ የግል ፡ ጠባይ ፡ ከሌለው ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይችልም ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ በታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩ ፡ ቤቶች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ትምህርት ፡ ለማግኘት ፡ ይችሉ ፡ ይሆናል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የማህበራዊ ፡ ኑሮው ፡ አካባቢ ፡ ወዲያውኑ ፡ የግል ፡ ጠባያቸውን ፡ በመደምሰስ ፡ አዕምሯቸውንም ፡ እንደ ፡ ባርኔጣቸው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ያደርገዋል ። ይህን ፡ ያልንበት ፡ ምክንያት ፡ ለመፍረድ ፡ ወይም ፡ ለመንቀፍ ፡ ሳይሆን ፡ አንድ ፡ የዱሮ ፡ ጸሐፊ ፡ እንደገለጸው ፡ ያየነውን ፡ ለመናገር ፡ ስንል ፡ ነው ።

አሌክሴይ ፡ በወጣቶቹ ፡ ወይዛዝርት ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ እንዳሳደረባቸው ፡ ለመገንዘብ ፡ ቀላል ፡ ነው ። እንደ ርሱ ፡ ያለ ፡ የከፋውና ፡ ሐሳቡ ፡ ያልተጣራ ፡ ሰው ፡ ሲገጥማቸው ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ስላሳለፈው ፡ የደስታ ፡ ጊዜና ፡ ስለወጣትነቱ ፡ ዘመን ፡ ከንቱነት ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ያወራላቸውም ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ የጻረ ፡ ሞት ፡ እራስ ፡ የተቀረጸበት ፡ ጥቁር ፡ ቀለበት ፡ አድርጓል ። ልጃገረዶቹ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ተደንቀው ፡ ነበር ።

ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ የእንግሊዝ ፡ ልምስል ፡ ባዩ ፡ ልጅ ፡ ሊዛ ፡ ( ወይም ፡ ቤትሲ ፤ አባቷ ፡ እንደሚጠራት ፡ ) ስለ ዚህ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ አጥብቃ ፡ ታስብ ፡ ነበር ። የሁለቱም ፡ ልጆች ፡ አባቶች ፡ ስለማይጠያየቁ ፡ አሌክሴይን ፡ ገና ፡ አላየችውም ፡ ነበር ። የገጠሬቤቱ ፡ ወጣት ፡ ወይዛዝርት ፡ ግን ፡ ያለእርሱ ፡ በስተቀር ፡ ስለሌላ ፡ ነገር ፡ አያወሩም ፡ ነበር ። ሊዛ ፡ አስራ ፡ ሰባት ፡ አመቷ ፡ ነበር ። የተዋበውና ፡ ዳማ ፡ መልኳ ፡ በሁለት ፡ ጥቋቁር ፡ ዓይኖች ፡ ያበራ ፡ ነበር ። ለአባቷ ፡ አንድ ፡ በመሆንዋ ፡ ተበላሽታና ፡ ተቀማጥላ ፡ ነበር ። ደስተኛነቷና ፡ ጨዋታዋ ፡ አባትዮውን ፡ ያስደስተው ፡ ነበር ። ሞግዚቷን ፡ ሚስ ፡ ጀክሰንን ፡ ግን ፡ ያበሳጫት ፡ ነበር ። ሚስ ፡ ጀክሰን ፡ ድርቅ ፡ ያለችና ፡ ባል ፡ ያላገባች ፡ የአርባ ፡ አመት ፡ ሴት ፡ ስትሆን ፡ ጉንጭዋን ፡ ቀለም ፡ ትቀባለች ፤ ሽፋኗንም ፡ ኩል ፡ ትኳላለች ፤ በስድስት ፡ በስድስት ፡ ወርም ፡ « ፓሜላ ፡ » የተባለውን ፡ መጽ

ሐፍ ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ታንባለች ።[19] ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራዋም ፡ በዓመት ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ሩብል ፡ ትቀበላለች ። የሩሲያን ፡ የሕዝብ ፡ አገርም ፡ በጣም ፡ ይሰለቻት ፡ ነበር ።

ሊዛ ፡ ናስቲያ ፡ የምትባል ፡ ከእርሷ ፡ በዕድሜ ፡ ትንሽ ፡ የምትበልጥ ፡ ገረድ ፡ አለቻት ፤ ሆኖም ፡ እንደ ፡ እመቤቷም ፡ ቀበጥ ፡ ናት ። ሊዛ ፡ ገረዷን ፡ ትወዳታለች ፤ ምሥጢሯንም ፡ ሁሉ ፡ ታካፍላታለች ፤ የቅብጠቷ ፡ አባሪ ፡ እንድትሆንም ፡ ጠየቀቻት ። ባጭሩ ፡ ናስቲያ ፡ በግብረ ፡ አበርነቷ ፡ በፕሪሉቺኖ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ በፈረንሳይ ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙ ፡ ግብረ ፡ አባሮች ፡ የበለጠች ፡ ሆና ፡ ተገኘች ።

ናስቲያ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ እመቤቷን ፡ ስታለብስ ፤ « ዛሬ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እንድወጣ ፡ ይፈቀድልኛል? » ስትል ፡ ጠየቀች ።

« እንዴታ! ለነገሩ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሄጂው? »

« ወደ ፡ ቱጊሎቮ ፡ ወደ ፡ ቤሬስቶቭ ፡ ቤት ፡ ነው ። ዛሬ ፡ የወጥቤታቸው ፡ ሚስት ፡ የክርስትና ፡ ቀን ፡ ስለሆን ፡ ትላንትና ፡ መጥታ ፡ ምሳ ፡ ጋብዛን ፡ ነበር ። »

« ዕውነትሽን ፡ ነው! » አለች ፡ ሊዛ ። « ጌቶቻቸው ፡ ተጣልተዋል ፤ አገልጋዮቻቸው ፡ ግን ፡ ይገባበዛሉ! »

« የጌቶቻችን ፡ መጣላት ፡ የእኛ ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም ፡ » ስትል ፡ መለሰች ፡ ናስቲያ ። ቀጥላም ፤ «ከዚህም ፡ በተረፈ ፡ እኔ ፡ የርስዎ ፡ ገረድ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ የአባትዎ ፡ ገረድ ፡ አይደለሁም ። እርስዎና ፡ ወጣቱ ፡ ቤሬስቶቭ ፡ ገና ፡ እንዳልተጣላችሁ ፡ ያውቃሉ ፤ ስለዚህ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ እንደአሻቸው ፡ ይጣሉ! » አለች ።

« ናስቲያ ፤ አሌክሴይ ፡ ቤሬስቶቭን ፡ ልብ ፡ ብለሽ ፡ ተመልከችና ፡ ምን ፡ እንደሚመስልና ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰውስ ፡ እንደሆነ ፡ ንገሪኝ ። »

ናስቲያ ፡ ቃል ፡ ገባችላት ፤ ሊዛም ፡ ገረዷ ፡ ተመልሳ ፡ እ

ስከትመጣ ፡ ድረስ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ኃጉታ ፡ ስትጠብቅ ፡ ዋለ ች ። ናስቲያ ፡ ወደማታ ፡ ጊዜ ፡ ተመልሳ ፡ መጣች ።

« ይሄውልዎት ፡ ሊዛቬታ ፡ ግሪጎሪየቭና ፡ » አለች ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ እንደገባች ፤ « ወጣቱን ፡ ቤሬስቶቭን ፡ አየሁት ፤ ደህና ፡ አድርጌም ፡ ተመለከትኩት ፤ ቀኑን ፡ ሙሉ ም ፡ በአንድነት ፡ ነበር ፡ የዋልነው ። »

« ምን? ንገሪኝ ፡ እስቲ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ከመጀመሪያው! »

« እንዴታ ፡ እነግርዎታለሁ ፡ እንጂ ። እኔ ፤ አኒስያ ፡ የጎሮ ቭና ፤ ኔኒላና ፡ ዱንያ ፡ ሁላችንም ፡ እዚያው ፡ ነበርን ፡ ... »

« እሱን ፡ ተይው! ከዚያስ ፡ በኋላ? »

« ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ከመጀመሪያው ፡ ልንገርዎት ፡ እንጂ ። ይሄውልዎት ፡ ልክ ፡ በምሳ ፡ ሰዓት ፡ ደረስን ። ክፍሉን ፡ ሰው ፡ መልቶት ፡ ነበር ። የኮልቢንና ፡ የዛኻሪየቭ ፡ አገልጋዮችም ፡ እ ዚያው ፡ ነበሩ ፤ የወኪላቸውም ፡ ሚስትና ፡ ልጆች ፤ የህሉፒን ፡ አገልጋዮችም ፡ ... »

« እሱን ፡ ተይውና ፡ ስለ ፡ ቤሬስቶቭ ፡ ንገሪኝ! »

« ይቆዩ ፡ እኮ ። ይሄውልዎት ፡ ወደ ፡ ገበታ ፡ ቀረብን ፤ የወኪሉ ፡ ሚስት ፡ ከጋባዧ ፡ ጐን ፡ ተቀመጠች ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ቀጥዬ ፡ ... ሴት ፡ ልጆቿ ፡ አኰረፉ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ግድ ፡ የለኝም ፡ ነበር ። »

« እየ ፡ ናስቲያ! ዝብርዝብ ፡ ስታበገር ፡ ሰው ፡ ታሰለቺለሽ! »

« እርስዎ ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ ችኩል ፡ ነዎት! ከዚያ ፡ በኋ ላ ፡ ምሳ ፡ በልተን ፡ ተነሳን ፡ ... ምሳ ፡ ስንበላ ፡ ሶስት ፡ ሰዓት ፡ ቆየን ። ግሩም ፡ ነበር ፤ ሰማያዊ ፤ ቀይና ፤ ዥንጉርጉር ፡ ጣፋ ጭ ፡ ምግብ ፡ ነበር ፡ ... ይሄውልዎት ፡ ከበላን ፡ በኋላ ፡ ድብቆሽ ፡ ለመጫወት ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ሄድን ፤ ወጣቱ ፡ ጌታም ፡ አብሮ ፡ መጣ ። »

« ታዲያስ? እንደሚባለው ፡ እውነት ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ነው? »

« መልከ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ያውም ፡ እረ ፡ ቆንጆ ፡ ነው ፤ ሎጋና ፡ ጉንጬ ፡ ቀይ ፡ ነው ። »

« እውነትሺን ፡ ነው! መልኩ ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አስቤ ፡ ነበር ። ታዲያስ? ምን ፡ ይመስልሻል? ተካኝ፫ርና ፡ አሳቢ ፡ ነው? »

« እረ ፤ በፍጹም! እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ቀበጥ ፡ ሰውም ፡ በሕይወቴ ፡ አይቼ ፡ አላውቅም ። ከኛ ፡ ጋር ፡ ድብቆሽ ፡ አብሮ ፡ ተጫወተ ። »

« ከናንተ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ድብቆሽ ፡ ተጫወተ! ውሸትሺን ፡ ነው! »

« በደንብ ፡ ተጫወተ ፡ እንጂ! ያውም ፡ ደግሞ ፡ ከመካከላችን ፡ አንዱን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ ይስማት ፡ ነበር ። »

« ናስቲያ ፡ ውሸትሺን ፡ ነው! »

« እውነቴን ፡ ነው! እኔማ ፡ ላመልጠው ፡ አልቻልኩም ። ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ከኛው ፡ ጋር ፡ ዋለ ። »

« ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚለው ፡ ፍቅር ፡ ይዞታል ፤ ሌላ ፡ ሰውም ፡ አያይም ። »

« ሆኖም ፡ እኔንና ፡ የወኪሉን ፡ ልጅ ፡ ታንያን ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ አየን ። የኩልቢን ፡ ፓሻንም ፡ ተመልክቷታል ፤ ሳስበው ፡ የተመለከተው ፡ ሁላችንንም ፡ ነው ፤ ይህ ፡ መጥፎ! »

« ይገርማል! በቤት ፡ ውስጥስ ፡ ስለርሱ ፡ ምን ፡ ያወራሉ? »

« እንደሚሉት ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ደግ ፡ ነው ፤ ደስተኛው ፡ ነው ። ጉድለቱ ፡ ብቻ ፡ ልጃገረዶች ፡ ማሳደድ ፡ ይወዳል ። እኔ ፡ ለራሴ ፡ ይሄ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አልልም ፤ ያልፍለታል ። »

« ላየው ፡ እንዴት ፡ እፈቅዳለሁ! » ስትል ፡ ሊዛ ፡ በረዥሙ ፡ ተነፈሰች ።

« ቀላል ፡ ነው ፡ እኮ ። ቱጊሎቮ ፡ ከዚህ ፡ እሩቅ ፡ አይደለም ፤ ሶስት ፡ ቬርስታ ፡ ቢያስኬድ ፡ ነው ። በእግርዎ ፡ ሽርሽር ፡ እያሉ ፡ ቢሄዱ ፤ አለበለዚያም ፡ በፈረስ ፡ በርግጥ ፡ ያገኙታል ። ዘወትር ፡ ጧት ፡ ጠበንጃውን ፡ ይዞ ፡ ይወጣል ። »

« አየ ፤ ይሄንንስ ፡ አላደርገውም ። እኔ ፡ እሱን ፡ ፍለጋ ፡ የመጣሁ ፡ ይመስለዋል ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ አባቶቻችን ፡ ጠበኞች ፡ ስለሆኑ ፡ ልንተዋወቅ ፡ አንችልም ፡ ... ስሚኝ ፡ ናስቲያ! እንዲህስ ፡ ባደርግ! የባላገር ፡ ቀሚስ ፡ ለብሼ ፡ ባላገር ፡ ብመስልስ! »

« አዎን ፤ እንደሱ ፡ ያድርጉ! እቤት ፡ የተሠራ ፡ ቀሚስ ፡ ይልበሱና ፡ ወደ ፡ ቱጊሎቮ ፡ በድፍረት ፡ ይሂዱ ። እኔ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፤ ቤሬስቶቭ ፡ ሳያይዎት ፡ አይቀርም ። »

« እንደባላገሮችም ፡ ልነጋገር ፡ እችላለሁ ። ናስቲያዬ! ናስቲያዬ! እንዴት ፡ ያለ ፡ ግሩም ፡ ሐሳብ ፡ ነው! » ሊዛ ፡ ይህን ፡ የቅብጠት ፡ ሐሳቧን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ አድርጋ ፡ ወደ ፡ መኝታዋ ፡ ሄደች ። በማግሥቱ ፡ ሐሳቧን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ መዘጋጀት ፡ ጀመረች ። ሰማያዊ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ እቤት ፡ የተሠራ ፡ ጨርቅና ፡ የነሐስ ፡ ቁልፍ ፡ ከገበያ ፡ እንዲገዛ ፡ ሰው ፡ ላከች ። በናስቲያ ፡ እርዳታ ፡ ሸሚዝና ፡ ጉርድ ፡ ቀደደችና ፡ የቤቱ ፡ ገረዶች ፡ ሁሉ ፡ እንዲሠፉ ፡ አደረገች ፤ ማታውንም ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ አለቀ ። ሊዛ ፡ አዲሱን ፡ ልብሷን ፡ አጥልቃ ፡ በመስታዋት ፡ እራሷን ፡ ተመለከተች ፤ ካሁን ፡ በፊት ፡ እንዲህ ፡ ቆንጆ ፡ ሆና ፡ ባለማየቷ ፡ ለርሷ ፡ ለራሷ ፡ ደነቃት ። ልምምድ ፡ ለማድረግም ፡ ዝቅ ፡ ብላ ፡ እጅ ፡ እየነሳች ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ተመላለሰች ፤ ከሸክላ ፡ እንደተሠራ ፡ ድመትም ፡ እራሷን ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አወዛወዘች ፤ የአገሬው ፡ ሰው ፡ እንደሚናገረውም ፡ ተናገረች ፤ ስትስቅም ፡ አፏን ፡ በእጅጌዋ ፡ አፈነች ፤ ናስቲያም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ትርኢት ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ስትል ፡ በሙሉ ፡ አጸደቀችላት ። ችግር ፡ የተፈጠረው ፡ በባዶ ፡ እግሯ ፡ በጓሮ ፡ በኩል ፡ መዘዋወር ፡ ስትሞክር ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ሣርና ፡ ቁጥቋጦው ፡ ለስላሳ ፡ እግሯን ፡ ጐዳው ፤ አሸዋና ፡ ጠጠሩም ፡ ክፉኛ ፡ ይወጋት ፡ ጀመር ። እዚህም ፡ ላይ ፡ እንደዚሁ ፡ ናስቲያ ፡ ብልሃት ፡ ፈለገችላት ። የ

ሊዛን ፡ እግር ፡ ለካችና ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ እሮጣ ፡ ከብት ፡ እረኛውን ፡ ትሮፊምን ፡ ፈልጋ ፡ አንድ ፡ ጥንድ ፡ የገመድ ፡ ጫማ ፡ እንዲያመጣ ፡ ጠየቀችው ። በማግሥቱ ፡ ሊዛ ፡ ገና ፡ ከመንጋቱ ፡ በፊት ፡ የቤቱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደተኛ ፡ ተነሣች ። ናስቲያ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ በር ፡ ላይ ፡ ቆማ ፡ የከብት ፡ እረኛው ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ጠበቀች ። ጥሩንባ ፡ ሲነፋ ፡ የመንደሩ ፡ ከብቶች ፡ በባለርስቱ ፡ ቤት ፡ አልፈው ፡ ሄዱ ። ትሮፊም ፡ ሲያልፍ ፡ ለናስቲያ ፡ ትንሽና ፡ ብሩህ ፡ ቀለም ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ጥንድ ፡ ነጠላ ፡ የገመድ ፡ ጫማ ፡ ሰጣት ፤ እርሷም ፡ ሃምሳ ፡ ኰፔክ ፡ ከፈለችው ። ሊዛ ፡ በጸጥታ ፡ የባላገር ፡ ቀሚሷን ፡ አጠለቀችና ፡ ስለ ፡ ሚስ ፡ ጃክስን ፡ በሹክሹክታ ፡ አንድ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ነግራት ፡ በኋለኛው ፡ በረንዳ ፡ ወጥታ ፡ በአትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ እሮጣ ፡ አለፈችና ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ሄደች ።

ጐህ ፡ ሲቀድ ፡ የምሥራቅን ፡ ሰማይ ፡ አብርቶት ፡ ነበር ፤ ደመናዎቹም ፡ ወርቅ ፡ ለብሰው ፡ የተሰለፉ ፡ በመምሰል ፡ መኳንንት ፡ የንጉሥን ፡ መምጣት ፡ እንደሚጠብቁ ፡ እነሱም ፡ ጸሐይን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። የሰማዩ ፡ መጥራት ፤ የማለዳው ፡ ቀዝቃዛነት ፤ ጤዛው ፤ የነፋስ ፡ ሽውታውና ፡ የወፎቹ ፡ ዝማሬ ፡ የሊዛን ፡ ልብ ፡ በልጅነት ፡ ደስታ ፡ መሉት ። ምናልባት ፡ የሚያውቀኝ ፡ ሰው ፡ ይገጥመኛል ፡ ብላ ፡ በመፍራት ፡ የምትበር ፡ እንጂ ፡ የምትራመድ ፡ አትመስልም ፡ ነበር ። የአባቷን ፡ እርስት ፡ ወደሚከልለው ፡ ጫካ ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ዝግ ፡ አለች ። አሌክሲይን ፡ መጠበቅ ፡ ያለባት ፡ እዚሁ ፡ ነበር ። ልቧ ፡ በኃይል ፡ ይመታ ፡ ጀመር ፤ ምክንያቱ ፡ ግን ፡ አልገባትም ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ፍርሐት ፡ በወጣትነታችን ፡ ጊዜ ፡ ስንቀብጥ ፡ የሚሰማን ፡ የተዋበ ፡ ስሜት ፡ ነው ። ሊዛ ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ውጋጋን ፡ ገባች ። ከጫካው ፡ ጥልቀት ፡ እፍን ፡ ያለ ፡ ድምጽ ፡ በጆሮዋ ፡ ስለገባ ፡ የደስታ ፡ ስሜቷ ፡ ወዲያው ፡ ተለወጠ ። ቀስ ፡ በቀስ ፡ በደስታ ፡ የሐሳብ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ሰመጠች ። አሰበች ፡ … ዳ

ሩ፡ ግን ፡ የአሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጃገረድ ፡ በጸደይ ፡ ወራት ፡ ከጧቱ ፡ በአሥራ ፡ አንድና ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ መካከል ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ እንደምታስብ ፡ ማን ፡ ሊያውቅ ፡ ይችላል? በግራና ፡ በቀኝ ፡ ረግረጎም ፡ ዛፎች ፡ በአጠሉበት ፡ መንገድ ፡ በሐሳብ ፡ ተመስጣ ፡ ስትሄድ ፡ ድንገት ፡ አንድ ፡ አዳኝ ፡ ውሻ ፡ እየጮኸ ፡ ወደርሷ ፡ እሮጦ ፡ መጣ ። ሊዛም ፡ በፍርሐት ፡ ጮኸች ። ወዲያውኑ ፡ አንድ ፡ ድምጽ ፤ «Tout beau, Sbogar, ici…» ብሎ ፡ ተጣራ ። አንድ ፡ ወጣት ፡ አዳኝም ፡ ከቁጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ አለ ። « አትፍሪ ፡ ቆንጆዬ! ውሻዬ ፡ አይናከስም ፡ » አላት ፡ ሊዛን ። ሊዛም ፡ ወዲያውኑ ፡ ፍርሐቱ ፡ ስለለቀቃት ፡ ይህን ፡ አጋጣሚ ፡ ልትጠቀምበት ፡ ፈጠነች ። « ፈራሁ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ » አለች ፡ የፍርሐትና ፡ የሐፍረት ፡ መልክ ፡ ቀላቅላ ፡ በማሳየት ። « እዩት ፡ እስቲ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያስፈራ! እንደገና ፡ ዘሎ ፡ ይይዘኛል ። » አሌክሴይ ፡ ( ማን ፡ እንደሆን ፡ አንባቢያችን ፡ በመላ ፡ ሳይገነዘብ ፡ አልቀረም ፡ ) ወደ ፡ ባላገሯ ፡ ልጃገረድ ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ ። « ከፈራሽስ ፡ ከአንቺ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ እሄዳለሁ ። ትፈቅጅልኛለሽ ፡ ከአንቺ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እንድራመድ? » አላት ። « ማን ፡ ይከለክልሃል? ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ለመሄድ ፡ ነፃ ፡ ነው ፡ » ስትል ፡ መለሰችለት ፡ ሊዛ ። « ከወዴት ፡ ነው ፡ የመጣሽው? » « ከፕሪሉቺኖ ፡ ነው ። የብረት ፡ ሠሪው ፡ የቫሲሊይ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ። ወደዚህ ፡ የመጣሁትም ፡ እንጉዳይ ፡ ለመልቀም ፡ ነው ። ( ሊዛ ፡ አንድ ፡ የልጥ ፡ ቅርጫት ፡ በገመድ ፡ አንጠልጥላ ፡ ይዛ ፡ ነበር ። ) « አንተስ ፡ ከወዴት ፡ ነው ፡ የመጣኸው? ከቱጊሎቮ ፡ ነው ፡ የመጣኸው? » « እርግጥ ። የወጣቱ ፡ ጌታዬ ፡ ሎሌ ፡ ነኝ ፡ » ሲል ፡ መለሰ ፡ አሌክሴይ ። አሌክሴይ ፡ ደረጃውን ፡ ከእርሷ ፡ ደረጃ ፡ ጋር ፡ ለማስተካከል ፡ ፈለገ ። ሊዛ ፡ ግን ፡ ተመለከተችውና ፡ ሳቀች ። « የለም ፡ ሎሌ ፡ አይደለህም ፤ ልታታልለኝ ፡ አትችልም! ወጣቱ ፡ ጌታ ፡ አንተው ፡ እራስህ ፡

ነህ ፡ » አለችው ። « በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ጌታ ፡ የመሰል
ኩሽ? » « ሁለመናህ ፡ ያስታውቃል ። » « እስቲ ፡ እኮ ፡ ገል
ጠሽ ፡ ንገሪኝ! » « አሁን ፡ ጌታና ፡ ሎሌ ፡ ሳይለይ ፡ ቀረ
ና ፡ ነው! አለባበስህም ፡ አነጋገርህም ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ ውሻህን ፡
የምትጠራውም ፡ እኛ ፡ እንደምንጠራው ፡ አይደለም ። » የሊዛ ፡
ውበት ፡ አሌክሴይን ፡ እየማረከው ፡ ሄደ ። ለመንደሩ ፡ ልጃገረ
ዶች ፡ እምብዛም ፡ አክብሮት ፡ አያሳይም ፡ ነበርና ፡ እጁን ፡ ጣል ፡
አድርጎ ፡ ሊያቅፋት ፡ ሞከረ ። ሊዛ ፡ ወደኋላ ፡ እመር ፡ ብላ ፡ ፊ
ቷን ፡ ኰስተር ፡ ስላደረገች ፡ አሌክሴይ ፡ ነገሩ ፡ ስለገረመው ፡
ሁለተኛ ፡ ሊያቅፋት ፡ አልሞከረም ። « ወደፊት ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ለ
መወዳጀት ፡ ያማረህ ፡ እንደሆን ፡ ክብርህን ፡ መጠበቅ ፡ አለብ
ህ ፡ » አለችው ፡ ቁርጥ ፡ አድርጋ ። « እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ መ
ናገር ፡ ያስተማረሽ ፡ ማን ፡ ነው? » ሲል ፡ ጠየቃት ፡ አሌክሴይ ፡
ከልቡ ፡ እየሳቀ ። « የወጣት ፡ እመቤትሽ ፡ ደንገጡር ፡ የሆነች
ው ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ናስቴንካ ፡ ናት ፡ ያስተማረችኝ? ትምህርት ፡
በምን ፡ አኳኋን ፡ እንደሚሰራጭ ፡ አሁን ፡ ገና ፡ ገባኝ! » ሊዛ ፡
እንደባላገር ፡ መነጋገሯን ፡ እንደዘነጋችው ፡ ስለተሰማት ፡ ባ
ላገር ፡ ለመምሰል ፡ ተፋጠነች ። « ወደትልቁ ፡ ቤት ፡ የማልሄ
ድ ፡ ይመስልሃል ፡ እንዴ? እዚያ ፡ እኮ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አያለሁ ፤
እሰማለሁም! እዚህ ፡ ቆሜ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ መነጋገሬን ፡ የቀ
ጠልኩ ፡ እንደሆን ፡ ብዙ ፡ እንጉዳይ ፡ ልለቅም ፡ አልችልም ።
አንተም ፡ መንገድህን ፡ ይዘህ ፡ ሂድ ፡ ጌታዬ ፤ እኔም ፡ መንገዴ
ን ፡ ይዤ ፡ እሄዳለሁ ። ደህና ፡ ዋል ፡ ጌታዬ ፡ » ሊዛ ፡ ለመሄድ ፡
ቃጣች ። አሌክሴይ ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ አስቀራት ። « ስምሽ ፡
ማን ፡ ይባላል ፡ ውቢቱ? » « አኩሊና ፡ ነው ፡ » አለች ፡ ሊዛ ፡
ጣቶቿን ፡ ከአሌክሴይ ፡ እጅ ፡ ፈልቅቃ ፡ ለማውጣት ፡ እየሞ
ከረች ። « ልቀቀኝ ፡ ጌታዬ ፤ ወደቤቴ ፡ የመመለሻዬ ፡ ሰዓት ፡
ነው ። » « ወዳጄ ፡ አኩሊና ፡ ሆይ ፤ ብረት ፡ ሠሪውን ፡ አባት
ሺን ፡ ቫሲሊይን ፡ ሄጄ ፡ አየዋለሁ ። » « ምን? » ስትል ፡ ጮኸ

ች ፡ ሊዛ ። « ስለእግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እንዳታደርግ! ከአንድ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ብቻዬን ፡ እጫካ ፡ ውስጥ ፡ መነጋገሬን ፡ ቢሰሙ ፡ ይገድሉኛል ። አባቴ ፡ ብረት ፡ ሠሪው ፡ ቫሲሊይ ፡ ሙልጭ ፡ አድርጎ ፡ ይገርፈኛል ።» « እንደገና ፡ ላይሽ ፡ እፈልጋለሁ ፤ ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሻላል? » « እንደገና ፡ እንጉዳይ ፡ ለመልቀም ፡ መምጣቴ ፡ አይቀርም ።» « እኮ ፡ መቼ? » « እኔ ፡ እንጃ ። ምናልባት ፡ ነገ ፡ እመጣ ፡ ይሆናል! » « ውድ ፡ አኩሊና ፡ ሆይ! ፈርቼ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እስምሽ ፡ ነበር ። ቀኑን ፡ ነገ ፡ አድርጊው ። ታዲያ ፡ እንድትመጪ! » « እሺ ፡ እመጣለሁ ። » « ትቀሪና ፡ እቀየማለሁ ። » « ግድየለም ፡ አልቀርም ። » « እስቲ ፡ አልቀርም ፡ ብለሽ ፡ ማይልኝ! » « ማሪያምን ፡ እመጣለሁ ። »

ሁለቱ ፡ ወጣቶች ፡ ተለያዩ ። ሊዛ ፡ ከጫካው ፡ ውስጥ ፡ ወጣችና ፡ ሜዳውን ፡ አቋርጣ ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ሹልክ ፡ ብላ ፡ ገባች ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ እርሻው ፡ ማሳ ፡ አፈትልካ ፡ ሮጠች ፤ እዚያም ፡ ናስቲያ ፡ ትጠብቃት ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ቦታ ፡ ደንበኛ ፡ ልብሷን ፡ ለውጣ ፡ ለበሰችና ፡ የምሥጢር ፡ ተካፋይዋን ፡ የጉጉት ፡ ጥያቄ ፡ በምሥጢራዊ ፡ አኳኋን ፡ እየመለሰች ፡ በእንግዳ ፡ ቤቱ ፡ ለመገኘት ፡ ፈጥና ፡ ሄደች ። ገበታው ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ነበር ፤ ቁርስም ፡ ተሰናድቶ ፡ ነበር ፤ ሚስ ፡ ጃክሰንም ፡ እንዲህ ፡ በማለዳ ፡ ጉንጭዋን ፡ ቀለም ፡ ተቀብታና ፡ ሽንጧን ፡ አጠባብቃ ፡ ዳቦ ፡ በቀጭኑ ፡ ትሸነሽን ፡ ነበር ። የሊዛ ፡ አባት ፡ልጁ ፡ እንዲህ ፡ በማለዳ ፡ በመነሳቷ ፡ አመሰገናት ። « ጧት ፡ እንደመነሳት ፡ ያለ ፡ ለጤና ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ » አለ ፡ በአስተዋይነት ። ስለዕድሜ ፡ እርዝማኔ ፡ በእንግሊዝ ፡ መጽሔቶች ፡ ላይ ፡ የተጻፉ ፡ ብዙ ፡ ምሳሌዎች ፡ በመጥቀስም ፡ ከመቶ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ የኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቮድካ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይጠጡና ፡ በበጋም ፡ ሆነ ፡ በክረምት ፡ ማልደው ፡ የሚነሱ ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ገለጸ ። ሊዛ ፡ አባቷ ፡ የተናገረውን ፡ እምብዛም ፡

7•

አልሰማችም ፡ ነበር ። ስለ ፡ ጢቱ ፡ ቀጠሮዋና ፡ በአኩሊናና ፡ በ
ወጣቱ ፡ አዳኝ ፡ መካከል ፡ ስለተደረገው ፡ ጭውውት ፡ ሁሉ ፡ እ
ያስታወሰች ፡ ታስብ ፡ ነበር ፤ ሕሊናዋንም ፡ ይቆረቁራት ፡ ጀ
መር ። ጭውውታቸው ፡ ከጨዋነት ፡ ድንበር ፡ እንዳላለፈና ፡
ቅብጠቷም ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ እንደማያስከትል ፤ እራሷን ፡ በከ
ንቱ ፡ አጽናናች ። የሕሊናዋ ፡ ጥሪ ፡ ከአስተያየቷ ፡ ዘልቆ ፡ ተ
ሰማት ። ዋናው ፡ የሰጋችበት ፡ ምክንያት ፡ በማግሥቱ ፡ የ
ሰጠችው ፡ ቀጠሮ ፡ ነበር ፤ የሰጠችውንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለመ
ስበር ፡ ትንሽ ፡ ነበር ፡ የቀራት ። ነገር ፡ ግን ፡ አሌክሴይ ፡ እርሷ
ን ፡ ጠብቆ ፡ ያጣት ፡ እንደሆን ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ሄዶ ፡ የብረ
ት ፡ ሠሪውን ፡ ልጅ ፡ ዕውነተኛዋን ፡ አኩሊናን ፡ ሊፈልግ ፡ ሆ
ነ ። እሷም ፡ ብጉር ፡ ያለባት ፡ ዱባ ፡ ቢጤ ፡ ልጅ ፡ ናት ። ስለዚ
ህ ፡ አሌክሴይ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ምሥጢርዋን ፡ የሚያውቅባ
ት ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ሊዛ ፡ ፈራች ። በሚቀጥለው ፡ ቀ
ን ፡ አኩሊናን ፡ መስላ ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ለመሄድ ፡ ወሰነች ።

የአሌክሴይ ፡ ደስታ ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ ነበር ። ቀኑን ፡
ሙሉ ፡ አዲስ ፡ ስለተዋወቃት ፡ ልጅ ፡ ሲያስብ ፡ ዋለ ፤ ሌሊት ፡
በሕልሙም ፡ ያቺ ፡ የውጋጋን ፡ ቆንጆ ፡ ትታየው ፡ ነበር ። ከን
ጋት ፡ በፊት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተነስቶ ፡ ለባበሰ ። ጠበንጃውንም ፡
ሳይዝ ፡ ከታማኝ ፡ ውሻው ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ በፍጥነት ፡ ወደቀ
ጠሮው ፡ ቦታ ፡ ሄደ ። ተጨንቆ ፡ ሲጠብቅ ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ አለ
ፈ ። በመጨረሻ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀሚስ ፡ በቁጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ው
ልብ ፡ ሲል ፡ አየ ፤ ውዲቱን ፡ አኩሊናን ፡ ሊቀበላትም ፡ ሮጦ ፡
ሄደ ። እርሷም ፡ የደስታ ፡ ምሥጋናውን ፡ በፈገግታ ፡ ተቀበለ
ች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አሌክሴይ ፡ በልጂቱ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የሥጋት
ና ፡ የሙከፋት ፡ ምልክት ፡ ወዲያው ፡ አየ ። ምክንያቱንም ፡
ጠየቃት ። ሊዛም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የፈጸመችው ፡ ሥራ ፡
ተገቢ ፡ አለመሆኑንና ፡ በዚህም ፡ መጸጸቷን ፡ ገልጻ ፡ ከነገረ
ችው ፡ በኋላ ፡ ያሁኑን ፡ ቀጠሮዋን ፡ ማክበር ፡ ግድ ፡ ቢሆን

ባትም ፣ ቅሉ ፣ ይህ ፣ የመጨረሻ ፣ ቀጠሮአቸው ፣ እንደሚሆን ፣ ገለጸችለት ። ወዳጅነታቸውም ፣ የማያዛልቅ ፣ መሆኑን ፣ በማስረዳት ፣ እንዲያቋርጡ ፣ ለመነችው ። እርግጥ ፣ ነው ፣ ይህን ፣ ሁሉ ፣ የተናገረችው ፣ በባላገር ፣ አነጋገር ፣ ነው ። ሆኖም ፣ አሌክሴይ ፣ በአንድ ፣ ተራ ፣ ልጃገረድ ፣ ላይ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ያልተለመደ ፣ ስሜትና ፣ አስተያየት ፣ በማየቱ ፣ ተደነቀ ። በተቻለው ፣ እንደበቱ ፣ አኩሊና ፣ ሐሳቧን ፣ እንድትለውጥ ፣ ለማድረግ ፣ ሞከረ ። ለርሷ ፣ ያለው ፣ ስሜት ፣ ንጹህ ፣ መሆኑን ፣ አረጋገጠላት ፤ ለመጸጸት ፣ እንደማያበቃትና ፣ ፈቃድዋን ፣ ሁሉ ፣ የሚፈጽም ፣ መሆኑንም ፣ አረጋገጠላት ። አንድ ፣ ቀን ፣ አልፎ ፣ አንድ ፣ ቀን ፣ ወይም ፣ በሳምንት ፣ ሁለት ፣ ቀን ፣ እርሷን ፣ ብቻዋን ፣ የማግኘትን ፣ ደስታ ፣ እንዳትነፍገውም ፣ ለመናት ። አነጋገሩም ፣ ከስሜት ፣ ጋር ፣ ስለነበር ፣ በዚያኑ ፣ ሰዓት ፣ ከእርሷ ፣ ፍቅር ፣ እንደያዘው ፣ ተሰማው ። ሊዛም ፣ ጸጥ ፣ ብላ ፣ አዳመጠችውና ፣ ንግግሩን ፣ ሲጨርስ ፣ እንዲህ ፣ አለችው ፤ « እኔን ፣ በመንደር ፣ ውስጥ ፣ እንደማትፈልግና ፣ ስለእኔም ፣ እንደማትጠይቅ ፣ ቃል ፣ ግባልኝ ። እኔ ፣ እራሴ ፣ ከምወስነው ፣ ቀጠሮ ፣ በስተቀር ፣ ሌላ ፣ ግንኙነት ፣ ለማድረግ ፣ እንደማትፈልግም ፣ ቃል ፣ ግባልኝ ። »አሌክሴይም ፣ « በሶስቱ ፣ ሥላሴ ፣ » ቃል ፣ ኪዳን ፣ ሊገባ ፣ ሲል ፣ ሊዛ ፣ በፈገግታ ፣ አቆመችውና ፤ « መሐላ ፣ እንድታደርግ ፣ አልጠይቅህም ። ቃልህ ፣ ይበቃኛል ፣ » አለችው ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ በወዳጅነት ፣ እየተጫዋወቱ ፣ ጐን ፣ ለጐን ፣ ሆነው ፣ በጫካው ፣ ውስጥ ፣ ተንሸራሸሩና ፤ « እንግዲህ ፣ መሄድ ፣ አለብኝ ፣ » አለች ፣ ሊዛ ። ተለያዩ ፤ አሌክሴይም ፣ ብቻውን ፣ ከቀረ ፣ በኋላ ፣ አንዲት ፣ ተራ ፣ የመንደር ፣ ልጃገረድ ፣ በሁለት ፣ ጊዜ ፣ መተያየት ፣ ብቻ ፣ እንዲህ ፣ አድርጋ ፣ ልትማርከው ፣ የቻለችበት ፣ ምክንያት ፣ አልገባው ፣ አለ ። ከአኩሊና ፣ ጋር ፣ ያለው ፣ ግንኙነት ፣ ደስታ ፣ የተመላበት ፣ ሆኖ ፣ አገኘው ፤ ምንም ፣ እንኳ ፣

ከዚች ፡ እንግዳ ፡ ከሆነች ፡ የባላገር ፡ ልጃገረድ ፡ ጋር ፡ የገባው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ ቢያገኘውም ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ለ መጣስ ፡ በሐሳቡም ፡ አልገባ ። በዕውነቱ ፡ አሌክሴይ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አሰቃቂ ፡ ቀለበት ፡ ቢያደርግም ፤ በምሥጢር ፡ ቢጻጻ ፍም ፤ የከፋው ፡ ቢመስልም ፤ ልበ ፡ ደግና ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ወ ጣት ፡ ነው ፤ ልቡ ፡ ያልተበላሸ ፡ በመሆኑም ፡ ንጹህ ፡ ደስታ ፡ ለመቀበል ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ነው ።

እኔን ፡ እራሴን ፡ ብቻ ፡ ለማስደሰት ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የሁለ ቱን ፡ ወጣቶች ፡ በየጊዜው ፡ መገናኘትና ፡ እያደገ ፡ የሚሄደ ውን ፡ መዋደድ ፤ መተማመን ፤ ሥራቸውንና ፡ ጨዋታቸውን ፡ በዝርዝር ፡ እገልጽ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አብዛኞቹ ፡ አንባቢዎቼ ፡ ከዚህ ፡ የማገኘውን ፡ ደስታ ፡ እንደማይካፈሉ ፡ አውቃለሁ ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሐተታ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚሰለች ፡ ስለሆነም ፡ እሱን ፡ ዘልየ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ አሌክሴይ ፡ ከሊ ዛ ፡ ጋር ፡ የጋለና ፡ የጠበቀ ፡ ፍቅር ፡ ያዘው ፤ ሊዛም ፡ ብዙ ፡ ገ ልጻ ፡ ባትናገርም ፡ እንደዚሁ ፡ የጠበቀ ፡ ፍቅር ፡ ያዛት ፡ ብዬ ፡ ባጭሩ ፡ እጠቅሳለሁ ። ሁለቱም ፡ የወደፊቱን ፡ ጊዜ ፡ ችላ ፡ በማ ለት ፡ የዕለት ፡ ደስታቸውን ፡ ተካፈሉ ።

ለዘላለሙ ፡ ተሳስረው ፡ የመኖር ፡ ሐሳብ ፡ በአዕምሮአ ቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ፤ ሆኖም ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳ ይ ፡ ገልጸው ፡ አልተነጋገሩም ። ምክንያቱም ፡ ግልጽ ፡ ነበር ። ምንም ፡ እንኳ ፡ አሌክሴይ ፡ አኩሊናን ፡ ቢወዳትም ፡ በእርሱ ና ፡ በአንጻሩ ፡ ተራ ፡ የባላገር ፡ ልጃገረድ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ይገነዘብ ፡ ነበር ። ሊዛም ፡ በአባቶቻቸው ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ጠብ ፡ ታውቅ ፡ ስለነበር ፡ ይታረቁ ፡ ይሆናል ፡ ብላ ፡ ተስፋ ፡ ለማድረግ ፡ አልቻለችም ፡ ነበር ። ከዚህም ፡ በስተቀ ር ፡ የቱጊሎቮ ፡ ወራሽ ፡ በፐሪሉቺኖ ፡ የብረት ፡ ሠሪ ፡ ልጅ ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ በማየቷ ፡ ከንቱነቷ ፡ በምሥጢራዊ ፡ የ ፍቅር ፡ ተስፋ ፡ ተነካ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያ

ለውን ፡ ግንኙነት ፡ ሊሰውጥ ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ተፈ
ጠረ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ብርዳም ፡ በሆነ ፡ ጧት ፡ ( በሩ
ሲያ ፡ የመጸው ፡ ወር ፡ ከተለመዱት ፡ ቀኖች ፡ ) ኢቫን ፡ ፔትሮ
ቪች ፡ ቤሬስቶቭ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣ ። ም
ናልባት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ቢያጋጥመኝ ፡ በማለትም ፡ አምስት ፡
ወይም ፡ ስድስት ፡ ኢዳኝ ፡ ውሻ ፤ አንድ ፡ አሽከርና ፡ አውሬ ፡
ቀስቃሽ ፡ ጥቂት ፡ የገባሮች ፡ ልጆች ፡ ይዞ ፡ ወጣ ። በዚሁ ፡ ጊ
ዜ ፡ ግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ሙሮምስኪይም ፡ ቀኑ ፡ ደስ ፡
ስላሰኘውና ፡ ስላጓጓው ፡ ሴት ፡ ፈረሱን ፡ አስጭኖ ፡ በእንግሊዝ ፡
ጠቀስ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ደንገላሳ ፡ ይመታ ፡ ጀመር ። ወደ ፡
ጫካው ፡ ሲጋልብ ፡ ጐረቤቱ ፡ የቀበሮ ፡ ጸጉር ፡ ክፈፍ ፡ ያለው ፡
ኰት ፡ ለብሶና ፡ በኩራት ፡ እኰርቻው ፡ ላይ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ተ
ቀምጦ ፡ አሽከሮቹ ፡ ከቁጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ በጩኸትና ፡ የቆ
ርቆሮ ፡ ድምጽ ፡ በማሰማት ፡ አባርረው ፡ የሚያስወጧቸውን ፡
ጥንቸሎች ፡ ሲጠብቅ ፡ አየው ። እንዲህ ፡ የሚገናኙ ፡ መሆናቸ
ውን ፡ ግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ቀድሞ ፡ ቢያውቅ ፡ ኖሮ ፡ ወ
ደሌላ ፡ አቅጣጫ ፡ ባመራ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከቤሬስቶቭ ፡
ጋር ፡ የተገናኘው ፡ በድንገት ፡ ነበር ፤ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለ
ው ፡ እርቀትም ፡ አጭር ፡ ነበር ። ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አልቻለ
ም ። ሙሮምስኪይ ፡ ከእግር ፡ እስከ ፡ እራሱ ፡ ኤውሮፓዊ ፡
ቢጤ ፡ ስለነበር ፡ ወደ ፡ ጠላቱ ፡ ጋልቦ ፡ ሄዶ ፡ በትህትና ፡ ሰላ
ምታ ፡ ሰጠው ። ቤሬስቶቭም ፡ በሰንሰለት ፡ የታሰረ ፡ ድብ ፡
ጌታው ፡ ለጨዋ ፡ ሰው ፡ ሰላምታ ፡ ስጥ ፡ ሲለው ፡ ሰላምታ ፡
እንደሚሰጥ ፡ ሁሉ ፡ አጸፋውን ፡ በትህትና ፡ መለሰ ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ጥንቸሏ ፡ ከጫካው ፡ ውስጥ ፡ ዘለለችና ፡ ወደ ፡ ሜዳው ፡
ሮጠች ። ቤሬስቶቭና ፡ አሽከሮቹ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ጮኹ ።
ውሾቹን ፡ ለቀቋቸውና ፡ ጥንቸሏን ፡ ለማባረር ፡ በኃይል ፡ ጋለ
ቡ ። የሙሮምስኪይ ፡ ፈረስ ፡ አደን ፡ ያልለመደች ፡ በመሆንዋ ፡

ደንግጣ ፡ በረገገች ። ሙሮምስኪይም ፡ ጥሩ ፡ ፈረሰኛ ፡ ነኝ ፡ ባ ይ ፡ ስለሆነና ፡ ከሰውየውም ፡ ጋር ፡ ለመለያየት ፡ መልካም ፡ አ ጋጣሚ ፡ ስላገኘ ፡ ልጓም ፡ ለቆ ፡ ጋለበ ። ነገር ፡ ግን ፡ ፈረሷ ፡ በኃይል ፡ ስትጋልብ ፡ ቆይታ ፡ ወደአላየችው ፡ ጉርጓድ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ስለደረሰች ፡ በድንገት ፡ ቀጥ ፡ አለች ። ሙሮምስኪይም ፡ ከኰርቻው ፡ ላይ ፡ ተፈንጥሮ ፡ ክፉኛ ፡ ወደቀ ። ውርጭ ፡ ባደረ ቀው ፡ መሬት ፡ ተዘርሮ ፡ ባለቆራጣ ፡ ጅራት ፡ ፈረሱን ፡ ሲሰ ድብ ፡ ሳለ ፡ እሷም ፡ ጋላቢ ፡ እጀርባዋ ፡ ላይ ፡ እንደሌለ ፡ በተ ረዳች ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ቀጥ ፡ ብላ ፡ ቆመች ። ኢቫን ፡ ፔትሮ ቪችም ፡ ወደ ፡ ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ዘንድ ፡ ጋልቦ ፡ ሄዶ ፡ ተጐድቶ ፡ እንደሆን ፡ ጠየቀው ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ የሙሮም ስኪይ ፡ አሽከር ፡ አመጸኛዋን ፡ ፈረስ ፡ አምጥቶ ፡ ልጓሟን ፡ ይዞ ፡ ቆመ ። ሙሮምስኪይን ፡ ደግፎ ፡ ካወጣው ፡ በኋላም ፡ ቤ ሬስቶቭ ፡ ሙሮምስኪይን ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ጋበዘው ። ሙሮምስ ኪይም ፡ ግብዣውን ፡ መቀበል ፡ ግድ ፡ ሆነበት ፤ ስለዚህ ፡ ቤሬ ስቶቭ ፡ በአንድ ፡ ፊት ፡ ጥንቸሏን ፡ ገድሎ ፡ በአንድ ፡ ፊት ፡ ደ ግሞ ፡ የቆሰለውንና ፡ የጦር ፡ እስረኛ ፡ የመሰለውን ፡ ጠላቱን ፡ ይዞ ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ።

ሁለቱ ፡ ጐረቤቶች ፡ ቁርስ ፡ ሲበሉ ፡ ሳለ ፡ በሙሉ ፡ ወዳ ጅነት ፡ ተጨዋወቱ ። ሙሮምስኪይ ፡ ከፈረስ ፡ በመውደቁ ፡ ም ክንያት ፡ በደረሰበት ፡ ጉዳት ፡ ፈረስ ፡ ለመቀመጥ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ገልጾ ፡ በመናገር ፡ ቤሬስቶቭ ፡ ሠረገላ ፡ ያስጭንለት ፡ ዘንድ ፡ ጠየቀ ። ቤሬስቶቭ ፡ እበር ፡ ድረስ ፡ ሙሮምስኪይን ፡ ሸኘው ። ሙሮምስኪይም ፡ ቤሬስቶቭ ፡ በማግሥቱ ፡ አሌክሴ ይን ፡ ይዞት ፡ እንዲመጣ ፡ ቃል ፡ ከገባለት ፡ በኋላ ፡ ሄደ ። በዚ ህ ፡ አኳኋን ፡ ስር ፡ ሰዶ ፡ የነበረው ፡ የጥንት ፡ ጠላትነታቸው ፡ በአንድ ፡ ጅራተ ፡ ቆራጣ ፡ ፈረስ ፡ አፋራምነት ፡ የሚደመሰስ ፡ መስሎ ፡ ታየ ።

ሊዛ ፡ ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪችን ፡ ለመቀበል ፡ ሮጣ ፡ መጣ

ችና ፤ « ምን ፡ ሆንክ ፡ አባብዬ? » ስትል ፡ ጮኻ ፡ በመደንቅ ፡ ጠየቀችው ። ቀጥላም ፤ « ምነው ፡ ታነክሳለህ? ፈረስህስ ፡ የ ት ፡ ናት? ይህስ ፡ የማነው ፡ ሠረገላ? » ብላ ፡ ጠየቀች ። « የማን ፡ እንደሆን ፡ ከቶ ፡ መላ ፡ ለመምታት ፡ አትችዪም ፡ my dear ፡ » ሲል ፡ መለሰ ፡ ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ የእንግሊዝ ፡ ዓይነት ፡ አመላለስ ፡ ይወድ ፡ ስለነበር ። ታሪኩንም ፡ በዝርዝር ፡ ነገራት ። ሊዛ ፡ የሰማችውን ፡ ለማመን ፡ አልቻለችም ። ገና ፡ መደነቋ ን ፡ ሳትጨርስ ፡ ቤሬስቶቭ ፡ ከልጁ ፡ ጋር ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ መጥቶ ፡ ምሳ ፡ የሚበላ ፡ መሆኑን ፡ ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ነ ገራት ። « ምን! » አለች ፡ በመደነቅና ፡ ፊቷ ፡ ነጭ ፡ እየሆነ ። « ቤሬስቶቭና ፡ ልጁ? ከኛ ፡ ጋር ፡ ነገ ፡ ምሳ ፡ ሊበሉ! አባባ ፤ አንተ ፡ የፈለግህን ፡ ማድረግ ፡ ትችላለህ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ አልገኝም ። » « አብደሻል ፡ እንዴ? » አለ ፡ አባትየው ። « ም ንድን ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ በድንገት ፡ አፋራም ፡ የሚያደርግሽ? ወይስ ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ እመቤት ፡ የደም ፡ ጥላ ቻ ፡ ይሰማሻል ፡ ልበል? እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ ዳግመኛ ፡ ልሰማ ፡ አልፈልግም ። » « የለም ፡ አባብዬ ፤ መሬት ፡ ከፍ ፡ ሰማይ ፡ ዝቅ ፡ ቢል ፡ ከነቤሬስቶቭ ፡ ፊት ፡ አልቀርብ ም ። » ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪችም ፡ እርሷን ፡ መቃወም ፡ ከን ቱ ፡ መሆኑን ፡ ደህና ፡ አድርጎ ፡ ስለሚያውቅ ፡ ትከሻውን ፡ ነቅነቅ ፡ አድርጎ ፡ ክርክሩን ፡ አቆመና ፡ ከማይረሳው ፡ የፈረስ ፡ ግልቢያው ፡ በኋላ ፡ እረፍት ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገባ ።

ሊዛቬታ ፡ ግሪጎርየቭና ፡ ወደ ፡ ክፍሏ ፡ ሄደችና ፡ ናስቲያ ን ፡ ጠራቻት ። ሁለቱም ፡ በማግሥቱ ፡ ስለሚመጡት ፡ እንግ ዶች ፡ ሰፊ ፡ ጭውውት ፡ አደረጉ ። አሌክሲይ ፡ ይህች ፡ ጨዋ ፡ እመቤት ፡ የእሱ ፡ አኩሊና ፡ ሆና ፡ ሲያገኛት ፡ ምን ፡ ያስብ ፡ ይሆን? ስለጠባይዋ ፤ ስለመሠረታዊ ፡ እምነቷና ፡ ስለጥንቁቅ ነቷ ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ ይወስድ ፡ ይሆን? ባንድ ፡ በኩል ፡ ደ ግሞ ፡ ሁለቱ ፡ በድንገት ፡ ሲገናኙ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓ

ይነት ፡ ስሜት ፡ እንደሚያድርበት ፡ ለማየት ፡ ሊዛ ፡ አጥብቃ ፡ ፈልጋ ፡ ነበር ። በድንገት ፡ አንድ ፡ ብሩህ ፡ ሐሳብ ፡ አገኘች ። ሐሳቡንም ፡ ለናስቲያ ፡ አካፈለቻት ። ሁለቱም ፡ በሐሳቡ ፡ ስለተደሰቱ ፡ በምንም ፡ መንገድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊያውሉት ፡ ቆረጡ ።

በማግሥቱ ፡ በቁርስ ፡ ሰዓት ፡ ልጁ ፡ አሁንም ፡ ከቤሬስቶቭ ፡ ቤተሰብ ፡ ለመደበቅ ፡ ቆርጣ ፡ እንደሆን ፡ አባቷ ፡ ጠየቃት ። « የአንተ ፡ ፍላጎት ፡ ስለሆነ ፡ ግድ ፡ የለም ፡ እቀበላቸዋለሁ ፡ አባባ ፡ » ስትል ፡ መለሰች ፡ ሊዛ ። ቀጥላም ፤ « ነገር ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ መስየ ፡ ብቀርብና ፡ የፈለግሁትንም ፡ ብሠራ ፡ እንደማትቆጣኝና ፡ የመደነቅና ፡ ያለመደሰትም ፡ ስሜት ፡ እንደማታሳይ ፡ ውለታ ፡ ግባልኝ ። » « እንደገና ፡ ደግሞ ፡ የተለመደውን ፡ ተንኰልሽን ፡ ልትሠሪ ፡ ነው! » አለ ፡ ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ እየሣቀ ። « ደህና ፡ ነው ፡ የፈለግሺውን ፡ አድርጊ ፤ የኔ ፡ ጥቁር ፡ ዓይን ፡ ቀበጥ! » አለ ። ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ግንባሯን ፡ ሳማት ፤ ሊዛም ፡ ዝግጅት ፡ ለማድረግ ፡ ሮጣ ፡ ሄደች ።

ልክ ፡ በስምንት ፡ ሰዓት ፡ በእጅ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ በስድስት ፡ ፈረሶች ፡ እየተሳበ ፡ በክቡና ፡ በድምቅ ፡ አረንጓዴው ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ ወደ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ ገባ ። የልጁ ፡ አባት ፡ ቤሬስቶቭ ፡ በሁለት ፡ የሙሮምስኪይ ፡ አሽከሮች ፡ ተደግፎ ፡ የበረንዳውን ፡ ደረጃ ፡ ወጣ ። ልጁም ፡ በፈረስ ፡ ተከትሎት ፡ መጥቶ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ወደሚጠብቃቸው ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ አንድነት ፡ ገቡ ። ሙሮምስኪይም ፡ እንግዶቹን ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀብሎ ፡ ከምሳ ፡ በፊት ፡ አትክልቱንና ፡ በረቱን ፡ እንዲጎበኙለት ፡ በደንብ ፡ በተደለደለ ፡ የጠጠር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ እየመራ ፡ ወሰዳቸው ። ሽማግሌው ፡ ቤሬስቶቭ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ ስላባከነው ፡ ጊዜና ፡ ጉልበት ፡ በልቡ ፡ የነቀፈታ ፡ ስሜት ፡ አደረበት ፤ ሆኖም ፡ ለትህትና ፡ ሲል ፡ ዝም ፡ አለ ። ልጅየው ፡ ግን ፡ የጥንቁቁን ፡ ባለርስት ፡ ነቀፌ

ታም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የእንግሊዝ ፡ መሳዩን ፡ ሰውዬ ፡ መደሰት ፡ ልብም ፡ ኢላለ ፡ ነበር ። እሱ ፡ የሚጠብቀው ፡ የጋባዡ ፡ ልጅ ፡ ብቅ ፡ እስኪትል ፡ ድረስ ፡ ነበር ። ስለ ፡ እርሷ ፡ ብዙ ፡ ሰምቷል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እንደምናውቀው ፡ ልቡን ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ ብት ማርከውም ፡ ቆንጆ ፡ ልጅ ፡ ሲያይ ፡ ስሜቱ ፡ እንደሚቀሰቀስ ፡ የታወቀ ፡ ነበር ።

ሶስቱም ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ ተመልሰው ፡ ተቀመጡ ። ሁለቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ስለዱሮ ፡ ጊዜ ፡ እያነሱ ፡ የ ወታደርነትን ፡ ሕይወት ፡ ተጨዋወቱ ። አሌክሲይ ፡ ግን ፡ ሊዛ ፡ ስትመጣ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ መታየት ፡ እንዳለበት ፡ ያስብ ፡ ነበር ። ግዴለሽና ፡ ዝምተኛ ፡ መምሰል ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ስለታየው ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ ተዘጋጀ ። በሩ ፡ ተከፈተ ። አሌክ ሴይ ፡ እራሱን ፡ በግዴለሽነትና ፡ በንቀት ፡ ዘወር ፡ አደረገ ። ይ ህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ፍቅር ፡ የማይነካትን ፡ እንኳ ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ በሚቀሰቅስ ፡ አኳኋን ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የገባችው ፡ ሴት ፡ ሊ ዛ ፡ ሳትሆን ፡ ሚስ ፡ ጃክሰን ፡ ነበረች ። ሚስ ፡ ጃክሰን ፡ ጉን ጭዋን ፡ ቀለም ፡ ተቀብታና ፡ ጥብቅ ፡ ያለ ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ስት ገባ ፡ ዓይኗን ፡ ቁልቁል ፡ ደፍታ ፡ ዝቅ ፡ ብላ ፡ እጅ ፡ ነሳች ። ስ ለዚህ ፡ የአሌክሴይ ፡ ታላቅ ፡ ዘዴ ፡ ሳይሠራለት ፡ ቀረ ። ገና ፡ ሐፍረቱ ፡ ሳይለቀው ፡ በሩ ፡ እንደገና ፡ ተከፈተና ፡ ሊዛ ፡ ገባች ። ሁሉም ፡ ተነሱ ። አባትየው ፡ ልጁን ፡ ለእንግዶቹ ፡ ሊያስተዋ ውቃት ፡ ሲል ፡ ድንገት ፡ ቆም ፡ አለና ፡ በችኮላ ፡ ከንፈሩን ፡ ነከሰ ። ጠይሟ ፡ ልጁ ፡ ሊዛ ፡ እስከጆሮዋ ፡ ድረስ ፡ ቀለም ፡ በመቀባት ፡ ከሚስ ፡ ጃክሰን ፡ ጋር ፡ የምትወዳደር ፡ ትመስ ላለች ። ጸጉሯም ፡ ከእውነተኛው ፡ ጸጉሯ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ የነ ጣና ፡ በውሸት ፡ የተጠቀለለ ፡ ሲሆን ፡ የሉዊ ፡ አስራ ፡ አራተ ኛውን ፡ ሰው ፡ ሰራሽ ፡ ጸጉር ፡ ይመስላል ። እጂጌዋም ፡ እንደ ማዳም ፡ ደ ፡ ፖምፓዱር ፡[20] ቀሚስ ፡ የተንጠለጠለ ፡ ነው ። ቅ ርጿ ፡ X እስኪመስል ፡ ጥብቅ ፡ ብላ ፡ ታስራለች ። የእናቷ ፡ አ

ልማዝዋ ፡ ለብድር ፡ ማያገር ፡ በሙሉ ፡ ስላልተሰጠ ፡ በጣቷ ፤
በአንገቷ ፡ ላይና ፡ በጆሮዋ ፡ ላይ ፡ ያንጸባርቅ ፡ ነበር ። አሌክ
ሴይ ፡ ይህች ፡ የተሽቆጠቆጠችና ፡ የምታስቅ ፡ ሴት ፡ አኩሊ
ና ፡ መሆንዋን ፡ ለማወቅ ፡ ከቶ ፡ አይችልም ፡ ነበር ። የአሌክ
ሴይ ፡ እባት ፡ የልጂቱን ፡ እጅ ፡ ለመሳም ፡ ብድግ ፡ አለ ። አሌ
ክሴይም ፡ ሳይወድ ፡ ያባቱን ፡ አርአያ ፡ ተከተለ ። ከንፈሩ ፡ ቀ
ጫጭን ፡ ጣቶቿን ፡ ዳሰስ ፡ ሲያደርገው ፡ ጣቶቿ ፡ ትንሽ ፡
የተንቀጠቀጡ ፡ መሰለው ። ወዲያውም ፡ ትናንሽ ፡ እግሯን ፡
አየ ። ይሄውም ፡ የሚያስቀናና ፡ የተዋበ ፡ ጫማዋን ፡ ለማሳየት ፡
ስትል ፡ ብቅ ፡ ያደረገችው ፡ መሆኑ ፡ ይታወቅ ፡ ነበር ። ጫማ
ዋን ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ የቀረውንም ፡ ልብሷን ፡ እምኖ ፡ ተቀበለ ።
ልጁ ፡ ልበ ፡ ቀና ፡ ስለሆነ ፡ የጉንጭዋን ፡ ቀለምና ፡ ቀለሙን
ም ፡ መጀመሪያ ፡ አላየውም ፡ ነበር ፤ ኋላም ፡ አልጠረጠረም ፡
ነበር ። ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪችም ፡ የገባውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
በማስታወስ ፡ አንዳችም ፡ ዓይነት ፡ የመደነቅ ፡ ስሜት ፡ እን
ዳያሳይ ፡ በተቻለው ፡ ሁሉ ፡ ሞከረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የልጂቱ ፡ ተን
ኰል ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ስላስገረመው ፡ ነገሩን ፡ አፍኖ ፡ ለመያ
ዝ ፡ አስቸገረው ። ትሁቷ ፡ እንግሊዛዊት ፡ ሴት ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡
የሚያስቅ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘችውም ፡ ነበር ። ፑድሩና ፡ ቀለሙ ፡
ከእርሷ ፡ የጌጥ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ የተሰረቀ ፡ መሆኑን ፡ ወዲያ
ው ፡ ስለተረዳች ፡ ንዴቷ ፡ ቀለም ፡ በተቀባው ፡ ጉንጯ ፡ ስር ፡
ፍም ፡ መስሎ ፡ ታየ ። ባለጌዋን ፡ ልጅም ፡ በቁጣ ፡ ዓይን ፡ ተመ
ለከተቻት ፤ ልጂቱ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ ወደፊት ፡ አስረዳለሁ ፡ በማ
ለት ፡ አይታ ፡ እንዳላየች ፡ ዝም ፡ አለች ።

ወደ ፡ ገበታ ፡ ቀርበው ፡ በየወንበራቸው ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ።
አሌክሴይም ፡ ዝንጉና ፡ አሳቢ ፡ ሰው ፡ መሰለ ። ሊዛም ፡ ፈገግ ፡
እያለች ፡ በዜማ ፡ ድምጽ ፡ ጥርሷን ፡ ዘግታ ፡ ትናገር ፡ ጀመር ።
ንግግሯም ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። አባትየው ፡ ግን ፡
ልጁ ፡ ይህን ፡ ያደረገችበትን ፡ ምክንያት ፡ ባያውቅ ፡ እንኳ ፡

ነገሩ ፡ እጅግ ፡ አስገረመው ። እንግሊዛዊቷ ፡ ሴትዮም ፡ እጅግ ፡ ከመናደዱ ፡ የተነሳ ፡ ቃል ፡ መናገር ፡ እንኳ ፡ አቃታት ። ከሁሉም ፡ እጅግ ፡ የተዝናናው ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እስኪጠግብ ፡ በላ ፤ አሳምሮ ፡ ጠጣ ፤ በገዛ ፡ ቀልዱም ፡ ሳቀ ፤ እያደር ፡ ወዳጅነት ፡ በተመላበት ፡ መንፈስም ፡ ይጨዋወት ፡ ጀመር ።

በመጨረሻ ፡ ከገበታ ፡ ተነሱ ። እንግዶቹም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ። ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ነፃ ፡ ስለሆነ ፡ መሳቅና ፡ ጥያቄ ፡ ማቅረብ ፡ ጀመረ ። « እነሱን ፡ ለማታለል ፡ ያሳሰበሽ ፡ ነገር ፡ ምንድን ፡ ነው? » ሲል ፡ ሊዛን ፡ ጠየቃት ። ቀጥሎም ፤ « እንዲያውም ፡ ፑድር ፡ ይስማማሻል! ሴቶች ፡ እንዴት ፡ እንደሚኳኳሉ ፡ አላውቅም ፤ እኔ ፡ አንቺን ፡ ብሆን ፡ ፑድር ፡ መቀባት ፡ እጀምር ፡ ነበር ። ብዙ ፡ አይደለም ፡ ታዲያ ፤ በጥቂቱ ። » ሊዛ ፡ ያሰበችውን ፡ ስለፈጸመች ፡ ደስ ፡ አላት ። የአባቷን ፡ አንገት ፡ በእጅዋ ፡ ጥምጥም ፡ አድርጋ ፡ ያዘችና ፡ የሰጣትን ፡ ምክር ፡ የምታስብበት ፡ መሆንዋን ፡ ተስፋ ፡ ሰጠችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተናደደችውን ፡ ሚስ ፡ ጃክሰንን ፡ ለማባበል ፡ ሮጣ ፡ ሄደች ። ሚስ ፡ ጃክሰን ፡ ግን ፡ በሬንም ፡ አልከፍትም ፤ የሊዛንም ፡ ማስረጃ ፡ አልሰማም ፡ ብላ ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ሊዛ ፡ ቀለም ፡ የተቀባችበት ፡ ምክንያት ፡ ጠይም ፡ ቆዳዋን ፡ ይዛ ፡ እንግዶች ፡ ፊት ፡ ለመቅረብ ፡ በማፈሯ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ገለጸችላት ። ለመጠየቅ ፡ አልደፈረችም ፡ ነበር ። ሚስ ፡ ጃክሰንም ፡ ስለ ... ይቅርታ ፡ እንደምታደርግላት ፡ እርግጠኛ ፡ ነበረች ። ሚስ ፡ ጃክሰንም ፡ ሊዛ ፡ ይህን ፡ ያደረገችው ፡ እርሷን ፡ ለማስቀየም ፡ አለመሆኑን ፡ ባመነች ፡ ጊዜ ፡ ንዴቷ ፡ በረደላት ። ለመታረቂያቸው ፡ ምልክት ፡ እንዲሆንም ፡ አንድ ፡ ጠርሙስ ፡ ቆዳ ፡ የሚያነጣ ፡ የእንግሊዝ ፡ ዘይት ፡ ሰጠቻት ። ሊዛም ፡ ከልብ ፡ አመስግና ፡ ተቀበለች ።

ሊዛ ፡ በማግሥቱ ፡ ወደ ፡ ቀጠሮው ፡ ቦታ ፡ እንደሄደች ፡

አንባቢ ፡ በቀላሉ ፡ ሊረዳ ፡ ይችላል ። « ትላንት ፡ የእኛን ፡ ጌ
ቶች ፡ ለመጠየቅ ፡ ሄደህ ፡ ነበር ፡ » አለችው ፡ ገና ፡ አሌክሴይ
ን ፡ እንዳገኘችው ። ቀጥላም ፤ « ታዲያስ ፡ የእኛ ፡ ወጣት ፡ እመ
ቤት ፡ ምን ፡ ትመስልሃለች? » ስትል ፡ ጠየቀችው ። አሌክሴ
ይም ፤ « ልብ ፡ ብየም ፡ አልተመለከትኋት ፡ » ሲል ፡ መለሰላ
ት ። « ያሳዝናል! » አለች ፡ ሊዛ ።« ለምን? » ሲል ፡ ጠየቃት ፡
አሌክሴይ ። « ምክንያቱም ፡ ሰዎች ፡ የሚሉት ፡ እውነት ፡ እ
ንደሆን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ልጠይቅህ ፡ ፈልጌ ፡ ነበር ... »
« ምን ፡ ይላሉ? » « የሚሉት ፡ እውነት ፡ ከሆነማ ... እኔ ፡
እርሷን ፡ እመስላለሁ ። « ከንቱ ፡ ወሬ ፡ ነው! እርሷ ፡ በ
አንቺ ፡ ዓይን ፡ ፍጹም ፡ ማስጠሎ ፡ ናት! » « አይ ፡ ጌታዬ ፤
እንዲህ ፡ አትበል ፤ የእኛ ፡ ወጣት ፡ እመቤት ፡ ውብ ፡ ናት ፤
ጽዱ ፡ ናት! እኔስ ፡ ደግሞ ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ ልወዳደ
ር ፡ እችላለሁ! » አሌክሴይም ፡ እርሷ ፡ በዓለም ፡ ከተዋቡት ፡
ወጣት ፡ ሴቶች ፡ ይበልጥ ፡ የተዋበች ፡ መሆንዋን ፡ አረጋገጠ
ላት ፤ ጥርጣሬ ፡ ፍጹም ፡ እንዳይገባትም ፡ እመቤቷን ፡ እያጥ
ላላ ፡ በሚያስቅ ፡ አኳኋን ፡ ስለገለጸላት ፡ ከልቧ ፡ ከት ፡ ብላ ፡
ሳቀች ። « ሆኖም ፡ » ስትል ፡ ተነፈሰችና ፡ « የእኔ ፡ ወጣት ፡
እመቤት ፡ የምታስቅ ፡ ብትሆንም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ያልተማረች ፡
ደንቆሮ ፡ አይደለችም ፡ » አለች ። « አይ ፡ »ሲል ፡ ጮኸ ፡
አሌክሴይ ፡ « ይኸ ፡ ነው ፡ ያስጨነቀሽ? ከፈለግሽ ፡ አሁኑኑ ፡
ላስተምርሽ ፡ እችላለሁ ።» ሊዛም ፤ « እሺ ፤ ምን ፡ ችገረኝ ።
ለምን ፡ አልሞክርም? » አለች ። « ይሻላል ፡ ወዳጄ ፤ በዪ ፡
አሁኑኑ ፡ እዚህ ፡ እንጀምር ፡ » አላት ። ተቀመጡ ። አሌክሴ
ይ ፡ ከኪሱ ፡ እርሳስና ፡ ደብተር ፡ አወጣ ፤ አኩሊናም ፡ ፊደሎ
ቹን ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አጠናች ። አሌክሴይ ፡ ልጂቱ ፡
እንዲህ ፡ በፍጥነት ፡ በማጥናቷ ፡ እጅግ ፡ ተደነቀ ። በማግሥ
ቱ ፡ ጧት ፡ ጽሕፈት ፡ መማር ፡ ለመሞከር ፡ ፈለገች ። በመጀመ
ሪያ ፡ እርሳሱ ፡ አልታዘዝ ፡ አላት ፤ ከጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ ግ

ን ፡ ፈደሎቹን ፡ በደንብ ፡ መጻፍ ፡ ጀመረች ። « ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው! ከላንካስተር ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ[21] ፡ እኛ ፡ ይበልጥ ፡ ፈጥነናል! »አለ ፡ አሌክሴይ ። እውነትም ፡ አኩሊና ፡ በሶስተኛው ፡ ትምህርት ፡ « ናታሊያ ፡ የባላባቱ ፡ ልጅ ፡ »[22] የሚለውን ፡ ቃል ፡ ለመጻፍ ፡ ቻለች ። ንባቧን ፡ እያቋረጠችም ፡ አሌክሴይን ፡ የሚያስደንቀው ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ትናገር ፡ ነበር ። በአንድ ፡ ቅጠል ፡ ወረቀት ፡ ላይም ፡ ከዚህ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የተቀዱ ፡ ምሳሌዎች ፡ ትጻጽፍ ፡ ጀመር ።

አንድ ፡ ሳምንት ፡ አለፈ ፤ ደብዳቤም ፡ ይጻጻፉ ፡ ነበር ። የፖስታ ፡ ሳጥናቸውም ፡ በአንድ ፡ ያረጀ ፡ ዋርካ ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ቀዳዳ ፡ ነበር ። ናስቲያ ፡ በምስጢር ፡ የፖስታ ፡ አመላላሽ ፡ ነበረች ። አሌክሴይ ፡ በጉልህ ፡ ፊደል ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ ወደ ፡ ዋርካው ፡ ቀዳዳ ፡ ወስዶ ፡ ሲያስቀምጥ ፤ በመናኛ ፡ ሰማያዊ ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ፍቅሩ ፡ የቦጫጨረችበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ያገኝ ፡ ነበር ። የአኩሊና ፡ አጻጻፍ ፡ በምትልከው ፡ ደብዳቤ ፡ ላይ ፡ እያደር ፡ ይሻሻል ፡ ጀመር ፤ አዕምሮዋም ፡ እየጐለመሰና ፡ እየተስፋፋ ፡ ሄደ ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ በኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤሬስቶቭና ፡ በግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ሙሮምስኪይ ፡ መካከል ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የተፈጠረው ፡ ግንኙነት ፡ እያደር ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄደ ። በሚቀጥለው ፡ ሁናቴ ፡ ምክንያትም ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ወዳጅነት ፡ ተለወጠ ። ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ሲሞት ፡ ንብረቱን ፡ ሁሉ ፡ አሌክሴይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ እንደሚወርሰው ፡ ዘወትር ፡ ያስብ ፡ ነበር ። አሌክሴይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ በሰፈሩ ፡ ካሉት ፡ ሀብታሞች ፡ አንደኛው ፡ ሲሆንም ፡ ሊዛን ፡ የማያገባበት ፡ አንድም ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡ ሲል ፡ አሰበ ። ሽማግሌው ፡ ቤሬስቶቭም ፡ በበኩሉ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጐረቤቱ ፡ ጥቂት ፡ እብድ ፡ ቢጤ ፡ ቢመስለውም ፡ ( ወይም ፡ እርሱ ፡ እንደሚለው ፡ እንግሊዝ ፡ ነክ ፡ የሆነን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አጥብቆ ፡ ቢወድም ፡ ) አንዳንድ ፡ መልካም ፡ ጠባይ ፡ እንዳለው ፤ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ብልህነ

ት ፡ መሆኑን ፡ አይክድም ፡ ነበር ። ግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ል ዑል ፡ ፕሮንስኪይ ፡ የተባለ ፡ የአንድ ፡ የታወቀና ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ዘመድ ፡ ነው ። ልዑሉ ፡ ለአሌክሴይ ፡ ወገንና ፡ ረዳት ፡ ሳይሆነው ፡ አይቀርም ፤ ( ሲል ፡ አሰበ ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮ ቪች ፡ ) ሙሮምስኪይም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ ሲያገኝ ፡ ል ጁን ፡ ያለጥርጥር ፡ ይድራታል ። ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ሁለ ቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሐሳባቸውን ፡ ደብቀው ፡ ቆዩ ። ግን ፡ ከዕ ለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ነገሩን ፡ ገልጸው ፡ ከልብ ፡ ተጨዋወቱ ና ፡ ተቃቀፉ ፤ ጉዳዩን ፡ በዝርዝር ፡ እንደሚያጠኑትም ፡ ተስፋ ፡ ተሰጣጡ ። ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፡ ነገሩን ፡ መከታተል ፡ ጀመሩ ። ሙሮምስኪይ ፡ አንድ ፡ ችግር ፡ ገጠመው ፤ ይሄውም ፡ ልጁ ፡ ቤትሲና ፡ አሌክሴይ ፡ ከዚያ ፡ ከማይረሳ ፡ የምሳ ፡ ግብ ዣ ፡ ዕለት ፡ በስተቀር ፡ ተያይተው ፡ ስለማያውቁ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያገናኛቸው ፡ ነበር ። እምብዛም ፡ እንዳልተዋደዱም ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ታየ ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ አሌክሴይ ፡ ወደ ፡ ፕሪሉቺ ኖ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ አልመጣም ፡ ነበር ። ኢቫን ፡ ፔትሮ ቪች ፡ ሊጠይቃቸው ፡ ሲሄድም ፡ ሊዛ ፡ ወደ ፡ ክፍሏ ፡ ትሄድ ፡ ነበር ። ግሪጐሪይ ፡ ኢቫኖቪችም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አሰበ ፤ « አሌክሴይ ፡ በየቀኑ ፡ ከመጣ ፤ ቤትሲ ፡ እርሱን ፡ መውደዷ ፡ አይቀርም ። ይሄ ፡ የተፈጥሮ ፡ ነገር ፡ ነው ። ጊዜ ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ ይወስነዋል ። »

ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ ያቀደውን ፡ ነገር ፡ ወደፍጻሜ ፡ ለማ ድረስ ፡ እንደሚችል ፡ እርግጠኛነት ፡ ተሰማው ። ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ጠራና ፡ የሲጋራ ፡ ማጨ ሻውን ፡ አቀጣጥሎ ፡ ጥቂት ፡ አረፍ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አ ለ ፤ « አሌክሴይ ፤ ምነው ፡ የጦር ፡ መኰንን ፡ ስለመሆን ፡ ማ ውራትህን ፡ ፈጽመህ ፡ ተውከው? የፈረሰኛ ፡ ልብስ ፡ ለመል በስ ፡ የነበረህ ፡ አምሮት ፡ ጠፋ ፡ እንዴ? » « እረ ፡ የለም ፤ አ ባብዬ ፡ » ሲል ፡ አሌክሴይ ፡ በአክብሮት ፡ መለሰና ፤ « ወደፊ



የመስፍን ፡ ቪያዜምስኪያ ፡ ሚስት ፡ የሆነችው ፡ ቬራ ፡
ቪያዜምስካያ ( ፲፯፻፺ — ፲፰፻፹፮ ዓ. ም. ) የፑሽኪን ፡
ቅርብ ፡ ወዳጅ ፡ ነበረች ።



የኦዴሳ ፡ ወደብ ። በዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ፑሽኪን ፡
በ ፲፰፻፳፫ — ፲፰፻፳፬ ዓ. ም. ይኖር ፡ ነበር ።



ሚኻይሎቭስኮዬ ፡ በሚባለው ፡ የፑሽኪን ፡ እናት ፡ ይኖሩበት ፡ የነበረ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ።



የጋኒባል ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ገባር ፡ የነበረችው ፡ የፑሽኪን ፡ ሞግዚት ፡ አሪና ፡ ሮዲዮኖቭና (፲፯፻፶፰ — ፲፰፻፳፰ ዓ. ም.) ። በ፲፯፻፺፱ ዓ. ም. ከገባርነት ፡ ነጻ ፡ ወጣች ። ምንም ፡ እንኳን ፡ መሃይም ፡ ብትሆንም ፡ በተፈጥሮዋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተሰጥዎ ፡ ነበረችው ። በርከት ፡ ያሉ ፡ የሕዝብ ፡ ዘፈን ፡ ተረትና ፡ ምሳሌ ፡ ለፑሽኪን ፡ ስላወጋችለት ፡ ባለቅኔው ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ይጠቀምባቸው ፡ ነበር ።



በቁንጅናዋ ፡ በጣም ፡ ይታወቅ ፡ የነበረችው ፡ አና ፡ ኬርን ( ፲፰፻ – ፲፰፻፸፱ ዓ. ም. ) ። ፑሽኪን ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ይወዳት ፡ ነበር ። ( ፑሽኪን ፡ በራሱ ፡ እጅ ፡ የሣለው ፡ ሥዕል ። ፲፰፻፳፱ ዓ. ም. )



ትሪጎርስኮዬ ፡ በምትባለው ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የፑሽኪን ፡ ወዳጆች ፡ የሆኑ ፡ የኦሲፖቭ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ። ፑሽኪን ፡ በየጊዜው ፡ ይጎበኛቸው ፡ ነበር ።



ባለቅኔውና ፡ የፑሽኪን ፡ ጓደኛ ፡ ቪልሄልም ፡ ኩኺልቤከር ( ፲፯፻፺፯ ፲፰፻፵፮ ዓ ም ) ። በታህሳስ ፡ አድማ ፡ ንቁ ፡ ተሳታፊ ፡ በመሆኑ ፡ የአሥር ፡ ዓመት ፡ ጽኑ ፡ እሥራት ፡ ተፈርዶበት ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ታሥሮ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሳይቤሪያ ፡ ለግዞት ፡ ተላከ ። እዚያው ፡ ታሥሮ ፡ ሞተ ።



ባለቅኔው ፡ ኮንድራቲይ ፡ ሪሌዬቭ ( ፲፯፻፺፭ — ፲፰፻፳፮ ዓ. ም. ) ። የታህሣስ ፡ አድማ ፡ መሪ ፡ በመሆኑ ፡ በስቅላት ፡ ተገደለ ።

ረሰኛ ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ ብገባ ፡ እንደማትፈቅድ ፡ ስለማውቅ ፡ ፍላጐትህን ፡ መፈጸም ፡ ተግባሬ ፡ ነው ፡ » አለ ። « መልካም ፡ ነው ፡ » አለ ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ። « ቁም ፡ ነገረኛ ፡ ልጅ ፡ መሆንህን ፡ ተረዳሁ ። ይህ ፡ ለኔ ፡ ታላቅ ፡ መጽናኛ ፡ ነው ። እ ኔም ፡ ብሆን ፡ ላስገድድህ ፡ ፍላጎት ፡ የለኝም ። ለጊዜው ፡ የመ ንግሥት ፡ ሥራ ፡ እንድትይዝ ፡ አላስገድድህም ። ግን ፡ ትዳር ፡ እንድትይዝ ፡ እፈልጋለሁ ። »

« ማንን ፡ እንዳገባ ፡ ትፈልጋለህ ፡ አባብዬ? » ሲል ፡ አሌ ክሴይ ፡ በመደነቅ ፡ ጠየቀ ።

« ሊዛቬታ ፡ ግሪጐሪየቭና ፡ ሙሮምስካያን ፡ ነው ። እኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ አትከፋም ፡ » ሲል ፡ ኢቫን ፡ ፔትሮቪች ፡ መ ለሰለት ።

« አባባ ፤ እኔ ፡ አሁን ፡ ለማግባት ፡ ገና ፡ ሐሳብም ፡ የለኝ ። »

« አሳቢው ፡ አንተ ፡ አይደለህም ፤ ስለዚህ ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ ለአንተ ፡ አስቤ ፡ ወስኜልሃለሁ ። »

« አባባ ፤ እኔ ፡ ሊዛ ፡ ሙሮምስካያን ፡ አልወዳትም ፡ እኮ ።»

« የኋላ ፡ ኋላ ፡ ትወዳታለህ ። ፍቅር ፡ በልማድ ፡ የሚመጣ ፡ ነገር ፡ ነው ። »

« እኔ ፡ እርሷን ፡ ለማስደሰት ፡ ችሎታ ፡ ያለኝ ፡ ሆኖ ፡ አይ ሰማኝም ። »

« ስለእርሷ ፡ ደስታ ፡ አትጨነቅ ። ይልቁንስ ፡ የአባትን ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸም ፡ አይበልጥም? ይሻላል ፡ እኮ! »

« አባባ ፡ ሆይ ፤ አንተ ፡ ወደድከም ፡ ጠላህም ፡ እኔ ፡ እንደ ሆንኩ ፡ ለማግባት ፡ ፍላጐት ፡ የለኝም ፤ አላገባምም ። »

« ወይም ፡ አግባ ፤ አለበለዚያ ፡ ግን ፡ እረግምሃለሁ ፤ እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡ ደግሞ ፡ ንብረቴንም ፡ ላገኛ ሁት ፡ ዋጋ ፡ ሸጬ ፡ አንድም ፡ ሳንቲም ፡ አላስተርፍልህም ። በ ነገሩ ፡ እንድታስብበት ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ እሰጥሃለሁ ፤ እስከዚያ ው ፡ ግን ፡ ከዓይኔ ፡ ጥፋ!»

አባቱ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ከአሰበ ፡ እንኳንስ ፡ እንደዚሁና ፡ ታራስ ፡ ስኮቲኒን ፡ እንዳለው ፡[23] « በምስማር ፡ » እንኳ ፡ ገፍቶ ፡ ለማውጣት ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ አሌክሴይ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ። አሌክሴይም ፡ የአባቱን ፡ አርአያ ፡ ስለሚከተል ፤ እሱንም ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲለውጥ ፡ ማድረግ ፡ እንደዚሁ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ሄዶ ፡ ስለቤተሰብ ፡ ሥልጣን ፡ ወሰንና ፡ ስለሊዛቬታ ፡ ግሪጎሪየቭና ፡ ጠባይ ፤ እንዲሁም ፡ አባቱ ፡ ደኃ ፡ ሊያደርገው ፡ ስለሰጠው ፡ ቁርጥ ፡ ቃል ፡ ከአሰላሰለ ፡ በኋላ ፤ በመጨረሻ ፡ ሐሳቡን ፡ በአኩሊና ፡ ላይ ፡ አሳረፈ ። ከእርሷ ፡ ጋር ፡ ጥልቅ ፡ ፍቅር ፡ እንደያዘው ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በግልጽ ፡ ተረዳ ። አንድ ፡ ተራ ፡ የባላገር ፡ ልጃገረድ ፡ አግብቶ ፡ እራሱ ፡ እየሠራ ፡ የመኖር ፡ የፍቅር ፡ ሐሳብ ፡ በአዕምሮው ፡ ውስጥ ፡ አለፈ ፤ ስለዚህ ፡ ቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ ደጋግሞ ፡ በአሰበ ፡ ቁጥር ፡ ነገሩ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ታየው ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ የጫካ ፡ ተፋቃሪዎች ፡ በዝናብ ፡ ምክንያት ፡ መገናኘታቸውን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አቋርጠው ፡ ነበር ። አገላለጹ ፡ ንጹሕ ፡ የሆነና ፡ አጻጻፉ ፡ የቁጣ ፡ የሆነ ፡ ደብዳቤ ፡ ለአኩሊና ፡ በመጻፍ ፡ ደስታቸውን ፡ የሚያጠፋ ፡ ነገር ፡ መፈጠሩን ፡ ከገለጸላት ፡ በኋላ ፡ እንዲጋቡ ፡ ጠየቃት ። ደብዳቤውን ፡ ወደ ፡ ዋርካው ፡ ቀዳዳ ፡ ፖስታ ፡ ቤት ፡ ከአስገባ ፡ በኋላ ፤ ደስ ፡ ብሎት ፡ ተኛ ።

በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ በማለዳ ፡ አሌክሴይ ፡ በሐሳቡ ፡ ቁርጠኛ ፡ ሆኖ ፡ ሙሮምስኪይን ፡ ለማየትና ፡ በግልጽ ፡ ስለጉዳዩ ፡ ለመነጋገር ፡ ሄደ ። እርጎራጌውን ፡ ለመቀስቀስና ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲደግፈው ፡ ለማድረግም ፡ ተስፋ ፡ ነበረው ። « ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ አሉ? » ሲል ፡ ጠየቀ ፡ ፈረሱን ፡ በፕሪሉቺኖ ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ በረንዳ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እያሰረ ። « እረ ፡ የሉም ፡ ጌታዬ ፤ ግሪጎሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ዛሬ ፡ በማለዳ ፡ ነው ፡ ወጥተው ፡ የሄዱት ፡ » ሲል ፡ መለሰ ፡ አሽከርየው ። « እንዴት ፡ የሚያበሳጭ ፡ ነገር ፡ ነው! » ሲል ፡ አሰበ ፡ አሌክሴይ ። « ሊዛቬታ ፡ ግ

ረጕሪየቭናስ ፡ እቤት ፡ ናቸው? » « አዎን ፡ ጌታዬ ። » አሌክሴ ይ ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ዱብ ፡ ብሎ ፡ ወረደና ፡ ልጓሙን ፡ ለአሽከ ሩ ፡ ሰጥቶ ፡ መምጣቱንም ፡ ሳያስታውቅ ፡ ሱተት ፡ ብሎ ፡ ገባ ።

« ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ያልቃል ፡ » ሲል ፡ አሰበ ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ ቤቱ ፡ እያመራ ። « ከእራሷ ፡ ከሴትዮዋ ፡ ጋር ፡ እኔው ፡ እራ ሴ ፡ እነጋገራለሁ ። » ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ሲገባ ፡ ክው ፡ ብ ሎ ፡ ደነገጠ ። ሊዛ ፤ ... የለም ፡ እርሷ ፡ አይደለችም ። ውዲቱ ፡ ጠይሟ ፡ አኩሊና ፡ የባላገር ፡ ልብስ ፡ ሳይሆን ፡ ነጭ ፡ የጧት ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ በመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ የእርሱን ፡ ደብዳቤ ፡ ታነብ ፡ ነበር ። በደብዳቤው ፡ በጣም ፡ ተመስጣ ፡ ስለነበረም ፡ ሲገባ ፡ እንኳ ፡ አልሰማችውም ፡ ነበር ። አሌክሴይ ፡ ደስታው ን ፡ ሊያፍነው ፡ አልቻለም ። ሊዛም ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ እራሷን ፡ ቀና ፡ ስታደርግ ፡ ጮኸች ፤ ለመሸሽም ፡ ሞከረች ። እርሱም ፡ በኃይል ፡ ይዞ ፡ ሊያስቀራት ፡ ሞከረ ። « አኩሊና! አኩሊና! » እያለም ፡ ጮኸ ። ሊዛም ፡ ልትነጥቀው ፡ ሞከረች ... «Mais laissez-moi donc, Monsieur; mais êtes-vous fou?» * እያለች ፡ ጮኸች ፡ ሲታገሉ ፡ ሳለ ። « አኩሊና! አኩሊና! ፍቅሬ! » እያለ ፡ ደ ጋግሞ ፡ ተናገረ ፤ እጅዋንም ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ሳማት ። ሚስ ፡ ጃ ክሰን ፡ ይህን ፡ ጉድ ፡ ስላየች ፡ ምን ፡ እንደምትል ፡ ጨነቃት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሩ ፡ ተከፈተና ፡ ግሪጕሪይ ፡ ኢቫኖቪች ፡ ገባ ።

« እንዴ! እንዴ! ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ እራሳችሁ ፡ ጨርሳችሁ ታል ... » ሲል ፡ ጮኸ ፡ ተናገረ ።

የታሪኩ ፡ ፍጻሜ ፡ ግልጽ ፡ ስለሆነ ፡ አንባቢ ፡ ከዚህ ፡ ት ርፍ ፡ ሥራ ፡ እንደሚያድነኝ ፡ አውቃለሁ ።

የኢቫን ፡ ቤልኪን ፡ ታሪኮች ፡
ተፈጸሙ ።

---

*ልቀቀኝ ፡ እባክህ ፤ አብደሃል ፡ እንዴ? ( በፈረንሳይኛ ። )

8*

# ዶግብሮቨሰኪይ።

# የመጀመሪያ ፡ ክፍል ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ትሮዬኩሮቭ ፡ የሚባል ፡ የጥንት ፡ የሩሲያ ፡ ባላባት ፡ ካሉት ፡ እርስቶቹ ፡ ባንደኛው ፡ ላይ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ሐብቱ ፤ ትውልዱና ፡ ወገኑም ፡ እርስቱ ፡ ባለበት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የተከበረ ፡ ሰው ፡ አድርጎት ፡ ነበር ። እርሱ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ በሠራ ፡ ቁጥር ፡ ጐረቤቶቹ ፡ ሥራውን ፡ ለማድነቅ ፡ በጣም ፡ ይቸኩላሉ ። የሠፈሩ ፡ ሹማምንትም ፡ ስሙን ፡ ሲሰሙ ፡ ያስካካሉ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ይህን ፡ ሁናቴ ፡ የሚገባኝ ፡ የአክብሮት ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ተቀበለ ። ቤቱ ፡ ዘወትር ፡ በእንግዳ ፡ እንደተመላ ፡ ነው ። እነኚህ ፡ ጠያቂዎቹ ፡ እርሱ ፡ በመኳንንት ፡ ተድላና ፡ ደስታ ፡ እስከኖረ ፡ ድረስ ፡ ምንጊዜም ፡ ሊጠይቁት ፡ የተዘጋጁና ፡ ሳቅና ፡ ስላቅ ፡ በተመላበትም ፡ ድግሱ ፡ ላይ ፡ ዘወትር ፡ ተካፋይ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈልጉ ፡ ናቸው ።

ግብዣውን ፡ አልቀበልም ፡ ለማለት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ አይደፍርም ። በተወሰኑ ፡ ቀናትም ፡ ፖክሮቭስኮዬ ፡

ወደተባለው ፡ ወደርሱ ፡ መንደር ፡ መጥተው ፡ እጅ ፡ ሳይነሱ ፡ አይቀሩም ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ትምህርት ፡ ያላለሰለሰው ፡ የጠባይ ፡ ጉድለት ፡ በግል ፡ ኑሮው ፡ ላይ ፡ ያሳይ ፡ ነበር ። ሁሉን ፡ ነገር ፡ ስለቀመሰና ፡ በምቾትና ፡ በመንቀባረር ፡ ስላደገ ፡ ማንኛውንም ፡ የሥጋዊ ፡ ፍላጐቱን ፡ መሙላትና ፡ ደካማ ፡ አዕምሮው ፡ ያሳሰበውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ የዘወትር ፡ ልማዱ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ሰውነቱ ፡ ጤናማ ፡ ቢሆንም ፡ ያለልክ ፡ ከመመገብ ፡ የተነሣ ፡ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ በአራት ፡ በአራት ፡ ቀን ፡ በቁንጣን ፡ በሽታ ፡ ይሠቃያል ። ማታ ፡ ማታም ፡ ዘወትር ፡ እንደሰከረ ፡ ነው ። በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ ባንደኛው ፡ በኩል ፡ አሥራ ፡ስድስት ፡ ገረዶች ፡ ይኖራሉ ። እነሱም ፡ ለሴትልጅነታቸው ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ የጥልፍ ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። የገረዶቹ ፡ መኖሪያ ፡ ክፍል ፡ መስኮቶች ፡ በእንጨት ፡ መቀርቀሪያ ፡ የተጠበቁ ፡ ናቸው ። መዝጊያዎቹም ፡ ዘወትር ፡ እንደተቆለፉ ፡ ናቸው ። ቁልፎቹንም ፡ የሚይዘው ፡ እራሱ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ወጣት ፡ እስረኞች ፡ በሁለት ፡ አሮጊት ፡ ጠባቂነት ፡ በተወሰነ ፡ ሰዓት ፡ በአትክልት ፡ ቦታ ፡ እንዲንሸራሸሩ ፡ ይፈቀድላቸዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ባል ፡ ያገኝላቸውና ፡ ሲሄዱ ፡ ሌሎች ፡ ልጃገረዶች ፡ ደግሞ ፡ በነርሱ ፡ ምትክ ፡ ይገባሉ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በገባሮቹና ፡ በአሽከሮቹ ፡ ላይ ፡ ጨካኝ ፡ ነው ። እነርሱ ፡ ግን ፡ በታማኝነት ፡ ያገለግሉታል ። በጌታቸው ፡ ሐብትና ፡ ዝና ፡ ስለሚኰሩና ፡ ከማንኛውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቀናል ፡ ብለው ፡ ስለሚያምኑም ፡ በጐረቤቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ያሰኛቸውን ፡ ይፈጽማሉ ።

የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ዋና ፡ ተግባሩ ፡ ባቅራቢያው ፡ ባለው ፡ ሰፊ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ማደንና ፡ ዘወትር ፡ ድግስ ፡ መደገስ ፡

ነው ። አዲስ ፡ ሰው ፡ በተዋወቀም ፡ ቁጥር ፡ በሰውዬው ፡ ላይ ፡ መቀለድ ፡ ይወዳል ። በጥንቶቹ ፡ ወዳጆቹም ፡ ላይ ፡ ከአንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በስተቀር ፡ እንደዚሁ ፡ ሲያሰኘው ፡ ያፌዝባቸዋል ። ይህ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ቀድሞ ፡ በክብር ፡ ዘበኛ ፡ ውስጥ ፡ መኰንን ፡ የነበረ ፡ የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ቅርብ ፡ ጐረቤት ፡ ነው ። ሰባ ፡ ገባሮችም ፡ አሉት ። ኪረላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ታላቅ ፡ ሹመት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሲንቅ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ ያከብሩት ፡ ነበር ። በወታደርነት ፡ አንድነት ፡ ስለነበሩም ፡ የወዳጁን ፡ ኃይለኛና ፡ የማይበገር ፡ ጠባይ ፡ ያውቃል ። እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ጊዜ ፡ ለያይቷቸው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በገንዘብ ፡ ኪሣራ ፡ ምክንያት ፡ አሁን ፡ ባለበት ፡ መንደሩ ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ መኖር ፡ ግድ ፡ ሆነበት ፤ ያለውም ፡ ሐብቱ ፡ ይኸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ አለሁልህ ፡ ሲል ፡ በርሱ ፡ ጠባቂነት ፡ ስር ፡ እንዲኖር ፡ ጠየቀው ። አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ግን ፡ ለመልካም ፡ ሐሳቡ ፡ ምሥጋናውን ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፡ በድህነት ፡ እራሱን ፡ ችሎ ፡ ለመኖር ፡ መረጠ ። ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በኋላም ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በእርጅና ፡ ምክንያት ፡ ከዋና ፡ ጀኔራልነት ፡ ማዕርጉ ፡ ተሰናብቶ ፡ ወደርስቱ ፡ ሲመለስ ፡ ሁለቱ ፡ ወዳጆች ፡ እንደገና ፡ በመገናኘታቸው ፡ ተደሰቱ ። ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮም ፡ ሁለቱ ፡ ሳይገናኙ ፡ አንድም ፡ ቀን ፡ አያሳልፉም ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ መጠየቅ ፡ ስለማይፈቅድ ፡ ይህን ፡ የጥንት ፡ ወዳጁን ፡ እታናሽ ፡ ቤቱ ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ይጐበኘው ፡ ነበር ። የሁለቱ ፡ ዕድሜ ፡ አንድ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደረጃቸውም ፡ አንድ ፡ ነበር ። አስተዳደጋቸውም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነበር ። ጠባያቸውና ፡ የሚያምራቸው ፡ ነገርም ፡ ተመሳሳይ ፡ ነበር ።

ባንዳንድ ፡ ረገድ ፡ ዕድላቸውም ፡ እንደዚሁ ፡ ተመሳሳይ ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ ያገቡት ፡ ለፍቅር ፡ ሲሆን ፡ የሁለቱም ፡ ሚስቶች ፡ ሞተዋል ። ሁለቱም ፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ ልጆች ፡ አሏቸው ። የአንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ልጅ ፡ የሚማረው ፡ በፔቴርቡርግ ፡ ከተማ ፡ ሲሆን ፡ የኪረላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ከአባቷ ፡ ጋር ፡ ትኖራለች ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ ዘወትር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይጠይቀው ፡ ነበር ፤ « ስማ ፡ አንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች! ያ ፡ ልጅህ ፡ ቮሎዲያ ፡ ጐበዝ ፡ ልጅ ፡ የወጣው ፡ እንደሆን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የደኃ ፡ ደኃ ፡ ቢሆንም ፡ ልጄን ፡ ማሻን ፡ እድርለታለሁ ። » አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይም ፡ እራሱን ፡ እያወዛወዘ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይመልሳል ፡ « የለም ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች! ልጄ ፡ ቮሎዲያና ፡ ያንተ ፡ ልጅ ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ እቻ ፡ ላቻ ፡ አይደሉም ። እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ደኃ ፡ የቅምጥል ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ አሽከር ፡ ከሚሆን ፡ የሱን ፡ ቢጤ ፡ ደኃ ፡ ሴት ፡ አግብቶ ፡ የቤቱ ፡ ጌታ ፡ ቢሆን ፡ ይሻላል ። »

በትዕቢተኛው ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችና ፡ በደኃ ፡ ጐረቤቱ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ስምምነት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይቀና ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ገበታ ፡ ተቀምጦ ፡ የግል ፡ አስተያየቱን ፡ ከጋባዡ ፡ አስተያየት ፡ ጋር ፡ ቢስማማም ፡ ባይስማማም ፡ በድፍረት ፡ ሲናገር ፡ ሁሉም ፡ ያደንቁ ፡ ነበር ። የአንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ አርዓያ ፡ በመከተልም ፡ የግል ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለማሰማት ፡ የሞከሩ ፡ ነበሩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በቁጣ ፡ ዓይን ፡ ስለሚገላምጣቸው ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ መሞከር ፡ ጨርሶ ፡ አቆሙ ። በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ ያልተወሰነ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተለዋወጠና ፡ ቁጭ ፡ አለ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ወደ ፡ አ

ደን ፡ ለመሄድ ፡ ተዘጋጀ ። በዚያኑ ፡ ዕለት ፡ አዋቢያ ፡ ፌረስ ፡ ጫኚዎቹና ፡ ግዳይ ፡ ሰብሳቢዎቹ ፡ በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ባሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ እንዲነሱ ፡ ትዕዛዝ ፡ ተሰጣቸው ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ምግብ ፡ ለመብላት ፡ ወደአሰበበት ፡ ቦታ ፡ ድንኳንና ፡ የወጥ ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ አስቀድሞ ፡ ተላከ ። ጋባዡና ፡ እንግዶቹም ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ አዳኝ ፡ ውሻዎች ፡ በምቾትና ፡ በጥጋብ ፡ ወደሚኖሩበት ፡ ቦታ ፡ አመሩ ። እነዚህ ፡ እንስሳት ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ለሚያደርግላቸው ፡ ልግስና ፡ በውሻ ፡ አንደበታቸው ፡ ያመሰግኑታል ። የታመሙ ፡ ውሻዎች ፡ የሚታከሙበትም ፡ ቲሞሽካ ፡ በተባለው ፡ የሠራተኞች ፡ ሐኪም ፡ የሚካሄድ ፡ የማስታመሚያ ፡ ቤት ፡ አለ ። ምርጥ ፡ ውሻዎች ፡ ቡችላዎቻቸውን ፡ የሚያጠቡበትም ፡ እንደዚሁ ፡ የተለየ ፡ ቦታ ፡ አላቸው ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ድርጅቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኩራት ፡ ይሰማው ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ሃያ ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ ይህንኑ ፡ ድርጅቱን ፡ ከአሁን ፡ ቀደም ፡ ለጎበኙት ፡ እንግዶቹ ፡ እንደገና ፡ ደግሞ ፡ በኩራት ፡ ለማሳየት ፡ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ሲያገኝ ፡ አያልፍም ። እነሆ ፡ አሁን ፡ የውሾቹን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ በእግዶቹና ፡ በሐኪሙ ፡ በቲሞሽካ ፡ እንዲሁም ፡ በውሻ ፡ ቤት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ታጅቦ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ይመለከታል ። ባንዳንድ ፡ የውሻ ፡ ቤቶችም ፡ ቆም ፡ እያለ ፡ ስለታመሙ ፡ ውሻዎች ፡ ይጠይቃል ። መልሱ ፡ ዕውነት ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ አንዳንድ ፡ የኃይል ፡ ቃል ፡ ይናገራል ። አንዳንዶቹን ፡ የሚወዳቸውንም ፡ ውሻዎች ፡ ወደርሱ ፡ እየጠራ ፡ በፍቅር ፡ ያጫውታቸዋል ። እንግዶቹም ፡ የኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ የውሻ ፡ ማሳደጊያ ፡ ወደዱም ፡ ጠሉም ፡ ማድነቅ ፡ ግድ ፡ ይሆንባቸዋል ። አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ግን ፡ ፊቱን ፡ ኰስትሮ ፡ ዝም ፡ ብሏል ። ዱብሮቭስኪይ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አደን ፡ እጅግ ፡ ቢወድም ፡ ያሉት ፡ አዳኝ ፡ ውሻዎች ፡ አራት ፡ ብቻ ፡ በመሆናቸው ፡ በኪሪላ ፡

ፔትሮቪች ፡ ሰፊ ፡ የውሻ ፡ ማሳደጊያ ፡ ድርጅት ፡ በልቡ ፡ ቅናት ፡ አደረበት ።

« ምነው ፡ እንዲህ ፡ ከፋህ ፡ ወንድሜ? የውሻ ፡ ማሳደጊያዬን ፡ አልወደድኸውምን? » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጠየቀው ።

« የውሻ ፡ ማሳደጊያህ ፡ በእውነቱ ፡ ወደር ፡ የለውም ። አሽከሮችህ ፡ እንኳ ፡ እንደውሾችህ ፡ የሚኖሩ ፡ አይመስለኝም ፡ » ሲል ፡ አንድሬይ ፡ዱብሮቭስኪይ ፡ በደረቁ ፡ መለሰ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከውሻ ፡ ጠባቂዎቹ ፡ አንደኛው ፡ ስለተቀየመ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

« ለእግዚአብሔርና ፡ ለጌታችን ፡ ምስጋና ፡ ይድረሳቸው ። እኛ ፡ እንደሆን ፡ ምንም ፡ የምናማርረው ፡ ነገር ፡ የለንም ። ይልቁንስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እርስታቸውን ፡ ለውሻ ፡ ቤታችን ፡ ለመለወጥ ፡ ይፈልጋሉ ። ይሄውም ፡ በጥጋብና ፡ በምቾት ፡ ለመኖር ፡ ሲሉ ፡ ነው ። »

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ አሽከሩ ፡ በተናገረው ፡ ቀልድ ፡ ከት ፡ ብሎ ፡ ሳቀ ። እንግዶቹም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የውሻ ፡ ጠባቂው ፡ የተናገረው ፡ አሽሙር ፡ እነሱንም ፡ የሚነካ ፡ ቢሆንም ፡ አብረው ፡ አስካኩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ፊቱ ፡ ተለወጠ ። አንድም ፡ ቃል ፡ አልተናገረም ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ አዲስ ፡ የተወለዱ ፡ ቡችላዎች ፡ ለኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በቅርጫት ፡ ቀረቡለት ። እሱም ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱን ፡ መረጠና ፡ የቀሩቱ ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጣሉ ፡ አዘዘ ። በዚህ ፡ መካከል ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያየው ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ጠፋ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ የውሻ ፡ ማሳደጊያውን ፡ ጐብኝቶ ፡ ከእንግዶቹ ፡ ጋር ፡ ተመለሰና ፡ ለእራት ፡ ሲቀመጥ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ እንደሌለ ፡ ተመለከተ ። ወዴት ፡ ሄደ ፡ ብሎም ፡ ጠየቀ ። በፈረስ ፡ ጋልበው ፡ እንዲደርሱበትና ፡

እንዲመልሱትም ፡ አዘዘ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በሕይወቱ ፡ ያለዱብሮቭስኪይ ፡ አደን ፡ ሄዶ ፡ አያውቅም ። ምክንያቱም ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ያዳኝ ፡ ውሻን ፡ ምልክት ፡ አጥርቶ ፡ ስለሚያውቅና ፡ ስለአደን ፡ ጉዳይ ፡ በሚነሳ ፡ ክርክርም ፡ ዘወትር ፡ ትክክለኛ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። የተላከው ፡ ፈረሰኛ ፡ ገና ፡ ከገበታ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ደርሶ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ መልእክቱን ፡ አልሰማው ፡ እንዳለና ፡ ለመመለስም ፡ እንዳልፈቀደ ፡ ለጌታው ፡ አስታወቀ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ መጠጥ ፡ ጠጥቶ ፡ እንደልማዱ ፡ ሞቅ ፡ ብሎት ፡ ስለነበር ፡ በቁጣ ፡ ገንፈለና ፡ እንደገና ፡ አሽከሩን ፡ በመላክ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በፍጥነት ፡ ካልተመለሰ ፡ ሌሊቱንም ፡ በፖክሮቭስኮዬ ፡ ካላሳለፈ ፡ ምንጊዜም ፡ ምሕረት ፡ የማያደርግለት ፡ መሆኑን ፡ እንዲነግረው ፡ አዘዘ ። አሽከሩ ፡ እንደገና ፡ ሽምጥ ፡ ጋለበ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ከገበታ ፡ ተነሣና ፡ እንግዶቹን ፡ አሰናብቶ ፡ ወደመኝታ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ።

በማግሥቱ ፡ ጧትም ፡ ከሁሉ ፡ ነገር ፡ አስቀድሞ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ አለ ፡ ወይ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ። ለጥያቄውም ፡ መልስ ፡ በባርኔጣ ፡ ቅርጽ ፡ የተጠቀለለ ፡ የወረቀት ፡ መልዕክት ፡ ተቀበለ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ወረቀቱን ፡ ጸሐፊው ፡ ጮኽ ፡ ብሎ ፡ ያንብ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ። የወረቀቱ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነበር ፤

« ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፤

ውሻ ፡ ጠባቂዎን ፡ ፓራሞሽካን ፡ ይቅርታ ፡ እንዲጠይቀኝ ፡ ካላዘዙት ፡ በስተቀር ፡ ወደ ፡ ፖክሮቭስኮዬ ፡ ለመመለስ ፡ አልሻም ። የምቀጣውና ፡ ምሕረት ፡ የማደርግለትም ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ ነኝ ። ገባሮችዎም ፡ ሆነ ፡ እራስዎ ፡ እንዲስቁብኝ ፡ አልፈቅድም ። ጥንታዊ ፡ ስም ፡ የያዝኩ ፡ ባላባት ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ መሣቂያ ፡ አይደለሁም ።

ታዛዥ ፡ አሽከርዎ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ።»

በዘመኑ ፡ የትህትና ፡ ሥርዓት ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ የብልግና ፡ ደብዳቤ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ ያናደደው ፡ የደብዳቤው ፡ ቃልና ፡ ያጻጻፉ ፡ ሥርዓት ፡ ሳይሆን ፡ በውስጡ ፡ የሰፈረው ፡ ሐሳብ ፡ ነው ።

«ምን! » ሲል ፡ እንደነጐድጓድ ፡ ጮኸና ፡ ካልጋው ፡ ውስጥ ፡ ባዶ ፡ እግሩን ፡ ዘሎ ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ዱብ ፡ አለ ። «እኔ ፡ አሽከሮቼን ፡ ይቅርታ ፡ እንዲጠይቁት ፡ ወደርሱ ፡ ልኬ ፡ እርሱ ፡ ሊቀጣና ፡ ሊምራቸው ፡ ነው! ምን ፡ ማለቱ ፡ ነው? ከማን ፡ ጋር ፡ ሊጣላ ፡ እንደሚፈልግ ፡ ያውቃል? ቆይ ፡ እሳየዋለሁ ... ኋላ ፡ ይጸጸተዋል ። ከኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጋር ፡ ሰይፍ ፡ መማዘዝ ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ ያያል ።»

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ልብሱን ፡ ለበሰና ፡ በተለመደው ፡ ኩራቱ ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡ አደኑ ፡ ሳይሳካለት ፡ ቀረ ። ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ያዩት ፡ አንድ ፡ ጥንቸል ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እሷንም ፡ ሳቷት ። በሜዳው ፡ ላይ ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ የተዘጋጀውም ፡ ምሳ ፡ እንደዚሁ ፡ ሳይቀጣ ፡ ቀረ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ምግቡ ፡ ስላልጣፈጠው ፡ ወጥ ፡ ቤቱን ፡ ደበደበው ። እንግዶቹንም ፡ አስቀየመ ። ሆኖ ፡ ብሎም ፡ ከአደን ፡ ሲመለስ ፡ ከነጭፍሮቹ ፡ በዱብሮቭስኪይ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አለፈ ።

ይህ ፡ ከሆነ ፡ ብዙ ፡ ቀናት ፡ አለፉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ ጐረቤቶች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጠብ ፡ ሳይበርድ ፡ ቀረ ። አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ወደ ፡ ፖክሮቭስኮዬ ፡ መሄዱን ፡ ተወ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ የዱብሮቭስኪይ ፡ መጥፋት ፡ ከልብ ፡ ቅር ፡ አሰኘው ። ንዴቱ ፡ እንዲወጣለትም ፡ ብዙ ፡ የስድብ ፡ ቃል ፡ መናገር ፡ ጀመረ ። የሰፈሩ ፡ ሰዎችም ፡ ነገሩን ፡ እየለወጡና ፡ እያባባሱ ፡ ለዱብሮቭስኪይ ፡ ነገሩት ። ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ጨርሶ ፡ እንዳይታረቁ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ሌላ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ተወለደ ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ መሬቱን ፡ እየ
ተዘዋወረ ፡ ሲመለከት ፡ የቤሬዛ ፡ ዛፎች ፡ ወዳሉበት ፡ ተጠጋ ።
በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዛፍ ፡ የሚቆርጥ ፡ የመጥረቢያ ፡ ድምጽ ፡ አዳ
መጠ ። ወዲያውም ፡ አንድ ፡ ዛፍ ፡ ተጠርምሶ ፡ ሲወድቅ ፡ ሰ
ማ ። ሰረገላ ፡ ነጂውንም ፡ ዛፉ ፡ ወደወደቀበት ፡ ቦታ ፡ በፍጥ
ነት ፡ እንዲነዳ ፡ አዘዘውና ፡ ወደ ፡ ቦታው ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡
ከፖክሮቭስኰዬ ፡ የመጡ ፡ ባላገሮች ፡ የቤሬዛ ፡ ዛፉን ፡ ሲ
ሰርቁ ፡ አገኛቸው ። እነሱም ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡
እግሬ ፡ አውጭኝ ፡ ብለው ፡ ሸሹ ። ዱብሮቭስኪይና ፡ ሰረገ
ላ ፡ ነጂው ፡ ሁለቱን ፡ እንደምንም ፡ ብለው ፡ ያዟቸውና ፡ ጥ
ፍር ፡ አድርገው ፡ አስረው ፡ ወደቤቱ ፡ ጓሮ ፡ ወሰዷቸው ።
ሦስቱ ፡ የጠላት ፡ ፈረሶችም ፡ እንደዚሁ ፡ ባሸናፊዎቹ ፡ እ
ጅ ፡ ተያዙ ። ዱብሮቭስኪይ ፡ በነገሩ ፡ እጅግ ፡ ተናደደ ። የ
ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ አሽከሮች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስመ ፡ ጥፉ ፡
ሰዎች ፡ ቢሆኑም ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ የጌታቸው ፡ ወዳጅ ፡ መ
ሆኑን ፡ ስለሚያውቁ ፡ በእርስቱ ፡ ላይ ፡ የተንኰል ፡ ተግባር ፡
ለመፈጸም ፡ ደፍረው ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። ይህን ፡ የተንኰል ፡
ተግባር ፡ የፈጸሙት ፡ የሁለቱን ፡ መጣላት ፡ ምክንያት ፡ አ
ድርገው ፡ መሆኑን ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ተገነዘበ ። ስለዚህ ፡ የ
ጦርነትን ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ጥሶ ፡ ከሠረቁት ፡ ግንድ ፡ ዱላ ፡
እንዲቀምሱና ፡ ፈረሶቹም ፡ እንደራሱ ፡ ፈረሶች ፡ እንዲሠሩ ፡
አደረገ ።

የዚህ ፡ ነገር ፡ ወሬ ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡ እኪሪላ ፡ ፔትሮቪ
ች ፡ ጆሮ ፡ ደረሰ ። እጅግ ፡ ስለተቆጣና ፡ ስለተናደደም ፡ ኪ
ስቴኖቭካ ፡ የተባለውን ፡ የገጠር ቤቱን ፡ እርስት ፡ ከመላው ፡ ገ
ባሮቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ለመውረርና ፡ ለመደምሰስ ፡ ባለቤቱንም ፡
ለማሰር ፡ ቆርጦ ፡ ተነሣ ። እንዳሰበው ፡ ለማድረግም ፡ የሚ
ችል ፡ ሰው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ ሐሳቡ ፡ ሌላ ፡
አቅጣጫ ፡ ያዘ ።

በታላቅ ፡ መኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ወዲያና ፡
ወዲህ ፡ እየተመላለሰ ፡ ሐሳቡን ፡ ሲያወጣና ፡ ሲያወርድ ፡ በ
ሦስት ፡ ፈረሶች ፡ የሚሳብ ፡ ሰረገላ ፡ ወደአጥር ፡ ግቢው ፡ በር ፡
ሲደርስ ፡ በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ እንዳጋጣሚ ፡ አየ ፤ ከሰረገላው
ም ፡ ውስጥ ፡ የቆዳ ፡ ቆብ ፡ ያጠለቀና ፡ የተሸለመለመ ፡ ካፖርት ፡
የለበሰ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ሰው ፡ ወጥቶ ፡ የእልፍኝ ፡ አስከልካ
ዩ ፡ ወደሚኖርበት ፡ ክፍል ፡ አመራ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡
ይህ ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ሻባሽኪን ፡ መሆኑን ፡ ስላ
ወቀ ፡ አስጠራው ። ከአንድ ፡ ደቂቃ ፡ በኋላም ፡ ሻባሽኪን ፡
እኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ በታላቅ ፡ አክብሮትና ፡
ትህትና ፡ እየደጋገመ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

« እንዴት ፡ አደርክ ። ስምህ ፡ ማን ፡ ነው? የመጣኸው
ስ ፡ ለምን ፡ ጉዳይ ፡ ነው? » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጠየቀው ።

« የምሄደው ፡ ወደከተማ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ከክቡር
ነትዎ ፡ የተሰጠ ፡ ትዕዛዝ ፡ እንዳለ ፡ በማለት ፡ እግረ ፡ መንገ
ዴን ፡ ኢቫን ፡ ዴምያኖቭን ፡ ለመጠየቅ ፡ ጉራ ፡ አልኩ ፡ »
ሲል ፡ መለሰ ።

« የመጣኸው ፡ ልክ ፡ በተፈለገው ፡ ሰዓት ፡ ነው ። ስም
ህ ፡ ማን ፡ ነው? በል ፡ ቮድካ ፡ እየጠጣህ ፡ የምነግርህን ፡ ስ
ማ ። »

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ያክብሮት ፡ አቀባበል ፡ ሕግ ፡ አስከባ
ሪውን ፡ እጅግ ፡ አስደሰተው ። የተጋበዘውን ፡ ቮድካ ፡ አል
ጠጣም ፡ በማለት ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ ለማ
ዳመጥ ፡ ተቀመጠ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጀመረ ፤ « አን
ድ ፡ ፍሬ ፡ ርስት ፡ ያለው ፡ ባለጌ ፡ ጐረቤት ፡ አለኝ ። እርስ
ቱን ፡ ልነጥቀው ፡ እፈልጋለሁ ። ታዲያ ፡ ምን ፡ ይመስልሃ
ል? »

« ክቡር ፡ ሆይ ፤ ወረቀቶች ፡ አሉን? ወይስ ፡ … »



ፑሽኪን ፡ የጻፈው ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ። በወረቀቱ ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ባለቅኔው ፡ ራሱ ፡ የሣለው ፡ የታህሣስ ፡ አድመኞች ፡ ስቅላትና ፡ « እኔም ... በቻልሁ ፡ ነበር » የሚል ፡ ቃላት ፡ ነው ( ፲፰፻፳፮ ዓ. ም. ) ።



በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ ፲፰፻፳፭ ዓ.ም. በፒተርስበርግ ፡ ከተማ ፡ በሴናት ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡
የተደረገው ፡ አድማ ።



ባለቅኔ ፡ የሙዚቃ ፡ ደራሲና ፡ ዘፋኝ ፡ የነበረችው ፡ ዚናኢዳ ፡ ቮልኮንስካያ ።

« ወዳጄ ፡ ምንም ፡ ወረቀት ፡ የለ ። የትዕዛዝ ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድነው ፡ ታዲያ? ዓላማችን ፡ እኮ ፡ እርስቱን ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ለመንጠቅ ፡ ነው ። ቆየኝ! ቆየኝ! ይህ ፡ እርስት ፡ የኛ ፡ ነበር ። የገዛነውም ፡ ስፒፂን ፡ ከተባለ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ለዱብሮቭስኪይ ፡ አባት ፡ ተሸጠ ። እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ማውጣት ፡ አይቻልም? »

« አዬ ፡ እንጃ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ። መሬቱ ፡ የተሸጠው ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ይሆናል ። »

« ወዳጄ ፡ እስቲ ፡ አስብና ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ ፈልግ ። »

« ለምሳሌ ፡ ከቡርነትዎ ፡ እርስቱ ፡ የሰውዬው ፡ መሆኑን ፡ የሚያረጋግጠውን ፡ ደብዳቤ ፡ እንደምንም ፡ ከጐረቤትዎ ፡ ማግኘት ፡ ቢችሉ ፡ እንኳ ፡ ይሆን ፡ ነበር ። »

« እሱስ ፡ ይገባኛል ። ክፋቱ ፡ ግን ፡ በእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ምክንያት ፡ ወረቀቶቹ ፡ ሁሉ ፡ አብረው ፡ ነደዱ ። »

« ምን ፡ አሉ ፡ ክቡር ፡ ሆይ! ወረቀቶቹ ፡ ተቃጥለዋል? ከዚህ ፡ የተሻለማ ፡ ምን ፡ አለ! ይህ ፡ ከሆነማ ፡ ሕገኛውን ፡ መንገድ ፡ እንከተላለን ። እርስዎም ፡ ያሰቡት ፡ ሁሉ ፡ ይፈጸምልዎታል ። »

« ይመስልሃልን? ስማ ፡ ወዳጄ ፤ እንግዲህ ፡ ባንተ ፡ መተማመኔ ፡ ነው ። ወሮታህንም ፡ እንደምንከፍልህ ፡ እመነኝ ። »

ሻባሽኪን ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነሣና ፡ ተሰናበተ ። ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮም ፡ ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ተግቶ ፡ ይከታተል ፡ ስለነበረ ፡ ልክ ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ የኪስቴኞቭካን ፡ መንደር ፡ ይዞ ፡ ለመቀመጥ ፡ የሚያስችለውን ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ በፍጥነት ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ካቅራቢያው ፡ ከተማ ፡ ትዕዛዝ ፡ ደረሰው ።

አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይም ፡ በዚህ ፡ ጥያቄ ፡ እጅግ ፡ ስለተደነቀ ፡ የኪስቴኞቭካን ፡ መንደር ፡ አባቱ ፡ ሲሞት ፡ በሕግ ፡ እንደወረሰውና ፡ በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ኪሪላ ፡ ፔት

ሮቪች ፡ እንደማያገባው ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ይሆን ፡ እርስቱን ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ቢል ፡ ለማጭበርበር ፡ መሆኑን ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡ የቁጣ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ገለጸ ።

ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ ሻባሽኪንን ፡ እጅግ ፡ አስደሰተው ። አንደኛ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ነገር ፡ አዋቂ ፡ አለመሆኑን ፡ ሁለተኛም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ግልፍተኛና ፡ ችኩል ፡ ሰው ፡ እወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ ለማስገባት ፡ ቀላል ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘበ ።

ኋላ ፡ ግን ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ከሕግ ፡ አስከባሪው ፡ የተላከለትን ፡ ደብዳቤ ፡ እንደገና ፡ በርጋታ ፡ ሲያነበው ፡ ለጥያቄው ፡ ዝርዝር ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ስለተገነዘበ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ቢጤ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ። ሆኖም ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ ።

ጉዳዩ ፡ እየተጓተተ ፡ ሄደ ። አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይም ፡ ዕውነትን ፡ የተመረኰዝኩ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ስላመነ ፡ ጉዳዩ ፡ እምብዛም ፡ አላሰጋውም ፡ ነበር ። ገንዘቡን ፡ ለመርጨትም ፡ ፍላጐትም ፡ ሆነ ፡ ችሎታ ፡ አልነበረውም ። ሕሊና ፡ ቢሶቹን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ለመናቅ ፡ የመጀመሪያ ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ እርሱ ፡ እራሱ ፡ እወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገባ ፡ አልተገነዘበውም ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ የጀመረው ፡ ጉዳይ ፡ ይፈጸም ፡ አይፈጸም ፡ እጅግም ፡ አላሰበበትም ፡ ነበር ። ሻባሽኪን ፡ ግን ፡ በኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ዳኞቹን ፡ በማስፈራራትና ፡ ጉቦ ፡ በመስጠት ፡ ሕጉንም ፡ በሚስማማው ፡ መንገድ ፡ በመተርጐም ፡ ጉዳዩን ፡ መከታተሉን ፡ ቀጠለ ። በመጨረሻ ፡ በከሳሹ ፡ በጀኔራል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችና ፡ በተከሳሹ ፡ በሌተና ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ የርስት ፡ ክርክር ፡ ውሳኔውን ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እንዲሰማና ፡ መስማማትና ፡ አለመስማማቱንም ፡ እንዲፈርም ፡ የካቲት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻… ዓ ፡ ም ፡ ከወረዳው ፡ ባለሥልጣን ፡ ጥሪ ፡ ደረሰው ። ዱብሮቭ

ስኪይም ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄደ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ቀድሞት ፡ አለፈ ። ሲተላለፉም ፡ በኩራት ፡ ተያዩ ። ዱብሮቭስኪይ ፡ በጠላቱ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የክፋት ፡ ፈገግታ ፡ ተመለከተ ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ከአንዱ ፡ ነጋዴ ፡ ወዳጁ ፡ ቤት ፡ እከተማ ፡ አድሮ ፡ በማግሥቱ ፡ እወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀረበ ። ከቁም ፡ ነገር ፡ የቆጠረው ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ወዲያውኑ ፡ ተከታትሎ ፡ ሲገባ ፡ ግን ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ ሁሉ ፡ የላባ ፡ ብዕራቸውን ፡ እጆሮአቸው ፡ ላይ ፡ ሻጥ ፡ እያደረጉ ፡ ተነሱ ። የፍርድ ፡ ቤቱም ፡ አባሎች ፡ በታዛዥነት ፡ እጅ ፡ ነሱት ። ማዕርጉንና ፡ ዕድሜውን ፡ የሰውነቱንም ፡ ግዙፍነት ፡ በማክበር ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ ወንበር ፡ አቀረቡለት ። በተከፈተው ፡ በር ፡ አጠገብም ፡ ተቀመጠ ። አንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ ግን ፡ ግድግዳውን ፡ ተደግፎ ፡ ቆመ ። ጸሐፊው ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ውሳኔ ፡ በዜማ ፡ ድምጽ ፡ ሲያነብም ፡ አካባቢው ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

ውሳኔውንም ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ፈረሙ ። ጸሐፊው ፡ አንብቦ ፡ ሲቀመጥ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ተነሣና ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ በመንሳት ፡ መዝገቡን ፡ እንዲፈርም ፡ አቀረበለት ። ረቺው ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ የላባ ፡ ብዕሩን ፡ ተቀበለና ፡ የልቡ ፡ ስለሞላለት ፡ በደስታ ፡ ፈረመ ።

ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ የዱብሮቭስኪይ ፡ ተራ ፡ ሆነ ። ጸሐፊው ፡ መዝገቡን ፡ አቀረበለት ፤ ዱብሮቭስኪይ ፡ ግን ፡ እራሱን ፡ እንደደፋ ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ቆመ ።

ጸሐፊው ፡ አሁንም ፡ መዝገቡን ፡ አቅርቦ ፡ መስማማት
ና ፡ አለመስማማቱን ፡ እንዲፈርም ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡
ያላሰበው ፡ ነገር ፡ አምጥቶ ፡ ፍርድ ፡ ለኔ ፡ ይገባኛል ፡ የሚል ፡ ከ
ሆነ ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅድለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ለበላይ ፡ ባለሥል
ጣን ፡ ይግባኝ ፡ ለማለት ፡ ማሰቡን ፡ እንዲገልጽ ፡ ጠየቀው ።

ዱብሮቭስኪይ ፡ ግን ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ አልተናገረ ።
ድንገት ፡ እራሱን ፡ ቀና ፡ አደረገ ፤ ዓይኑንም ፡ አፈጠጠ ።
መሬቱንም ፡ በኃይል ፡ ረገጠና ፡ ጸሐፊውን ፡ ቢገፋው ፡ ባፍ ፡
ጢሙ ፡ ተደፋ ። የቀለም ፡ ቢልቃጡንም ፡ አንስቶ ፡ ወደ ፡ ሕ
ግ ፡ አስከባሪው ፡ ወረወረው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተ
ደናገጠ ።

« እንዴት! የእግዜር ፡ ቤት ፡ ሊረክስ ፡ ይገባልን? » ሲል ፡
በጩኸት ፡ ተናገረ ፡ « እናንት ፡ የተረገማችሁ ፡ ትውልዶች ፡
ውጡ! » ወደ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፤ « አዳ
ኞች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መቅደስ ፡ ውሻ ፡ ይዘው ፡
ሲገቡ ፡ ማን ፡ አይቶ ፡ ያውቃል? ክቡር ፡ ሆይ ፡ በቤተ ፡ መቅ
ደሱ ፡ ውስጥ ፡ ውሾች ፡ እንዴት ፡ ይሯሯጡበት! ቆይ ፡ አ
ሳያችኋለሁ! » በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዘበኞቹ ፡ ጩኸቱን ፡ ስለሰሙ ፡
ወደፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ገስግሰው ፡ በመግባት ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡
ከብዙ ፡ ችግር ፡ በኋላ ፡ ጥርቅም ፡ አድርገው ፡ ያዙት ። ወደ
ውጭ ፡ አውጥተውም ፡ እሰረገላው ፡ ላይ ፡ አሳፈሩት ። ኪሪ
ላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ በመላው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ ታጅ
ቦ ፡ ወጣ ። ዱብሮቭስኪይ ፡ በድንገት ፡ መናደዱና ፡ አዕምሮው
ን ፡ መሣቱ ፡ ለመርታት ፡ የነበረውን ፡ ዕድል ፡ አበላሸበት ፤ ሐ
ሳቡንም ፡ መረዘበት ። ዳኞቹ ፡ ስለመልካም ፡ አገልግሎታቸው ፡
ከኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ የምሥጋና ፡ ቃል ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።
እርሱ ፡ ግን ፡ አንድም ፡ በጎ ፡ ቃል ፡ ሳይናገር ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡
ወደ ፡ ፖክሮቭስኰዬ ፡ አመራ ። በዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡
አልጋ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ተኛ ። የሰፈሩም ፡ ሐኪም ፡ ፍጹም ፡

ደንቆሮ ፡ ስላልነበረ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ እየበጣና ፡ ባልቅትና ፡ በስፓኝ ፡ ዝምብም ፡ ገላውን ፡ እያስመጠጠ ፡ አከመው ። ሲመሽም ፡ ሕመምተኛው ፡ ጥቂት ፡ ተሻለውና ፡ ነፍሱን ፡ አወቀ ። በማግሥቱም ፡ ወደ ፡ ኪስቴኖቭካ ፡ መንደር ፡ ወሰዱት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ ካሁን ፡ ወዲያ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሊቆጥረው ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

ጊዜው ፡ እያለፈ ፡ ሄደ ። አሳዛኙ ፡ ዱብሮቭስኪይም ፡ ጤናው ፡ ሳይመለስለት ፡ ቀረ ። እርግጥ ፡ ነው ፡ አለቅጥ ፡ መናደዱ ፡ ትቶት ፡ ነበር ። ግን ፡ ኃይሉ ፡ እየደከመ ፡ ሄደ ፤ ሥራውንም ፡ ተወ ። ከክፍሉ ፡ ሳይወጣም ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ በሐሳብ ፡ ባሕር ፡ ሰምጦ ፡ ይቆይ ፡ ነበር ። የልጁ ፡ሞግዚት ፡ የነበረች ፡ የጐሮቭና ፡ የምትባል ፡ ደግ ፡ ሴት ፡ አሁን ፡ የርሱ ፡ የራሱ ፡ ሞግዚት ፡ ሆነች ። እንደ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ እየተጠነቀቀችለት ፡ የሚበላበትንና ፡ የሚተኛበትን ፡ ሰዓት ፡ ታስታውሰው ፡ ነበር ። መግባም ፡ ታስተኛው ፡ ነበር ። አንድሬይ ፡ ዱብሮቭስኪይም ፡ በትህትና ፡ ይታዘዛት ፡ ነበር ። ከሌላም ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አይነጋገርም ፡ ነበር ። ስለንብረቱ ፡ ለማሰብና ፡ ለማዘዝም ፡ አለመቻሉን ፡ የጐሮቭና ፡ ባስተዋለች ፡ ጊዜ ፡ ለልጁ ፡ ለዱብሮቭስኪይ ፡ ማስታወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘበች ። ልጁ ፡ በፔቴርቡርግ ፡ በሚገኝ ፡ የምድር ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ መኰንን ፡ ነው ። ከሂሳብ ፡ ደብተር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ገጽ ፡ ቀዳ ፡ አወጣችና ፡ ሃሪቶን ፡ ለተባለው ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ ቃሉን ፡ አጻፈች ። በኪስቲኖቭካ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ማንበብና ፡ መጻፍ ፡ የሚችል ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ያንኑ ፡ ዕለትም ፡ ደብዳቤውን ፡ ወደከተማ ፡ ፖስታ ፡ ቤት ፡ ላከችው ።

አሁን ፡ አንባቢው ፡ ከታሪኩ ፡ ዕውነተኛ ፡ ጀግና ፡ ጋር ፡ መተዋወቅ ፡ አለበት ።

ቭላዲሚር ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ያደገው ፡ በጦር ፡ መኰንን ፡ ማሰልጠኛ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ነው ። ትምህርቱን ፡ እንደጨረሰም ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ መኰንን ፡ ሆነ ። አባቱ ፡ ለልጁ ፡ ምቾትና ፡ ድሎት ፡ ቅር ፡ የማይለው ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ከቤቱ ፡ የሚላክለት ፡ ገንዘብ ፡ ልጁ ፡ ካሰበው ፡ በላይ ፡ ነበር ። እጅግ ፡ ከመንደላቀቁም ፡ የተነሣ ፡ ማንኛውም ፡ የሥጋዊ ፡ ደስታ ፡ አይቀረውም ፡ ነበር ። ስለወደፊቱ ፡ ጊዜ ፡ ባለማሰብም ፡ ቁማር ፡ እየተጫወተ ፡ እብዙ ፡ እዳ ፡ ውስጥ ፡ ይገባ ፡ ነበር ። ይህንንም ፡ የሚያደርገው ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ባለጸጋ ፡ ሚስት ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ምኞት ፡ መቸም ፡ በደኃ ፡ ወጣት ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ አያሌ ፡ መኰንኖች ፡ እመኖሪያ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ተሰብስበው ፡ እሶፋው ፡ ላይ ፡ ሲዝናኑና ፡ ሲጋራ ፡ ሲያጨሱ ፡ የቭላዲሚር ፡ ሎሌ ፡ ግሪሻ ፡ አንድ ፡ ደብዳቤ ፡ አምጥቶ ፡ ሰጠው ፤ ጽሕፈቱና ፡ ማህተሙም ፡ ወጣቱን ፡ ልጅ ፡ አስደነገጠው ። ወዲያው ፡ ደብዳቤውን ፡ ከፈተና ፡ የሚቀጥለውን ፡ ቃል ፡ አነበበ ።

« ጌታችን ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ሆይ ፤ እኔ ፡ አሮጊት ፡ ሞግዚትህ ፡ ስለ ፡ አባትህ ፡ ጤንነት ፡ ልገልጽልህ ፡ ደፈርኩ ። ጌቶች ፡ ክፉኛ ፡ ታመዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አነጋገራቸው ፡ የተዘባረቀ ፡ ነው ። እንደ ፡ ሕፃን ፡ ልጅም ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ተቀምጠው ፡ ይውላሉ ። መሞትና ፡ መሰንበት ፡ ግን ፡ የግዜር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። ፈጣን ፡ አሞራ ፡ ሆይ ፡ ናልን ፡ ወደኛ ። እስከ ፡ ፔሶችኖዬ ፡ ድረስ ፡ ፈረሶች ፡ እንልክልሃለን ። እንደምንሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠን ፡ ነው ፡ ይባላል ። ካሁን ፡ ወዲያም ፡ የሱ ፡ ነን ፡ ይላሉ ። እኛ ፡ ግን ፡ ምንጊዜም ፡ ቢሆን ፡

ያንተ ፡ አገልጋዮች ፡ ነን ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገርም ፡ ከቶ ፡ ሰ ምተን ፡ አናውቅም ። አንተ ፡ በፔቴርቡርግ ፡ ስለምትኖር ፡ ለቈማሩ ፡ አቤት ፡ ለማለት ፡ ትችላለህ ። እንዲህ ፡ ስንበደል ፡ ዝም ፡ አይልም ።

አሪና ፡ የገሮሮቭና ፤ ታዛዥ ፡ ሞግዚትህና ፡ ባሪያህ ።

ለግሪሻ ፡ የናትነት ፡ ሰላምታዬን ፡ አቀርባለሁ ። በሚገ ባ ፡ ያገለግልሃልን? እኛ ፡ ጋ ፡ ዝናብ ፡ ሲዘንብ ፡ ይሄው ፡ ከ ሳምንት ፡ በላይ ፡ ሊሆን ፡ ነው ። ከብት ፡ እረኛው ፡ ሮዲያም ፡ በቅዱስ ፡ ኒኮላዎስ ፡ አጥቢያ ፡ ሞተ ። »

ቭላዲሚር ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ እጅግም ፡ ግልጽ ፡ ያልሆ ኑትን ፡ መስመሮች ፡ በጥልቅ ፡ ስሜት ፡ ደጋግሞ ፡ ደጋግ ሞ ፡ አነበባቸው ። እናቱ ፡ የሞተችበት ፡ ገና ፡ በሕፃንነቱ ፡ ሲ ሆን ፡ ወደፔቴርቡርግ ፡ የተላከውም ፡ በስምንት ፡ ዓመቱ ፡ ነበር ። አባቱንም ፡ እምብዛም ፡ አያውቅም ። ሆኖም ፡ ጥልቅ ፡ ያባት ፡ ፍቅር ፡ ነበረው ። ከቤተሰብ ፡ ኑሮ ፡ ተነጥሎ ፡ በመቆ የቱም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ኑሮ ፡ እጅግ ፡ ይናፍቅና ፡ ይወ ድ ፡ ነበር ።

አባቱን ፡ የማጣት ፡ ነገር ፡ ክፉኛ ፡ አስቀቀው ። ከሞግ ዚቱ ፡ ደብዳቤ ፡ ሊረዳው ፡ የቻለውም ፡ የምስኪን ፡ አባቱ ፡ ሁናቴ ፡ እጅግ ፡ አሳዘነው ። አባቱ ፡ ባንድ ፡ በሩቅ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ወድቆና ፡ ባንድ ፡ ቂል ፡ አሮጊት ፡ ሴትና ፡ አሽከሮች ፡ እጅ ፡ ተይዞ ፡ ከባድ ፡ አደጋም ፡ ደርሶበት ፡ በሥጋና ፡ በመን ፈስ ፡ እየተሰቃየ ፡ ሲመነምን ፡ በዓይነ ፡ ሕሊና ፡ ተመለከተው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቭላዲሚር ፡ እራሱን ፡ እንደ ፡ ወንጀለኛ ፡ ቆ ጥሮ ፡ ነቀፈ ። ከአባቱ ፡ ደብዳቤ ፡ ከደረሰው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። እርሱ ፡ ግን ፡ ምናልባት ፡ አባቴ ፡ ላደን ፡ ወደሩ ቅ ፡ ቦታ ፡ ሄዶ ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ የርስቱን ፡ ጉዳይ ፡ ያጠ ናቅቅ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ሳይጠይቅ ፡ ቀረ ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ ወደአባቱ ፡ ለመሄድ ፡ ቆረጠ ። ያባቱ ፡ ጤ

ንነት ፡ የርሱን ፡ በቅርብ ፡ መገኘት ፡ የሚጠይቅ ፡ ከሆነም ፡ ከጦር ፡ መኰንንነቱ ፡ ጨርሶ ፡ ለመሰናበት ፡ ወሰነ ። ጓደኞቹ ፡ መጨነቁን ፡ ሲያዩ ፡ ትተውት ፡ ሄዱ ። ቭላዲሚርም ፡ ብቻውን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የማመልከቻ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈና ፡ ሲጋራውን ፡ አቀጣጥሎ ፡ በሐሳብ ፡ ባሕር ፡ ሰመጠ ። ያንኑ ፡ ዕለትም ፡ ማመልከቻውን ፡ አስገባና ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደመንገደኞች ፡ ጣቢያ ፡ አመራ ።

ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ወደኪስቴኞቭካ ፡ ወደሚወስደው ፡ የመንገደኞች ፡ ጣቢያ ፡ ሲደርስ ፡ ልቡ ፡ በሐዘንና ፡ በትካዜ ፡ ተመላ ። ምናልባት ፡ አባቱን ፡ በሕይወት ፡ አላገኘው ፡ ይሆናል ፡ በማለትም ፡ ፍርሃት ፡ አደረበት ። በገጠር ፡ የሚጠብቀው ፡ አስተካከዥ ፡ ኑሮም ፡ በአእምሮው ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ሥዕል ፡ ተነድፎ ፡ ይታየው ፡ ጀመር ። እርቀቱ ፤ ብቸኝነቱ ፤ ድህነቱና ፡ ያልለመደው ፡ የርስት ፡ አጠባበቅ ፡ ጉዳይ ፡ በሐሳቡ ፡ ተሰብስቦ ፡ መጣ ። እጣቢያው ፡ እንደደረሰ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ሹሙ ፡ ጋ ፡ ሄዶ ፡ ፈረሶች ፡ ጠየቀ ። ሹሙም ፡ የሚሄድበትን ፡ ቦታ ፡ ከጠየቀው ፡ በኋላ ፡ ከኪስቴኞቭካ ፡ የመጡ ፡ ፈረሶች ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ እሱን ፡ ሲጠብቁ ፡ እንደቆዩ ፡ ገለጸለት ። ወዲያውኑም ፡ የዱሮ ፡ ሰረገላ ፡ ነጂው ፡ አንቶን ፡ ብቅ ፡ አለ ። ቭላዲሚርን ፡ በልጅነቱ ፡ ወደፈረስ ፡ ጋጣ ፡ ይዞት ፡ ይሄድ ፡ የነበረውና ፡ ትንሽ ፡ ፈረሱንም ፡ ይጠብቅለት ፡ የነበረው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ነበር ። አንቶን ፡ ቭላዲሚርን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እንባው ፡ ወረደ ። እመሬት ፡ ላይ ፡ ተደፍቶም ፡ አባቱ ፡ በሕይወት ፡ መኖራቸውን ፡ ነገረውና ፡ ፈረሶቹን ፡ ለመጫን ፡ እሮጦ ፡ ወጣ ። ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪችም ፡ የቀረበለትን ፡ ቁርስ ፡ አልበላም ፡ ብሎ ፡ በችኰላ ፡ ጉዞውን ፡ ቀጠለ ። አንቶን ፡ ሰረገላውን ፡ በገጠር ፡ መንገድ ፡ እየነዳ ፡ ሲሄድ ፡ እግረመንገዳቸውን ፡ ጨዋታ ፡ ጀመሩ ።

« ባባቱና ፡ በኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ክ
ስ ፡ ምንድነው ፡ አንቶን? »

« እግዜር ፡ ይወቅ ፡ ጌታዬ ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪ
ች ። እንደሚሉትማ ፡ ጌቶች ፡ ከኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጋር ፡
ተጣሉና ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሰሳቸው ።
ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ እርሱ ፡ እራሱ ፡ እንደ ፡ ዳኛ ፡ ነው ።
አሽከር ፡ በጌታው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ የለበትም ፡
እንጂ ፡ እንደኔ ፡ ቢሆን ፡ ጌቶች ፡ አባትዎ ፡ ከኪሪላ ፡ ፔትሮ
ቪች ፡ ጋር ፡ መጣላት ፡ የለባቸውም ፡ ነበር ። ጨርሶ! ድንጋ
ይና ፡ ቅል ፡ አቻ ፡ ላቻ ፡ አይደሉም ። »

« እህ! ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ የፈቀደውን ፡ ሁሉ ፡ ማድረ
ግ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ። »

« አዎን ፡ ጌታዬ ። ሌላው ፡ ቀርቶ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪውን ፡
እንኳ ፡ ከጤፍ ፡ አይቆጥረውም ፡ ይላሉ ። የጸጥታ ፡ ዘበኞች ፡
አለቃም ፡ እንደ ፡ አሽከሩ ፡ ይታዘዝለታል ። ትልቅ ፡ የሚባሉ
ትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እየመጡ ፡ እጅ ፡ ይነሱታል ። እስከነ
ተረቱ ፡ አተላ ፡ በፈሰሰበት ፡ አሳማ ፡ አያጠፋም ። »

« እርስታችንንስ ፡ ሊወስድ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ዕው
ነት ፡ ነውን? »

« ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እንዲህ ፡ ሲባል ፡ ሰምተናል ። በቀደም ፡
ለት ፡ ባንድ ፡ የክርስትና ፡ ድግስ ፡ ላይ ፡ የፖክሮቭስኮዬ ፡
የደብር ፡ ደዋይ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤ « የመንቀባረር ፡
ጊዜአችሁ ፡ አለፈ ። እንግዲህ ፡ እኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እጅ ፡
መግባታችሁ ፡ ነው ። » በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብረት ፡ ሰሪው ፡ ሚኪ
ታ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ፡ « ምነው ፡ ምነው ፡ ሳቬሊ
ች! ለምን ፡ ወዳጆችህን ፡ ታሳዝናለህ? እንግዶቹንስ ፡ ለም
ን ፡ ታስቀይማለህ? ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ለራሱ ፡ ጌታ ፡ ነ
ው ፤ አንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪችም ፡ ቢሆን ፡ ለራሱ ፡ ጌታ ፡ ነ
ው ፤ ሁላችንም ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርና ፡ የንጉሡ ፡ ነን ።
የሰውን ፡ አፍ ፡ መለጐም ፡ አይቻልም ። »

« እሀ! እንግዲያው ፡ ትሮዬኩሮቭ ፡ ጌታችሁ ፡ እንዲሆ
ን ፡ አትፈልጉማ? »

« ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን? እግዜር ፡ አያድርገው ። የራሱ ፡ ሰዎች ፡ እንኳ ፡ መከራቸውን ፡ እንዳዩ ፡ ናቸው ። ሌሎች ፡ ሰ ዎችማ ፡ አግኝቶ ፡ እንኳንስ ፡ ሥጋቸውንና ፡ ቆዳቸውንም ፡ አይተው ። የለም! የለም! እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ የአንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪችን ፡ ጤና ፡ ይመልስልን ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከ ወሰዳቸው ፡ ካንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ጌታ ፡ አንፈልግም ። አሳ ልፈህ ፡ አትስጠን ። እኛም ፡ ምንጊዜም ፡ አንለይህም ። » ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ አለንጋውን ፡ ሾጥ ፡ ልጓሙን ፡ ሳብ ፡ አደረገ ። ፈረሶቹም ፡ ገሠገሡ ።

ሽማግሌው ፡ ሰረገላ ፡ ነጂ ፡ በተናገረው ፡ ቃል ፡ ዱብሮ ቭስኪይ ፡ ልቡ ፡ ስለተነካ ፡ ዝም ፡ አለ ። ሐሳብም ፡ ያዘው ። አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ከተጓዙም ፡ በኋላ ፡ ግሪሻ ፡ ዱብሮቭ ስኪይን ፡ ቀስቅሶ ፤ « ፖክሮቭስኮዬ ፡ ያውና! » ሲል ፡ እየ ፈነደቀ ፡ ተናገረ ። ዱብሮቭስኪይም ፡ እራሱን ፡ ቀና ፡ አደ ረገ ፤ የሚጓዙት ፡ ባንድ ፡ ሰፊ ፡ ሐይቅ ፡ አጠገብ ፡ ነበር ። ከ ዚህ ፡ ሐይቅ ፡ ውስጥ ፡ የሚመነጭ ፡ አንድ ፡ ወንዝ ፡ እየተ ጠማዘዘ ፡ ይወርድና ፡ ባሻገር ፡ ባሉት ፡ ጋራዎች ፡ መካከ ል ፡ ገብቶ ፡ ላይን ፡ ይጠፋል ። ከነዚህ ፡ ጋራዎች ፡ ባንደኛው ፡ ላይ ፡ ጥቅጥቅ ፡ ያለውን ፡ ጫካ ፡ ዘልቆ ፡ ያንድ ፡ ትልቅ ፡ የ ድንጋይ ፡ ቤት ፡ አረንጓዴ ፡ ጣራና ፡ ፎቅ ፡ ይታያል ። ባን ድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አምስት ፡ጉልላትና ፡ አንድ ፡ ጥንታ ዊ ፡ ደወል ፡ ያለው ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ቆምዋል ። በዙሪ ያውም ፡ የገበሬዎች ፡ ጎጆና ፡ የአትክልት ፡ ቦታቸው ፡ እ ንዲሁም ፡ ውኃ ፡ መቅጃቸው ፡ አለ ። ዱብሮቭስኪይ ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ ያውቀዋል ። በዚህ ፡ ጋራ ፡ ላይ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ከምታንሰው ፡ ከማሻ ፡ ትሮዬኩሮቫ ፡ ጋር ፡ ሲጫወት ፡ እን ደነበር ፡ አስታወሰ ። ያንጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እጅግ ፡ ውብ ፡ ነ

በረች ። ስለእርሷ ፡ እንቶንን ፡ ሊጠይቀው ፡ ፈለገና ፤ ድንገ
ተኛ ፡ ሐፍረት ፡ ስለያዘው ፡ ዝም ፡ አለ ።

ወደቤቱ ፡ እየተጠጉ ፡ ሲሄዱም ፡ በመናፈሻ ፡ ዛፎቹ ፡
ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ሲውለበለብ ፡ አየ ፤ ዳሩ ፡ ግ
ን ፡ በገጠርም ፡ ሆነ ፡ በከተማ ፡ ሰረገላ ፡ ነጂዎች ፡ ዘንድ ፡ ትዕ
ቢተኛነት ፡ አይጠፋምና ፡ እንቶን ፡ ፈረሶቹን ፡ ሽምጥ ፡ እንዲ
ጋልቡ ፡ ስላደረገ ፡ ድልድዩን ፡ በፍጥነት ፡ ተሻግረው ፡ መን
ደሩን ፡ አለፉ ። መንደሩን ፡ ወደኋላ ፡ ትተው ፡ ዳገቱን ፡ ሲወ
ጡም ፡ ቭላዲሚር ፡ የጥድ ፡ ዛፎች ፡ አየ ። በግራ ፡ በኩል ፡ ባ
ለው ፡ ክፍት ፡ ቦታም ፡ ቀይ ፡ ጣራ ፡ ያለው ፡ ግራጫ ፡ ቤት ፡
ተመለከተ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ በጣም ፡ ተሸበረ ። እነሆ ፡
ወደኪስቴኞቭካ ፡ መንደርና ፡ ወደአባቱ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ደረሰ ።

ካስር ፡ ደቂቃም ፡ በኋላ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።
አከባቢውንም ፡ ሊገልጹት ፡ በማይቻል ፡ ስሜት ፡ ተመለ
ከተው ። የተወለደበትን ፡ ቦታ ፡ ካየ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመ
ት ፡ አልፏል ። በልጅነቱ ፡ ጊዜ ፡ ባጥሩ ፡ ዙሪያ ፡ የተተከሉ
ት ፡ የቤሬዛ ፡ ችግኞች ፡ ዛሬ ፡ ትልልቅ ፡ ዛፎች ፡ ሆነው ፡ አ
ገኛቸው ። በሶስት ፡ ያበባ ፡ መደቦች ፡ አጊጦ ፡ የነበረው ፡
ግቢም ፡ ዛሬ ፡ አረምና ፡ ሳር ፡ የበቀለበት ፡ ሜዳ ፡ ሆኖ ፡ በው
ስጡ ፡ አንድ ፡ የታሠረ ፡ ፈረስ ፡ ሲግጥ ፡ አየ ። ውሾቹ ፡ ከ
ፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ጮኹ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንቶን ፡ መሆኑን ፡
በተመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ ጸጉራማ ፡ ጅራታቸውን ፡ እያወዛወዙ ፡
ዝም ፡ አሉ ። የቤት ፡ አሽከሮቹና ፡ ገረዶቹ ፡ ሁሉ ፡ እየሮጡ ፡
ከቤት ፡ ወጥተው ፡ ሰረገላውን ፡ ከበቡት ። ወጣቱን ፡ ጌታ
ቸውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜም ፡ ደስታቸውን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ገለ
ጹ ። ዱብሮቭስኪይም ፡ በናፍቆት ፡ በከበቡት ፡ ሰዎች ፡ መሐ
ከል ፡ እንደምንም ፡ አልፎ ፡ ተሸራርፈው ፡ ያለቁትን ፡ ደረ
ጃዎች ፡ ወጣ ። እበሩ ፡ ላይ ፡ ሞግዚቱ ፡ የጐሮቭና ፡ አንገቱ
ን ፡ ጥምጥም ፡ አድርጋ ፡ ይዛ ፡ አለቀሰች ። እርሱም ፤

« እንዴት ፡ ነሽ ፡ ሞግዚቴ? እንዴት ፡ ነሽ ፡ ሞግዚቴ?» እያለ ፡ ያሳደገችውን ፡ አሮጊት ፡ ሴት ፡ አቅፎ ፡ ያዛት ። «አባቴስ ፡ እንዴት ፡ ነው? የት ፡ አለ? ብዙ ፡ ተለውጧልን? » ብሎ ፡ ጠየቃት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ የገረጣና ፡ የመነመነ ፡ እረጅም ፡ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ የጧት ፡ ልብሱን ፡ ለብሶና ፡ የማታ ፡ ቆቡን ፡ አጥልቆ ፡ እግሮቹን ፡ በግድ ፡ እየጐተተ ፡ ወደአዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

« ቮሎዲያ ፡ መጣህን? » ሲል ፡ በደካማ ፡ ድምጽ ፡ ተናገረ ። ቭላዲሚርም ፡ አባቱን ፡ እቅፍ ፡ አድርጎ ፡ ሳመው ።

በልጁ ፡ መምጣት ፡ ሕመምተኛው ፡ ሽማግሌ ፡ የተሰማው ፡ ደስታ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ በመሆኑ ፡ ጉልበቶቹ ፡ ተብረከረኩ ። ቭላዲሚር ፡ ባይደግፈው ፡ ኑሮ ፡ ይወድቅ ፡ ነበር ።

« ለምን ፡ ተነሱ? » ስትል ፡ የጐሮቭና ፡ ጠየቀች ። « እርስዎ ፡ ለራስዎ ፡ መቆም ፡ አይችሉ ፡ እንደሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ መሮጥ ፡ ያምርዎታል ። »

ሽማግሌውን ፡ ሰው ፡ ወደመኝታ ፡ ቤቱ ፡ ወሰዱት ። ከልጁ ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሐሳቡ ፡ ስለባከነበት ፡ የሚናገረው ፡ ቃል ፡ የተዘባረቀ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ንግግሩንም ፡ አቆመ ፤ ከባድ ፡ ድካምም ፡ ተጫነው ። ቭላዲሚር ፡ አባቱን ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ሁናቴ ፡ ላይ ፡ ስላገኘው ፡ እጅግ ፡ ተደነቀ ። ማረፊያውንም ፡ እዚያው ፡ አባቱ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አድርጎ ፡ ሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲወጡና ፡ ብቻውን ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ እንዲቀር ፡ ጠየቀ ። አገልጋዮቹም ፡ ትዕዛዙን ፡ በመቀበል ፡ ግሪሻን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ማድ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። እዚያም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ያገር ፡ ቤት ፡ መስተንግዶ ፡ አደረጉለትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጥያቄ ፡ እያቀረቡ ፡ ያጫውቱት ፡ ጀመር ።

# ምዕራፍ ፡ ፲ ።

በድማሥ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡
አስከሬን ፡ ተጋድሟል ።

ወጣቱ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ እቤቱ ፡ ከገባ ፡ ከጥቂት ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ የርስቱን ፡ ጉዳይ ፡ ለመከታተል ፡ ፈለገ ። አባቱ ፡ ግን ፡ በመታመሙ ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሊሰጠው ፡ አልቻለም ። ጉዳዩን ፡ የሚከታተል ፡ ልዩ ፡ ሰውም ፡ አልነበረም ። ቭላዲሚር ፡ ያባቱን ፡ ወረቀቶች ፡ ሲመረምር ፡ ከሕግ ፡ አስከባሪው ፡ መጀመሪያ ፡ የተላከውን ፡ ማዘዣና ፡ አባቱ ፡ የሰጠውን ፡ መልስ ፡ እረቂቅ ፡ ብቻ ፡ ሊያገኝ ፡ ቻለ ። ከነዚህ ፡ ወረቀቶች ፡ ስለክሱ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ሊረዳ ፡ ስላልቻለም ፡ ትክክለኛው ፡ ፍርድ ፡ ለኛ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በመተማመን ፡ ውጤቱን ፡ ለመጠበቅ ፡ ወሰነ ።

በዚህ ፡ መካከል ፡ የአንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ ጤና ፡ በየጊዜው ፡ እየባሰ ፡ ሄደ ። ቭላዲሚር ፡ ያባቱ ፡ የመጨረሻ ፡ ሰዓት ፡ መቃረቡን ፡ ስላወቀ ፡ ካጠገቡ ፡ አልተለየውም ።

ይህ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፡ ፍርድ ፡ ይግባኝ ፡ የመጠየቂያው ፡ ጊዜ ፡ አንድም ፡ ሥራ ፡ ሳይሠራ ፡ አለፈ ። የኪስቴኞቭካ ፡ መንደር ፡ የትሮዬኩሮቭ ፡ ሆነች ፤ ሻባሽኪንም ፡ ወደኪረላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጋ ፡ ሄዶ ፡ እጅ ፡ እየነሳና ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለዎት ፡ እያለ ፡ አዲሱን ፡ እርስት ፡ እርስዎ ፡ እራስዎ ፡ ሄደው ፡ ይረከባሉ ፡ ወይስ ፡ ወኪል ፡ ይልካሉ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ። ኪረላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ግራ ፡ ገባው ። በተፈጥሮው ፡ ለሐብት ፡ የሚስገበገብ ፡ ሰው ፡ ባይሆንም ፡ ቅሉ ፡ ቂም ፡ ለመበቀል ፡ ሲል ፡ የፈጸመው ፡ ተግባር ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ መጥፎ ፡ እንደሆነ ፡ በተረዳው ፡ ጊዜ ፡ ሕሊናው ፡ ይወቅሰው ፡ ጀመር ። ጠላ

ቷ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ የልጅነት ፡ ጓደኛው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሁናቴ ፡ ላይ ፡ እንደወደቀ ፡ ስላወቀም ፡ ድል ፡ ማድረጉ ፡ ለልቡ ፡ ደስታ ፡ ሳይሰጠው ፡ ቀረ ። ሻባሽኪንን ፡ በቁጣ ፡ ዓይን ፡ እየተመለከተ ፡ እንዴት ፡ አድርጐ ፡ ሊያዋርደው ፡ እንደሚችል ፡ አሰበ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ መንገድ ፡ ስላጣ ፤

« ሂድ ፡ ጡጣ! ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ አለብኝ ፡» ሲል ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ ተናገረው ።

ሻባሽኪን ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ መቆጣቱን ፡ ሲያይ ፡ ቶሎ ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ ወጣ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተንጐራደደ ፡ እጅግ ፡ በተናደደ ፡ ጊዜ ፡ የሚያፏጨውን ፡ « የድል ፡ ነጐድጓድ ፡ ይሰማ ፡ »[25] የሚለውን ፡ ዜማ ፡ ጀመረ ።

በመጨረሻም ፡ ፈረስ ፡ እንዲጫን ፡ አዘዘና ፡ የብርድ ፡ ካፖርቱን ፡ ደርቦ ፡ ሰረገላውን ፡ እራሱ ፡ እየነዳ ፡ ሄደ ።

የአንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪችን ፡ ትንሽ ፡ ቤት ፡ ባየ ፡ ጊዜም ፡ ሕሊናው ፡ ተበጠበጠ ። መጀመሪያ ፡ የኃይለኛነትና ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ የመወጣት ፡ ሐሳብ ፡ አዕምሮውን ፡ ደፍኖት ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ሕሊናው ፡ ይከነክነው ፡ ጀመር ። ከጥንት ፡ ጐረቤቱ ፡ ጋር ፡ እንደገና ፡ እርቅ ፡ ለማድረግና ፡ ቂም ፡ በቀሉንም ፡ ደምስሶ ፡ ሐብቱን ፡ ለመመለስ ፡ ወሰነ ። ልቡን ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ በጐ ፡ ሐሳብ ፡ ካጽናና ፡ በኋላ ፡ ወደጐረቤቱ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ እየጋለበ ፡ ሂዶ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

እንዳጋጣሚ ፡ ሕመምተኛው ፡ አንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ በመኝታ ፡ ቤቱ ፡ መስኮት ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ፊቱ ፡ በቁጣ ፡ ተለወጠ ። የገረጡት ፡ ጉንጮቹ ፡ ፍም ፡ መሰሉ ። ዓይኖቹም ፡ እሳት ፡ ለበሱ ። የተዘባረቀ ፡ ቃል ፡ ተናገረ ። የሂሳብ ፡ መዝገቡን ፡ ሲመረምር ፡ የነበረው ፡ ልጁ ፡ እራሱን ፡ ቀና ፡ አድር

ጐ ፡ ሲመለከት ፡ ያባቱ ፡ በድንገት ፡ መለወጥ ፡ አስደነገጠ ው ። ሕመምተኛው ፡ ሽማግሌ ፡ በቁጣና ፡ በጥላቻ ፡ መንፈ ስ ፡ በጣቱ ፡ ወደ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ ያመለከት ፡ ጀመር ። የጧ ት ፡ ልብሱን ፡ ሰብሰብ ፡ አድርጐ ፡ ከወንበሩ ፡ ለመነሳት ፡ ብድግ ፡ ሲል ፡ ወዲያው ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ወደቀ ። ል ጁ ፡ ወደአባቱ ፡ ተንደርድሮ ፡ ሄደ ፤ የሽማግሌው ፡ ሰውነት ፡ ግን ፡ በድን ፡ ሆነ ፤ ትንፋሹም ፡ ቁርጥ ፡ አለ ፤ ልቡም ፡ ቆመ ።

« ቶሎ ፡ ወደከተማ ፡ ሂዱና ፡ ሐኪም ፡ ጥሩ! » ሲል ፡ ቭ ላዲሚር ፡ ጮኸ ።

ወዲያውኑ ፡ አንደኛው ፡ አሽከሩ ፡ ገባና ፤

« ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ይፈልጉዎታል ፡ » ሲል ፡ ነገ ረው ።

ቭላዲሚር ፡ ክፉኛ ፡ ገላመጠውና ፤

« አሽከሮቹን ፡ ልኬ ፡ ካጥር ፡ ግቢ ፡ ሳላስወጣህ ፡ በፍ ጥነት ፡ ሂድ ፡ በልና ፡ ንገረው ፡ » ሲል ፡ አዘዘው ።

አሽከሩ ፡ የታዘዘውን ፡ ለመፈጸም ፡ በቅጽበት ፡ ወጣ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የጐሮቭና ፡ እጆቿን ፡ እያርገበገበች ፤

« ጌታዬ ፡ ሆይ! እራስህን ፡ ትጐዳለህ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮ ቪች ፡ ሁላችንንም ፡ እያስተርፈንም ፡ » ስትል ፡ በለቅሶ ፡ ድ ምጽ ፡ ተናገረች ።

« ዝም ፡ በይ! ይልቁንስ ፡ አንቶንን ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ከተማ ፡ ላኪውና ፡ ሐኪም ፡ ይዞ ፡ ይምጣ ፡ » ሲል ፡ ቭላዲ ሚር ፡ በቁጣ ፡ ተናገረ ።

የጐሮቭናም ፡ ከክፍሉ ፡ ወጥታ ፡ ሄደች ።

በአዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ። አሽ ከሮቹና ፡ ገረዶቹ ፡ ሁሉ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ ለመመልከ ት ፡ ወደ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ ሄደው ፡ ነበር ። ወደ ፡ ኪረላ ፡ ፔ

ትሮቪች ፡ የተላከው ፡ አሽከር ፡ የወጣት ፡ ጌታውን ፡ መልዕ ክት ፡ ሲያደርስ ፡ የጐሮቭና ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ሆና ፡ ሰማች ። ኪ ሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ እጋሪው ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጠ ፡ መልዕ ክቱን ፡ ሲሰማ ፡ ፊቱ ፡ እንደ ፡ ጨለማ ፡ ጠቆረ ። በሃቻ ፡ ፈ ገግታና ፡ በማስፈራራት ፡ ዓይን ፡ የተሰበሰቡትን ፡ አሽከሮ ች ፡ ተመለከታቸውና ፡ በዝግታ ፡ ካጥር ፡ ግቢው ፡ ውስጥ ፡ ሠረገላውን ፡ ነድቶ ፡ ወጣ ። አንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ ካ ንድ ፡ ደቂቃ ፡ በፊት ፡ ተቀምጦበት ፡ ወደነበረውም ፡ መስኰ ት ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እንደበፊቱ ፡ ሊያ የው ፡ አልቻለም ። ሞግዚቷም ፡ ጌታዋ ፡ ያዘዛትን ፡ መልዕ ክት ፡ ረስታ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ተገትራ ፡ ቆመች ። አሽከሮቹና ፡ ገረዶቹ ፡ ስላዩት ፡ ሁናቴ ፡ እየጮኹ ፡ ሲያወሩ ፡ ቭላዲሚር ፡ ድንገት ፡ በመካከላቸው ፡ ብቅ ፡ አለና ፤

« ሐኪምም ፡ መጥራት ፡ አያስፈልግ ። አባቴ ፡ አርፏ ል ፡ » ሲል ፡ ባጭሩ ፡ ተናገረ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ተደናገጡ ። አገልጋዮቹ ፡ በሙ ሉ ፡ ወደታላቁ ፡ ጌታቸው ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ እየተንደረደሩ ፡ ገቡ ። ሽማግሌውን ፡ ጌታ ፡ ቭላዲሚር ፡ ደግፎ ፡ አስቀመጠ ው ። እወንበር ፡ ላይ ፡ ዝልፍልፍ ፡ ብሎ ፡ ወድቋል ። ቀኝ ፡ እ ጁ ፡ ቁልቁል ፡ ወደመሬት ፡ ተንጠልጥሏል ፤ እራሱም ፡ እደ ረቱ ፡ ላይ ፡ ተደፍቷል ። ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሕይወት ፡ ምል ክት ፡ አይታይበትም ። ሰውነቱ ፡ ገና ፡ ትኩስ ፡ ቢሆንም ፡ ቅ ሉ ፡ በሞት ፡ ተሸማቋል ። የጐሮቭና ፡ ይህን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ኡ!ኡ! ብላ ፡ አለቀሰች ። አገልጋዮቹም ፡ ሁሉ ፡ የጌታቸውን ፡ እሬሳ ፡ ከበው ፡ እያለቀሱ ፡ በሚገባ ፡ አጠቡና ፡ በ ፲፯፻፺፯ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ፡ አልብሰው ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ለጌታቸው ፡ ሲያሳልፉበት ፡ በነበረው ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ አጋደሙት ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ ሥርዓተ ፡ መቃብሩ ፡ ሆነ ። የምስኪኑ ፡ ሽማግሌ ፡ አስከሬን ፡ በልባስ ፡ ተሸፍኖና ፡ ዙሪያውን ፡ በሻማ ፡ ተከቦ ፡ እገበታው ፡ ላይ ፡ አረፈ ። አስከሬኑን ፡ ወደመጨረሻ ፡ ማረፊያው ፡ ቦታ ፡ ለመውሰድ ፡ የተዘጋጁ ፡ አሽከሮች ፡ የምግብ ፡ ቤቱን ፡ መሉት ። ቭላዲሚርና ፡ ሦስት ፡ አሽከሮች ፡ አስከሬኑን ፡ አነሱ ። ቄሱም ፡ ከፊት ፡ ቀድሞ ፡ መራ ። ዲያቆኑም ፡ የሥርዓተ ፡ መቃብር ፡ ዜማ ፡ እያዜመ ፡ ተከተለ ። እነሆ ፡ የኪስቴኞቭካ ፡ ጌታ ፡ ዳግመኛ ፡ የማይመለስበትን ፡ የቤቱን ፡ በር ፡ አልፎ ፡ ወጣ ። ቤተ ፡ ክርስትያኑ ፡ ባሻገር ፡ ስለነበር ፡ አስከሬኑን ፡ ተሸክመው ፡ በጫካው ፡ ውስጥ ፡ አለፉ ። ቀኑ ፡ ብሩህና ፡ ቀዝቃዛ ፡ ነበር ። ወራቱ ፡ መጸው ፡ ስለነበር ፡ ቅጠሎቹ ፡ ከዛፉ ፡ ላይ ፡ እየረገፉ ፡ ይወድቁ ፡ ነበር ።

ጫካውን ፡ ዘልቀው ፡ ሲወጡ ፡ የኪስቴኞቭካን ፡ የእንጨት ፡ ቤተ ፡ ክርስትያንና ፡ በዛፍ ፡ የታጠረውን ፡ የመቃብር ፡ ቦታ ፡ አዩ ። የቭላዲሚር ፡ እናት ፡ የተቀበረችውም ፡ እዚህ ፡ ቦታ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ የርሷ ፡ ዓጽም ፡ ባረፈበት ፡ ጐን ፡ ሌላ ፡ መቃብር ፡ ከሁለት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ተቆፍሮ ፡ ይጠብቃል ።

ጌታቸውን ፡ ለመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ለመሰናበት ፡ የመጡ ፡ ባላገሮች ፡ የኪስቴኞቭካን ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ መልተውታል ። ወጣቱ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ እመካከል ፡ ቆሟል ። አያለቅስም ፤ አይጸልይም ። ፊቱ ፡ ግን ፡ ያስፈራል ። አሳዛኙ ፡ ሥርዓተ ፡ ጸሎት ፡ ተፈጸመና ፡ አስከሬኑን ፡ ለመሰናበት ፡ መጀመሪያ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ቀረበ ። ከእርሱ ፡ በኋላም ፡ አገልጋዮቹ ፡ ቀጠሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያስከሬኑ ፡ ሣጥን ፡ በምስማር ፡ ተዘጋ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶቹ ፡ ዋይ ፡ ዋዬ! እያሉ ፡ አለቀሱ ።

ወንዶቹም ፡ እንባቸውን ፡ በመዳፋቸው ፡ ጠረጉ ። ቭላዲሚ ርና ፡ ሦስት ፡ አሽከሮቹ ፡ አስከሬኑን ፡ ተሸክመው ፡ ወደመ ቃብር ፡ ቦታው ፡ ወሰዱት ። መላው ፡ የመንደሩ ፡ ሰውም ፡ ተከትሎ ፡ ሄደ ። በመጨረሻም ፡ አስከሬኑ ፡ ወደመቃብር ፡ ወረደ ። ሰውም ፡ በፍጥኑ ፡ አፈር ፡ እያነሳ ፡ አለበሰውና ፡ ወዲ ያው ፡ ጉድጓዱ ፡ ሞላ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ የመጨረሻ ፡ ስንብቱን ፡ አቅርቦ ፡ ተበተነ ። ቭላዲሚር ፡ ከሌሎቹ ፡ ሁ ሉ ፡ ቀድሞ ፡ ሄደና ፡ ወደ ፡ ኪስቴኞቭካ ፡ ጫካ ፡ ገባ ።

የጐሮቭና ፡ በጌታዋ ፡ ስም ፡ ሆና ፡ ቀሳውስቱን ፡ ጋበ ዘቻቸው ። ወጣቱ ፡ ጌታዋ ፡ በግብዣው ፡ ላይ ፡ እንደማይገ ኝም ፡ አስታወቀቻቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እሷ ፡ መምሬ ፡ አንቶንና ፡ ባለቤታቸው ፡ ፌዶቶቭና ፡ እንዲሁም ፡ ዲያቆ ኑ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ሚቹ ፡ ጌታ ፡ ቤት ፡ በእግራቸው ፡ አመሩ ። እግረ ፡ መንገዳቸውንም ፡ ስለሟቹ ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ ጠባ ይና ፡ ስለልጁ ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ ከየጐሮቭና ፡ ጋር ፡ በሰ ፊው ፡ አወሩ ። ትሮዬኩሮቭ ፡ ወደ ፡ አንድሬይ ፡ ዱብሮቭ ስኪይ ፡ ቤት ፡ ደርሶ ፡ መመለሱን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለሰማ ፡ አንዳንዶቹ ፡ አዋቂ ፡ ነን ፡ ባዮች ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ያስከት ላል ፡ እያሉ ፡ ይተነብዩ ፡ ነበር ።

« ይሁን ፡ ያለው ፡ አይቀርም ። ነገር ፡ ግን ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ የኛ ፡ ጌታ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆነ ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናል ። መቸም ፡ እርሱ ፡ ጥሩ ፡ ልጅ ፡ ለመሆኑ ፡ አንድና ፡ ሁለት ፡ የለውም ፡ » አለች ፡ የቄሱ ፡ ባለቤት ።

« ጌታችን ፡ እሱ ፡ ካልሆነ ፡ ታዲያ ፡ ማን ፡ ሊሆን ፡ ብለሽ ፡ ነው? » ስትል ፡ የጐሮቭና ፡ ንግግሯን ፡ አቋረጠቻትና ፡ እን ዲህ ፡ ስትል ፡ ቀጠለች ፡ « ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ የሚፎከ ረው ፡ እንዲያው ፡ ነው ። አሞራው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ የዋዛ ፡ ሰው ፡

አይደለም ። ለሙብቱ ፡ መታገል ፡ አሳምሮ ፡ ያውቃል ። በእ ግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ደግሞ ፡ ወዳጆቹም ፡ ይረዱታል ። ኪ ሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እንዲያ ፡ አለቅጥ ፡ ሲኰራ ፡ የኔ ፡ ግሪሻ ፡ « ጥፋ ፡ ከዚህ! አንተ ፡ ውሻ! » ብሎ ፡ ሲጮኽበት ፡ ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ሄደ ።»

« እንዴት! እንዴት ፡ የጐሮቭና! ግሪሻ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ እንደምን ፡ ደፍሮ ፡ ሊናገር ፡ ቻለ? እኔስ ፡ የኪሪላ ፡ ፔትሮቪ ችን ፡ ዓይን ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ከማየት ፡ ጳጳሱን ፡ መገላመጥ ፡ ይ ቀናኛል ። ገና ፡ ሳየው ፡ ብቻ ፡ በፍርሃት ፡ እርበደበዳለሁ ፤ ላብም ፡ ያጠምቀኛል ፤ ጀርባዬም ፡ አውቆ ፡ ይጐብጣል ፡ » አለ ፡ ዲያቆኑ ።

« አዬ ፡ ከንቱነት! ለአንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ የተደረ ገው ፡ ፍትሐት ፡ ለኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይደ ረግለታል ። ምናልባት ፡ ሥርዓተ ፡ መቃብሩ ፡ ይበልጥ ፡ ያማ ረ ፡ ይሆናል ። እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሰውም ፡ ይጋበዝ ፡ ይሆናል ። ዞ ሮ ፡ ዞሮ ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ » ሲሉ ፡ ቄሱ ፡ ተናገሩ ።

« አባታችን ፡ ሆይ ፤ ቀሳውስቱን ፡ ሁሉ ፡ ለመጋበዝ ፡ አ ስበን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ሳ ይፈቅድልን ፡ ቀረ ። ምግብ ፡ እንኳ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ። ትልቅ ፡ ድግስም ፡ ለመደገስ ፡ እንችል ፡ ነበር ። ምን ፡ ይሆናል ፡ ሳ ይቻል ፡ ቀረ ። ሆኖም ፡ እንግዶቻችን ፡ ጥቂት ፡ ስለሆናች ሁ ፡ ጥሩ ፡ አድርገን ፡ እንጋብዛችኋለን ፡ » አለች ፡ የጐሮቭና ።

ሰዎቹ ፡ ይህን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ሲሰሙ ፡ እርምጃቸው ን ፡ አፋጥነው ፡ እሚቹ ፡ ጌታ ፡ እዱብሮቭስኪይ ፡ ቤት ፡ ደ ረሱ ። እዚያም ፡ ምግብና ፡ መጠጡ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ጠበቃቸው ።

ቭላዲሚር ፡ ግን ፡ ሰውነቱን ፡ በማድከም ፡ ሐዘኑን ፡ ለ መርሳት ፡ ሲል ፡ ወደጫካው ፡ ውስጥ ፡ እርቆ ፡ ገባ ። ወዴት ፡ እንደሚሄድ ፡ ሳያውቅም ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

እጆቹንና ፡ ፊቱን ፡ የዛፎቹ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ሲቧጥጧቸውና ፡ እግሮቹም ፡ እረግረጉ ፡ ውስጥ ፡ ሲሰምጡ ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ አልተሰማውም ። በመጨረሻም ፡ በቁጥቋጦ ፡ የተከበበች ፡ አንድ ፡ ጨፌ ፡ ቦታ ፡ አገኘ ። ቅጠላቸው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በረገፈው ፡ ዛፎች ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ትፈሳለች ። ቭላዲሚር ፡ እዚች ፡ ቀዝቃዛ ፡ ጨፌ ፡ ላይ ፡ አረፍ ፡ አለ ። ብዙ ፡ አሳዛኝ ፡ ሐሳቦችም ፡ በአዕምሮው ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ። ብቸኝነቱም ፡ ጠልቆ ፡ ተሰማው ። የወደፊቱም ፡ ጊዜ ፡ ጥቁር ፡ ደመና ፡ ለብሶ ፡ ታየው ። የትሮዬኩሮቭ ፡ ጠላትነት ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ አደጋ ፡ እንደሚያስከትልም ፡ ተረዳው ። የወረሰውም ፡ ጥቂት ፡ ሐብት ፡ ወደሌላ ፡ ሰው ፡ የተላለፈ ፡ እንደሆን ፡ ምስኪን ፡ ድኃ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚቀር ፡ ተገነዘበ ። ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ተቀምጦ ፡ ትንሿ ፡ ወንዝ ፡ አንዳንድ ፡ የረገፉ ፡ ቅጠሎችን ፡ ይዛ ፡ በርጋታ ፡ ስትወርድ ፡ ይመለከት ፡ ስለነበር ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ ዕድል ፡ እንደዚሁ ፡ እንደሆነ ፡ በጉልህ ፡ ሊመለከት ፡ ቻለ ። ቀኑ ፡ እየመሸ ፡ መሄዱን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ወደቤቱ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ ጀመረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የጫካውን ፡ መግቢያና ፡ መውጫ ፡ ባለማወቁ ፡ ብዙ ፡ ከማሰነ ፡ በኋላ ፡ እንዳጋጣሚ ፡ ወደቤቱ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ አገኘ ።

ወደቤቱ ፡ ሲሄድም ፡ ቄሱንና ፡ ተከታዮቻቸውን ፡ ሲመጡ ፡ አያቸው ። ይህ ፡ አጋጣሚ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያስከትላል ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ ስላደረበትም ፡ ወዲያው ፡ ምልስ ፡ አለና ፡ እጫካው ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ተደበቀ ። እነሱም ፡ ሳያውቁ ፡ ከልብ ፡ እየተጨዋወቱ ፡ አለፉ ።

« ከክፉ ፡ ነገር ፡ እርቆ ፡ ደግ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ነው ፤ እኛ ፡ እዚህ ፡ የምንቆይበት ፡ ምክንያት ፡ የለንም ፤ የሆነው ፡ ቢሆን ፡ እኛን ፡ አያገባንም ፡ » ሲል ፡ ቄሱ ፡ ለሚስቱ ፡ ተናገረ ።

የቄሱም ፡ ሚስት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መለሰች ። ነገር ፡ ግን ፡ ቭላዲሚር ፡ ቃሉን ፡ ሊሰማ ፡ አልቻለም ።

እቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ሲደርስም ፡ ባላገሮችና ፡ የቤት ፡ አሽከሮች ፡ አጥር ፡ ግቢውን ፡ መልተውት ፡ አየ ። ያልተለመደ ፡ ጩኸትና ፡ ጫጫታም ፡ ከሩቅ ፡ ሰማ ። በሰረገላዎቹ ፡ ቤት ፡ አጠገብም ፡ ሁለት ፡ ሌሎች ፡ ሰረገላዎች ፡ ቆመው ፡ አየ ። የወታደር ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ሰዎችም ፡ እደረጃው ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ሲያወሩ ፡ ተመለከተ ።

« ምንድን ፡ ነው ፡ ነገሩ? እነዚህ ፡ ሰዎችስ ፡ እነማን ፡ ናቸው? ምንስ ፡ ይፈልጋሉ ፡ » ሲል ፡ ሮጦ ፡ ሊቀበለው ፡ የመጣውን ፡ አሽከሩን ፡ አንቶንን ፡ በቁጣ ፡ ጠየቀው ። ሽማግሌው ፡ አንቶንም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፤

« ጌታዬ ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ሆይ! እነዚህ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ለትሮዬኩሮቭ ፡ አሳልፈው ፡ ሊሰጡን ፡ ነው ። ካንተ ፡ ከጌታችን ፡ ነጥቀው ፡ ሊወስዱን ፡ ነው ። »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቭላዲሚር ፡ እራሱን ፡ ደፋ ። አገልጋዮቹም ፡ በምስኪን ፡ ጌታቸው ፡ ዙሪያ ፡ ተሰብስበው ፡ እጁን ፡ እየሳሙና ፡ እያለቀሱ ፤

« አንተ ፡ አባታችን ፡ ነህ ፤ ካንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ጌታ ፡ አንፈልግም ። አንተን ፡ ከምንከዳ ፡ ሞትን ፡ እንመርጣለን ። እዘዘንና ፡ ድራሻቸውን ፡ እናጥፋው ፡ » ሲሉ ፡ ጠየቁት ።

ቭላዲሚር ፡ ተመለከታቸውና ፡ ልቡ ፡ ተነካ ።

« እናንተ ፡ እዚሁ ፡ ጸጥ ፡ ብላችሁ ፡ ተቀመጡ ። እኔ ፡ ሄጄ ፡ ከሰዎቹ ፡ ጋር ፡ እነጋገራለሁ ። »

« አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ! ንገራቸው ። እነኚህን ፡ የተረገሙ ፡ ፍጡሮች ፡ አሳፍርልን ፡ » ሲሉ ፡ በጩኸት ፡ ጠየቁት ።

ቭላዲሚርም ፡ ወደሹሞቹ ፡ ሄደ ። ሻባሽኪን ፡ ባርኔጣውን ፡ ደፍቶና ፡ ሽንጡን ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡ በትዕቢት ፡

አካባቢውን ፡ ይመለከት ፡ ነበር ። ቁመተ ፡ ረጅምና ፡ ሰውነ
ተ ፡ ሙሉ ፤ ፊተ ፡ ቀይና ፡ ረዛም ፤ ዕድሜውም ፡ ወደ ፡ ሃምሳ ፡
ዓመት ፡ የሚጠጋው ፡ ምስለኔ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ ሲመጣ ፡
ባየው ፡ ጊዜ ፡ በጕረና ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፤

« በወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ካሁ
ን ፡ ወዲያ ፡ የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ መሆናችሁን ፡ ደግሜ ፡ አስ
ታውቃችኋለሁ ። ወኪሉም ፡ ሻባሽኪን ፡ ነው ። ትዕዛዙን ፡
ሁሉ ፡ ፈጽሙ ። እናንተም ፡ ሴቶቹ ፡ ብትወዱትና ፡ ብታከ
ብሩት ፡ ይሻላል ። ይህን ፡ ካደረጋችሁ ፡ እሱም ፡ እጅግ ፡ ይ
ወዳችኋል ። »

ምስለኔው ፡ ይህን ፡ ሻካራ ፡ ቀልድ ፡ ተናግሮ ፡ ሳቀ ።
ሻባሽኪንና ፡ ሌሎቹም ፡ ሹሞች ፡ የርሱን ፡ አርአያ ፡ ተከት
ለው ፡ ሳቁ ። ቭላዲሚር ፡ ግን ፡ በንዴት ፡ ተቃጠለ ። ንዴ
ቱንም ፡ በመደበቅ ፡ ምስለኔውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ፤

« ነገሩ ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ ለማወቅ ፡ ይፈቀድልኝ ። »

« እኛ ፡ የመጣነው ፡ ይህንን ፡ እርስት ፡ ለኪሪላ ፡ ፔትሮ
ቪች ፡ ለማዛወርና ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ በጊ
ዜ ፡ እንዲወጡ ፡ ለማሳሰብ ፡ ነው ፡ » ሲል ፡ ብልሁ ፡ ምስለ
ኔ ፡ መለሰ ።

« ውሳኔውን ፡ ለአገልጋዮቹ ፡ ከመናገራችሁ ፡ በፊት ፡ ለ
ኔ ፡ ለባለቤቱ ፡ ማስታወቅ ፡ ትችሉ ፡ ነበር ። »

« ለነገሩ ፡ አንተ ፡ ማነህ? የርስቱ ፡ ባለቤት ፡ አንድሬይ ፡
ጋቭሪሎቪች ፡ እንደሆን ፡ በእግዚር ፡ ፈቃድ ፡ ሞቷል ። አ
ንተ ፡ ማን ፡ እንደሆንክ ፡ እኛ ፡ አናውቅም ። ልናውቅም ፡ አን
ሻም ፡ » ሲል ፡ ሻባሽኪን ፡ ቭላዲሚርን ፡ ትኩር ፡ ብሎ ፡ እያ
የ ፡ ተናገረ ።

« ወጣቱ ፡ የኛ ፡ ጌታ ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ነ
ው ፡ » ሲል ፡ ከሰዎቹ ፡ መሐል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተናገረ ።

« ማነው ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ደፍሮ ፡ የተናገረ! የምን ፡ ጌ

ቃ! የማንስ ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች! ጌታችሁ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ነው ። ትሰሙኛላችሁ ፤ እናንተ ፡ ደንቆሮች! »
ሲል ፡ ምስለኔው ፡ በማስፈራራት ፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

« የለም ፡ አይደለም! » ሲል ፡ ያው ፡ የመጀመሪያው ፡ ድምጽ ፡ አሁንም ፡ በጩኸት ፡ ተናገረ ።

« ይኸማ ፡ ኢድማ ፡ ነው! አንተ ፡ የጭቃ ፡ ሹም ፡ ና ፡ ወዲህ! » ሲል ፡ ምስለኔው ፡ በኃይል ፡ ቃል ፡ አዘዘ ።

ከሰዎቹም ፡ መሐል ፡ ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ቀረበ ።

« ደፍሮ ፡ የመለሰልኝን ፡ ሰው ፡ አሁኑኑ ፡ ፈልገህ ፡ አውጣልኝ ። አሳየዋለሁ! »

ጭቃ ፡ ሹሙ ፡ ወደተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ እንደተናገረ ፡ ጠየቀ ። ግን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ መልስ ፡ ሳይሰጠው ፡ ቀረ ። ወዲያውም ፡ ከወደኋላ ፡ በኩል ፡ ያሉት ፡ ማጉረምረም ፡ ጀመሩ ። ጉርምርምታውም ፡ እያደገ ፡ ሄደና ፡ ከመቅጽበት ፡ ወደ ፡ ታላቅ ፡ ጩኸት ፡ ተለወጠ ። ምስለኔውም ፡ ድምጹን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ሊያባብላቸው ፡ ሞከረ ።

« በኋ ፡ ጐበዝ ፡ ምን ፡ እንጠብቃለን? እንበላቸዋ! » ሲሉ ፡ አሽከሮቹ ፡ ጮኹ ። አንድነት ፡ ሆነውም ፡ ወደፊት ፡ ገፉ ።

ሻባሽኪንና ፡ ሌሎቹ ፡ ሸሽተው ፡ ወደቤት ፡ ገቡና ፡ በሩን ፡ ከውስጥ ፡ ቆለፉ ።

« ስብረን ፡ እንግባ ፡ ጐበዝ ፡ » ሲሉ ፡ አሁንም ፡ አሽከሮቹ ፡ ጮኹና ፡ ወደፊት ፡ ገሠገሡ ።

« ተው! እናንተ ፡ ደንቆሮች ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በቁጣ ፡ ድምጽ ፡ ተናገረ ። « እራሳችሁንም ፡ እኔንም ፡ ዕዳ ፡ ውስጥ ፡ ትጥላላችሁ ። ሂዱ ፡ ወደየቤታችሁ ። እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ልቀር ፡ እችላለሁ ። ንጉሣችን ፡ መሐሪ ፡ ነውና ፡ አትፍሩ ። እኔው ፡ እራሴ ፡ አቤት ፡ ብዬ ፡ እመለከታለሁ ። እንዲህ ፡ ስንበደል ፡ ዝም ፡ አይልም ። ሁላችንም ፡ የሱ ፡ ልጆች ፡ ነን ። ነገር ፡

ግን ፡ የውንብድና ፡ ሥራ ፡ ስትሠሩ ፡ እንዴት ፡ ሊረዳችሁ ፡ ይ ችላል? »

የወጣቱ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ቃልና ፡ የጠራ ፡ ድምጽ ፡ እንዲሁም ፡ ግርማው ፡ የተፈለገውን ፡ ውጤት ፡ አስገኘ ። የ ተሰበሰቡት ፡ ሰዎች ፡ ወዲያው ፡ ጸጥ ፡ አሉና ፡ በየፊናቸው ፡ ተ ሰማሩ ። አጥር ፡ ግቢውም ፡ ጭር ፡ አለ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ሹሞቹ ፡ ቤት ፡ ዘግተው ፡ እንደተቀመጡ ፡ ነበር ። በመጨ ረሻ ፡ሻባሽኪን ፡ በሩን ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ከፈተና ፡ ወደበረንዳ ው ፡ ወጣ ። እየተሽቆጠቆጠና ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ እየነሳ ም ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ስላደረገው ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ማመስ ገን ፡ ጀመረ ።

ቭላዲሚር ፡ ግን ፡ በጥላቻ ፡ መንፈስ ፡ ሰማውና ፡ መልስ ፡ ሳይሰጠው ፡ ቀረ ።

« ጊዜው ፡ ስለመሸ ፡ ብትፈቅድልን ፡ እዚሁ ፡ ለማደር ፡ አስበናል ። ብንሄድም ፡ ምናልባት ፡ ሰዎችህ ፡ እመንገድ ፡ ላይ ፡ ጠብቀው ፡ ሳይጠናወቱን ፡ አይቀሩም ። መልካም ፡ ፈቃድህ ፡ ሆኖ ፡ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ሳር ፡ ብታስጐዘጉዝልን ፡ መልካ ም ፡ ነበር ። ማለዳ ፡ ተነስተን ፡ ወደየቤታችን ፡ እንሄዳለን ፡ » አለ ፡ ሻባሽኪን ።

« የፈቃዳችሁን ፡ ማድረግ ፡ ትችላላችሁ ። እኔ ፡ ካሁን ፡ ወዲያ ፡ የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ አይደለሁም ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስ ኪይ ፡ በግዴለሽነት ፡ መለሰለት ።

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ወደአባቱ ፡ ክፍል ፡ ገባና ፡ ቆለፈ ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

« እንግዲህ ፡ የኔ ፡ ነገር ፡ አለቀ ፡ ደቀቀ ፡ ማለት ፡ ነዋ ፡ » ሲል ፡ ቭላዲሚር ፡ እራሱ ፡ ለራሱ ፡ ተናገረ ። « ዛሬ ፡ ጧት ፡

የምበላው ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦና ፡ መጠጊያ ፡ በታም ፡ ነበረኝ ። ነ
ገ ፡ ግን ፡ የተወለድኩበትንና ፡ አባቴ ፡ የሞተበትን ፡ ቤት ፡ አ
ባቴን ፡ ለገደለውና ፡ እኔንም ፡ ድኃ ፡ ላደረገኝ ፡ ሰው ፡ ለቅቄ ፡
መሄድ ፡ አለብኝ ። » ቭላዲሚር ፡ ጥርሱን ፡ ነክሶ ፡ የእናቱን ፡
ሥዕል ፡ አተኩሮ ፡ ያይ ፡ ጀመር ። ነጭ ፡ የጧት ፡ ልብሷ
ን ፡ ለብሳና ፡ ቀይ ፡ ጽጌረዳ ፡ እጸጉሯ ፡ ላይ ፡ ሻጥ ፡ አድርጋ ፡
እደረጃ ፡ መወጣጫ ፡ ላይ ፡ ደገፍ ፡ እንዳለች ፡ ሰዓሊው ፡ አ
ንስቷታል ።

« ይህ ፡ ሥዕል ፡ ባባቴ ፡ ጠላት ፡ እጅ ፡ ሊገባ ፡ ነውን? »
ሲል ፡ ቭላዲሚር ፡ አሰበ ። « ምናልባት ፡ ከስብርባሪ ፡ ወንበ
ር ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ እንጨት ፡ ቤት ፡ ይጥሉት ፡ ይሆናል ።
ወይም ፡ ደግሞ ፡ በመተላለፊያው ፡ ላይ ፡ ተሰቅሎ ፡ ያሽከ
ሮቹ ፡ መሣቂያና ፡ መሣለቂያ ፡ ይሆናል ። አባቴ ፡ የሞተ
በት ፡ የመኝታ ፡ ቤትም ፡ የርስት ፡ ጠባቂዎቹ ፡ ወይም ፡ የቁባ
ቶቹ ፡ መስፈሪያ ፡ ይሆናል ። የለም! የለም! ይህን ፡ የሐዘን ፡
ቤት ፡ እኔን ፡ አስወጥቶ ፡ የርሱ ፡ ንብረት ፡ ሊያደርገው ፡ አይ
ችልም ። »

ቭላዲሚር ፡ እንደገና ፡ ጥርሱን ፡ ነከሰ ። ክፉ ፡ ክፉ ፡ ሐ
ሳብም ፡ በአዕምሮው ፡ መጣ ። የጸሐፊዎቹም ፡ ድምጽ ፡ ዘል
ቆ ፡ ይሰማው ፡ ጀመር ። እንደቤቱ ፡ ጌታ ፡ ሁሉ ፡ ያን ፡
አምጡ ፡ ይህን ፡ ውሰዱ ፡ እያሉ ፡ ሲያዙ ፡ የትካዜ ፡
ሐሳቡን ፡ በጠበጡት ። በመጨረሻም ፡ ሙሉ ፡ ጸጥታ ፡
ሆነ ።

ቭላዲሚር ፡ ሣጥኖቹንና ፡ የጠረጴዛ ፡ ኪሶቹን ፡ እየከ
ፈተ ፡ የሟች ፡ አባቱን ፡ ወረቀቶች ፡ ይፈትሽ ፡ ጀመር ። አብ
ዛኞቹ ፡ ስለቤት ፡ ውስጥ ፡ ጉዳይና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሥራ ፡
ተግባሮች ፡ የተጻፉ ፡ ስለነበሩ ፡ ሳያነብ ፡ እየቀደደ ፡ ጣላ
ቸው ። ከነዚሁ ፡ ውስጥ ፡ « ከሚስቴ ፡ የተላኩ ፡ ደብዳቤዎ
ች ፡ » የሚል ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ አገኘ ። በጋለ ፡ ስሜትም ፡ ደ

ብዳቤዎቹን ፡ ማንበብ ፡ ጀመረ ። ደብዳቤዎቹ ፡ የተጻፉት ፡ በ
ቱርክ ፡ ዘመቻ ፡ ጊዜ ፡[26] ሲሆን ፡ አድራሻቸው ፡ ከኪስቴኖ
ቭካ ፡ ወደጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ነበር ። ሚስቱ ፡ ብቸኝነቷንና ፡ የ
ቤት ፡ ተግባሯን ፡ እየገለጸች ፡ በመለያየታቸው ፡ እጅግ ፡ ታ
ዝናለች ። በፍጥነት ፡ ወደቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ከውድ ፡ የሕይ
ወት ፡ ጓደኛው ፡ ጋር ፡ በዓይነ ፡ ሥጋ ፡ ይተያይ ፡ ዘንድም ፡ ት
ለምነዋለች ። ባንደኛው ፡ ደብዳቤዋም ፡ ላይ ፡ ስለሕጻኑ ፡ ስ
ለቭላዲሚር ፡ ጤንነት ፡ መሥጋቷን ፡ ትገልጽለታለች ። በ
ሌላ ፡ ላይ ፡ደግሞ ፡ ልጅዋ ፡ ገና ፡ በሕጻንነቱ ፡ ብልህ ፡ በመ
ሆኑ ፡ እየተደሰተች ፡ ወደፊት ፡ ብሩህና ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ እን
ደሚጠብቀው ፡ ታይለታለች ። ቭላዲሚር ፡ ደብዳቤዎቹን ፡
በማንበብ ፡ እጅግ ፡ ስለተመሰጠና ፡ በተቀደሰ ፡ የትዳር ፡ ዓ
ለም ፡ ውስጥ ፡ ስለሰመጠ ፡ ሌላውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እረሳ ።
የቅድመ ፡ አያቱ ፡ የጠረጴዛ ፡ ሰዓት ፡ ከሌሊቱ ፡ አምስት ፡ ሰ
ዓት ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ እስኪደውል ፡ ድረስም ፡ ጊዜ ፡ መብረሩ
ን ፡ ጭራሽ ፡ ዘንግቶት ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ ደብዳቤዎቹን ፡
እኪሱ ፡ ከተተና ፡ ሻማ ፡ ብድግ ፡ አድርጎ ፡ ከክፍሉ ፡ ወጣ ።
በአዳራሹ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ሹሞቹ ፡ ተኝተው ፡ ነበር ፤ በጠረጴ
ዛውም ፡ ላይ ፡ ብርጭቆዎች ፡ ነበሩ ። ቤቱም ፡ ክፉኛ ፡ አረቂ ፡
አረቂ ፡ ይሸት ፡ ነበር ። ቭላዲሚር ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊ
ያ ፡ ቤቱ ፡ ሲሄድ ፡ የተኙትን ፡ ሹሞች ፡ ተጸይፏቸው ፡ አለ
ፈ ። በሩም ፡ ተቆልፎ ፡ አገኘው ፤ ቁልፉን ፡ ስላጣውም ፡ ወ
ደአዳራሹ ፡ ተመለሰ ። ቁልፉንም ፡ እጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ተቀ
ምጦ ፡ አገኘው ፤ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ ሲገባም ፡ አንድ ፡ የተጋ
ደመ ፡ ሰው ፡ አደናቀፈው ። ይኸው ፡ ሰውዬ ፡ አንድ ፡ የሚ
ያንጸባርቅ ፡ መጥረቢያ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ነበር ። ቭላዲሚር ፡ ሻ
ማውን ፡ ወደሰውዬው ፡ ዘወር ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ብረት ፡ ሠሪ
ው ፡ አርኺፕ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳ ።

« ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ እዚህ? » ብሎ ፡ ጠየቀው ።

« ውይ! ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ነህ ፡ እንዴ? ስብሐ
ት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ! ሻማ ፡ ይዘህ ፡
መምጣትህ ፡ በጀ ፡ » ሲል ፡ አርኺፕ ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡
ተናገረ ።

ቭላዲሚርም ፡ ብረት ፡ ሰሪውን ፡ በመደነቅ ፡ ዓይን ፡
ተመለከተውና ፤

«እዚህ ፡ ምን ፡ አስደበቀህ? » ሲል ፡ ጠየቀው ።

« እ ... ሁሉም ፡ እቤት ፡ መሆናቸውን ፡ ለማወቅ ፡ ስል ፡
መጣሁ ፡ » ብሎ ፡ በማወላወል ፡ ድምጽ ፡ መለሰ ።

« መጥረቢያስ ፡ የያዝከው ፡ ለምንደነው? » አለው ።

« መጥረቢያ ፡ የያዝኩት? ዋ ፡ ጌታዬ! ባሁን ፡ ጊዜ ፡ ሰ
ው ፡ መጥረቢያ ፡ ሳይዝ ፡ እንዴት ፡ ይሄዳል? እነዚህ ፡ ጸሐ
ፊዎች ፡ ተንኰለኞች ፡ ናቸው ፤ በሰው ፡ ላይ ፡ ምን ፡ እንደሚ
ፈጽሙ ፡ ማን ፡ ያውቃል ... ? »

« ሰክረሃል ። መጥረቢያውን ፡ አስቀምጥና ፡ ሂድ ፤ ተኝ
ተህ ፡ ይውጣልህ ። »

« ሰክረሃል? እኔ? ጌታዬ ፡ አንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ ሆ
ይ ፤ እግዜር ፡ ይመስክርብኝ ፡ አንድ ፡ ጠብታ ፡ እንኳ ፡ አል
ቀመስኩም ። በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰዓት ፡ መጠጥ ፡ የሚያ
ስብ ፡ ማን ፡ ነው? ጸሐፊዎች ፡ የቤቱን ፡ ጌታ ፡ አስወጥተው ፤
በኛ ፡ ላይ ፡ ፈላጭ ፡ ቆራጭ ፡ ሲሆኑ ፡ ታይቶና ፡ ተሰምቶ ፡ ያ
ውቃልን? እነዚህ ፡ እርጉሞች ፡ ስሙልኝ ፡ እንዴት ፡
እንደሚያኰርፉ! ጩርሻቸው ፡ ጊዜ ፡ የመጣው ፡
ይመጣል! »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ፊቱን ፡ ኰስትሮ ፡ ጥቂ
ት ፡ ከቆየ ፡ ኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

« ስማ ፡ አርኺፕ ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሐሳብ ፡ ይቅርብ
ህ ። የጸሐፊዎቹ ፡ ጥፋት ፡ አይደለም ። ፋኖሱን ፡ አብራና ፡
ይልቅ ፡ ተከተለኝ ። »

አርኪፕ ፡ ሻማውን ፡ ከጌታው ፡ እጅ ፡ ተቀበለና ፡ ፋኖሱን ፡ ከወጥቤቱ ፡ ፈልጎ ፡ አምጥቶ ፡ አበራ ። ሁለቱም ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ በበረንዳው ፡ በኩል ፡ ወጡና ፡ ወደአጥር ፡ ግቢው ፡ ሄዱ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዘበኛው ፡ የብረት ፡ ሳህን ፡ አጋጨ ፤ ውሾቹም ፡ መጮኽ ፡ ጀመሩ ።

« ዘበኛው ፡ ማን ፡ ነው? » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ጠየቀ ።

« እኛ ፡ ቫሲሊሳና ፡ ሉኬሪያ ፡ ነን ፡ » ሲል ፡ አንድ ፡ ቀጭን ፡ ድምጽ ፡ መለሰ ።

« ሂዱ ፡ እቤታችሁ ፡ አታስፈልጉም ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ አዘዘ ።

« መሄድ ፡ ትችላላችሁ ፡ » ሲል ፡ በተጨማሪ ፡ አርኺፕ ፡ ተናገረ ።

« እግዜር ፡ ይስጥልን ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ » ሲሉ ፡ ሴቶቹ ፡ መለሱና ፡ ወደየቤታቸው ፡ በፍጥነት ፡ ሄዱ ።

ዱብሮቭስኪይ ፡ እርምጃውን ፡ ወደፊት ፡ ቀጠለ ። ሲሄድ ፡ ሳለም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ተጠጉትና ፡ ተጣሩ ። ዱብሮቭስኪይም ፡ የአንቶንና ፡ የግሪሻ ፡ ድምጽ ፡ መሆኑን ፡ አወቀ ።

« ለምን ፡ አልተኛችሁም? » ሲል ፡ ጠየቃቸው ።

« እንደምን ፡ አድርገን ፡ ልንተኛ ፡ እንችላለን? እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገርስ ፡ ይደርስብናል ፡ ብሎ ፡ ማን ፡ አሰበ? » ሲል ፡ አንቶን ፡ መለሰ ።

« ቀስ ፡ በል ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ነገሩን ፡ አቋረጠውና ፡ « የጎሮቭና ፡ የት ፡ ናት ፡ » ብሎ ፡ ጠየቀው ።

« እዋናው ፡ ቤት ፡ እክፍሏ ፡ ውስጥ ፡ ናት ፡ » ሲል ፡ ግሪሻ ፡ መለሰ ።

« ሂድና ፡ አምጣት ፤ ሰዎቻችን ፡ ሁሉ ፡ ከቤቱ ፡ ለቀው ፡ እንዲወጡም ፡ አድርግ ፤ ከጸሐፊዎቹ ፡ በቀር ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ እቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዳይቀር ። አንተ ፡ ደግሞ ፡ እንቶን ፡ ሂድና ፡ ሠረገላውን ፡ ጫን ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ አዘዘ ።

ግሪሻ ፡ ሄደና ፡ በፍጥነት ፡ እናቱን ፡ ይዞ ፡ ተመለሰ ። አሮጊቷ ፡ ሴት ፡ ያን ፡ ሌሊት ፡ ልብሷን ፡ አላወለቀችም ፡ ነበር ። ከጸሐፊዎቹ ፡ በስተቀር ፡ እንቅልፍ ፡ ባይኑ ፡ የዞረ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

« ሁሉም ፡ እዚህ ፡ ናቸው? እቤት ፡ ውስጥ ፡ የቀረ ፡ ሰው ፡ የለም? » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ጠየቀ ።

« ከጸሐፊዎቹ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የቀረ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ » ሲል ፡ ግሪሻ ፡ መለሰ ።

« ጥቂት ፡ ሣር ፡ ወይም ፡ ገለባ ፡ አምጡ ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ አዘዘ ።

ሰዎቹም ፡ ወደጋጣ ፡ ሄዱና ፡ እቅፍ ፡ ሣር ፡ ይዘው ፡ መጡ ።

« እበረንዳው ፡ ላይ ፡ አድርጉት ፤ እንደሱ ... እንግዲህ ፡ ጐበዝ ፡ እሳት ፡ አቀብሉኝ ። »

አርኺፕ ፡ ፋኖሱን ፡ አስጠጋለትና ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በስንጥር ፡ እሳቱን ፡ አቀጣጠለ ።

« ቆይ ፡ እስቲ ፤ ያዳራሹን ፡ በር ፡ የዘጋሁት ፡ ይመስለኛልና ፡ ሂደህ ፡ ክፈተው ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ አርኺፕን ፡ አዘዘው ።

አርኺፕ ፡ ወደአዳራሹ ፡ ሮጦ ፡ ቢሄድ ፡ በሩን ፡ ተከፍቶ ፡ አገኘው ።

« በሩን ፡ ክፈተው? የለም ፡ አላደርገውም ፡ » ሲል ፡ በማጉረምረም ፡ ተናገረና ፡ በሩን ፡ ቆልፎት ፡ ወደ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ተመለሰ ።

ዱብሮቭስኪይ ፡ ሣሩን ፡ በስንጥር ፡ እሳት ፡ ሲያያዘው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቃጠሎ ፡ ተነሣና ፡ አጥር ፡ ግቢውን ፡ በሙሉ ፡ አበራው ።

« ወይኔ! ወይኔ! ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ምንድነው ፡ የምታደርገው? » ስትል ፡ የጐሮቭና ፡ በሚያሳዝን ፡ ድምጽ ፡ ጮኸች ።

« ዝም ፡ በይ! ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሰንብቱ ፤ እግዜር ፡ ወደመራኝ ፡ እሄዳለሁ ። ካዲሱ ፡ ጌታችሁ ፡ ጋር ፡ በደስታ ፡ ያኑራችሁ ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ተሰናበታቸው ።

« አባታችን! ጠባቂያችን ፡ ሆይ! ካንተው ፡ ጋር ፡ እንሞታለን ፡ እንጂ ፡ አንለይህም ። ካንተ ፡ ጋር ፡ አብረን ፡ እንሄዳለን ፡ » ሲሉ ፡ ሁሉም ፡ አለቀሱ ።

ሠረገላም ፡ ተጭኖ ፡ ቀረበ ፤ ዱብሮቭስኪይም ፡ ከግሪሻ ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠ ። ከሰዎቹ ፡ ጋርም ፡ በኪስቴኖቭካ ፡ ጫካ ፡ እንዲገናኙ ፡ ተቃጠረና ፡ አንቶን ፡ ፈረሶቹን ፡ ባለንጋው ፡ ሾጥ ፡ አድርጐ ፡ ካጥር ፡ ግቢው ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ።

ነፋስ ፡ መንፈስ ፡ ጀመረ ። ከአንድ ፡ ደቂቃ ፡ በኋላም ፡ የሳቱ ፡ ነበልባል ፡ ቤቱን ፡ አለበሰው ። ፍም ፡ የመሰለ ፡ ጭስ ፡ በቤቱ ፡ እናት ፡ ላይ ፡ ይቡለቀለቅ ፡ ጀመር ። መስተዋቱም ፡ እየተሰበረ ፡ እመሬቱ ፡ ላይ ፡ ተከሰከሰ ። ጣሪያና ፡ ግድግዳውም ፡ እየተጠረመሰ ፡ ወደቀ ። « እርዱን! ተቃጠልን! » የሚል ፡ አሳዛኝ ፡ ጩኸትና ፡ ኡኡታም ፡ ተሰማ ።

« የታባታችሁ! » ሲል ፡ አርኺፕ ፡ እሳቱን ፡ በተንኰል ፡ ፈገግታ ፡ ተመለከተው ።

« ልጄ ፡ ሆይ ፤ እነዚህን ፡ የተረገሙ ፡ ሰዎች ፡ አድናቸው ፤ እግዜር ፡ ውለታህን ፡ ይከፍልሃል ፡ » ስትል ፡ የጐሮቭና ፡ ጠየቀችው ።

«እረ ፡ በፍጹም ፡» ሲል ፡ ብረት ፡ ሠሪው ፡ መለሰ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ ድርብ ፡ መዝጊያ ፡ ያለውን ፡ መስኰት ፡ ለመስበር ፡ ብቅ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያውኑ ፡ ጣራው ፡ ተጠርምሶ ፡ እላያቸው ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። ከዚያ ፡ በ ኋላ ፡ ጩኸት ፡ መሰማቱ ፡ ቀረ ።

የቤቱ ፡ አሽከሮች ፡ አጥር ፡ ግቢውን ፡ ከመቅጽበት ፡ መ ሉት ። ሴቶቹ ፡ እየተጯጯሁ ፡ ዕቃቸውን ፡ ለማዳን ፡ ተሯሯ ጡ ። ልጆቹም ፡ የሳቱን ፡ ነበልባል ፡ እያዩ ፡ በመደሰት ፡ ጨፈሩ ። የሳቱ ፡ ፍንጣሪ ፡ እየተወረወረም ፡ ባካባቢው ፡ ያ ሉትን ፡ ጐጆዎች ፡ ኢያያዛቸው ።

«እሰይ ፡ የልባችን ፡ ደረሰ ፤ እንዴት ፡ ይንቀለቀላል! ፖክሮቭስኮዬ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ሲመለከቱት ፡ እጅግ ፡ ሳያስ ደስት ፡ አይቀርም ፡» ሲል ፡ አርኺፕ ፡ ተናገረ ።

በዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ዓይኑን ፡ ማረከው ። አንድ ፡ ድመት ፡ በሚቃጠል ፡ እንጨት ፡ ላይ ፡ ሆና ፡ የም ትዘልበት ፡ ቦታ ፡ ጠፍቷት ፡ ስትጨነቅ ፡ አየ ። በዙሪያዋም ፡ እሳት ፡ ይንቀለቀል ፡ ነበር ። ምስኪኗ ፡ እንስሳ ፡ ሚያው! ሚያ ው! እየለች ፡ በማሳዘን ፡ እርዳታ ፡ ለመነች ። ሕጻናቱ ፡ የድመ ቷን ፡ መጨነቅ ፡ እያዩ ፡ ይስቁ ፡ ጀመር ።

«እናንተ ፡ ሰይጣኖች ፡ ምን ፡ ያስቃችኋል ፡» ሲል ፡ ብ ረት ፡ ሰሪው ፡ በቁጣ ፡ ተናገረና ፡ «እግዜርን ፡ አትፈሩምን? ከ ግዜር ፡ ፍጡሮች ፡ አንዷ ፡ ስትጠፋ ፡ እናንተ ፡ ትደሰታላ ችሁ? የማትረቡ ፡» አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ መሰላል ፡ አምጥ ቶ ፡ በእሳት ፡ እተያያዘው ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ አስደገፈና ፡ ድ መቷን ፡ ለማዳን ፡ ወጣ ። እሷም ፡ ዓላማው ፡ ገባትና ፡ በምስ ጋና ፡ ስሜት ፡ እጅጌው ፡ ላይ ፡ ጥብቅ ፡ አለች ፤ ብረት ፡ ሠሪ ውም ፡ ክፉኛ ፡ ተቃጥሎ ፡ ድመቷን ፡ ይዞ ፡ ወደመሬት ፡ ወረደ ።

« ጐበዝ! እንግዲህ ፡ ደህና ፡ ሰንብቱ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ የምሠራው ፡ ነገር ፡ የለኝም ። ደስታ ፡ ለናንተ ፡ ይሁን ። በ ድያችሁም ፡ እንደሆን ፡ ማሩኝ ፡ » ሲል ፡ ለተከዙት ፡ አገል ጋዮች ፡ ተናገረ ።

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮም ፡ ብረት ፡ ሠሪው ፡ መሰስ ፡ ብ ሎ ፡ ሄደ ። እሳቱም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ መንደዱን ፡ ቀ ጠለና ፡ በመጨረሻ ፡ ጠፋ ። ታላቅ ፡ የፍም ፡ ክምርም ፡ በ ጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ደምቆ ፡ አበራ ። ቤታቸው ፡ የተቃጠ ለባቸው ፡ የኪስቴኖቭካ ፡ መንደር ፡ ሰዎችም ፡ በፍሙ ፡ ዙ ሪያ ፡ ያንዣብቡ ፡ ጀመር ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

በማግሥቱ ፡ የቃጠሎው ፡ ወሬ ፡ በቀበሌው ፡ ተነዛ ። እያንዳንዱም ፡ ሰው ፡ ስለቃጠሎው ፡ የግል ፡ አስተያየቱን ፡ ሰጠ ። አንዳንዶቹ ፡ የዱብሮቭስኪይ ፡ ሰዎች ፡ ከቀብሩ ፡ በ ኋላ ፡ ሰክረው ፡ በዝርክርክነት ፡ እሳት ፡ አስነስተው ፡ ቤቱን ፡ አቃጠሉት ፡ እያሉ ፡ አወሩ ። ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ጸሐፊዎቹ ፡ የቤት ፡ ማሞቂያ ፡ ግብግ ፡ አድርገው ፡ በስካር ፡ አቃጠሉ ት ፡ ሲሉ ፡ ተናገሩ ። ብዙዎች ፡ ደግሞ ፡ ቃጠሎው ፡ በድን ገተኛ ፡ አደጋ ፡ ተነስቶ ፡ የቤቱ ፡ ነዋሪዎችና ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ ተቃጥለው ፡ ሞቱ ፡ ሲሉ ፡ አመኑ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ከመበሳጨትና ፡ ተስፋ ፡ ከመቁረጥ ፡ የተነ ሳ ፡ አሰቃቂውን ፡ አደጋ ፡ እራሱ ፡ እንደፈጸመው ፡ ያወቁ ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ።

ትሮዬኩሮቭ ፡ በማግሥቱ ፡ የቃጠሎውን ፡ ቦታ ፡ መጥ ቶ ፡ ጕበኛና ፡ ወዲው ፡ ምርመራ ፡ አስደረገ ። ምስለኔውና ፡ ሕግ ፡ አስፈጻሚው ፤ ጠበቃውና ፡ ጸሐፊው ፤ ዱብሮቭስኪይ



ባለቅኔው ፡ ዬቭጌኒይ ፡ ባራቲንስኪይ ( ፲፰፻ — ፲፰፻፵፬ ዓ. ም. ) ።
የገጣሚነት ፡ ስጦታውን ፡ ፑሽኪን ፡ በአድናቆት ፡ ዓይን ፡ ይመለ
ከተው ፡ ነበር ።



በሞስኮ ፡ ከተማ ፡ የሚገኘው ፡ ትቬር
ስኮይ ፡ ቡልቫር ( ፲፰፻፴ ዓ. ም. ) ።



ቦልሻያ ፡ ኒኪትስካያ ፡ መንገድ ፡ በሞስ
ኮ ፡ ከተማ ( ፲፰፻፴ ዓ. ም. ) ።



የታህሣስ ፡ አድማ ፡ ተካፋይ ፡ የነበረው ፡ የሙራቪዮቭ ፡ ሚስት ፡ የሆነችው ፡ አሌክሳንድራ ፡ ሙራቪዮቫ ። ባሏ ፡ ወደግዞት ፡ በሄደበት ፡ ጊዜ ፡ ልትከተለው ፡ ስትቆርጥ ፡ ፑሽኪን ፡ ለታህሣሳውያን ፡ ግዞተኞች ፡ የጻፈላቸውን ፡ ግጥም ፡ ይዛ ፡ እንድታስረክባቸው ፡ ብአደራ ፡ ሰጣት

ና ፤ ሞግዚቱ ፡ የጐሮቭና ፤ አሽከሩ ፡ ግሪሻና ፡ ሠረገላ ፡ ነጂው ፡
አንቶን ፤ እንዲሁም ፡ ብረት ፡ ሠሪው ፡ አርኪፕ ፤ እንደሌሉ ፡
ተረጋገጠ ። የቤቱ ፡ ጣሪያ ፡ ተቃጥሎ ፡ ሲወድቅ ፡ ጸሐፊዎ
ቹ ፡ እንደሞቱ ፡ አገልጋዮቹ ፡ ሁሉ ፡ መሰከሩ ። የተቃጠለው
ም ፡ አጥንታቸው ፡ ተቆፍሮ ፡ ወጣ ። ቫሲሊሳና ፡ ሉኬሪያ ፡
የተባሉት ፡ ሴቶች ፡ እሳቱ ፡ ከመነሳቱ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቀደም ፡
ብሎ ፡ ዱብሮቭስኪይንና ፡ ብረት ፡ ሠሪውን ፡ አርኪፕን ፡
አይተናቸዋል ፡ ሲሉ ፡ ተናገሩ ። አርኪፕ ፡ በሕይወት ፡ እ
ንዳለና ፡ ቃጠሎውንም ፡ ያስነሳው ፡ እሱ ፡ ብቻ ፡ ባይሆንም ፡
ዋናው ፡ መሪ ፡ እሱ ፡ እንደነበር ፡ ብዙዎቹ ፡ ቃላቸውን ፡
ሰጡ ። ዱብሮቭስኪይም ፡ ክፉኛ ፡ ተጠረጠረ ። ኪሪላ ፡ ፔት
ሮቪች ፡ ሁናቴውን ፡ በዝርዝር ፡ ጽፎ ፡ ላገረ ፡ ገዢው ፡ አቀረ
በና ፡ አዲስ ፡ ክስ ፡ ተጀመረ ።

ወዲያውም ፡ የሰውን ፡ ሁሉ ፡ ጆሮ ፡ የሚማርክ ፡ አንድ ፡
ወሬ ፡ ተሰማ ። በእንትና ፡ ቀበሌ ፡ ሽፍቶች ፡ ገብተው ፡ ሕ
ዝቡን ፡ አሸበሩት ፤ ባለሥልጣኖቹ ፡ የወሰዱት ፡ እርምጃም ፡
ሽፍቶቹን ፡ ለማገድ ፡ የሚችል ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ ። አንዱ ፡
ካንዱ ፡ የባሰ ፡ ንጥቂያና ፡ ዘረፋ ፡ ይከታተል ፡ ጀመር ። መ
ንገዱም ፡ መንደሩም ፡ አስፈሪ ፡ ሆነ ። ብዙ ፡ ሽፍቶች ፡ የ
መሉባቸው ፡ ሠረገላዎች ፡ በቀን ፡ ብርሃን ፡ ባውራጃው ፡ እየ
ተዘዋወሩ ፡ መንገደኞችንና ፡ ፖስታ ፡ አመላላሺዎችን ፡ ያ
ቆሙ ፡ ጀመር ። እመንደርም ፡ ውስጥ ፡ እየገቡ ፡ የባለርስቶች
ን ፡ ቤት ፡ እየዘረፉ ፡ አቃጠሉ ። የሽፍቶቹ ፡ አለቃ ፡ በብል
ሀነቱና ፡ በደፋርነቱ ፡ እንዲሁም ፡ በቸርነቱ ፡ ዝናው ፡ የታ
ወቀ ፡ ሰው ፡ ሆነ ። ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ ታሪክም ፡ ይነገ
ርለት ፡ ጀመር ። የዱብሮቭስኪይ ፡ ስም ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ አ
ፍ ፡ ገባ ። የደፋሮቹ ፡ ሽፍታዎች ፡ አለቃ ፡ እሱ ፡ እንጂ ፡ ሌ
ላ ፡ ሰው ፡ እንዳልሆነም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አመነ ። አንድ ፡ ነገ
ር ፡ ብቻ ፡ ያስደንቅ ፡ ነበር ፤ ይሄውም ፡ የትሮዬኩሮቭ ፡ ሐ

ብት ፡ አለመነካት ፡ ነው ። ሽፍቶቹ ፡ አንድም ፡ የትሮዬኩሮቭን ፡ ጐተራ ፡ አልዘረፉም ፤ ከሠረገላዎቹም ፡ አንዱንም ፡ ይዘው ፡ አላቆሙም ። ትሮዬኩሮቭ ፡ በተለመደው ፡ ትዕቢቱ ፡ ይህ ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ ባውራጃው ፡ እጅግ ፡ ስለምፈራና ፡ በመንደሬም ፡ ኃይለኛ ፡ የፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ ስላለኝ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ተመጻደቀ ። መጀመሪያ ፡ ጐረቤቶቹ ፡ በትሮዬኩሮቭ ፡ ትዕቢት ፡ ሳቁ ። ሽፍቶቹ ፡ መጥተው ፡ የደለበውን ፡ ሐብቱን ፡ ከዛሬ ፡ ከነገ ፡ ይዘርፉት ፡ ይሆናል ፡ እያሉም ፡ ተጠባበቁ ። ኋላ ፡ ግን ፡ ሽፍቶች ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ አለቅጥ ፡ እንደሚፈሩትና ፡ እንደሚያከብሩት ፡ ማመንና ፡ መስማማት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ። ዱብሮቭስኪይ ፡ በየጊዜው ፡ በሚፈጽመው ፡ አዲስ ፡ የውንብድና ፡ ሥራ ፡ አንዳችም ፡ ጊዜ ፡ ሳይያዝ ፡ በማምለጡ ፡ ለትሮዬኩሮቭ ፡ ኩራት ፡ ጨመረለት ። ባገረ ፡ ገገርውና ፡ በምስለኔዎቹ ፡ እንዲሁም ፡ በዘበኞቹ ፡ ላይ ፡ ይቀልድ ፡ ጀመር ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የትሮዬኩሮቭ ፡ መንደር ፡ የሚያከብረው ፡ የጥቅምት ፡ ፩ቀን ፡ በዓል ፡ መጣ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የተቀደሰ ፡ በዓል ፡ እንዴት ፡ እንደሚከበርና ፡ ሌላውንም ፡ ሁናቴ ፡ ከመግለጻችን ፡ በፊት ፡ አንባቢአችንን ፡ ከአዲሶች ፡ ሰዎችና ፡ ወይም ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ በታሪኩ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ባጭሩ ፡ ከጠቀስናቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ አሁን ፡ በደንብ ፡ ማስተዋወቅ ፡ ይገባናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

የታሪካችን ፡ ጀግና ፡ ሴት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ በጥቂቱ ፡ ያነሣናት ፡ የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ልጅ ፡ እንደሆነች ፡ አንባቢ ፡ በመላ ፡ ሳያውቅ ፡ አልቀረም ። ይህ ፡ ታሪክ ፡ ሲጻፍ ፡

ዕድሜዋ ፡ አስራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነበር ። ውበቷም ፡ ፍጹም ፡ ሙሉ ፡ ሆኖ ፡ አብቦ ፡ ነበር ። አባቷ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ቢወዳትም ፡ ቅሉ ፡ በተለመደው ፡ ሻካራ ፡ ጠባዩ ፡ ያስተዳድራታል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ያሰኛትን ፡ ሁሉ ፡ ለመፈጸም ፡ በተቻለው ፡ ይሞክራል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በአራዊት ፡ ጠባዩ ፡ ያስፈራራታል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ እሱ ፡ ላይ ፡ መለጠፏን ፡ ቢያውቅም ፡ እምነት ፡ ሊጥልባት ፡ ግን ፡ አልቻለም ። ስሜቷንና ፡ ሐሳቧን ፡ ትደብቀው ፡ ነበር ። ምክንያቱም ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ሁናቴ ፡ እንደሚቀበለው ፡ ከቶ ፡ ስለማታውቅ ፡ ነው ። ጓደኛም ፡ የላትም ። አስተዳደጓም ፡ የብቸኝነት ፡ ነበር ። የሰፈሩ ፡ ሰው ፡ ሚስቶችና ፡ ሴት ፡ ልጆቻቸው ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ እምብዛም ፡ አይጎበኙትም ። ምክንያቱም ፡ እርሱ ፡ መጫወትና ፡ ማውጋት ፡ የሚወደው ፡ ከወንዶች ፡ ጋር ፡ እንጂ ፡ ከሴቶች ፡ ጋር ፡ ስላልሆነ ፡ ነው ። ቆንጂት ፡ ባባቷ ፡ ድግስ ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ እንግዳዎች ፡ ጋር ፡ አብራ ፡ የምትቀርበው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነው ። በአስራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የፈረንሳይ ፡ ደራሲዎች ፡ ድርሰት ፡ የተመላው ፡ ሰፊ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እሷ ፡ እንድትጠቀምበት ፡ ቀርቦላታል ። አባቷ ፡ ግን ፡ « ወደር ፡ የሌለው ፡ ወጥ ፡ ቤት ፡ » ከሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ስላላነበበ ፡ ልጁ ፡ ደህና ፡ መጽሐፍ ፡ እንድታነብ ፡ በመምረጥ ፡ ረገድ ፡ ሊረዳት ፡ አልቻለም ። ማሻም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጽሐፎች ፡ ካነበበች ፡ በኋላ ፡ የፍቅር ፡ መጽሐፎችን ፡ መረጠች ። በዚህ ፡ አኳኋንም ፡ ትምህርቷን ፡ ለመጨረስ ፡ ቻለች ። የመጀመሪያ ፡ አስተማሪዋ ፡ ማድሚዜል ፡ ሚሚ ፡ ትባል ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በዚች ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ እምነት ፡ ጥሎባት ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ወዳጅነት ፡ ያስገኘው ፡ ፍሬ ፡ በጉልህ ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፡ በምሥጢር ፡ ወደሌላው ፡ እርስቱ ፡ አዛወራት ።

ሆኖም ፡ ማድሚዜል ፡ ሚሚ ፡ መልካራ ፡ ትዝታ ፡ ት ታ ፡ ሄደች ። በተፈጥሮዋ ፡ መልካም ፡ ልጃገረድ ፡ ነበረች ። በኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ዘንድ ፡ የነበራትንም ፡ መወደድ ፡ አ ልፋ ፡ ተርፋ ፡ ባለማደፍረሷ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ እርሷ ፡ ብቻ ፡ የተለየች ፡ ሆና ፡ ተገኘች ። ሌሎቹን ፡ የሚያቀርባቸውን ፡ ሴቶች ፡ ግን ፡ በየጊዜው ፡ ይለዋወጣቸው ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ማድሚዜል ፡ ሚሚን ፡ ከሌሎቹ ፡ አብልጦ ፡ ይ ወዳት ፡ ነበር ። የማድሚዜል ፡ ሚሚን ፡ ደቡባዊ ፡ መልክ ፡ የያዘና ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ የሞላው ፡ ዓይነ ፡ ጥቋቁር ፡ ጠረን ገሎ ፡ ቢጤ ፡ ልጅ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ያሳድግ ፡ ነበር ። በ መስኮቱ ፡ በኩል ፡ በባዶ ፡ እግራቸው ፡ የሚሯሯጡት ፡ እ ያሌ ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ መልካቸው ፡ ቁርጥ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችን ፡ ቢመስልም ፡ የገባር ፡ ልጆች ፡ ተብ ለው ፡ ይጠሩ ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ይህን ፡ ትንሽ ፡ ልጁን ፡ ሳሻን ፡ ፈረንሳይኛ ፡ የሚያስተምርለት ፡ መምህር ፡ ከሞስኮ ፡ ወደፖክሮቭስኮዬ ፡ አስመጣ ። መምህሩም ፡ አ ሁን ፡ በገለጽነው ፡ ሁናቴ ፡ ላይ ፡ ደረሰ ።

የዚህ ፡ ሰው ፡ ደርባባነትና ፡ ትህትና ፡ በኪሪላ ፡ ፔትሮ ቪች ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ ስሜት ፡ አሳደረበት ። ዲፕሎማው ንና ፡ እንዲሁም ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ በግል ፡ መምህርነት ፡ መ ሥራቱን ፡ የሚመሰክር ፡ ከኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ዘመድ ፡ ጋ ፡ የተጻፈ ፡ ደብዳቤ ፡ አቀረበ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ይህን ፡ ሁ ሉ ፡ መረመረና ፡ በፈረንሳዊው ፡ ሰው ፡ ወጣትነት ፡ ብቻ ፡ ሳ ይደሰት ፡ ቀረ ። ይሄውም ፡ ለመምህርነት ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ ትዕግስተኛና ፡ የበሰለ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ብሎ ፡ በመገመት ፡ ሳይሆን ፡ ሌላ ፡ ጥርጣሬ ፡ ስላደረበት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ጥ ርጣሬውን ፡ በፍጥነት ፡ ለማስወገድ ፡ ሲል ፡ ማሻ ፡ ወደር ሱ ፡ እንድትመጣ ፡ አዘዘ ። እርሱ ፡ ፈረንሳይኛ ፡ ስለማይና ገረም ፡ ማሻ ፡ እንድታስተረጉም ፡ አደረገ ።

« ነይ ፡ ወዲህ ፡ ማሻ ። ግድየለም ፡ እቀጥርሃለሁ ፡ በይ
ና ፡ ለዚህ ፡ ለሙሴ ፡ ንገሪው ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጃገረዶቼን ፡
እንዳትነካ ፡ በይና ፡ አስጠንቅቂው ። የነካህ ፡ እንደሆን ፡ አ
ንተ ፡ የውሻ ፡ ልጅ ፡ አሳይሃለሁ … በይ ፡ ማሻ ፡ ተርጉሚ
ለት ። »

ማሻ ፡ አፈረች ። ወደ ፡ መምህሩም ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ « ጠ
ባይህን ፡ አሳምረህ ፡ እንደምትኖር ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ ይሉሃ
ል ፡ » ስትል ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ነገረችው ።

ፈረንሳዩም ፡ ወደርሷ ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፡ « ምንም ፡ እንኳ ፡
መወደድን ፡ ባላገኝም ፡ መከበርን ፡ እንደማላጣ ፡ ተስፋ ፡ አ
ለኝ ፡ » ሲል ፡ መለሰ ።

ማሻም ፡ መልሱን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ተረጐመች ።

« ማለፊያ ፡ ማለፊያ ። መወደድም ፡ ሆነ ፡ መከበር ፡
አያስፈልገውም ። ተግባሩ ፡ ሳሻን ፡ መጠበቅና ፡ ጅኦግራፊ
ና ፡ ሰዋስው ፡ ማስተማር ፡ ነው ። ተርጉሚለት ። »

ማሻም ፡ ያባቷን ፡ ሸካራ ፡ ንግግር ፡ አለስልሳ ፡ ተረጐ
መችና ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ፈረንሳዩን ፡ አሰናበተው ። ፈ
ረንሳዊውም ፡ ከቤቱ ፡ ባንደኛው ፡ ወገን ፡ ወደተዘጋጀለት ፡ ክ
ፍል ፡ ሄደ ።

ማሻ ፡ ፈረንሳዊውን ፡ ከቁም ፡ ነገርም ፡ አልቆጠረችውም ።
በመኳንንት ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ የንቀትና ፡ የጥላቻ ፡ መንፈ
ስ ፡ ስለወረሰች ፡ መምህር ፡ ሲባል ፡ በሷ ፡ ቤት ፡ እንደአ
ሽከር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ አናጢ ፡ ቢጤ ፡ የሚቆጠር ፡ ሰው ፡
ነው ። አሽከርና ፡ አናጢም ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ ከሰው ፡ ቁጥር ፡
የሚገቡ ፡ አይደሉም ። በዚህ ፡ የተነሳ ፡ በሙሴ ፡ ዴፎርዥ ፡
ላይ ፡ ያሳደረችበትን ፡ ስሜት ፡ ልትረዳው ፡ አልቻለችም ።
ምን ፡ ያህል ፡ ግራ ፡ እንደገባውና ፡ እንደተናደደ ፡ ድምጹ
ም ፡ እንዴት ፡ እንደተለወጠ ፡ ፈጽሞ ፡ አልተመለከተችም ።

ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ በየጊዜው ፡ ታገኘው ፡ ነበር ።
ነገር ፡ ግን ፡ እምብዛም ፡ ቀና ፡ ብላ ፡ አታየውም ፡ ነበር ። ኋ
ላ ፡ ግን ፡ በድንገት ፡ ስለርሱ ፡ የነበራት ፡ አስተያየት ፡ ተለወ
ጠና ፡ በሌላ ፡ ዓይን ፡ ትመለከተው ፡ ጀመር ።

በኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡
የድብ ፡ ግልገሎች ፡ ያድጉ ፡ ነበር ። እነርሱም ፡ የፖክሮቭ
ስኮዬ ፡ ጌታ ፡ ዋና ፡ መደሰቻው ፡ ነበሩ ። ገና ፡ በሕጻንነታ
ቸው ፡ ድቦቹ ፡ ወደ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ክፍል ፡ እንዲመ
ጡ ፡ ይደረግና ፡ ከድመትና ፡ ከውሻ ፡ ቡችላ ፡ ጋር ፡ እያታ
ገለ ፡ ጌትየው ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ይጫወታል ። ባደጉም ፡ ጊ
ዜ ፡ በሰንሰለት ፡ ይታሠሩና ፡ ደንበኛውን ፡ ጨዋታ ፡ ይጀ
ምራሉ ። ለምሳሌ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ መስ
ኮት ፡ አቅጣጫ ፡ አንድ ፡ ድብ ፡ ይታሠርና ፡ በፊቱ ፡ እያ
ሌ ፡ ምስማር ፡ ያገጠጠበት ፡ ባዶ ፡ የወይን ፡ በርሚል ፡ ይቆ
ማል ። ድቡም ፡ በርሚሉን ፡ ያሸትና ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ በመዳ
ፉ ፡ ይነካዋል ። ምስማሩ ፡ ሲወጋውም ፡ ይቆጣና ፡ ከበርሚ
ሉ ፡ ጋር ፡ ትንቅንቅ ፡ ይጀምራል ። ምስማሩም ፡ ይበልጥ ፡
ይጎዳዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ድቡ ፡ ንዴት ፡ ያሰክረውና ፡ እያ
ጓራ ፡ እበርሚሉ ፡ ላይ ፡ እየተወረወረ ፡ ይፈጠፈጣል ። በከ
ንቱ ፡ የሚናደድበትን ፡ በርሚል ፡ ከፊቱ ፡ ላይ ፡ ሲያነሱለት ፡
ብቻ ፡ ያርፋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ድቦች ፡ እሰረ
ገላ ፡ ላይ ፡ ይታሠሩና ፡ እንግዶች ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ እ
ሰረገላው ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድቦቹ ፡ ጋሪ
ውን ፡ ወደፈለጉበት ፡ አቅጣጫ ፡ እየጐተቱ ፡ ይወስዱታል ።
ዋናው ፡ የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ መደሰቻ ፡ ግን ፡ የሚቀጥለ
ው ፡ ነው ።

አንድ ፡ የተራበ ፡ ድብ ፡ ባንድ ፡ ባዶ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡
እግድግዳ ፡ ላይ ፡ በተመታ ፡ ቀለበት ፡ በገመድ ፡ ይታሠራል ።
የገመዱም ፡ እርዝማኔ ፡ በክፍሉ ፡ ወርድ ፡ መጠን ፡ ስለሆነ ፡

ካውሬው ፡ አፍ ፡ ለመዳን ፡ የሚቻለው ፡ እሬት ፡ ለፊቱ ፡ ማዶ ፡ ባለው ፡ ማዕዘን ፡ በመቆም ፡ ብቻ ፡ ነው ። አንድ ፡ አላዋቂ ፡ ሰው ፡ ወደበሩ ፡ ጋ ፡ እንዲመጣ ፡ ይደረግና ፡ አዘንግተው ፡ ወደውስጥ ፡ ይገፉታል ። በሩንም ፡ ከውጭ ፡ በኩል ፡ ከቆለፉበት ፡ በኋላ ፡ ምስኪኑ ፡ ሰው ፡ ጸጉሩ ፡ ከሚኰሰኵሰው ፡ የድብ ፡ ባህታዊ ፡ ጋር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይቆማል ። ይህ ፡ የፈረደበት ፡ እንግዳ ፡ ልብሱ ፡ ከተቀደደና ፡ ሰውነቱ ፡ ከተቧጠጠ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ መዳኛውን ፡ ቦታ ፡ ፈልጐ ፡ ያገኝና ፡ ይቆማል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የተራበው ፡ አውሬ ፡ ከእርሱ ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ እርቆ ፡ ሲዘልና ፡ በኋላ ፡ እግሩም ፡ ብድግ ፡ እያለ ፡ ሲያጓራ ፤ ገመዱንም ፡ በጥሶ ፡ ወደርሱ ፡ ለመድረስ ፡ ሲታገል ፡ ሰውዬው ፡ እግድግዳው ፡ ላይ ፡ ተለጥፎ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ መቆየት ፡ ግድ ፡ ይሆንበታል ። እነሆ ፡ የዚህ ፡ የሩሲያ ፡ መኰንን ፡ እረቂቅ ፡ መደሰቻ ፡ ይኸ ፡ ነበር!

የፈረንሳዩ ፡ መምህር ፡ መጥቶ ፡ ጥቂት ፡ ቀናት ፡ ከሰነበተ ፡ በኋላ ፡ ትሮዬኩሮቭ ፡ የድቡን ፡ ቤት ፡ ሊያቀምሰው ፡ አሰበ ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጧት ፡ መምህሩን ፡ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ አስጠራውና ፡ በጨለመ ፡ ቦታ ፡ እየመራ ፡ ሲወስደው ፡ ድንገት ፡ ከጐን ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ በር ፡ ተከፈተ ። ሁለት ፡ አሽከሮችም ፡ ፈረንሳዩን ፡ ወደክፍሉ ፡ ገፍተው ፡ አስገቡትና ፡ በሩን ፡ ከውጭ ፡ ቆለፉበት ። መምህሩ ፡ ድንጋጤው ፡ ሲያልፍለት ፡ ከታሰረ ፡ ድብ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ መቆሙን ፡ አወቀ ። አውሬውም ፡ ከሩቁ ፡ እያሸተተና ፡ እያጉረመረመ ፡ በኋላ ፡ እግሩ ፡ ቆሞ ፡ ወደእንግዳው ፡ እየገሠገሠ ፡ መጣ ። ፈረንሳዩም ፡ ሰውዬ ፡ ሳይርበደበድና ፡ ሳይራወጥ ፡ ድቡን ፡ በርጋታ ፡ ጠበቀው ። አውሬው ፡ ሲጠጋው ፡ ዴፎርዥ ፡ ከኪሱ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ሽጉጥ ፡ አውጥቶ ፡ በተራበው ፡ ድብ ፡ ጆሮ ፡ ላይ ፡ አስደገፈና ፡ ተኰሰው ። ድቡም ፡ ተንከባሎ ፡ ወደቀ ። ሰው ፡ ሁሉም ፡ ወደክፍሉ ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ።

በሩም ፡ ወለል ፡ ብሎ ፡ ተከፈተ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ በ ሰራው ፡ ቀልድ ፡ ውጤት ፡ እየተደነቀ ፡ ገባ ።

ኋላም ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጨዋታ ፡ መ ኖሩን ፡ ለዱፎርዥ ፡ ማን ፡ እንዳስጠነቀቀውና ፡ በኪሱስ ፡ ሽጉጥ ፡ አቀባብሎ ፡ ለምን ፡ እንደገባ ፡ ሙሉ ፡ ማስረጃ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠየቀ ። ማሻን ፡ አስጠራት ። እሷም ፡ በፍጥነት ፡ መጥታ ፡ ያባቷን ፡ ጥያቄ ፡ ለፈረንሳዩ ፡ አስተረጐመች ።

« ስለ ፡ ድቡ ፡ ምንም ፡ የሰማሁት ፡ ነገር ፡ የለኝም ። ይ ሁን ፡ እንጂ ፡ ሽጉጥ ፡ ዘወትር ፡ አይለየኝም ። ምክንያቱም ፡ በእንግድነት ፡ ላይ ፡ የሚደርስብኝን ፡ ውርደት ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ ለማለፍ ፡ ስለማልችል ፡ ነው ፡ » ሲል ፡ ዱፎርዥ ፡ መለሰ ።

ማሻ ፡ በመደነቅ ፡ ተመለከተችውና ፡ ቃሉን ፡ ለኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ተረጐመች ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥ ፡ ድቡ ፡ እንዲነሳና ፡ ቆዳው ፡ እንዲገፈፍ ፡ አዘዘ ። ቀጥሎም ፡ ወደሰዎቹ ፡ ዘወር ፡ አለና ፤ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

« ጐበዝ ፡ ሰው ፡ አይደለምን? ፍርሃት ፡ የሚባል ፡ ነገ ር ፡ ጨርሶ ፡ የለበትም ። በውነቱ ፡ እኔ ፡ እራሴ ፡ ልመሰክር ለት ፡ እችላለሁ ። »

ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ፈረንሳዩን ፡ ሰውዬ ፡ ወደደው ። ሁለተኛ ፡ ሊፈታተነውም ፡ ከቶ ፡ አልሞከረም ።

ይህ ፡ ሁናቴ ፡ ይልቁንም ፡ በማሻ ፡ ላይ ፡ የበለጠ ፡ ስሜት ፡ አሳደረባት ። ዱፎርዥ ፡ በሞተው ፡ ድብ ፡ አጠገብ ፡ በጸጥታ ፡ ቆሞ ፡ በርጋታ ፡ እንዴት ፡ እንዳነጋገራት ፡ በሐሳቧ ፡ እየመጣ ፡ ይታያት ፡ ጀመር ። ጀግንነት ፤ ኩራትና ፡ ክብርን ፡ መጠበቅ ፡ በተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ የሚገኝ ፡ ስጦታ ፡ አለመሆ ኑን ፡ ተገነዘበች ። ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮም ፡ ለወጣቱ ፡ መም

ሀር ፡ በየጊዜው ፡ እያደገ ፡ የሚሄድ ፡ ክብር ፡ ታሳየው ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ መቀራረብና ፡ መወዳ ጀት ፡ ተፈጠረ ። ማሻ ፡ እጅግ ፡ የተዋበ ፡ ድምጽና ፡ ታላቅ ፡ የሙዚቃ ፡ ስጦታ ፡ ስለነበራት ፡ ዴፎርዥ ፡ ሊያስተምራት ፡ ፈቀደ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ማሻ ፡ ሳታውቀው ፡ ከዴፎርዥ ፡ ጋር ፡ ፍቅር ፡ እንደያዛት ፡ አንባቢው ፡ በቀላሉ ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል ።

## ሁለተኛ ፡ ክፍል ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

ከአሁን ፡ በፊት ፡ በጠቀስነው ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ አጥቢያ ፡ እንግዶቹ ፡ መምጣት ፡ ጀመሩ ። አንዳንዶቹ ፡ በዋናው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፤ አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡ በጋሻጃግሬውና ፡ በቄሱ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ በሐብታም ፡ ባላገሮች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዲያርፉ ፡ ተደረገ ። ጋጣውን ፡ የእንግዶቹ ፡ ፈረሶች ፡ መሉት ። የሠረገላው ፡ ቤትና ፡ አጥር ፡ ግቢውም ፡ እንደዚሁ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሠረገላዎች ፡ ተመላ ። ጧት ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ የቅዳሴ ፡ ደወል ፡ ሲደወል ፡ ሁሉም ፡ ወደአዲሱ ፡ የጡብ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ አመሩ ።

ቤተ ፡ ክርስትያኑን ፡ ያሠራው ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ነው ። በየዓመቱም ፡ ስጦታ ፡ እያደረገ ፡ ያጌጠዋል ። ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ለመሳለም ፡ የመጡ ፡ ብዙ ፡ ክቡራን ፡ መኳንንት ፡ ስለነበሩ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያኑ ፡ ሞላ ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ተራ ፡ ገበሬዎቹ ፡ በቤተ ፡ ክርስትያኑ ፡ ቅጥር ፡ ዙሪያ ፡ ቆሙ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ገና ፡ ስላልመጣም ፡ ስርዓተ ፡

ቅዳሴው ፡ አልተጀመረም ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ ኪሪላ ፡ ፔ ትሮቪች ፡ በስድስት ፡ ፈረሶች ፡ በሚጐተት ፡ ጋሪ ፡ እየተሳበ ፡ መጣና ፡ ከልጁ ፡ ከማሻ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ወደተዘጋጀለት ፡ ቦታ ፡ በዝግታ ፡ ሄደ ። የወንዱና ፡ የሴቱ ፡ ዓይን ፡ ሁሉ ፡ ወደልጂቱ ፡ ተወረወረ ። የመጀመሪያዎቹ ፡ ቁንጅናዋን ፡ ለማድነቅ ፡ ነው ። ሁለተኛዎቹ ፡ ደግሞ ፡ አለባበሷን ፡ ለማየት ፡ ነው ። ቅዳሴው ፡ ተጀመረ ፤ ቀሳውስቱና ፡ ዲያቆናቱም ፡ ማዜም ፡ ጀመሩ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ አብሮ ፡ ያዜም ፡ ጀመር ። ወደግራና ፡ ወደቀኝ ፡ ሳይመለከትም ፡ ፀሎቱን ፡ ቀጠለ ። ዲያቆኑ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ « ይህን ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ላሳነጹት ፡ ለ ... » እያለ ፡ ስሙን ፡ ሲያነሣው ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ይሰግድ ፡ ነበር ።

ቅዳሴው ፡ ተፈጸመና ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ መጀመሪያ ፡ ሄዶ ፡ መስቀሉን ፡ ተሳለመ ። የቀሩትም ፡ በተራቸው ፡ እንደዚሁ ፡ ተሳለሙ ። ኋላም ፡ ጐረቤቱ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እየመጡ ፡ እጅ ፡ ነሱት ። ሴት ፡ ወይዘሮቹም ፡ ማሻን ፡ ከበቧት ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ከቤተ ፡ ክርስትያኑ ፡ ሲወጣ ፡ መላውን ፡ ሰው ፡ ለምሳ ፡ ጋበዘና ፡ እሰረገላው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደቤቱ ፡ አመራ ። እንግዶቹም ፡ በየሰረገላቸው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ ተከተሉት ።

ቤቱ ፡ በእንግዳ ፡ ተመላ ። አዲስ ፡ እንግዶች ፡ በላይ ፡ በላዩ ፡ ስለመጡም ፡ የቤቱን ፡ ባለቤት ፡ ለመገናኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆነ ። ሴት ፡ ወይዘሮቹ ፡ ዘመኑ ፡ ያለፈበትን ፡ ውድ ፡ ቀሚሳቸውን ፡ ለብሰውና ፡ ያልማዝና ፡ የሉል ፡ ጌጣቸውን ፡ አድርገው ፡ በዙሪያ ፡ ተቀመጡ ። ወንዶቹም ፡ የዓሣ ፡ እንቁላልና ፡ የቮድካ ፡ አረቂ ፡ ያለበትን ፡ ጠረጴዛ ፡ ከበው ፡ እየጮኹ ፡ ያወሩ ፡ ጀመር ፤ በታላቁ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ገበታ ፡ የተዘጋጀው ፡ ለሰማኒያ ፡ ሰዎች ፡ ነበር ። አሳላፊዎቹም ፡ መጠጥ ፡ በያይነቱ ፡ የያዙ ፡ ጠርሙሶች ፡ እገበታው ፡

ላይ ፡ ለመደርደርና ፡ የገበታውንም ፡ ልብስ ፡ ለማስተካከል ፡ ጉድ ፡ ጉድ ፡ ይሉ ፡ ነበር ። በመጨረሻ ፡ የእልፍኝ ፡ አስከል ካዩ ፡ ምሳ ፡ ቀርቧል ፡ ሲል ፡ አስታወቀ ። መጀመሪያ ፡ ኪ ራላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ተቀመጠ ። ቀጥሎም ፡ ሴት ፡ ወይዛዝርቱ ፡ እንደየማዕርጋቸው ፡ በርጋታ ፡ ቦታቸውን ፡ ያዙ ። ወጣቶ ቹም ፡ ሴቶች ፡ እንደደነገጠ ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ አንድነት ፡ እ ጅብ ፡ ብለው ፡ ተቀመጡ ። ከፊት ፡ ለፊታቸውም ፡ ወንዶቹ ፡ ተቀመጡ ። በገበታው ፡ መጨረሻም ፡ መምህሩና ፡ ሳሻ ፡ ተ ቀመጡ ።

አሳላፊዎቹ ፡ ለእንግዶቹ ፡ እንደየማዕርጋቸው ፡ ማሳለ ፍ ፡ ጀመሩ ። የሰሐኑና ፡ የማንኪያው ፡ ኳኳታም ፡ ከንግዶቹ ፡ ጩኸት ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ተደባለቀ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ገ በታውን ፡ በደስታ ፡ ዓይን ፡ ተመለከተና ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ለ ጋስ ፡ አስተናጋጅ ፡ በመሆኑ ፡ ጥልቅ ፡ ደስታ ፡ ተሰማው ። ል ክ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በስድስት ፡ ፈረሶች ፡ የሚሳብ ፡ ሰረገላ ፡ ወ ደ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ ገባ ።

« ማነው? » አለ ፡ ጌትዮው ።

« አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ነው ፡ » ሲሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መለሱ ።

በሩ ፡ ተከፈተ ። ፊተ ፡ ክብና ፡ ፊንጣጣ ፡ የጠቀጠቀው ፤ ሦስት ፡ ድርብርብ ፡ አገጭ ፡ ያንጠለጠለ ፡ አንድ ፡ የሃምሳ ፡ ዓመት ፡ ግድንግድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እየነሳና ፡ ፈገግ ፡ እያለ ፡ ይቅርታም ፡ ለመጠየቅ ፡ እየተዘጋጀ ፡ ወደገበታ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ።

« መጠጊያ ፡ እንደሆን ፡ እዚህ ፡ አለ! ግባና ፡ ተቀመጥ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ። ለቅዳሴ ፡ ለምን ፡ እንዳልመጣህና ፡ ለ ምሳስ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደዘገየህ ፡ እስቲ ፡ ንገረን ። ለ ወትሮህ ፡ እንኳ ፡ ኃይማኖታዊና ፡ ግብግም ፡ ወዳድ ፡ ነበር ክ ፡ » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጠየቀው ።

አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ ያፍ ፡ ፎጣውን ፡ ወደአረንጓ ዴ ፡ ካባው ፡ የቁልፍ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ አስገብቶ ፡ እያሰረ ፡ « ይቅርታ ፤ ጥፋተኛ ፡ ነኝ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ሆይ! መንገ ድ ፡ የጀመርኩት ፡ እንኳ ፡ ገና ፡ በጊዜ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አስር ፡ ቬርስታ ፡ እንኳ ፡ ሳልሄድ ፡ ከሰረገላዬ ፡ የፊት ፡ እግሮ ች ፡ ያንደኛው ፡ ላስቲክ ፡ ለሁለት ፡ ጉምድ ፡ አለ ። ደግነቱ ፡ ከመንደር ፡ እሩቅ ፡ ስላልነበርኩ ፡ ሰዎቼ ፡ ሄደው ፡ ብረት ፡ ሰ ሪውን ፡ ፈልገው ፡ እስኪያስሩ ፡ ድረስ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ አለ ፈ ። ምን ፡ ይደረግ ። በኪስቴኖቭካ ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ አቋር ጬ ፡ ለመምጣት ፡ ስለፈራሁም ፡ በዙሪያ ፡ ጥምዝ ፡ መንገ ድ ፡ መምጣት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ። »

« እረ ፡ ግና! » ብሎ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ነገሩን ፡ አ ቋረጠውና ፤

« ለካ ፡ ጉበዝ ፡ ሰው ፡ አይደለህም! ምንድነው ፡ የሚያ ስፈራህ? » ሲል ፡ ጠየቀው ።

« ወዳጄ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ምንድነው ፡ የሚያስፈ ራህ ፡ ትለኛለህ ፡ እንዴ? ዱብሮቭስኪይ ፡ ነዋ! እሱ ፡ ሰውን ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ የሚያስገባው ፡ በድንገት ፡ ነው ። ማንንም ፡ መ ንገደኛ ፡ እንደማያሳልፍም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያውቃል ። በተለ ይም ፡ እኔን ፡ ቢያገኘኝ ፡ አይለቀኝም ። »

« በተለይ ፡ አንተን ፡ የማይለቅበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድ ነው ፡ ወንድሜ? »

« ምነዋ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ነገሩን ፡ ስታውቀው ። የ ሟቹን ፡ የአንድሬይ ፡ጋቭሪሎቪችን ፡ ክስ ፡ እረሳኸው ፡ እን ዴ? ምነው ፡ እንኳ ፡ አንተን ፡ አስደስታለሁ ፡ ብዬ ፡ ማለት ፡ ለትክክለኛው ፡ ፍርድና ፡ ለንጹህ ፡ ሕሊና ፡ ስል ፡ አንድሬይ ፡ ጋቭሪሎቪች ፡ የኪስቴኖቭካ ፡ መሬት ፡ የያዘው ፡ በሕግ ፡ ሳይሆ ን ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አልመሰከርኩም? ሟቹስ ፡ ነ ፍሱን ፡ ይማርና ፡ እበቀልሃለሁ ፡ አላለኝም? ልጁስ ፡ ያባቱን ፡

ቃል ፡ ይፈጽም ፡ እንደሆን ፡ ማን ፡ ያውቃል? እስካሁን ፡ መቸም ፡ እግዜር ፡ ጠብቆኛል ። ለጊዜው ፡ የዘረፉኝም ፡ አንድ ፡ ጐተራ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ምን ፡ አለ ፡ በለኝ ፡ ውለው ፡ አድረው ፡ ቤቴንም ፡ ሳይዘርፉት ፡ አይቀሩም ። »

« እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡ ያንተ ፡ ቤትስ ፡ ሊዘረፍ ፡ የሚገባ ፡ ነው ። ያቺ ፡ ትንሽ ፡ ሣጥንህ ፡ በገንዘብ ፡ አፍ ፡ ድረስ ፡ ጢም ፡ እንዳለች ፡ እርገጠኛ ፡ ነኝ ፡ » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በቀልድ ፡ አኳኋን ፡ ተናገረ ።

« የለም ፤ የለም ፤ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። ሙሉ ፡ የነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ ዱሮ ፡ ቀረ ። አሁንስ ፡ ባዶ ፡ ናት ። »

« ወዴት ፤ ወዴት ፤ ፓፍኑቲች ። እናውቅሃለን ፡ እኮ ። ገንዘብህን ፡ እምን ፡ ላይ ፡ ታውለዋለህ? ኑሮህ ፡ እንደሆን ፡ እንደ ፡ አሳማ ፡ ነው ። እንግዳም ፡ አትቀበል ። ባላገሮችህንም ፡ እንደላም ፡ ነው ፡ የምታልባቸው ። ገንዘብ ፡ ከማጐር ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ታስባለህና ፡ ነው ። »

ፓፍኑቲች ፡ ያለውድ ፡ ፈገግ ፡ አለና ፡ « ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ሆይ ፤ የምትናገረው ፡ ቀልድ ፡ ነው ፤ በውነቱ ፡ እምልልሃለሁ ፡ ምንም ፡ የለኝ ፡ » አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፓፍኑቲች ፡ የወዳጁን ፡ መርዘኛ ፡ ቀልድ ፡ ለመሸሽ ፡ ሲል ፡ በቅቤ ፡ የራሰ ፡ የአሳ ፡ ዳቦ ፡ ባፉ ፡ ሙሉ ፡ ገመጠና ፡ ዋጠ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ተወውና ፡ ወደአዲሱ ፡ ምስለኔ ፡ ዘወር ፡ አለ ። ምስለኔው ፡ እኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤት ፡ ሲጋበዝ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜው ፡ ነበር ። የተቀመጠውም ፡ በገበታው ፡ ጫፍ ፡ ከመምህሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበር ።

« ታዲያስ ፡ አቶ ፡ ምስለኔ ፤ ዱብሮቭስኪይን ፡ አትይዘውምን? » ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ምስለኔውም ፡ ደንግጦ ፡ እጅ ፡ እየነሳና ፡ ፈገግ ፡ እያለ ፡ በመኰላተፍ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፤

« ክቡር ፡ ሆይ! በተቻለን ፡ ሁሉ ፡ እንሞክራለን ። »

« እ! በተቻለን ፡ ሁሉ ፡ እንሞክራለን! ሰው ፡ ሁሉ ፡ በተ ቻለው ፡ ሲሞክር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሆኖ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ጠቃሚ ፡ ውጤት ፡ አልተገኘም ። መያዝስ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ያስፈልጋል? የዱብሮቭስኪይ ፡ ወንበዴነት ፡ ለምስለኔ ፡ ሰርጉ ፡ ነው ። ለጉዞና ፡ ለምርመራ ፡ የሚወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ እኪሱ ፡ ያስገባል ። ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጠቃሚ ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ ተብሎ ፡ ይጥፋ? እውነት ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ አቶ ፡ ምስለኔ? »

ምስለኔው ፡ ግራ ፡ ስለገባው ፡ « እውነት ፡ ነው ፡ ክቡር ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ » ሲል ፡ መለሰ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እንግዶቹ ፡ በሳቅ ፡ ፈነዱ ።

« ሰውዬው ፡ ዕውነቱን ፡ በመናገሩ ፡ እወደዋለሁ ። ሆኖም ፡ ሟቹ ፡ ምስለኔ ፡ ታራስ ፡ አሌክሴዬቪች ፡ አጉድሎና ል ። አቃጥለው ፡ ባይገድሉት ፡ ኖሮ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ቀበሌው ፡ ጸጥታ ፡ ባገኘ ፡ ነበር ። ስለዱብሮቭስኪይ ፡ ምን ፡ ትኩስ ፡ ወሬ ፡ አለ? በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የት ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ታየ ፡ ይባላል? » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጠየቀ ።

« እኔ ፡ ቤት ፡ ነበር ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ሆይ ። ያለፈው ፡ ማክሰኞ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ እህል ፡ በልቷል ፡ » የሚል ፡ የሴት ፡ ድምጽ ፡ ተሰማ ።

የሰው ፡ ሁሉ ፡ ዓይንም ፡ ወደ ፡ አና ፡ ሳቪሽና ፡ ግሎቦቫ ፡ ዞወር ፡ አለ ። ይህች ፡ ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ሴት ፡ በደግነቷና ፡ በዘወትር ፡ የደስታ ፡ መንፈሷ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የተወደደች ፡ ነበረች ። እሷ ፡ የምትለውን ፡ ለመስማት ፡ ሁሉም ፡ በናፍቆት ፡ ጠበቁ ።

« ከሦስት ፡ ሳምንት ፡ በፊት ፡ ለልጄ ፡ ለቫኒውሻ ፡ ገንዘብ ፡ ለመላክ ፡ አሽከሬን ፡ ወደፖስታ ፡ ቤት ፡ ላክሁት ። ልጄን ፡ አላማግጠውም ። ብፈልግም ፡ ደግሞ ፡ አልችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ እንደምታውቁት ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ መኰንን ፡ በ

ጽዳት ፡ መኖር ፡ ስላለበት ፡ የማገኛትን ፡ ጥቂት ፡ ገቢ ፡ ለል ጇ ፡ ለቫኒውሻ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ አካፍለዋለሁ ። በዚህ ፡ የተነሣ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ሩብል ፡ ላክሁለት ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ካንደዬም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ባሳቤ ፡ ቢመጣ ም ፡ ከተማው ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ወዲህም ፡ እግዜር ፡ ይጠብ ቅልኛል ፡ በማለት ፡ ተጽናናሁ ። ማታ ፡ ግን ፡ አሽከሬ ፡ ደሙ ፡ ምጥጥ ፡ ብሎና ፡ ልብሱ ፡ ተቀዳዶ ፡ በእግሩ ፡ ተመልሶ ፡ መ ጣ ። ባየሁትም ፡ ጊዜ ፡ « ምን ፡ ሆንክ! ምንድነው ፡ ነገሩ! » ብዬ ፡ ጮኹ ። « እና ፡ ሳቪሽና ፡ ሆይ ፤ እነዚያ ፡ ወንበዴዎ ች ፡ ዘረፉኝ ፤ ሊገድሉኝም ፡ ነበር ፤ ዱብሮቭስኪይም ፡ እራሱ ፡ እዚያው ፡ ነበር ። ሊሰቅለኝ ፡ አሰበና ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ እራርቶል ኝ ፡ ለቀቀኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ገንዘቡንም ፡ ፈረሱንም ፡ ሠረገላ ውንም ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ዘረፉኝ ፡ » አለና ፡ መለሰልኝ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የምናገረው ፡ ጠፋኝ ። አምላኬ ፡ ሆይ ፤ ልጄ ፡ ቫኒውሻ ፡ ምን ፡ ይበጀው ፡ እንግዲህ! አልኩኝ ። ምንም ፡ ለማድረግ ፡ ስላልቻልኩም ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፌ ፡ የሆነውን ፤ ነገ ር ፡ ሁሉ ፡ በዝርዝር ፡ ገለጽኩለትና ፡ ያላንዳች ፡ ሳንቲም ፡ ም ርቃቴን ፡ ብቻ ፡ ላክሁለት ።

ከአንድ ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ ወደ ፡ አጥር ፡ ግቢዬ ፡ ገባ ። አንድ ፡ ጄኔራልም ፡ ላይዎት ፡ እፈልጋለሁ ፡ ሲል ፡ ጠየቀ ። እኔም ፡ ም ን ፡ ቸገረኝ ፡ በደስታ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ እንዲገባ ፡ አዘ ዝኩ ። ዕድሜው ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ የሚሆን ፡ መ ልክ ፡ ጥቁርና ፡ ጸጉረ ፡ ጥቁር ፡ እሪዝና ፡ ጢም ፡ ያለው ፡ ቁ ርጥ ፡ ኩልኔቭን ፡ የሚመስል ፡ ሰው ፡[37] ገባ ። « የሚቼ ፡ ባለ ቤትዎ ፡ የኢቫን ፡ አንድሬየቪች ፡ ወዳጅና ፡ የጦር ፡ ጓደኛ ው ፡ ነኝ ፡ » ሲል ፡ እራሱን ፡ አስተዋወቀና ፡ « እርስዎ ፡ እ ዚህ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ስለማውቅ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ሳልፍ ፡ የ ጥንት ፡ ወዳጄን ፡ ባለቤት ፡ ሳልጠይቅ ፡ አልሄድም ፡ በማለ

ት ፡ ጕራ ፡ አልኩኝ ፡ » አለ ። እኔም ፡ እቤት ፡ የተገኘውን ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ አቀረብኩለትና ፡ ስለብዙ ፡ ነገር ፡ ስንጨዋወት ፡ ቆይተን ፡ በመጨረሻ ፡ የዱብሮቭስኪይ ፡ ወሬ ፡ ተነስቶ ፡ የደረሰብኝን ፡ አደጋ ፡ አጫወትኩት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጄኔራሉ ፡ ፊቱን ፡ ኰስተረና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፡ « የሚገርም ፡ ነገር ፡ ነው ። ዱብሮቭስኪይ ፡ የሚያጠቃው ፡ ጥቂቶችን ፡ ሐብታሞች ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ አይደለም ፡ ሲሉ ፡ ሰምቼ ፡ ነበር ። ያውም ፡ ቢሆን ፡ ደግሞ ፡ ድርሻውን ፡ ይወስዳል ፡ እንጂ ፡ ጨርሶ ፡ አይዘርፍም ። ሰው ፡ ይገድላል ፡ ብሎም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አምቶት ፡ አያውቅም ። አንድ ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራ ፡ ተደርጓልና ፡ አሽከርዎን ፡ ቢያስጠሩት ፡ መልካም ፡ ነው ። »

አሽከሬን ፡ አስጠራሁትና ፡ ቶሎ ፡ መጣ ። ጄኔራሉን ፡ ባየ ፡ ጊዜም ፡ ወዲያው ፡ ክው ፡ ብሎ ፡ ደነገጠ ።

« ዱብሮቭስኪይ ፡ እንዴት ፡ እንደዘረፈህና ፡ ሊሰቅልህስ ፡ እንዴት ፡ እንደፈለገ ፡ አጫውተን ፡ እስቲ ፡ ወንድሜ? » አለና ፡ ጄኔራሉ ፡ ጠየቀው ። አሽከሬም ፡ ተንቀጥቅጦ ፡ እጫማው ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፤

« ይማሩኝ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አጥፍቻለሁ ። ሰይጣን ፡ ነው ፡ ያሳሳተኝ ። ዋሽቻለሁ ፡ » አለ ።

« እንግዲያውስ ፡ ዕውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ ለእመቤትህ ፡ ንገራቸው ። እኔም ፡ አደምጣለሁ ፡ » ሲል ፡ ጄኔራሉ ፡ መለሰለት ።

አሽከሬ ፡ ግን ፡ ድንጋጤው ፡ ሊያልፍለት ፡ አልቻለም ።

« በልኰ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ የት ፡ እንዳገኘኸው ፡ ንገረን ፡ » አለና ፡ ጄኔራሉ ፡ ደግሞ ፡ ጠየቀው ።

« እሁለቱ ፡ የጥድ ፡ ዛፎች ፡ ጋ ፡ ነው ፡ ጌታዬ ። እሁለቱ ፡ የጥድ ፡ ዛፎች ፡ ጋ ። »

« ምን ፡ አለህ ፡ ታዲያ? »

« የማን ፡ አሽከር ፡ እንደሆንኩ ፤ ወደየትና ፡ ለምንስ ፡ ጉዳይ ፡ እንደምሄድ ፡ ጠየቀኝ ። »

« ቀጥሎስ? »

« ቀጥሎ ፡ ደብዳቤውንና ፡ ገንዘቡን ፡ ስጠኝ ፡ አለኝና ፡ ሰጠሁት ። »

« እሱስ ፡ ምን ፡ አደረገው? »

« ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ይቅርታ ፡ ያድርጉልኝ ። »

« እኰ ፡ ምን ፡ አደረገው? »

« ደብዳቤውንም ፡ ገንዘቡንም ፡ መለሰልኝና ፡ « ሂድ ፡ መንገድህን ፡ ቀጥል ፡ ወደፖስታው ፡ ቤት ፡ » አለኝ ።

« አንተስ ፡ ምን ፡ አደረግህ? »

« ምህረት ፡ ያድርጉልኝ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ! »

« ቆይ ፡ አሳይሃለሁ ፡ » አለ ፡ ጄኔራሉ ፡ ኰስተር ፡ ብሎ ፡ « እርስዎ ፡ ደግሞ ፡ እመቤቴ ፡ ሆይ ፡ የዚህን ፡ የወስላታ ፡ ሳጥን ፡ ያስበርብሩና ፡ እጁን ፡ ለእኔ ፡ ይስጡኝ ፤ አስተምረዋለሁ ። ዱብሮቭስኪይ ፡ እራሱ ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ መኰንን ፡ ስለነበር ፡ በሌላ ፡ መኰንን ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተግባር ፡ እንደማይ ፈጽም ፡ ማስታወስ ፡ አለብዎት ፡ » አለኝ ።

እኔም ፡ ክቡርነቱ ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ በመላ ፡ ስለገ ባኝ ፡ ልከራከር ፡ አልፈለግሁም ። ሰረገላ ፡ ነጂዎቹ ፡ አሽ ከሬን ፡ እሰረገላው ፡ ሳጥን ፡ ላይ ፡ አሰሩት ። ገንዘቡም ፡ ተገ ኘ ። ጄኔራሉም ፡ ምሣውን ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ በላና ፡ ወዲ ያው ፡ ሄደ ። አሽከሬንም ፡ አብሮ ፡ ወሰደው ። በማግሥቱ ፡ አሽከሬ ፡ እጫካ ፡ ውስጥ ፡ ባንድ ፡ የዋርካ ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ የ ፊጥኝ ፡ ታስሮና ፡ ልቡ ፡ እስቲጠፋ ፡ ተደብድቦ ፡ ተገኘ ። »

የአና ፡ ሳቪሽናን ፡ ታሪክ ፡ ሁሉም ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ሰ ሙ ። በተለይም ፡ ደግሞ ፡ ወጣቶቹ ፡ ሴቶች ፡ አደነቁ ። አብ ዛኞቹ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ የፍቅር ፡ ጀግና ፡ አድርገው ፡ ስለ ቆጠሩት ፡ በልባቸው ፡ የእሱ ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፤ ይልቁንም ፡ ደ

ግም ፡ የቀን ፡ ሕልም ፡ የምትወደውና ፡ የሚስ ፡ ራድክሊፍ
ን ፡[29] አሰቃቂና ፡ ምስጢራዊ ፡ ታሪክ ፡ ስትሰማ ፡ ያደገችው ፡
ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ በታሪኩ ፡ ተደሰተች ።

« እቤትሽ ፡ መጥቶ ፡ የነበረው ፡ ዕውነት ፡ ዱብሮቭስ
ኪይ ፡ ይመስልሻል ፡ አና ፡ ሳቪሽና? በጣም ፡ ተሳስተሻል ።
የጐበኘሽ ፡ ሰው ፡ በውነቱ ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ አላውቅም ፤
ዱብሮቭስኪይ ፡ እንዳልሆነ ፡ ግን ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ፡ » አለና ፡
ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ተናገረ ።

« ዱብሮቭስኪይ ፡ አይደለም? ታዲያ ፡ ማን ፡ ሊሆን ፡ ይ
ችላል ፡ ጌታዬ? በያውራ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ መንገደኞችን ፡ እያ
ቆመ ፡ የሚፈትሽ ፡ ከእርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ አለ? »

« እሱን ፡ አላውቅም ። ሰውዬው ፡ ግን ፡ ዱብሮቭስኪ
ይ ፡ አይደለም ። እኔ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ የማውቀው ፡ ገና ፡
በልጅነቱ ፡ ነው ። ጸጉሩ ፡ አሁን ፡ ጠቁሮ ፡ እንደሆን ፡ አላው
ቅም ፡ እንጂ ፡ ያንጊዜ ፡ ነጣ ፡ ያለና ፡ ዞማ ፡ ነበር ። በዕድሜ
ው ፡ ግን ፡ ከልጄ ፡ ከማሻ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ እንደሚበል
ጥ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ። ስለዚህ ፡ ዕድሜው ፡ ሃያ ፡ ሦስት ፡
ዓመት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰላሳ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ አይደለም ። »

« እርግጥ ፡ ነው ፡ ክቡር ፡ ሆይ ፡ » አለ ፡ ምስለኔው ፤
« ስለዱብሮቭስኪይ ፡ የተጻፈ ፡ መግለጫ ፡ በኪሴ ፡ ውስጥ ፡ አ
ለ ። በመግለጫው ፡ ላይ ፡ እንደተጻፈውም ፡ የዱብሮቭስኪ
ይ ፡ ዕድሜ ፡ ሃያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነው ። »

« እውነት! እስቲ ፡ አንብብልንና ፡ እንስማው ። ምና
ልባት ፡ ባጋጣሚ ፡ ያገኘነው ፡ እንደሆን ፡ እንዳያመልጠን ፡
ብናውቀው ፡ አይከፋም ። »

ምስለኔውም ፡ የነተበ ፡ ወረቀት ፡ ቢጤ ፡ ከኪሱ ፡ አወ
ጣና ፡ በኩራት ፡ መልክ ፡ ዘርግቶ ፡ በዜማ ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡
ሲል ፡ ማንበብ ፡ ጀመረ ፤

« የጥንት ፡ አገልጋዮቹ ፡ በሰጡት ፡ መረጃ ፡ መሠረት ፡
የተዘጋጀ ፡ የዱብሮቭስኪይ ፡ መልክ ፡ መግለጫ ፤

12*

ዕድሜው ፤ ሃያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፤ ቁመቱ ፡ መጠነኛ ፤ ጢሙን ፡ የተላጨ ፤ ዓይኑ ፡ ቡናማ ፤ ጸጉሩ ፡ ነጣ ፡ ያለ ፤ አ ፍንጫው ፡ ቀጥ ፡ ያለ ፤ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የሌለበት ። »

« ይሄው ፡ ነው? » አለና ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጠየቀ ።

« ይሄው ፡ ነው ፡ ጌታዬ ፡ » አለ ፡ ምስለኔው ፡ ወረቀቱን ፡ እያጣጠፈ ።

« ጉሽ ፡ አቶ ፡ ምስለኔ! እንዲህ ፡ አርጊም ፡ ማስረጃ ፡ የለ! በሰጠኸው ፡ መግለጫ ፡ መሠረት ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ ለማ ግኘት ፡ አያዳግትም ። ቁመቱ ፡ መጠነኛ ፡ ያልሆነና ፡ ነጣ ፡ ያለ ፡ ጸጉር ፡ የሌለው ፡ አፍንጫው ፡ ቀጥ ፡ ያላለና ፡ ዓይኑ ፡ ቡ ናማ ፡ ያልሆነ ፡ ከኛ ፡ ውስጥ ፡ ማን ፡ አለ? አንተ ፡ ከዱብሮ ቭስኪይ ፡ ጋር ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ሙሉ ፡ ተነጋግረህ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ሳታውቀው ፡ እንደምትለያይ ፡ በፈለግከው ፡ ል ወራረድ ። ጸሐፊዎች ፡ ሲባሉ ፡ ዕውነትም ፡ ብልሆች ፡ ና ቸው! »

ምስለኔውም ፡ ወረቀቱን ፡ በትህትና ፡ ወደኪሱ ፡ መለ ሰና ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ የተጠበሰ ፡ ጅግራውንና ፡ ቅቅል ፡ ጎመ ኑን ፡ መከስከስ ፡ ጀመረ ። አሳላፊዎቹም ፡ ምግብ ፡ በያይነ ቱ ፡ ማምጣታቸውንና ፡ ብርጭቆዎችንም ፡ በላይበላዩ ፡ መ ሙላታቸውን ፡ ቀጠሉ ። ብዙ ፡ የኰካዝ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠርሙሶች ፡ በተኩስ ፡ ድምጽ ፡ እየተከፈቱ ፡ በሻምፓኝ ፡ ስም ፡ ተጠጡ ። የሰውም ፡ ፊት ፡ እየቀላ ፡ ጨዋታውም ፡ እየ ሞቀና ፡ እየደመቀ ፡ ሄደ ።

« ምንም ፡ ቢሆን ፡ እንደሟቹ ፡ እንደ ፡ ታራስ ፡ አሌ ክሴዬቪች ፡ ያለ ፡ ምስለኔ ፡ ምንጊዜም ፡ አይመጣ ፡ » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « መሳሳት ፡ የሚሉ ፡ ነገር ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። አንዳችም ፡ ነገር ፡ አያመልጠውም ፡ ነበር ። ተቃ ጥሎ ፡ መሞቱ ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል ። እሱ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ ከ ወንበዴዎቹ ፡ መካከል ፡ አንዳቸውም ፡ አያመልጡም ፡ ነ

በር ። ሁሉንም ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ይይዛቸው ፡ ነበር ። ዱብሮ ቭስኪይም ፡ ቢሆን ፡ ይያዝ ፡ ነበር ፤ ጉቦ ፡ ሰጥቶም ፡ ሊያመ ልጥ ፡ አይችልም ፡ ነበር ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ታራስ ፡ አሌክሴ ዬቪች ፡ የጉቦውን ፡ ገንዘብ ፡ ይቀበለው ፡ ነበር ። ዳኑ ፡ ግን ፡ አይለቀውም ፡ ነበር ። ታራስ ፡ አሌክሴዬቪች ፡ እንዲህ ፡ ያ ለ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ከንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ ሰዎቼን ፡ ይዤ ፡ ወስላቶቹን ፡ ካልተከታተልኳቸው ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ መ ንገድ ፡ የለም ። መጀመሪያ ፡ ሃያ ፡ ሰዎች ፡ አስታጥቅና ፡ ወ ደ ፡ ጫካው ፡ ልኬ ፡ ወንበዴዎቹን ፡ እንዲጠርጉ ፡ አደርጋለ ሁ ። የኔ ፡ ሰዎች ፡ ፈሪ ፡ አይደሉም ። ከድብ ፡ ጋር ፡ እንኳ ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ የሚጋጠሙ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ለወንበዴ ዎች ፡ ፍንክች ፡ የሚሉ ፡ አይደሉም ፡ » አለ ።

የድብ ፡ ነገር ፡ በመነሳቱም ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ በጸጉራሙ ፡ ድብ ፡ የቀመሰው ፡ ቡጥጫ ፡ ትዝ ፡ አለ ውና ፡ « ድብህ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ » ብሎ ፡ ጠየቀው ።

« ሚሻማ ፡ አርፎ ፡ » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « በጠ ላቱ ፡ እጅ ፡ የክብር ፡ ሞት ፡ ሞተ ። ገዳዩም ፡ ያውና ፡ » ሲ ል ፡ ወደፈረንሳዩ ፡ ጠቆመ ። « ብድርህን ፡ መለሰልህ ፡ ታስ ታውስ ፡ የለም? » አለው ።

« እንዴት ፡ አላስታውስም? » አለ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲ ች ፡ እራሱን ፡ እያከከ ። « ደህና ፡ አድርጌ ፡ አስታውሳለሁ ፡ እንጂ ። አወይ ፡ ሚሻ! ሞተና ፡ አረፈዋ! በውነቱ ፡ በጣም ፡ አዘንኩ ። እንዴት ፡ አስቂኝና ፡ ብልህ ፡ ነበር! እንደሱ ፡ ያለ ፡ ድብ ፡ ምንጊዜም ፡ አታገኝም ። ለነገሩ ፡ ሙሴ ፡ ለምንድነው ፡ የገደሉት? » ሲል ፡ ጠየቀ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በቤቱና ፡ በንብረቱ ፡ ሁሉ ፡ ኩራ ት ፡ ስለሚሰማው ፡ የፈረንሳዩን ፡ ታሪክ ፡ በደስታ ፡ ማውራ ት ፡ ጀመረ ። እንግዶቹም ፡ ስለሚሻ ፡ ሞት ፡ ከልብ ፡ ተመስ

ጠው ፡ ሲሰሙ ፡ ዴሮርዥ ፡ ግን ፡ ጨዋታው ፡ ስለሱ ፡ ጉብዝና ፡ መሆኑን ፡ ባለማወቅ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ ቁንጥንጥ ፡ ተማሪውን ፡ እረፍ ፡ እያለ ፡ ይቆጣው ፡ ነበር ።

ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ የፈጀው ፡ የእራት ፡ ግብዣ ፡ በመጨረሻ ፡ ተፈጸመ ። ጋባዡ ፡ ያፍ ፡ ፎጣውን ፡ እጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ ፤ ሰው ፡ ሁሉም ፡ ተነስቶ ፡ ወደእንግዳ ፡ ማረፊያ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ። እዚያም ፡ ቡናና ፡ ካርታ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ጠበቃቸው ። እምግብ ፡ ቤቱ ፡ የተጀመረው ፡ ታላቅ ፡ የመጠጥ ፡ ግብዣም ፡ ቀጠለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

ከምሽቱ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ገደማ ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንግዶች ፡ ለመሄድ ፡ ተነሱ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ባለቤቱ ፡ ሞቅ ፡ ስላለው ፡ ያጥር ፡ ግቢው ፡ በር ፡ እንዲዘጋና ፡ እስከማግሥቱ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳይሄድ ፡ አዘዘ ። ወዲያውም ፡ የሙዚቃ ፡ ጨዋታ ፡ ተሰማ ፤ የዳንስ ፡ አዳራሹም ፡ በር ፡ ተከፈተ ፤ ዳንስም ፡ ተጀመረ ። ባለቤቱና ፡ የቅርብ ፡ ወዳጆቹ ፡ ባንድ ፡ የማዕዘን ፡ ቦታ ፡ ተቀምጠው ፡ መጠጥ ፡ በላይ ፡ በላዩ ፡ እየገለበጡ ፡ የወጣቶቹን ፡ ጭፈራ ፡ ባድናቆት ፡ ይመለከቱ ፡ ጀመር ። ጠና ፡ ያሉት ፡ ሴቶች ፡ የካርታ ፡ ጨዋታ ፡ ያዙ ። የወታደር ፡ ሰፈር ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ ፡ የወንዶቹ ፡ ቁጥር ፡ ከሴቶቹ ፡ ያነሰ ፡ ነበር ። ሻል ፡ ሻል ፡ ያሉትም ፡ ወንዶች ፡ ወዲያው ፡ ተያዙ ። ከሌሎቹ ፡ ሁሉ ፡ ጐልቶ ፡ የሚታየውና ፡ ብዙ ፡ የሚደንሰው ፡ መምህሩ ፡ ነበር ። የቫልስ ፡ ጨዋታ ፡ አሳምሮ ፡ በማወቁም ፡ ወጣቶቹ ፡ ሴቶች ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ለመደነስ ፡ ይሻሙት ፡ ነበር ።

በተለይም ፡ እርሱና ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ እየደነሱ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የአዳራሹን ፡ ወለል ፡ ሲዞሩት ፡ ሌሎቹ ፡ ወጣት ፡ ሴቶች ፡ በማሽሟጠጥ ፡ ዓይን ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር ። እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ሲሆን ፡ ባለቤቱ ፡ ስለታከተው ፡ የዳንሱ ፡ ጨዋታ ፡ እንዲቆምና ፡ እራት ፡ እንዲቀርብ ፡ አዞ ፡ ወደመኝታ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ ።

የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ መሄድ ፡ ለሰዎቹ ፡ የነፃነትና ፡ የመዝናናት ፡ ስሜት ፡ ሰጣቸው ። ወንዶቹ ፡ ከሴቶቹ ፡ አጠገብ ፡ ለመቀመጥ ፡ ደፈሩ ፤ ልጃገረዶቹም ፡ መሳቅና ፡ ማሾክሾክ ፡ ጀመሩ ፤ አሮጊቶቹም ፡ ከገበታ ፡ ማዶ ፡ በጨኸት ፡ ይነጋገሩ ፡ ጀመር ፤ ወንዶቹም ፡ መጠጣታቸውን ፤ መከራከራቸውን ፤ መሳቃቸውን ፡ ቀጠሉ ። በጠቅላላው ፡ ግብዣው ፡ እጅግ ፡ አስደሳችና ፡ መልካም ፡ ትዝታ ፡ የተመላበት ፡ ነበር ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ የደስታው ፡ ተካፋይ ፡ አልሆነም ፡ ነበር ። ይሄውም ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ነበር ። እንደከፋው ፡ ሰው ፡ ፊቱን ፡ ኩስትሮና ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ከመቀመጡ ፡ ሌላ ፡ አበላሉም ፡ እንደፈዘዘና ፡ ልቡ ፡ እንደተሰቀለ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ለካስ ፡ የወንበዴዎቹ ፡ ወሬ ፡ ሥጋት ፡ አሳድሮበት ፡ ኖሮዋል ። ይህ ፡ ሥጋቱ ፡ ተገቢ ፡ ለመሆኑም ፡ አሁኑኑ ፡ እንረዳዋለን ።

የገንዘብ ፡ ሣጥኔ ፡ ባዶ ፡ ናት ፡ ሲል ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስክርብኝ ፡ ያለው ፡ ዕውነቱን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሲዋሽ ፡ አልነበረም ። ገንዘቡን ፡ ከሣጥኗ ፡ ውስጥ ፡ አውጥቶ ፡ ወደአንድ ፡ የቆዳ ፡ ከረጢት ፡ ውስጥ ፡ በማዛወር ፡ ከሸሚዙ ፡ ሥር ፡ እደረቱ ፡ ላይ ፡ አንጠልጥሎት ፡ ይዞራል ። ስለዚህ ፡ ሣጥኗ ፡ በውነትም ፡ ባዶ ፡ ነበረች ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ ያደረገበትም ፡ ምክንያት ፡ ሰውን ፡ ባለማመኑና ፡ ከዘወትር ፡ ፍርሃትና ፡ ሥጋት ፡ ለመዳን ፡ ሲል ፡ ነው ። ባልለመደው ፡ ቤት ፡ ማደር ፡ ግድ ፡ ስለሆነበትና ፡ ምናልባት ፡ ደግሞ ፡ እራቅ ፡ ያለና ፡ ሌቦች ፡ በቀላሉ ፡ ሰብረው ፡ የሚገቡበ

ት ፡ ክፍል ፡ ይሰጠኝ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ በመፍራት ፡ የሚያ ስተማምን ፡ ጓደኛ ፡ መፈለግ ፡ ጀመረ ። በመጨረሻም ፡ ዴፎርዥን ፡ መረጠ ። አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ዴፎርዥን ፡ የመረጠበትም ፡ ምክንያት ፡ በሰውነቱ ፡ ጥንካሬና ፡ እርሱን ፡ ትግ ፡ ባለው ፡ ቁጥር ፡ የሚያንቀጠቅጠውን ፡ ድብ ፡ ዴፎርዥ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ጀግንነት ፡ እንደተጋጠመው ፡ ስለሚያውቅ ፡ ነው ። እንግዶቹ ፡ ከጠረጴዛው ፡ በተነሱ ፡ ጊዜ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ በፈረንሳዊው ፡ አካባቢ ፡ ማንዣበብ ፡ ጀመረ ። እየሳለና ፡ ጉሮሮውን ፡ እየጠራረገም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፤

« እ-እ ፡ እርስዎ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ለማደር ፡ እችላለሁን ፡ ሙሴ? ምክንያቱም ፡ ...»

ዴፎርዥም ፡ በትህትና ፡ እጅ ፡ ነስቶ ፤ «Que désire, monsieur?»* አለና ፡ ጠየቀው ።

« ሙሴ ፡ በመስኮብኛ ፡ መናገር ፡ ገና ፡ አለማወቅዎ ፡ ያሳዝናል ። ዠ ፡ ቨ ፡ ሟ ፡ ሼ ፡ ቩ ፡ ኩሼ ፡ ኰምፕሬኔ ፡ ቩ**? »

«Monsieur, très volontiers, veuillez donner des ordres en conséquence. ***» አለና ፡ ዴፎርዥ ፡ መለሰለት ።

አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ዕውቀቱ ፡ እጅግ ፡ ስለተደሰተ ፡ ትዕዛዝ ፡ ለመስጠት ፡ ወዲያውኑ ፡ ፈጥኖ ፡ ሄደ ።

እንግዶቹ ፡ ደህና ፡ እደሩ ፡ እየተባባሉ ፡ ወደየተዘጋጀላቸው ፡ ክፍል ፡ አመሩ ። አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ ከፈረንሳዊው ፡ ጋር ፡ ወደማደሪያ ፡ ክፍሉ ፡ ሄደ ። ሌሊቱ ፡ ጽልመት ፡

---

* ምን ፡ ይፈልጋሉ? ( በፈረንሳይኛ ። )

** በእርስዎ ፡ ክፍል ፡ እንድተኛ ፡ ይፈቅዱልኛል? ( በፈረንሳይኛ ። )

*** እሺ ፡ ጌታዬ ። የሚያስፈልገውን ፡ ትዕዛዝ ፡ ይስጡ ። ( በፈረንሳይኛ ። )

ስለነበር ፡ ዴፎርዥ ፡ ፋኖስ ፡ እያበራ ፡ ቀደመ ። አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ በሽሚዙ ፡ ሥር ፡ የደበቀው ፡ ገንዘብ ፡ መኖርና ፡ አለመኖሩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ደረቱን ፡ እየዳበሰ ፡ ተከተለው ፤።

ወደክፍሉም ፡ ውስጥ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ መምህሩ ፡ ሻማ ፡ አበራና ፡ ልብሳቸውን ፡ ማውለቅ ፡ ሲጀምሩ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ የበሩን ፡ ቁልፍና ፡ መስኮቶቹን ፡ መፈተሽ ፡ ጀመረ ። የማያስተማምኑ ፡ ሆነው ፡ ስላገኛቸውም ፡ እራሱን ፡ ነቀነቀ ። የበሩ ፡ መቀርቀሪያ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ የመስኮቶቹ ፡ የክረምት ፡ ተደራቢ ፡ መዝጊያም ፡ ገና ፡ አልገባም ፡ ነበር ። ይህን ፡ አቤቱታ ፡ ለዴፎርዥ ፡ ለማቅረብ ፡ ሞከረ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ዕውቀቱ ፡ የተወሰነ ፡ በመሆኑ ፡ ሊያስረዳው ፡ አልቻለም ። ፈረንሳዊውም ፡ ነገሩ ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ ስላልገባው ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ንግግሩን ፡ ማቆም ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። አልጋቸው ፡ የተዘረጋው ፡ ማዶ ፡ ለማዶ ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ ከተኙ ፡ በኋላ ፡ ፈረንሳዩ ፡ መብራቱን ፤ ፡ አጠፋው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ማጥፋት ፡ የሚለውን ፡ የመስኮብኛ ፡ ግሥ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ሰዋስው ፡ በማራባት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጮኸ ፤

« ፑርኳ ፡ ቩ ፡ ያጠፉታል ፤ ፑርኳ*? በጨለማ ፡ ለመዶርሚር ፡ **አልችልም ። »

ዴፎርዥ ፡ ሰውዬው ፡ ለምን ፡ እንደሚጮኽ ፡ ስላልገባው ፡ ደህና ፡ እደር ፡ አለውና ፡ ተኛ ።

አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ የብርድ ፡ ልብሱን ፡ ወደትከሻው ፡ ሳብ ፡ እያደረገ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አጉመተመተ ፤

« ምን ፡ የተረገመ ፡ ባዕድ ፡ ነው! ሻማውን ፡ ለምንድ

---

* ሻማውን ፡ ለምን ፡ አጠፉት? ( በፈረንሳይኛ ። )

** ለመተኛት ። ( በፈረንሳይኛ ። )

ነው ፡ ያጠፋው? በሱ ፡ አይብስም ፡ ይልቅ? ያለመብራት ፡ ል ተኛ ፡ አልችልም ። ሙሴ! ሙሴ! ዠ ፡ ቨ ፡ አቬክ ፡ ቩ ፡ ፓር ሌ* ፡ » ሲል ፡ ተጣራ ። ፈረንሳዊው ፡ ግን ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳ ይሰጠው ፡ ቀረ ። እንዲያውም ፡ ማኩረፍ ፡ ጀመረ ። በዚ ህ ፡ ጊዜ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አሰበ ፤

« እኔ ፡ ለራሴ ፡ ዓይኔን ፡ መክደን ፡ አቅቶኛል ፤ ይኸ ፡ የ ፈረንሳዊው ፡ አውሬ ፡ ግን ፡ ያኰርፋል ። ባልተዘጋው ፡ በር ፡ ወይም ፡ በመስኰቱ ፡ ተንጠላጥለው ፡ ሌቦች ፡ ቢገቡስ? ይ ህ ፡ አውሬ ፡ እንደሆን ፡ መድፍም ፡ ቢተኰስ ፡ አይነቃ! »

« ሙሴ! ሙሴ! ሰይጣን ፡ ይዞህ ፡ ይሂድ! »

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ጸጥ ፡ አለ ። የመጠ ጡ ፡ ኃይልና ፡ ድካሙ ፡ ፍርሃቱን ፡ አስረሳው ። ቀስ ፡ በቀስም ፡ እንቅልፍ ፡ እየተጫነው ፡ ሄደና ፡ ወዲያው ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ ተኛ ።

ቆይቶ ፡ አንድ ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ ቀሰቀሰው ። በንቅ ልፍ ፡ ልቡ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሸሚዙን ፡ አንገት ፡ ይዞ ፡ ሲ ጐትተው ፡ ተሰማው ። አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ ዓይኑን ፡ ገ ለጠ ። ድብዝዝ ፡ ባለው ፡ የመጸው ፡ የንጋት ፡ ብርሃን ፡ ዴፎ ርዥን ፡ አጠገቡ ፡ ቆሞ ፡ አየው ። ፈረንሳዊው ፡ ባንድ ፡ እጁ ፡ ሽጉጥ ፡ ይዞ ፡ በሌላ ፡ እጁ ፡ ደግሞ ፡ የገንዘቡን ፡ ከረጢት ፡ ማሰሪያ ፡ ይፈታ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲ ች ፡ ክው ፡ ብሎ ፡ ደነገጠ ።

« ከስከሴ ፡ ሙሴ? ከስከሴ?** » እያለ ፡ በፍርሃት ፡ ድምጽ ፡ ተናገረ ።

« ዝም ፡ በል! ዝም ፡ በል! » አለ ፡ ፈረንሳዩ ፡ በጠራ ፡ መ ስኰብኛ ።

---

* ከእርስዎ ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ እፈልጋለሁ ። ( በፈረን ሳይኛ ። )

** ምንድነው ፡ ጌታዬ ፤ ምንድነው ፡ ጌታዬ? ( በፈረንሳይ ኛ ። )

« ዝም ፡ በል! አለበለዚያ ፡ ግን ፡ ትሞታለህ ። እኔ ፡ ዱ ብሮቭስኪይ ፡ ነኝ ። »

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

ካሁን ፡ ቀደም ፡ በታሪካችን ፡ ላይ ፡ ልንገልጸው ፡ ያል ቻልነውን ፡ አሁን ፡ እንገልጽ ፡ ዘንድ ፡ ያንባቢያችንን ፡ መ ልካም ፡ ፈቃድ ፡ እንጠይቃለን ።

ካሁን ፡ በፊት ፡ በጠቀስነው ፡ የፖስታ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ መንገደኛ ፡ ሰው ፡ ጥግ ፡ ይዞ ፡ ተቀምጧል ። እንደትህትናውና ፡ እንደትዕግሥቱ ፡ ማዕር ግ ፡ የሌለው ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ይመስላል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ሲባል ፡ ደግሞ ፡ በፖስታ ፡ ቤት ፡ ሹ ም ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ መብት ፡ የሌለው ፡ ነው ። መና ኛ ፡ ሰረገላው ፡ እግሩ ፡ ዘይት ፡ እንዲቀባለት ፡ እጓሮ ፡ ቆሟ ል ። ሰውዬው ፡ ሐብት ፡ የሌለው ፡ መሆኑን ፡ የሚመሰክር ም ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ሳጥን ፡ በሰረገላው ፡ ላይ ፡ አለ ። መንገ ደኛው ፡ ሰውዬ ፡ ሻይም ፡ ቡናም ፡ ሳይጠይቅ ፡ ተቀምጦ ፡ ብቻ ፡ በመስኮቱ ፡ አሻግሮ ፡ እየተመለከተ ፡ ያፏጫል ። በሌላ ፡ ክፍል ፡ ተቀምጣ ፡ የነበረችው ፡ የፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ሚ ስት ፡ በሰውዬው ፡ ፉጨት ፡ እጅግ ፡ ስለተበሳጨች ፡ ዝቅ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ተናገረች ፤

« እግዜር ፡ ዛሬስ ፡ ብሎ ፡ ብሎ ፡ የሚያፏጭ ፡ ሰው ፡ ላ ከልን ። ደሞ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ የሚያፏጨው! ምነው ፡ በፈ ነዳ ፡ ይህ ፡ የተረገመ ፡ ባዕድ! »

« ምን ፡ አለበት ፡ ብለሽ ፡ ነው? ተይው ፡ ያፏጭ ፡ » አለ ፡ ባልዮው ።

« ፉጨት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንደሚያስከትል ፡ አታውቅም? » አለች ፡ ቁጡ ፡ ባለቤቱ ።

« ቶሎ ጨብጪት ፡ ገንዘብ ፡ ከቤት ፡ ያስወጣል ፡ ማለትሽ ፡ ነው? አዬ ፡ ፓኮምብና ፤ ሰውዬው ፡ አፏጨም ፡ አላፏጨም ፡ እኛ ፡ እንደሆን ፡ ገንዘብ ፡ የለንም! »

« ሲዶሪች ፡ እንግዲያው ፡ እንዲሄድ ፡ አድርገዋ ፤ እዚህ ፡ የምታቆየው ፡ ለምንድን ፡ ነው? ፈረስ ፡ ስጠውና ፡ የሄደበት ፡ ይሂድ ። »

« ይጠብቅ ፡ ግድየለም ፤ ፓኮምብና ። በጋጣ ፡ ያሉት ፡ ሦስት ፡ ትሮይካ* ፡ ናቸው ። አራተኛው ፡ በእረፍት ፡ ላይ ፡ ነው ። ምናልባት ፡ ደግሞ ፡ ጨዋ ፡ መንገደኛ ፡ ይመጣ ፡ ይሆናል ። ላንድ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ብዬ ፡ እዳ ፡ ውስጥ ፡ አልገባም ። ይሄዋ! አላልኩሽም! አንድ ፡ ሰው ፡ እየጋለበ ፡ መጣ ። እንዴት ፡ ይፈጥናል! ጄኔራልስ ፡ እንደሆን ፡ ማን ፡ ያውቃል! »

አንድ ፡ ሰረገላ ፡ ወደ ፡ በረንዳው ፡ ተጠጋ ። ሰረገላ ፡ ነጂውም ፡ ከሰረገላው ፡ ላይ ፡ ዱብ ፡ ብሎ ፡ ወረደና ፡ የሠረገላውን ፡ ማጥን ፡ በር ፡ ከፈተ ። ወዲያውም ፡ የወታደር ፡ ካፖርት ፡ የለበሰና ፡ ነጭ ፡ ባርኔጣ ፡ የደፋ ፡ ወጣት ፡ ሰውዬ ፡ የገንዘብ ፡ ማጥን ፡ የያዘ ፡ አሽከር ፡ አስከትሎ ፡ ወደፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ። አሽከርዬው ፡ የገንዘቡን ፡ ማጥን ፡ በመስኮቱ ፡ ጠርዝ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ።

« ፈረሶች ፡ እፈልጋለሁ! » ሲል ፡ መኰንኑ ፡ ግርማ ፡ ባለው ፡ ድምጽ ፡ ተናገረ ።

« አሁኑኑ! » አለና ፡ የፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ መለሰ ። « የፈቃድ ፡ ወረቀትዎስ ፡ የት ፡ አለ ፡ እባክዎ? »

« የፈቃድ ፡ ወረቀት ፡ የለኝም ፤ የምሄደውም ፡ ዋናውን ፡ መንገድ ፡ ይዤ ፡ አይደለም ። ማን ፡ እንደሆንኩ ፡ አታውቅም? »

የፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ጉድ ፡ ጉድ ፡ አለና ፡ ወዲያው ፡ ነጂዎቹን ፡ ፈጥኖ ፡ ለማዘዝ ፡ ሮጦ ፡ ወጣ ። ወጣቱም ፡ ሰውዬ ፡ በ

---

* በሦስት ፡ ፈረሶች ፡ የሚጐተት ፡ ሰረገላ ።

ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከተንጐራደደ ፡ በኋላ ፡ ወደ ሌላው ፡ ክፍል ፡ ሄዶ ፡ የፖስታ ፡ ቤቱን ፡ ሹም ፡ ሚስት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቃት ፤

« ማነው ፡ ይሄ ፡ መንገደኛ? »

« እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ። ፈረንሳይ ፡ ነው ፡ መሰል ። ፈረሶች ፡ እየጠበቀ ፡ ሲያፏጭ ፡ ይሄው ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ሆነው ። ይህ ፡ እርጉም ፡ ሰው ፡ ሰልችቶኛል ፡ » ስትል ፡ መለሰች ።

ወጣቱም ፡ ሰውዬ ፡ ፈረንሳዩን ፡ በፈረንሳይኛ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አናገረው ።

« ወዴት ፡ ነው ፡ የምትሄደው? »

« ወደሚቀጥለው ፡ ከተማ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ለመምህርነት ፡ በደብዳቤ ፡ ወደቀጠረኝ ፡ ወዳንድ ፡ ባለርስት ፡ ቤት ፡ እሄዳለሁ ። ዛሬ ፡ እደርሳለሁ ፡ በማለት ፡ ተስፋ ፡ ነበረኝ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ክቡር ፡ የፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ፈቃዳቸው ፡ ሳይሆን ፡ ቀረ ። እዚህ ፡ አገር ፡ ፈረስ ፡ ማግኘት ፡ ችግር ፡ ነው ፡ ጌታዬ ። »

« ወደየትኛው ፡ ባለርስት ፡ ጋ ፡ ነው ፡ የምትሄደው? »

« ወደሙሴ ፡ ትሮዬኩሮቭ ፡ ጋ ፡ ነው ። »

« ትሮዬኩሮቭ? ማነው ፡ እሱ ፡ ይሄ ፡ ትሮዬኩሮቭ? »

« Ma foi, mon officier... * ስለርሱ ፡ እምብዛም ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ አልሰማሁም ። ኩሩና ፡ ትዕቢተኛ ፡ ከመሆኑ ፡ ሌላ ፡ በአገልጋዮቹም ፡ ላይ ፡ ጨካኝ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። በእርሱ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ አይቆይም ። ስሙን ፡ በሰሙም ፡ ጊዜ ፡ ሁሉም ፡ ይርበደበዳሉ ። ከመምህሮቹም ፡ ጋር ፡ ቀዛና ፡ ፈዘዛ ፡ አይወድም ፡ አሉ ። እንዲያውም ፡ ሁለቱን ፡ ገርፎ ፡ ገደላቸው ፡ ይባላል ። »

---

* አዩ ፡ ጌታ ፡ መኰንን ፡ ... ( በፈረንሳይኛ ። )

« ታዲያ ፡ አንተ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አውሬ ፡ ለማገል ገል ፡ ፈቅደህ ፡ መሄድህ ፡ ነው? »

« ምን ፡ ላድርግ ፡ ጌታዬ ። መልካም ፡ ደመወዝ ፡ ቆርጠ ልኛል ። ባመት ፡ ሦስት ፡ ሺ ፡ ሩብል ፡ ከቀለብ ፡ ጋር ፡ እገኛ ለሁ ። ምናልባት ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ ከሌሎቹ ፡ የተሻለ ፡ ዕድል ፡ ይገጥመኝ ፡ ይሆናል ። አሮጊት ፡ እናት ፡ ስለአለችኝም ፡ የደ መወዜን ፡ ግማሽ ፡ ለችግሯ ፡ እንዲረዳት ፡ እልክላታለሁ ። ባ ምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥም ፡ ለወደፊቱ ፡ ጊዜ ፡ እራሴን ፡ የሚ ያስችለኝ ፡ ገንዘብ ፡ አጠራቅማለሁ ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡ bon-soir* ብዬ ፡ ፓሪስ ፡ እገባና ፡ በገንዘቤ ፡ እነግዳለሁ ። »

« ከትሮዬኩሮቭ ፡ ቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ አንተን ፡ የሚያ ውቅህ ፡ ሰው ፡ አለን? » ብሎ ፡ መኰንኑ ፡ ጠየቀው ።

« ማንም ፡ የሚያውቀኝ ፡ ሰው ፡ የለም ። የቀጠረኝም ፡ ባንድ ፡ ሞስኮ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ ወዳጁ ፡ በኩል ፡ ነው ። እኔም ፡ ሥራውን ፡ ላገኝ ፡ የቻልኩት ፡ የዚሁ ፡ ሰውዬ ፡ ወጥ ቤት ፡ በሆነ ፡ ባንድ ፡ ያገሬ ፡ ሰው ፡ አማካይነት ፡ ነው ። ት ምህርቴ ፡ እንኳ ፡ መምህርነት ፡ ሳይሆን ፡ ብስኩት ፡ ጋጋ ሪነት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በናንተ ፡ አገር ፡ መምህር ፡ በጣ ም ፡ ተፈላጊና ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ስለሰማሁ ፡ ... »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መኰንኑ ፡ አሰበና ፡ የፈረንሳዊውን ፡ ንግግ ር ፡ አቋርጦ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ፤

« ስማ ፤ ይህን ፡ ሥራ ፡ ትተህ ፡ አሁኑኑ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ለመመለስ ፡ አስር ፡ ሺ ፡ ሩብል ፡ እጅ ፡ በጅ ፡ ብሰጥህ ፡ ምን ፡ ትላለህ? »

ፈረንሳዊውም ፡ መኰንኑን ፡ በመደነቅ ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተውና ፡ በፈገግታ ፡ እራሱን ፡ ነቀነቀ ።

የፖስታ ፡ ቤቱም ፡ ሹም ፡ ወደክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገባና ፤

---

* ደህና ፡ ሁኑ ። ( በፈረንሳይኛ ። )

« ፈረሶቹ ፡ ተዘጋጅተዋል ፡ » አለ ።

አሽከሩም ፡ ይህንኑ ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፡ ተናገረ ።

« አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆይ ፤ ላንድ ፡ አፍታም ፡ እባክህ ፡ ከክፍሉ ፡ ውጣ ፡ »አለ ፡ መኰንኑ ። የፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ሹምና ፡ አሽከሩ ፡ ከክፍሉ ፡ ወጥተው ፡ ሄዱ ። መኰንኑ ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፤ « ቀልዴን ፡ አይደለም ። አስር ፡ ሺ ፡ ሩብል ፡ ልሰጥህ ፡ እችላለሁ ። እኔ ፡ ካንተ ፡ የምፈልገው ፡ ከዚሁ ፡ አገር ፡ እንድትጠፋና ፡ ወረቀትህን ፡ እንድትሰጠኝ ፡ ነው ፡ » አለው ።

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ የገንዘብ ፡ ሣጥኑን ፡ ከፈተና ፡ አያሌ ፡ የባንክ ፡ ኖት ፡ እየመዘዘ ፡ አወጣ ።

ፈረንሳዊውም ፡ ዓይኑን ፡ አፍጥጦ ፡ እየተመለከተ ፡ ምን ፡ እንደሚናገር ፡ ጨነቀው ።

« እኔ ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ እንድጠፋና ፡ ለወረቀቶቼ ፡ ስትል ፡ ነው! » ሲል ፡ ደጋግሞ ፡ በመደነቅ ፡ ተናገረ ። « ወረቀቴ ፡ ይሄው ፡ ... ግና ፡ ስትቀልድ ፡ ይመስለኛል ። ወረቀቴን ፡ የምትፈልገው ፡ ለምንድን ፡ ነው? »

« እሱ ፡ ያንተ ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም ። እኔ ፡ የምጠይቅህ ፡ ትስማማለህ ፡ ወይስ ፡ አትስማማም ፡ ብዬ ፡ ነው ። »

ፈረንሳዊው ፡ በጆሮው ፡ የሰማውን ፡ ሳያምን ፡ ወረቀቱን ፡ አውጥቶ ፡ ለወጣቱ ፡ መኰንን ፡ ሰጠው ። መኰንኑም ፡ በፍጥነት ፡ ወረቀቱን ፡ አነበበ ።

« ፓስፖርትህስ? ...መልካም ፤ የምስክር ፡ ወረቀትህስ? ... እሱን ፡ መመልከት ፡ አለብኝ ። የመታወቂያ ፡ ወረቀትህስ? ... ማለፊያ ፡ ነው ። እነሆ ፡ ገንዘቡን ፡ እንካ ። እንግዲህ ፡ በቀጥታ ፡ መመለስ ፡ ትችላለህ ። ደህና ፡ ሁን ። »

ፈረንሳዊው ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ድርቅ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

መኰንኑም ፡ ተመልሶ ፡ መጣና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፤

« ዋናውን ፡ ነገር ፡ እረስቼ ፡ ልሄድ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ በኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ ምሥጢር ፡ ሆኖ ፡ እንዲቀር ፡ ቃል ፡ ግባልኝ ። »

« ቃል ፡ ገብቻለሁ ፡ » ሲል ፡ ፈረንሳዊው ፡ መለሰ ። « ነገር ፡ ግን ፡ ወረቀቶቼን ፡ ... ያለነሱ ፡ እምን ፡ እገባለሁ? » አለ ።

« ቀረብ ፡ ወዳለው ፡ ከተማ ፡ ስትገባ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ዘረፈኝ ፡ በልና ፡ አስታውቅ ። ያምኑሃል ፤ አስፈላጊውንም ፡ ወረቀት ፡ ይሰጡሃል ። እግዚአብሔር ፡ በፍጥነት ፡ ወደፓሪስ ፡ ይመልስህ ። እናትህንም ፡ በጤና ፡ ለማግኘት ፡ ያብቃህ ። »

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ወጣና ፡ እሰረገላው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ጋለበ ።

የፖስታ ፡ ቤቱም ፡ ሹም ፡ በመስኰት ፡ ተመለከተና ፡ ሠረገላው ፡ ላይን ፡ ሲጠፉ ፡ ወደሚስቱ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤

« ሰውዬው ፡ ማን ፡ እንደነበር ፡ ታውቂያለሽ ፡ ፓኾሞቭና? ዱብሮቭስኪይ ፡ እኮ ፡ ነው! »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ ወደመስኰቱ ፡ ስትሮጥ ፡ መጣች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ እርቆ ፡ ሄዶ ፡ ነበር ። ባሏንም ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ መሳደብ ፡ ጀመረች ፤

« ሲዶሪች ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትፈራም? ቀደም ፡ ብለህ ፡ ለምን ፡ አልነገርከኝም? ሰረቅ ፡ አድርጊ ፡ አየው ፡ ነበር ። ተመልሶስ ፡ ይመጣ ፡ እንደሆን ፡ ማን ፡ ያውቃል! አዬ! እንዳው ፡ ከንቱ ፡ ሰው ፡ ነህ! »

ፈረንሳዊው ፡ ሰውዬ ፡ እንደተተከለ ፡ እንጨት ፡ አለበት ፡ ቦታ ፡ ቆሞ ፡ ቀረ ። ከመኰንኑ ፡ ጋር ፡ ያደረገው ፡ ስምምነትና ፡ የተቀበለውም ፡ ገንዘብ ፡ ህልም ፡ መስሎ ፡ ታየው ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ የገንዘቡ ፡ ጥቅል ፡ እኪሱ ፡ ውስጥ ፡ ስለነበር ፡ ነገሩ ፡ ዕውነት ፡ መሆኑን ፡ ሊመሰክርለት ፡ ቻለ ።

እከተማው ፡ ድረስ ፡ የሚወስደው ፡ ፈረስ ፡ ለመከራየት ም ፡ ወሰነ ። ነጂው ፡ በጣም ፡ እያዘገመ ፡ ስለሄደ ፡ እከተማው ፡ ሲደርሱ ፡ ጨለማ ፡ ነበር ።

በዘበኛ ፡ ፊንታ ፡ አንድ ፡ የፈረሰ ፡ የዘበኛ ፡ ቤት ፡ በቆ መበት ፡ በር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳዊው ፡ ነጂውን ፡ እንዲ ያቆም ፡ አዘዘውና ፡ ከሰረገላው ፡ ላይ ፡ ወርዶ ፡ በግሩ ፡ እያዘ ገመ ፡ ሰረገላውንና ፡ ሳጥኑን ፡ ነጂው ፡ እንዲወስደው ፡ በም ልክት ፡ ነገረው ። ፈረንሳዊው ፡ በዱብሮቭስኪይ ፡ ስጦታ ፡ እጅግ ፡ እንደተደነቀ ፡ ሁሉ ፡ ሰረገላ ፡ ነጂውም ፡ በፈረንሳ ዊው ፡ ሰውዬ ፡ ልግስና ፡ እለቅጥ ፡ ተገረመ ። ምናልባት ፡ ፈ ረንሳዊው ፡ አዕምሮው ፡ ልክ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ በማሰ ብም ፡ እጅ ፡ እየነሳ ፡ አመሰገነው ። ወደከተማ ፡ ለመግባት ፡ ስላልፈቀደም ፡ የወዳጁ ፡ ወደሆነ ፡ ወዳንድ ፡ የመጠጥ ፡ ቤት ፡ ጐራ ፡ አለ ። እዚያም ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ አሳለ ፈና ፡ በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ጋሪውንና ፡ ሳጥኑን ፡ አስረክቦ ፡ ፊቱን ፡ አሳብጦና ፡ ዓይኑን ፡ አቅልቶ ፡ ስስቱን ፡ ፈረሶች ፡ ብ ቻ ፡ እየሳበ ፡ ተመለሰ ።

ዱብሮቭስኪይ ፡ እንዳየነው ፡ ሁሉ ፡ የፈረንሳዊውን ፡ ወ ረቀት ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ በትሮዬኩሮቭ ፡ ፊት ፡ በድፍረ ት ፡ ቀርቦ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ለመኖር ፡ ቻለ ። በምስጢር ፡ ሊፈጽመው ፡ ያቀደው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደሆን ፡ ባይታወ ቅም ፡ ቅሉ ፡ ( በኋላ ፡ እናውቀዋለን ፡ ) በጠባዩ ፡ አንዳችም ፡ እ ንከን ፡ የለበትም ፡ ነበር ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ትንሹን ፡ ልጅ ፡ ሳሻን ፡ በማስተማር ፡ ረገድ ፡ እምብዛም ፡ ግድ ፡ የለውም ፡ ነበር ። ልጁ ፡ እንደልቡ ፡ እንዲቦርቅ ፡ ይፈቅድለት ፡ ነበር ። ለስሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልጁን ፡ በእርግጥ ፡ ምን ፡ እንደሚያስ

ተምረውም ፡ አይናገርም ፡ ነበር ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናን ፡ ሙዚቃ ፡ በማስተማር ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ትጉህ ፡ ነበር ። ዘወትር ፡ በፒያኖው ፡ አጠገብ ፡ እጐንዋ ፡ ተቀምጦም ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ያሳልፍ ፡ ነበር ።

የቤቱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወጣቱን ፡ መምህር ፡ ይወደው ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ አደን ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ በሚያሳየው ፡ ጀግንነትና ፡ ብልህነት ፡ ያደንቀው ፡ ነበር ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ በትጉህነቱና ፡ በትህትናው ፤ ሳሻም ፡ እንደ ልቡ ፡ እንዲፈነድቅ ፡ ስለሚፈቅድለት ፤ አገልጋዮቹም ፡ ከደረጃው ፡ ጋር ፡ ስለማይመሳሰለው ፡ ቸርነቱ ፡ ያፈቅሩት ፡ ነበር ። እሱም ፡ እራሱ ፡ ከቤተሰቡ ፡ ጋር ፡ መስመሩና ፡ መዋሐዱ ፡ ይሰማው ፡ ነበር ።

በመምህርነት ፡ ስም ፡ ተቀጥሮ ፡ ሥራ ፡ ከጀመረበት ፡ ቀን ፡ አንስቶና ፡ እስከታሪካዊው ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ትሁትና ፡ ወጣት ፡ ፈረንሳዊ ፡ ስሙ ፡ ሲነሳ ፡ ብቻ ፡ የሰፈሩን ፡ ባለርስቶች ፡ የሚያንቀጠቅጣቸው ፡ ኃይለኛ ፡ ሽፍታ ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥም ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ከፖክሮቭስኰዬ ፡ አንድም ፡ ጊዜ ፡ አልወጣም ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ የሠፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ስለሚፈጽመው ፡ የውንብድና ፡ ተግባር ፡ እራሳቸው ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ እየፈጠሩ ፡ ያወሩ ፡ ነበር ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ጭፍሮቹ ፡ ጌታቸው ፡ በሌለበት ፡ ዝርፊአቸውን ፡ ቀጥለው ፡ ይሆናል ።

ከግል ፡ ጠላቱና ፡ እመከራ ፡ ላይ ፡ ከጣሉት ፡ ሰዎች ፡ ካንደኛው ፡ ጋር ፡ በአንድ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ አብሮ ፡ በተኛ ፡ ጊዜ ፡ ፈተናውን ፡ ሊያሸንፍ ፡ አልቻለም ። ሰውዬው ፡ የገንዘቡን ፡ ከረጢት ፡ እንደያዘ ፡ ስላወቀም ፡ ለመውሰድ ፡ ቆረ

ጠ ። ከመምህርነት ፡ ወደወንበዴነት ፡ ከመቅጽበት ፡ በመ ለወጥም ፡ ምስኪኑን ፡ አንቶን ፡ ፓፍኑቲችን ፡ እንዴት ፡ እንዳስደነገጠው ፡ አይተናል ።

ሌሊቱን ፡ በፖክሮቭስኮዬ ፡ ያሳለፉት ፡ እንግዶች ፡ በ ማግሥቱ ፡ ጧት ፡ በሶስት ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ ማረፊ ያ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ተሰበሰቡ ። የሻዩ ፡ ጀበናም ፡ እን ፋሎቱ ፡ ይቡለቀለቅ ፡ ነበር ። ፊት ፡ ለፊትም ፡ ማሪያ ፡ ኪ ሪሎቭና ፡ የጧት ፡ ልብሷን ፡ ለብሳ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ። ኪ ሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ የጧት ፡ ካባና ፡ የደጅ ፡ ጫማውን ፡ አ ድርጎ ፡ እንኰላ ፡ በሚያህል ፡ ስኒ ፡ ሻይ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ።

አንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ መጨረሻ ፡ ገባ ። ፊቱ ፡ ስለገረጣና ፡ የከፋው ፡ ስለመሰለም ፡ « ደህና ፡ አይደለህ ም ፡ ወይ ፡ » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጠየቀው ። አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አጉመትምቶ ፡ መለሰና ፡ አንዳ ችም ፡ ነገር ፡ እንዳላደረገ ፡ ሁሉ ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ የተቀመጠውን ፡ መምህር ፡ በፍርሃት ፡ ይመለከተው ፡ ጀመር ። ከጥቂት ፡ ደ ቂቃም ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ ወደቤት ፡ ውስጥ ፡ ገባና ፡ የአንቶን ፡ ፓፍኑቲች ፡ ሰረገላ ፡ ዝግጁ ፡ መሆኑን ፡ አስታወ ቀ ። አንቶን ፡ ፓፍኑቲችም ፡ በችኰላ ፡ እንግዶቹን ፡ ተሰና በተ ። የቤቱም ፡ ባለቤት ፡ እንዲቆይ ፡ ቢለምነው ፡ እምቢ ፡ በማለት ፡ ከቤት ፡ ወጣና ፡ እሰረገላው ፡ ላይ ፡ ተሳፍሮ ፡ ገሥገ ሠ ። ሰውየው ፡ ምን ፡ እንደነካው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ግራ ፡ ገባው ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ምናልባት ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ በመብላት ም ፡ ታሞ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ አሰበ ።

ከሻይና ፡ ከመሰነባበቻ ፡ ቁርስ ፡ በኋላ ፡ ሌሎቹም ፡ እን ግዶች ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄዱ ። ፖክሮቭስኮዬም ፡ ጭር ፡ ማለትና ፡ ባዶ ፡ መሆን ፡ ጀመረች ። ሕይወትም ፡ በተለመደ ው ፡ መንገድ ፡ ቀጠለ ።

ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

እንዳችም ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ሳይሆን ፡ ብዙ ፡ ቀናት ፡ አለፉ ። የፖክሮቭስኩዬ ፡ ነዋሪዎች ፡ ሕይወት ፡ የሚስለች ፡ ነበር ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ በየቀኑ ፡ ወደ ፡ አደን ፡ መሄዱ ን ፡ ቀጠለ ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ ማንበቧን ፤ መንሸራ ሸሯንና ፡ የሙዚቃ ፡ ትምህርት ፡ ማጥናቷን ፡ እንደዚሁ ፡ ቀጠ ለች ። በተለይም ፡ የሙዚቃ ፡ ትምህርቷን ፡ ተግታ ፡ ታጠና ፡ ነበር ። ወጣቱ ፡ ፈረንሳዊ ፡ ያለውን ፡ ተሰጥዎ ፡ ለመናቅና ፡ ች ላ ፡ ለማለት ፡ የማትችል ፡ መሆንዋን ፡ ልቧ ፡ ያለ ፡ ውድ ፡ በግ ድ ፡ ይነግራትና ፡ ያሳምናት ፡ ጀመር ። እሱም ፡ በበኩሉ ፡ ተ ገቢ ፡ አክብሮትን ፡ ሳይጥስ ፡ ክብሯንና ፡ ኩራቷን ፡ ስለጠ በቀላት ፡ ተደሰተች ። ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ አስደሳች ፡ ስሜት ም ፡ በየጊዜው ፡ እየተሸነፈች ፡ ሄደች ። ዴፎርዥ ፡ በሌለ በት ፡ ሰዓት ፡ ይከፋታል ፤ እሱ ፡ ሲኖር ፡ ግን ፡ ሌላውን ፡ ነ ገር ፡ ሁሉ ፡ እርግፍ ፡ አድርጋ ፡ ትተዋለች ። ስለማንኛውም ፡ ነገር ፡ የሱን ፡ አስተያየት ፡ ትጠይቃለች ፤ ዘወትርም ፡ እሱ ፡ በሚሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ትስማማለች ። ምናልባት ፡ ገና ፡ ፍቅር ፡ አልያዛት ፡ ይሆናል ፤ አጋጣሚ ፡ ጊዜ ፡ ሲመጣ ፡ ግን ፡ በልቧ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ብው ፡ ብሎ ፡ ለ መንደድ ፡ ዝግጁ ፡ ነበር ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ መምህሯ ፡ ወደሚጠብቃት ፡ አዳራሽ ፡ ስትገባ ፡ ፊቱ ፡ ምጥጥ ፡ ብሎና ፡ የታወከ ፡ መስሎ ፡ አገኘችው ። የፒያኖውን ፡ ክዳን ፡ ከፍታ ፡ ማዜም ፡ ስትጀ መር ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ « እራሴን ፡ አሞኛል ። » የሚል ፡ ምክንያት ፡ አቀረበና ፡ ትምህርቱን ፡ አቋረጣት ። የዜማውን ፡ መጽሐፍ ፡ አጥፎም ፡ በእጅዋ ፡ አንድ ፡ የማስታወሻ ፡ ወረቅ ት ፡ በፍጥነት ፡ ሰጣት ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ ሳታስብ ፡ ተ ቀበለችውና ፡ ወዲያው ፡ ቆጫት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ዱብሮቭስኪ

ይ ፡ ሄዶ ፡ ነበር ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ወደክፍሏ ፡ ሄዳ ፡ ማስታወሻውን ፡ ስትገልጥ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ቃል ፡ አነበበች ።

« ዛሬ ፡ ማታ ፡ በአንድ ፡ ሰዓት ፡ በወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ያትክልት ፡ ቦታ ፡ እንድትገኚ ። ላነጋገርሽ ፡ እፈልጋለሁ ። »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ ለማወቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ናፍቆት ፡ አደረባት ። ስሜቱን ፡ ይገልጽልኛል ፡ ብላ ፡ ስትጠብቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜዋ ፡ ነበር ። ይህ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በልቧ ፡ ስትሻ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ፈርታ ፡ ነበር ። ያሰበችው ፡ ነገር ፡ በቃል ፡ ሲረጋገጥላት ፡ ለመስማት ፡ መፈለጓ ፡ አልቀረም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እሷን ፡ ለማግባት ፡ ደረጃው ፡ ከማይፈቅድለት ፡ ሰው ፡ አንደበት ፡ የፍቅር ፡ ቃል ፡ መስማት ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ አልታያት ፡ አለ ። ወደ ፡ ቀጠሮው ፡ ቦታ ፡ ለመሄድ ፡ ቆረጠች ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ እርግጠኛ ፡ አልነበረችም ። ይሄውም ፡ የመምህሩን ፡ የፍቅር ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ እንደምትቀበለው ፡ ነበር ። በመኳንንት ፡ ቁጣ ፤ ወይስ ፡ በወዳጅነት ፡ ተግሣጽ ፤ በሣቅና ፡ በቀልድ ፤ ወይስ ፡ በልበ ፡ እሩህሩህነት ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሰዓቱን ፡ አሁንም ፡ አሁንም ፡ ትመለከት ፡ ነበር ። ጊዜው ፡ ጨለመ ፤ ሻማም ፡ በራ ፤ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ሊጠይቁት ፡ ከመጡት ፡ የጐረቤት ፡ እንግዶቹ ፡ ጋር ፡ « ቦስተን ፡ » የተባለውን ፡ የካርታ ፡ ጨዋታ ፡ ጀመረ ። በገበታ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ የጠረጴዛ ፡ ሰዓት ፡ ለአንድ ፡ ሰዓት ፡ ሩብ ፡ ጉዳይ ፡ ሲል ፡ ደወለ ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ ወደ ፡ በረንዳው ፡ ሹልክ ፡ ብላ ፡ ወጣችና ፡ መለስ ፡ ቀለስ ፡ ብላ ፡ ተመልክታ ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ሮጣ ፡ ሄደች ።

ጊዜው ፡ ጽልመት ፡ ነበር ። ሰማዩ ፡ በደመና ፡ ስለተሸፈነም ፡ ወደፊት ፡ ሁለት ፡ እርምጃ ፡ ለማየት ፡ እንኳ ፡ አይቻልም ፡ ነበር ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ግን ፡ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ዱሮ ፡ በለመደችው ፡ መንገድ ፡ ሄደችና ፡ ከጥቂት ፡

ደቂቃ ፡ በኋላ ፡ እወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ደረሰች ። እዚያም ፡ በ ዴፎርዥ ፡ ፊት ፡ ትንፋሽ ፡ እንዳያጥራትና ፡ ቸኩላ ፡ የመጣ ች ፡ እንዳትመስል ፡ ጥቂት ፡ አረፍ ፡ ለማለትና ፡ ለመዝናናት ፡ ቆመች ። ዴፎርዥ ፡ ግን ፡ እፊት ፡ ለፊቷ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

« ጥያቄዬን ፡ ተቀብለሽ ፡ በመምጣትሽ ፡ አመሰግንሻለ ሁ » ሲል ፡ ዝቅ ፡ ባለና ፡ ሐዘን ፡ በለበሰ ፡ ድምጽ ፡ ተናገ ረ ። « ባትመጪ ፡ ኖሮ ፡ ተስፋ ፡ በቆረጥኩ ፡ ነበር ። »

ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ ያዘጋጀችውን ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ መለሰችለት ፤

« ጥያቄህን ፡ በመቀበሌ ፡ ለመጸጸት ፡ እንደማታበቃኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ። »

እሱ ፡ ምንም ፡ አልመለሰም ፤ ድፍረቱን ፡ ሰብስብ ፡ ለ ማድረግ ፡ የሚሞክር ፡ መሰለ ። በመጨረሻም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተነፈሰ ፤

« ትቸሽ ፡ ለመሄድ ፡ ጊዜው ፡ ያስገድደኛል ። ምናል ባት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ፡ ትሰሚው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ ልነግርሽ ፡ የሚገባኝ ፡ አንድ ፡ ነ ገር ፡ አለ ። »

ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ምንም ፡ አልመለሰችም ። ይህ ፡ ቃል ፡ የፍቅሩ ፡ መግለጫ ፡ ዋዜማ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ አሰበች ። እ ሱም ፡ እራሱን ፡ ደፋ ፡ አድርጎ ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፤

« እኔ ፡ ላንቺ ፡ እንደምመስልሽ ፡ አይደለሁም ። እኔ ፡ ፈረንሳዊው ፡ ዴፎርዥ ፡ ሳልሆን ፤ ዱብሮቭስኪይ ፡ ነኝ ። »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ጮኸች ።

« አይዞሽ ፡ አትደንግጪ ፤ ስሜ ፡ ሊያስፈራራሽ ፡ አይገባ ም ። እነሆ ፡ አባትሽ ፡ ቁራሽ ፡ ዳቦ ፡ የነሣኝና ፡ ከአባቴ ፡ ር ስት ፡ ነቅሎ ፡ ያባረረኝ ፤ ለውንብድናም ፡ ያደረሰኝ ፡ ምስኪ ኑ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ነኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለራስሽም ፡ ሆነ ፡ ላባት ሽ ፡ መፍራት ፡ የለብሽም ። ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጽሚል ። ይ

ቅር ፡ ብዬዋለሁ ። ያዳንሽውም ፡ አንቺ ፡ እንደሆንሽ ፡ ማወቅ ፡ አለብሽ ። የመጀመሪያውን ፡ ቂም ፡ በቀሌን ፡ ለመወጣት ፡ የፈለግኩት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ነበር ። በመኖሪያ ፡ ቤቱ ፡ እየዞ ርኩ ፡ እሳት ፡ የምለኩስበትን ፡ ቦታና ፡ ወደመኝታ ፡ ቤቱ ፡ የ ምገባበትን ፡ መንገድ ፤ እንዳያመልጥ ፡ ለማድረግ ፡ የምችል በትንም ፡ ዘዴ ፡ ሳሰላስል ፡ አንቺ ፡ እንደሰማይ ፡ መልአክ ፡ እ ልፍ ፡ ስትይ ፡ ባየሁ ፡ ጊዜ ፡ ልቤ ፡ ይቀዘቅዝ ፡ ነበር ። አንቺ ፡ የምትኖሪበት ፡ ቤት ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ፤ ካንቺ ፡ ጋር ፡ በሥጋ ፡ የተዛመደም ፡ በኔ ፡ እጅ ፡ መጥፋት ፡ የለበትም ፡ ስል ፡ አሰብ ኩ ። ቂም ፡ በቀል ፡ የመወጣትንም ፡ ሐሳብ ፡ ዕብደት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ከአዕምሮዬ ፡ አስወጣሁት ። ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ነጭ ፡ ል ብስሽን ፡ ከሩቅ ፡ ለማየት ፡ በፖክሮቭስኮዬ ፡ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ እዘዋወር ፡ ነበር ። አንቺ ፡ ሳታውቂው ፡ ስትንሸራ ሽሪ ፡ እኔ ፡ ከቁጥቋጦ ፡ ወደ ፡ ቁጥቋጦ ፡ እየተዘዋወርኩ ፡ እመ ለከትሽ ፡ ነበር ። ያንቺ ፡ ጠባቂ ፡ በመሆኔና ፡ እኔ ፡ ባለሁበት ም ፡ ቦታ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ አደጋ ፡ እንደማይደርስብሽ ፡ በ ማወቁ ፡ ለልቤ ፡ ደስታ ፡ ይሰማው ፡ ነበር ። በመጨረሻም ፡ ዕድል ፡ ገጠመኝና ፡ አንቺ ፡ ቤት ፡ ለመኖር ፡ በቃሁ ። እነዚ ህ ፡ ሦስት ፡ ሳምንታት ፡ ለኔ ፡ የደስታ ፡ ጊዚያት ፡ ነበሩ ። የ ነሱ ፡ ትዝታ ፡ አሳዛኝ ፡ ሕይወቴን ፡ ብርሃን ፡ ያጐናጽፈዋል ። እነሆ ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ ስመኖር ፡ የማያስችለኝ ፡ ወሬ ፡ ደር ሶኛል ። ዛሬውኑና ፡ አሁኑኑ ፡ ካንቺ ፡ መለየት ፡ አለብኝ ። ነ ገር ፡ ግን ፡ ከመሄዴ ፡ በፊት ፡ እንዳትቀየሚኝና ፡ እንዳታዝ ኝብኝ ፡ ስለራሴ ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ገልጬ ፡ ልነግርሽ ፡ ፈቀ ድኩ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ አስቢው ። ሲወ ለድ ፡ ዕድሉ ፡ ለሌላ ፡ እንደሆነም ፡ እወቂ ። አንቺን ፡ ለመው ደድ ፡ የሚችል ፡ መሆኑንና ፡ ከቶ ፡ ... »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለስለስ ፡ ያለ ፡ ፉጨት ፡ ተሰማ ። ዱብሮ ቭስኪይም ፡ ንግግሩን ፡ አቆመ ። እጅዋን ፡ ያዝ ፡ አድርጐ

ም ፣ ወደሚነያው ፣ ከንፈሩ ፣ አስጠጋው ። ፉጨቱ ፣ ደግሞ ፣ ተሰማ ።

« ይቅርታ ፣ አድርጊልኝ ። ፉጨቱ ፣ ለኔ ፣ ነው ፤ መሄድ ፣ አለብኝ ፤ ጥቂት ፣ የዘገየሁ ፣ እንደሆን ፣ ሕይወቴ ፣ ይጠፋል ፡ » አላት ።

ጥቂት ፣ እርምጃዎችም ፣ ወደኋላ ፣ ተራመደ ። ማሪያ ፣ ኪሪሎቭናም ፣ አለችበት ፣ ቦታ ፣ ቆማ ፣ ቀረች ። ዱብሮቭ ስኪይ ፣ እንደገና ፣ ተመለሰና ፣ እጅዋን ፣ ያዝ ፣ አደረገው ። በለ ስለሰ ፣ ድምጽም ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ ተናገራት ፤

« ምናልባት ፣ አደጋ ፣ ቢደርስብሽና ፣ የሚረዳሽና ፣ የ ሚከላከልልሽም ፣ ሰው ፣ ብታጪ ፣ የኔን ፣ እርዳታ ፣ ለመጠ የቅ ፣ ቃል ፣ ትገቢልኛለሽ? አገልግሎቴን ፣ ለመቀበል ፣ ቃል ፣ ትሰጪኛለሽ? »

ማሪያ ፣ ኪሪሎቭና ፣ ዝም ፣ ብላ ፣ አለቀሰች ። ፉጨቱም ፣ ለሦስተኛ ፣ ጊዜ ፣ ተሰማ ። ዱብሮቭስኪይም ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ ጮኸ ፤

« ልታስገድይኝ ፣ ትፈልጊያለሽ? መልስ ፣ እስክትሰጪኝ ፣ ድረስ ፣ አልሄድም ። ቃል ፣ ትገቢልኛለሽ ፣ ወይስ ፣ አትገቢ ልኝም? »

« ቃል ፣ ገብቼልሃለሁ ፣ » ስትል ፣ ምስኪኗ ፣ ቆንጅዬ ፣ ዝቅ ፣ ባለ ፣ ድምጽ ፣ ተናገረች ።

ከዱብሮቭስኪይ ፣ ጋር ፣ ባደረገችው ፣ ግንኙነት ፣ አለ ቅጥ ፣ ተበሳጭታ ፣ ከአትክልቱ ፣ ቦታ ፣ ወደቤት ፣ ተመለሰ ች ። እንደተመለሰችም ፣ የቤቱ ፣ ሰው ፣ ሁሉ ፣ ተሸብሮና ፣ በአጥር ፣ ግቢውም ፣ ውስጥ ፣ ብዙ ፣ ሰዎች ፣ ተሰብስበው ፣ አ የች ። በበረንዳው ፣ አጠገብም ፣ አንድ ፣ ሰረገላ ፣ ቆሞ ፣ ነ በር ። ከሩቅም ፣ የኪሪላ ፣ ፔትሮቪች ፣ ድምጽ ፣ ዘልቆ ፣ ይ ሰማ ፣ ነበር ። ከቤት ፣ ውስጥ ፣ መጥፋቷ ፣ ይታወቅብኛል ፣ ብላ ፣ በመፍራትም ፣ ፈጥና ፣ ወደ ፣ ክፍሏ ፣ ሄደች ። ከኪሪ

ላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ጋር ፡ አዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ተገናኙ ። ምስለ ኔውንም ፡ እንግዶቹ ፡ ከበው ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ያቀርቡለ ት ፡ ነበር ። ምስለኔውም ፡ የወታደር ፡ ልብሱን ፡ ለብሶና ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ ከግር ፡ እስከራሱ ፡ ታጥቆ ፡ ጥያቄአቸ ውን ፡ ምሥጢራዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ይመልስላቸው ፡ ነበር ።

« ማሻ ፤ የት ፡ ነበርሽ? ሙሴ ፡ ዴፎርዥን ፡ አይተሻል? » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ጠየቃት ።

ማሻም ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አቃታት ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ንግግሩን ፡ በመቀጠል ፤ እንዲ ህ ፡ አለ ፤

« ይገርምሻል ፤ ምስለኔው ፡ ዴፎርዥን ፡ ለመያዝ ፡ መ ጥቷል ፤ ዱብሮቭስኪይ ፡ እራሱ ፡ ነው ፡ እያለም ፡ ያረጋግጥ ልኛል ። »

« እነሆ ፡ መግለጫው ፡ ክቡር ፡ ሆይ ፡ » ሲል ፡ ምስ ለኔው ፡ ባክብሮት ፡ ቃል ፡ ተናገረ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ነገሩን ፡ አቋረጠውና ፤ እንዲህ ፡ አለው ፤

« ወዳጄ ፡ ሆይ ፤ ከመግለጫህ ፡ ጋር ፡ እንትን ፡ ግባ ፤ በታውን ፡ ታውቀዋለህ ። ጉዳዩን ፡ እኔ ፡ እራሴ ፡ ሳላጣራ ፡ ፈረንሳዊውን ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጥህም ። ያን ፡ ቀጣፊ ፡ ዋሾ ፡ አን ቶን ፡ ፓፍኑቲችን ፡ ማን ፡ ያምናል ። ምናልባት ፡ በሕልሙ ፡ መምህሩ ፡ ሲሰርቀው ፡ ታይቶት ፡ ይሆናል ። እንግዲያው ፡ ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ጧት ፡ ምነው ፡ ሳይነግረኝ ፡ ቀረ? »

« ክቡር ፡ ሆይ ፤ ፈረንሳዊው ፡ ስላስፈራራውና ፡ አንድ ፡ ቃ ል ፡ እንዳይተነፍስም ፡ ስላስማለው ፡ ነው ፡ » ሲል ፡ ምስለ ኔው ፡ መለሰ ።

« የውሸት ፡ ቋት! » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « ጉዳዩን ፡ እኔው ፡ እራሴ ፡ በፍጥነት ፡ አጣራዋለሁ ። መምህሩ ፡ የት ፡ ነው? » ሲል ፡ ወደአዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ በዚያን ፡ ሰዓት ፡ የገባ ውን ፡ አንዱን ፡ አሽከሩን ፡ ጠየቀው ።

« የትም ፡ ቦታ ፡ ሊገኝ ፡ አልቻለም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ » ሲ
ል ፡ አሽከሩ ፡ መለሰ ።

« ፈልጉታ! » ሲል ፡ ትሮዬኩሮቭ ፡ ጥርጣሬ ፡ እየገባው ፡ በጩኸት ፡ ቃል ፡ ተናገረ ።

« ያን ፡ የተከበረ ፡ መግለጫህን ፡ እስቲ ፡ አሳየኝ ፡ » አለና ፡ ምስለኔውን ፡ ጠየቀው ። ምስለኔውም ፡ ወዲያው ፡ ወረቀቱን ፡ አቀረበ ።

« እህ! ዕድሜው ፡ ሃያ ፡ ሦስት ፤ ቁመቱ ፡ መጠነኛ ፤ ጢሙን ፡ የተላጨ ፤ ዓይኑ ፡ ቡናማ ፤ ... ይህስ ፡ ሆነ ። ግን ፡ ይሄ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። መምህሩ ፡ የት ፡ አለ? »

« ሊገኝ ፡ አልቻለም ፡ » የሚል ፡ መልስ ፡ አሁንም ፡ ተሰማ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ሥጋት ፡ አደረበት ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ በሞትና ፡ በሕይወት ፡ መካከል ፡ ተሰቃየች ።

« ማሻ ፡ ሰውነትሽ ፡ ተለውጧል ። አስፈራርተውሻል ፡ » አለና ፡ አባቷ ፡ ተናገረ ።

« የለም ፡ አባባ ፤ እራሴን ፡ ስላመመኝ ፡ ነው ። »

« ሂጂ ፡ ወደክፍልሽ ። አይዞሽ ፡ አትፍሪ ። »

ማሻም ፡ ያባቷን ፡ እጅ ፡ ሳመችና ፡ ፈጥና ፡ ወደክፍሏ ፡ ሄደች ። አልጋዋ ፡ ላይ ፡ ወድቃም ፡ እየተንሰቀሰቀች ፡ ታለቅስ ፡ ጀመር ። ገረዶችም ፡ ወደክፍሏ ፡ ሮጠው ፡ ሄደው ፡ በችግር ፡ ልብሷን ፡ አወለቁላትና ፡ በቀዝቃዛ ፡ ውኃና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መድኃኒት ፡ ሊያስታግሷት ፡ ቻሉ ። ኋላም ፡ አስተኟትና ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ይዟት ፡ ሄደ ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ፈረንሳዊው ፡ ሰውዬ ፡ ሊገኝ ፡ አልቻለም ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ባዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ወደላይና ፡ ወደታች ፡ እየተንጐራደደ ፡ « የድል ፡ ነጋሪቶች ፡ ድምጻችሁን ፡ አሰሙ ፡ » እያለ ፡ በኃይል ፡ ያፏጭ ፡ ጀመር ። እ

ንግዶቹም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አሾከሾኩ ። ምስለኔውም ፡ ቂል ፡ መሰለ ፤ ፈረንሳዊውም ፡ ሳይገኝ ፡ ቀረ ። እርሱ ፡ እንደ ሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ደርሶት ፡ አምልጧል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በምን ፡ አኳኋንና ፡ ማን ፡ እንዳስጠነቀቀው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊያውቅ ፡ አልቻለም ።

የጠረጴዛው ፡ ሰዓት ፡ ከምሽቱ ፡ አምስት ፡ ሰዓት ፡ ሲል ፡ ደወለ ። ነገር ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊተኛ ፡ አልፈለገም ። በመጨረሻ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ምስለኔውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ ተናገረው ፤

« ታዲያስ! እንግዲህ ፡ ሌሊቱን ፡ እዚህ ፡ አታድር ፤ ቤቴ ፡ ሆቴል ፡ አይደለም ። ወንድሜ ፡ ሆይ ፤ ሰውዬው ፡ እውነት ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ከሆነ ፡ እሱን ፡ ለመያዝ ፡ ፈጣን ፡ መሆን ፡ ነበረብህ ። ሂድ ፡ ወደቤትህ ፤ ለሌላው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ፈጠን ፡ በል ። » ወደእንግዶቹም ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ « እናንተም ፡ እንግዲህ ፡ ወደየቤታችሁ ፡ ሂዱ ። በሉ ፡ ሰረገላዎቻችሁ ፡ እንዲጫኑ ፡ እዘዙ ፤ እኔ ፡ መተኛት ፡ እፈልጋለሁ ። »

እነሆ ፡ ትሮዬኩሮቭ ፡ እንግዶቹን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ የብልግና ፡ ጠባይ ፡ ሸኛቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

አሁንም ፡ ደግሞ ፡ አንዳችም ፡ ዓይነት ፡ አስደናቂ ፡ ነገር ፡ ሳይታይ ፡ ብዙ ፡ ቀናት ፡ አለፉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ቀጥሎ ፡ በመጣው ፡ የበጋ ፡ ወራት ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ቤተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ለውጥ ፡ ተደረገ ።

ከእርሱ ፡ እርስት ፡ ሰላሣ ፡ ቬርስታ* ፡ ያህል ፡ እርቆ ፡ የ

---

* ቬርስታ — የዱሮ ፡ ሩሲያ ፡ የርዝመት ፡ መለኪያ ፡ ነው ። በግምት ፡ ከአንድ ፡ ኪሎሜትር ፡ ትንሽ ፡ ይበልጣል ።

ልዑል ፡ ቬሬይስኪይ ፡ እርስት ፡ ይገኛል ። ልዑሉ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚቀመጥ ፡ እርስቱን ፡ የሚጠብቅለት ፡ አንድ ፡ ከሥራ ፡ የተሰናበተ ፡ የሻለቃ ፡ ነበር ። በፖክሮቭስኩዬና ፡ በአርባቶቮ ፡ ቀበሌዎች ፡ መካከል ፡ የነበረውም ፡ ግንኙነት ፡ ተቋርጦ ፡ ነበር ። በግንቦት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ልዑሉ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ተመለሰና ፡ በሕይወቱ ፡ አይቶት ፡ ወደማያውቀው ፡ መንደሩ ፡ ሄደ ። ተድላና ፡ ደስታ ፡ የለመደ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ብቸኛነቱ ፡ ወዲያው ፡ አሰለቸው ። በመጣ ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡ ዱሮ ፡ ከተዋወቀው ፡ ከትሮዬኩሮቭ ፡ ጋር ፡ ምሳ ፡ ለመብላት ፡ ሄደ ።

ልዑሉ ፡ ዕድሜው ፡ ሃምሳ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ ከዕድሜው ፡ በላይ ፡ በጣም ፡ ያረጀ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ከልክ ፡ በላይ ፡ ስለሚወስድ ፡ ጤናውን ፡ ጐድቶት ፡ ነበር ። የማይጠፉ ፡ ምልክትም ፡ ትቶበታል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ያለውና ፡ የግል ፡ ባሕርይ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ነበር ። ይልቁንም ፡ ደግሞ ፡ ዘወትር ፡ በማህበር ፡ መካከል ፡ መገኘት ፡ የለመደ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ለሴቶች ፡ ትህትና ፡ በማሳየት ፡ ረገድ ፡ የሠለጠነ ፡ ነበር ። ዘወትርም ፡ መደሰትን ፡ ይፈልግ ፡ ነበር ። ሁልጊዜም ፡ ይሠለቸው ፡ ነበር ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ዓለምን ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ የሚያውቀው ፡ ይህ ፡ ልዑል ፡ ስለጐበኘው ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ቆጥሮት ፡ እጅግ ፡ ተደሰተ ። እንደልማዱ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ለእንግዳው ፡ እርስቱን ፡ እያዞረ ፡ ሲያስጐበኘው ፡ በተለይ ፡ የውሻ ፡ ማሳደጊያውን ፡ ቦታ ፡ አሳየው ። ልዑሉ ፡ ግን ፡ የውሾቹ ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ እጅግ ፡ ስለከረፋው ፡ በሽቶ ፡ በተነከረ ፡ መሐረብ ፡ አፍንጫውን ፡ አፍኖ ፡ በችኰላ ፡ ወጣ ። የተከረከሙ ፡ ዛፎች ፡ ያሉበት ፡ የጥንት ፡ ጊዜ ፡ ያትክልት ፡ ቦታና ፡ ባለ ፡ አራት ፡ ማዕዘኑ ፡ ኩሬ ፡ እንዲሁም ፡

ቀጥ ፡ ያለው ፡ ቀጭን ፡ መንገድ ፡ ልዑሉ ፡ የሚወደው ፡ ዓይነት ፡ አልነበረም ። እሱን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ የእንግሊዞች ፡ ዓይነት ፡ ያትክልት ፡ ቦታና ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕጸዋት ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ የዚያኛውን ፡ ማመስገኑና ፡ ማድነቁ ፡ አልቀረም ። አንድ ፡ አሽከር ፡ መጥቶ ፡ ምሳ ፡ ቀርቧል ፡ ሲል ፡ ስላስታወቀ ፡ ወደቤት ፡ ተመለሱ ። ልዑሉ ፡ እጅግ ፡ ስለደከመው ፡ ያነክስ ፡ ነበር ፤ በጉብኝቱም ፡ መጸጸት ፡ ጀምሮ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ባዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ስለተቀበለቻቸው ፡ ይህ ፡ ተንኰለኛ ፡ ሰው ፡ በውበቷ ፡ ተደነቀ ። ትሮዬኩሮቭም ፡ እንግዳውን ፡ በእርሷ ፡ አጠገብ ፡ አስቀመጠው ። ልዑሉም ፡ በልጂቱ ፡ መገኘት ፡ እጅግ ፡ ስለተደሰተ ፡ መንፈሱ ፡ ታደሰ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጨዋታ ፡ በማውራትም ፡ የልጂቱን ፡ ጆሮ ፡ ለመማረክ ፡ ቻለ ። ከምሳ ፡ በኋላ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ፈረስ ፡ ግልቢያ ፡ እንዲሄዱ ፡ ሐሳብ ፡ አቀረበ ። ልዑሉ ፡ ግን ፡ ጫማው ፡ የከፋይ ፡ መሆኑን ፡ ምክንያት ፡ በመስጠትና ፡ ቁርጥማት ፡ አለብኝ ፡ ብሎ ፡ በመቀለድ ፡ በሠረገላ ፡ እንዲንሸራሸሩ ፡ መረጠ ። ይህንን ፡ ማድረጉም ፡ ከውቢቱ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ እንዳይለያይ ፡ ሲል ፡ ነው ። ሠረገላው ፡ ተጫነ ፤ ሁለቱ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ወጣቷ ፡ ቆንጆም ፡ ተቀምጠው ፡ ሄዱ ። ወሬውም ፡ ያለማቋረጥ ፡ ቀጠለ ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ ዓለማዊው ፡ ሰው ፡ የሚያጕርፍላትን ፡ የሙገሣ ፡ ቃልና ፡ የብልህነት ፡ አስተያየቱን ፡ በደስታ ፡ ስትሰማ ፡ ድንገት ፡ ቬሬይስኪይ ፡ ወደኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ የሚያልፉት ፡ የተቃጠለ ፡ ቤት ፡ ምን ፡ እንደነበርና ፡ ባለቤቱስ ፡ እርሱ ፡ እንደሆን ፡ ጠየቀው ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ፊቱን ፡ ኰሰተረ ። የተቃጠለው ፡ ቤት ፡ የቀሰቀሰበት ፡ ትዝታ ፡ የሚያስደስት ፡ አልነበረም ። ቤቱ ፡ ቀድሞ ፡ የዱብሮቭስኪይ ፡ እንደነበርና ፡ አሁን ፡ ግን ፡ የርሱ ፡ እንደሆነ ፡ ገለጸ ።

« የዱብሮቭስኪይ? » አለና ፡ ደገመ ፡ ቬሬይስኪይ ። « ም ን! የዚያ ፡ የታወቀ ፡ ሽፍታ? »

« ያባቱ ፡ ነበር ፡ » አለና ፡ መለሰ ፡ ትሮዬኩሮቭ ። « አባ ትየም ፡ ቢሆን ፡ እንዲሁ ፡ ወንበዴ ፡ ቢጤ ፡ ነበር ። »

« ሪናልዶስ[28] ፡ እምን ፡ ደረሰ? በሕይወት ፡ ነው? አሁንም ፡ አልተያዘም? »

« በሕይወት ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ በመፈለግ ፡ ላይ ፡ ነ ው ፤ ምስለኔዎቻችን ፡ ከሌቦች ፡ ጋር ፡ መተባበራቸውን ፡ እ ስከቀጠሉ ፡ ድረስ ፡ ሊያዝ ፡ አይችልም ። ዱብሮቭስኪይ ፡ ወደአርባቶቮስ ፡ መጥቶ ፡ አልነበረም ፡ ልዑል? »

« አዎን ፤ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አቃጥሎ ፡ ይሁን ፡ ዘርፎ ፡ ሄደ ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፤ ይህን ፡ ዝነኛ ፡ ሰ ው ፡ ማወቅ ፡ የሚያስደስት ፡ አይመስልሽም? »

« የሚያስደስት? » አለ ፡ ትሮዬኩሮቭ ። « ታውቀዋለች ፡ እንጂ ። ሦስት ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ሙዚቃ ፡ ሲያስተምራ ት ፡ ነበር ። ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ላስተማረበ ት ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ አልወሰደም ። »

እዚህ ፡ ላይ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ የፈረንሳዊ ፡ መምህ ሩን ፡ ታሪክ ፡ መዘርዘር ፡ ጀመረ ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ጨ ነቃት ፤ ቬሬይስኪይም ፡ ታሪኩን ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ ካዳመጠ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ አስደናቂ ፡ ሆኖ ፡ ስለተሰማው ፡ ወሬው ን ፡ ለወጠው ። ከሽርሽሩ ፡ ሲመለሱም ፡ ሠረገላው ፡ እንዲ ጫን ፡ አዘዘ ፤ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እንዲያድር ፡ አጥብቆ ፡ ቢለምነውም ፡ ቅሉ ፡ ከሻይ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ ፈጥኖ ፡ ሄደ ። ከመሄዱ ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ከማሪ ያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ እንዲጎበኘው ፡ ጋበዘው ፤ ኩሩው ፡ ትሮዬኩሮቭም ፡ ግብዣውን ፡ ተቀበለ ። ምክንያቱም ፡ ልዑል ፡ ቬሬይስኪይ ፡ ባለሁለት ፡ ኮከብ ፡ ማዕርግና ፡ ባለሦስት ፡ ሺ ፡ ገባር ፡ ስለሆነ ፡ እኩያዬ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በመገመት ፡ ነው ።

ከሁለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችና ፡ ልጁ ፡ ማሻ ፡ ልዑል ፡ ቬሬይስኪይን ፡ ለመጎብኘት ፡ ሄዱ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ወደ ፡ አርባቶቮ ፡ መንደር ፡ በተጠጋም ፡ ጊዜ ፡ የገበሬዎቹን ፡ ንጹህና ፡ ብሩህ ፡ ጐጆዎች ፡ እንዲሁም ፡ በእንግሊዝ ፡ ምኽግ ፡ ዓይነት ፡ የተሠራውን ፡ የልዑሉን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ማድነቅ ፡ ግድ ፡ ሆነበት ። በቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንገታቸው ፡ ላይ ፡ ቃጭል ፡ የታሰረባቸው ፡ የስዊዝ ፡ አገር ፡ ላሞች ፡ የሚግጡበት ፡ አረንጓዴ ፡ መስክ ፡ አለ ። በቤቱም ፡ ዙሪያ ፡ ሰፊ ፡ መናፈሻ ፡ ቦታ ፡ አለ ። ጋባዡ ፡ እንግዶቹን ፡ እበረንዳው ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀበላቸው ፤ እጁንም ፡ ለውቢቱ ፡ ዘረጋላትና ፡ ተያይዘው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ የተሸቆጠቆጠ ፡ አዳራሽ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ። ለሶስት ፡ ሰዎች ፡ የተዘጋጀ ፡ ጠረጴዛም ፡ ጠበቃቸው ። ልዑሉ ፡ ወደመስኮቱ ፡ መራቸውና ፡ ከበፊታቸው ፡ ያለውን ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ የተፈጥሮ ፡ ውበት ፡ እንዲመለከቱ ፡ አደረጋቸው ። በመስኮቱ ፡ አኳያ ፡ የቮልጋ ፡ ወንዝ ፡ ይፈሳል ። በወንዙም ፡ ፈረሰኛ ፡ ውኃ ፡ ላይ ፡ ዕቃ ፡ የተጫኑ ፡ ታላላቅ ፡ ጀልባዎችና ፡ « የሞት ፡ ወጥመድ ፡ » የተባሉ ፡ ታናናሽ ፡ የዓሣ ፡ ማጥመጃ ፡ ጀልባዎች ፡ ይንሳፈፋሉ ። ከወንዙ ፡ ማዶም ፡ ጋራዎችና ፡ መስኮች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በመንደር ፡ አጊጠው ፡ ይታያሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልዑሉ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የገዛቸውን ፡ ሥዕሎች ፡ በሥርዓት ፡ ሰቅሎ ፡ ያስቀመጠበትን ፡ ክፍል ፡ አስጐበኛቸው ። ልዑሉም ፡ የያንዳንዱን ፡ ሥዕል ፡ ዓላማና ፡ የሠዓሊውን ፡ ታሪክ ፤ እንዲሁም ፡ የሥዕሉን ፡ ጥሩነትና ፡ ጉድለት ፡ ለማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ገለጸላት ። ስለሥዕሎቹም ፡ ሲናገር ፡ ዕውቀቱን ፡ ለመግለጽ ፡ እንደሚሞክር ፡ ሰው ፡ ሳይሆን ፡ ከስሜትና ፡ ከዓይነ ፡ ሕሊና ፡ ጋር ፡ ነበር ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ በደስታ ፡ አዳመጠችው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገበታ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ። ትሮዬኩሮቭ ፡ የቀረበለትን ፡ ማለፊያ ፡

የወይን ፡ ጠጅ ፡ እየጠጣ ፡ የልዑሉ ፡ ወጥቤት ፡ ያዘጋጀው
ን ፡ ጣፋጭ ፡ ምግብ ፡ ከሰከሰ ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ ለሁለ
ተኛ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ካየችው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ያላንዳች ፡ ፍርሃ
ትና ፡ ሐፍረት ፡ ተዝናንታ ፡ ትጫወት ፡ ጀመር ። ከምሳ ፡ በ
ኋላም ፡ ወደ ፡ አትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ወስዶ ፡ አንሸራሸራቸውና ፡
በአንድ ፡ ሰፊ ፡ ሐይቅ ፡ ዳርቻ ፡ ባለ ፡ የወይን ፡ ተክል ፡ ስር ፡
ቡና ፡ ጋበዛቸው ። ሐይቁም ፡ በደሴቶች ፡ ያጌጠ ፡ ነበር ።
ድንገት ፡ የሙዚቃ ፡ ጨዋታ ፡ ተሰማ ፤ ስድስት ፡ መቅዘፊያ ፡
ያለውም ፡ ጀልባ ፡ ወደ ፡ ወይኑ ፡ ተክል ፡ ቀረበ ። ልዑሉና ፡
እንግዶቹ ፡ በጀልባው ፡ ላይ ፡ ሆነው ፡ በደሴቶቹ ፡ ዙሪያ ፡
ቀዘፉ ። አንዳንዶቹንም ፡ ደሴቶች ፡ ሲጐበኙ ፡ ባንደኛው ፡
ላይ ፡ የእምነበረድ ፡ ሐውልት ፤ በሁለተኛው ፡ ላይ ፡ ባዶ ፡
ዋሻ ፤ በሦስተኛው ፡ ላይ ፡ ምሥጢራዊ ፡ ጽሑፍ ፡ የተቀረጸ
በት ፡ ሐውልት ፡ አዩ ። በተለይ ፡ ይህ ፡ ሐውልት ፡ የማሪያ ፡
ኪሪሎቭናን ፡ የማወቅ ፡ ስሜቷን ፡ ቀሰቀሰው ። ልዑሉም ፡
የሚሰጣት ፡ መልስ ፡ ትህትና ፡ የተመላበት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡
አጥጋቢ ፡ አልነበረም ። ጊዜው ፡ ሳያውቁት ፡ አለፈ ፤ መምሸ
ትም ፡ ጀመረ ። ልዑሉም ፡ በብርድና ፡ በቅዝቃዜ ፡ አመካ
ኝቶ ፡ እንግዶቹን ፡ በፍጥነት ፡ ወደቤት ፡ ይዟቸው ፡ ተመለሰ ።
እዚያም ፡ የሻይ ፡ ጀበና ፡ ፈልቶ ፡ ጠበቃቸው ። ልዑሉም ፡
እሱ ፡ ያላገባ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ የቤት ፡
አስተናጋጅነቱን ፡ ቦታ ፡ ትይዝለት ፡ ዘንድ ፡ ጠየቃት ። እሷ
ም ፡ ሻዩን ፡ እየቀዳች ፡ የደማሙን ፡ ሰው ፡ የማያልቅ ፡ ጨ
ዋታ ፡ መስማቷን ፡ ቀጠለች ። ድንገት ፡ የተኩስ ፡ ድምጽ ፡
ተሰማ ፤ ሰማዩም ፡ በርችት ፡ ብሩህ ፡ ሆነ ። ልዑሉ ፡ ለማሪያ ፡
ኪሪሎቭና ፡ እትከሻ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ የሚደረግ ፡ ሻል ፡ ሰጣት
ና ፡ እሷንም ፡ አባቷንም ፡ ወደበረንዳው ፡ እንዲወጡ ፡ ጠየ
ቃቸው ። በቤቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀለማት ፡ በሰማዩ ፡
ላይ ፡ እየፈነዱና ፡ እየተሰራጩ ፡ የዘምባባና ፡ የፏፏቴ ፤ የ

ዝናብና ፣ የከዋክብት ፣ መልክ ፣ እየሠሩ ፣ ይወርዱ ፣ ነበር ። አንዱ ፣ ሲጠፋ ፣ ሌላው ፣ ተግ ፣ ብሎ ፣ ይፈነዳል ። ማሪያ ፣ ኪሪሎቭና ፣ በትርኢቱ ፣ እንደ ፣ ሕጻን ፣ ልጅ ፣ ተደሰተች ። ልዑሉም ፣ በልጂቱ ፣ መደሰት ፣ መልካም ፣ ስሜት ፣ አደረበት ። ኪሪላ ፣ ፔትሮቪችም ፣ ልዑሉ ፣ ይህን ፣ ሁሉ ፣ ነገር ፣ ያዘጋ ጀው ፣ ለኔ ፣ ክብርና ፣ እኔን ፣ ለማስደሰት ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ በማሰ ብ ፣ እጅግ ፣ ተደሰተ ።

የእራት ፣ ግብዣው ፣ እንደምሳ ፣ ግብዣው ፣ ሁሉ ፣ ግሩ ም ፣ ነበር ። ከዚህ ፣ በኋላ ፣ እንግዶቹ ፣ ወደ ፣ ተዘጋጀላቸው ፣ ክፍል ፣ አመሩ ። በማግሥቱ ፣ ጧትም ፣ እንደገና ፣ እንደሚ ገናኙ ፣ ተስፋ ፣ ተሰጣጡና ፣ ከትሁቱ ፣ ጋባዣቸው ፣ ጋር ፣ ተሰነባበቱ ።

## ምዕራፍ ፣ ፲፩ ።

ማሪያ ፣ ኪሪሎቭና ፣ በተከፈተው ፣ መስኮት ፣ አጠገብ ፣ በክፍሏ ፣ ውስጥ ፣ ተቀምጣ ፣ የጥልፍ ፣ ሥራ ፣ ትሠራ ፣ ነበር ። ኰንራድን[30] ፣ የወደደችው ፣ ሴት ፣ በፍቅር ፣ ሐሳብ ፣ በመዋ ጧ ፣ ጽጌረዳ ፣ ስትጠልፍ ፣ በአረንጓዴ ፣ ሐር ፣ ጠለፈች ። ማሪያ ፣ ኪሪሎቭና ፣ ግን ፣ ምንም ፣ እንኳ ፣ ሐሳቧ ፣ እሩቅ ፣ ቦ ታ ፣ ቢሆንም ፣ የጥልፍ ፣ ሥራዋን ፣ አላዘባረቀችም ። በረ ቂቅ ፣ የተነደፈውን ፣ ያላንዳች ፣ ስሕተት ፣ በትክክል ፣ ገል ብጣ ፣ በጨርቁ ፣ ላይ ፣ ትጠልፍ ፣ ነበር ።

ድንገት ፣ የአንድ ፣ ሰው ፣ እጅ ፣ በተከፈተው ፣ መስኰ ት ፣ ቀስ ፣ ብሎ ፣ ተዘረጋና ፣ አንድ ፣ ደብዳቤ ፣ በጥልፍ ፣ ሥ ራዋ ፣ ላይ ፣ አስቀምጦ ፣ ወዲያውኑ ፣ ጠፋ ። ማሪያ ፣ ኪሪ ሎቭናም ፣ ከምንጊዜው ፣ እልም ፣ ብሎ ፣ እንደሄደ ፣ ለማየ ት ፣ ጊዜ ፣ አልነበራትም ። ያነየውኑም ፣ አንድ ፣ አሽከር ፣ ገ ባና ፣ አባቷ ፣ እንደሚፈልጋት ፣ አስታወቀ ። ደብዳቤውን ፣

ጣቶቿ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ እመሐረቧ ፡ ሥር ፡ ደበቀችና ፡ ወደ ፡ አባቷ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በፍጥነት ፡ ሄደች ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ብቻውን ፡ አልነበረም ፤ ልዑል ፡ ቬሬይስኪይም ፡ አብሮት ፡ ነበር ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ስት መጣ ፡ ልዑሉ ፡ ባልተለመደ ፡ ሐፍረት ፡ ብድግ ፡ አለና ፡ በጸ ጥታ ፡ እጅ ፡ ነሣት ።

« ነይ ፡ ወዲህ ፡ ማሻ ፡ » አላት ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « የ ምነግርሽ ፡ ቸር ፡ ወሬ ፡ አለኝ ፤ እንደሚያስደስትሽም ፡ ተ ስፋ ፡ አደርጋለሁ ። እነሆ ፡ እጮኛ ፡ አገኘሽ ፤ ልዑሉ ፡ ሊያ ገቡሽ ፡ ይፈልጋሉ ። »

ማሻ ፡ ክው ፡ ብላ ፡ ደነገጠች ፤ ፊቷንም ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ ሸፈነው ። ልዑሉ ፡ ወደርሷ ፡ ተጠጋና ፡ እጅዋን ፡ ይዞ ፡ ፈቃ ዷ ፡ ቢሆን ፡ ታስደስተው ፡ ዘንድ ፡ በሚያሳዝን ፡ ድምጽ ፡ ጠየቃት ። ማሻ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አለች ።

« ትስማማለች ፡ እንጂ! » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « ይስሙ ፡ ልዑል ፡ ሆይ ፤ ልጃገረዶች ፡ እስማማለሁ ፡ የሚ ለውን ፡ ቃል ፡ ለመናገር ፡ ይቸግራቸዋል ። በሉ ፡ እንግዲህ ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፡ ተሳሳሙ ፤ ደስ ፡ ይበላችሁም ። »

ማሻ ፡ እንደቆመች ፡ ቀረች ። ሽማግሌው ፡ ልዑል ፡ እ ጅዋን ፡ ሳማት ፤ ድንገት ፡ እንባዋ ፡ በጉንጮቿ ፡ ላይ ፡ ኰ ለል ፡ ብሎ ፡ ወረደ ። ልዑሉም ፡ ከፋው ።

« ሂጂ! ሂጂ! » አላት ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « ሂጂና ፡ እን ባሽን ፡ አድርቀሽ ፡ የደስታ ፡ መልክሽን ፡ ይዘሽ ፡ ተመለ ሺ ። ልጃገረዶች ፡ በታጩ ፡ ጊዜ ፡ ዘወትር ፡ ያለቅሳሉ ፡ » አለ ፡ ወደልዑሉ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ። « ልማዳቸው ፡ ነው ። መ ቸስ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፤ እንግዲህ ፡ ልዑል ፡ ሆይ ፡ ስለዋናው ፡ ነገር ፡ እንነጋገር ፤ ማለት ፡ ስለጥሎሹ ። »

ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ሂጂ ፡ ስለተባለች ፡ ደስ ፡ አላት ። ፈጥናም ፡ ወደክፍሏ ፡ ሄደችና ፡ በሩን ፡ ቆለፈች ። የልዑሉ ፡

ሚስት ፡ መሆኗ ፡ እየታያትም ፡ ተንሰቅስቃ ፡ አለቀሰች ። ል ዑሉንም ፡ ድንገት ፡ አስቀያሚና ፡ አጸያፊ ፡ ሆኖ ፡ አገኘችው ። ከእርሱ ፡ ጋር ፡ መጋባትም ፡ እንደመቃብር ፡ ድንጋይ ፡ አስፈ ራራት ።

« የለም ፡ የለም ፡ » አለች ፡ ዲጋግማ ፡ በጭንቋ ። « መሞ ት ፡ ወይ ፡ መመነን ፤ ወይም ፡ ዱብሮቭስኪይን ፡ ማግባት ፡ ይ ሻለኛል ። » በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደብዳቤውን ፡ አስታወሰችና ፡ ከእር ሱ ፡ ዘንድ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ በማመን ፡ በናፍቆት ፡ አነ በበችው ። እውነትም ፡ የተጻፈው ፡ በእርሱ ፡ እጅ ፡ ነበር ። ቃሉም ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

« እተለመደው ፡ ቦታ ፡ ዛሬ ፡ ከምሽቱ ፡ በአራት ፡ ሰዓ ት ፡ እንገናኝ ። »

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

ጨረቃዋ ፡ ደምቃለች ፤ ሰዓቱም ፡ ፀጥ ፡ ያለ ፡ የሐምሌ ፡ ምሽት ፡ ነው ። ነፋሱ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሽው ፡ ይላል ፤ የአት ክልቱ ፡ ዕጸዋትም ፡ በርጋታ ፡ ይወዛወዛሉ ።

እንደላባ ፡ ቀላል ፡ የሆነችው ፡ ውብ ፡ እመቤት ፡ እቀጠ ሮው ፡ ቦታ ፡ ደረሰች ። ማንም ፡ የሚታይ ፡ ሰው ፡ አልነበረ ም ። ድንገት ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ከወይን ፡ ሐረጉ ፡ በስተኋ ላ ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ እፊቷ ፡ ቆመ ።

« ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አውቃለሁ ፡ » አላት ፡ ዝቅ ፡ ባለና ፡ በሐዘን ፡ ድምጽ ። « የሰጠሽኝን ፡ ተስፋ ፡ አስታውሺ ። »

« ልታድነኝ ፡ እንደምትፈልግ ፡ አውቃለሁ ፡ » አለች ፡ ማ ሻ ፡ « ነገር ፡ ግን ፡ አትቆጣና ፡ ሰግቻለሁ ። እንዴት ፡ ልትረ ዳኝ ፡ ትችላለህ? »

« ከምትጠይው ፡ ሰው ፡ ላድንሽ ፡ እችላለሁ ። »

« እንዳትነካው ፡ እለምንሃለሁ ። እኔን ፡ ትወደኝ ፡ እንደሆን ፡ አትንካው ። የጭካኔ ፡ ተግባር ፡ ምክንያት ፡ ልሆን ፡ አልፈቅድም ።»

« አልነካውም ። ያንቺ ፡ ፍላጐት ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ። ሕይወቱንም ፡ ያዳንሽው ፡ አንቺ ፡ ነሽ ። ባንቺ ፡ ስም ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የጭካኔ ፡ ተግባር ፡ አልፈጽምም ። እኔ ፡ ምንም ፡ ወንጀለኛ ፡ ብሆንም ፡ ቅሉ ፡ አንቺ ፡ ግን ፡ ንጹህ ፡ መሆን ፡ አለብሽ ። ታዲያ ፡ ከጨካኝ ፡ አባትሽ ፡ እንዴት ፡ ላድንሽ ፡ እችላለሁ? »

« ተስፋ ፡ አለ ። በእንባዬና ፡ በጭንቄ ፡ ሕሊናውን ፡ ሳልቀሰቅሰው ፡ አልቀረም ። እርግጥ ፡ ነው ፤ የማይበገር ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ በጣም ፡ ይወደኛል ። »

« እሱስ ፡ ከንቱ ፡ ተስፋ ፡ ነው! ልቅሶሽን ፡ የሚቆጥረው ፡ ልጃገረዶች ፡ ለፍቅር ፡ ሳይሆን ፡ ለጥቅም ፡ ሲያገቡ ፡ እንደሚሰማቸው ፡ ሐፍረትና ፡ ጥላቻ ፡ ነው ። አንቺ ፡ ሳትፈቅጂ ፡ በግድ ፡ እስደስትሻለሁ ፡ ብሎ ፡ ቢቆርጥስ? ለዘለዓለሙ ፡ ያንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ሚስት ፡ ሆነሽ ፡ እንድትኖሪ ፡ ወደ ፡ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ጐትቶ ፡ ቢወስድሽስ? »

« ይህ ፡ ከሆነስ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይቻልም ። ናና ፡ አድነኝ ፤ ሚስትህም ፡ እሆናለሁ ። »

ዱብሮቭስኪይ ፡ ተንቀጠቀጠ ፤ ፊቱም ፡ ፍም ፡ መሰለ ። ወዲያውም ፡ ደሙ ፡ ምጥጥ ፡ አለ ፤ ለረጅም ፡ ጊዜም ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

« ባለሽ ፡ ብርታት ፡ ሁሉ ፡ አባትሽን ፡ ለምኚው ። እጫማው ፡ ላይ ፡ ወድቀሽ ፤ የጨረጨሰና ፡ ጊዜውን ፡ በከንቱ ፡ ያሳለፈ ፡ ሽማግሌ ፡ ሚስት ፡ ስትሆኚ ፡ አበባው ፡ ልጅነትሽ ፡ እንዴት ፡ እንደሚጠወልግ ፡ ገልጸሽ ፡ ንገሪው ። እምቢ ፡ ያለ ፡ እንደሆንም ፡ እሱን ፡ የሚያሰጋውና ፡ አንቺን ፡ የሚያድንሽ ፡ ሰው ፡ እንዳለ ፡ ዕውነቱን ፡ አፍርጠሽ ፡ ንገሪው ።

ሐብት ፣ ያንድ ፣ አፍታ ፣ ደስታ ፣ እንኳ ፣ እንደማይሰጥሽ ፣ አስረጂው ። ሐብት ፣ የሚያጽናናው ፣ ድህነትን ፣ ብቻ ፣ እን ደሆነና ፣ ያውም ፣ ደግሞ ፣ ላጭር ፣ ጊዜና ፣ ወረቱ ፣ እስኪ ያልፍ ፣ ድረስ ፣ እንደሆነ ፣ ንገሪው ። ሰላምና ፣ ጸጥታም ፣ ንሺ ው ፤ ቢቆጣሽና ፣ ቢያስፈራራሽም ፣ ፍንክች ፣ አትበይ ። አን ድ ፣ ቅንጣት ፣ ተስፋ ፣ እስካለ ፣ ድረስ ፣ ተስፋ ፣ አትቁረጪ ። ሌላ ፣ መንገድ ፣ ጨርሶ ፣ ከታጣ ፣ ግን ፣ ... »

እዚህ ፣ ላይ ፣ ዱብሮቭስኪይ ፣ ፊቱን ፣ በእጆቹ ፣ ሸፈ ነ ፤ ትንፋሹም ፣ አጠረው ፤ ማሻም ፣ አለቀሰች ።

« አዎይ ፣ ክፉው ፣ ዕድሌ! አዎይ ፣ ክፉው ፣ ዕድሌ! » አለ ፣ በመረረ ፣ ቃል ። « ላንቺ ፣ ሕይወቴን ፣ ብሰዋ ፣ እፈ ቅድ ፣ ነበር ። አንቺን ፣ ከሩቅ ፣ ማየትና ፣ እጅሽን ፣ መንካ ት ፣ ወሰን ፣ የሌለው ፣ ደስታ ፣ ይሰጠኛል ። እነሆ ፣ አሁን ፣ ወደሚገነፍለው ፣ ልቤ ፣ አስጠግቼሽ ፤ « መልአክ ፣ ሆይ ፣ አ ብረን ፣ እንሙት! » የማለት ፣ ዕድል ፣ ሲገጥመኝ ፣ እኔ ፣ ምስኪ ኑ ፣ ይህን ፣ ጸጋ ፣ እምቢ ፣ ብዬ ፣ መመለስና ፣ በተቻለኝ ፣ አቅ ሜ ፣ ሁሉ ፣ መከላከል ፣ ግድ ፣ ይሆንብኛል ። ለማይገባኝና ፣ ላገ ኘሁት ፣ ታላቅ ፣ ዋጋ ፣ እጫማሽ ፣ ላይ ፣ ወድቄ ፣ ሰማያትን ፣ ለማ መስገን ፣ አልደፍርም ። አንቺን ፣ ... ልጠላው ፣ ይገባል ። ነገር ፣ ግን ፣ ካሁን ፣ ወዲያ ፣ በልቤ ፣ የጥላቻ ፣ ስሜት ፣ የለም ። »

ቀጭን ፣ ወገቧን ፣ በእጁ ፣ ይዞ ፣ በቀስታ ፣ ወደልቡ ፣ አ ስጠጋት ። እሷም ፣ በሙሉ ፣ እምነት ፣ እራሷን ፣ በወጣቱ ፣ ወ ንበዴ ፣ ትከሻ ፣ ላይ ፣ ጣል ፣ አደረገች ። ሁለቱም ፣ ዝም ፣ አሉ ።

ጊዜው ፣ በረረ ።

« መሄድ ፣ አለብኝ ፣ » አለች ፣ ማሻ ፣ በመጨረሻ ።

ዱብሮቭስኪይ ፣ ከእንቅልፉ ፣ የነቃ ፣ መሰለ ። እጅዋን ፣

አንስቶ ፡ እጣቷ ፡ ላይ ፡ ቀለበት ፡ ሰካላትና ፡ እንዲህ ፡ አላት ፤

« እርዳታዬን ፡ ለማግኘት ፡ የፈለግሽ ፡ እንደሆን ፡ ይህንን ፡ ቀለበት ፡ ወስደሽ ፡ እዋርካው ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ ጣይው ። እኔ ፡ የማደርገውን ፡ አውቃለሁ ። »

ዱብሮቭስኪይ ፡ እጅዋን ፡ ሳማትና ፡ በዛፎቹ ፡ ውስጥ ፡ አሳብሮ ፡ ሄደ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፯ ።

ልዑል ፡ ቬሬይስኪይ ፡ ልጂቱን ፡ ማግባት ፡ እንደፈለገ ፡ የጐረቤቱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አወቀ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ መልዕክት ፡ ይደርሰው ፡ ጀመር ። የሠርጉም ፡ ድግስ ፡ ዝግጅቱ ፡ ተጀመረ ። ማሻ ፡ ግን ፡ ቁርጠኛውን ፡ ቃል ፡ ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ አስተላለፈችው ። ለሽማግሌው ፡ እጮኛዋ ፡ የምታሳየው ፡ ስሜትም ፡ ቀዝቃዛና ፡ የተሸፈነ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ልዑሉ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ አልሰጋበትም ፡ ነበር ። እሱ ፡ የፈለገው ፡ ፍቅር ፡ አልነበረም ። በቃል ፡ ባትናገርም፡ ዝም ፡ ብላ ፡ መስማማቷ ፡ ለሱ ፡ በቂው ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ በረረ ። ማሻም ፡ በመጨረሻ ፡ ቁርጥ ፡ እርምጃ ፡ ለመውሰድና ፡ ለልዑሉ ፡ ደብዳቤ ፡ ለመጻፍ ፡ ወሰነች ። በደብዳቤዋም ፡ ላይ ፡ ለርሱ ፡ አንድ ፡ ቅንጣት ፡ ፍቅር ፡ እንደሌላት ፡ እውነቱን ፡ በመግለጽ ፡ ልቡ ፡ እንዲራራላትና ፡ ከአባቷም ፡ ጭካኔና ፡ ጭቆና ፡ እንዲያድናት ፡ ለመነችው ። ደብዳቤውንም ፡ በምስጢር ፡ ሰጠችው ። እሱም ፡ ደብዳቤውን ፡ ብቻውን ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ አነበበው ። ነገር ፡ ግን ፡ እጮኛው ፡ በጻፈችው ፡ ዕውነተኛ ፡ ቃል ፡ ልቡ ፡

ፈጽሞ ፡ አልተነካም ፡ ነበር ። እንዲያውም ፡ የሠርጉ ፡ ጊዜ ፡ እንዲፋጠን ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ደብዳቤው ን ፡ ለወደፊት ፡ አማቹ ፡ አሳየው ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ በቁጣ ፡ ገነፈለ ። ልዑሉም ፡ ደ ብዳቤውን ፡ ማሳየቱን ፡ ማሻ ፡ እንዳታውቅበት ፡ ለማድረ ግ ፡ በብዙ ፡ ለመነው ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ የማይነግራ ት ፡ ለመሆኑ ፡ ተስማማ ። ነገር ፡ ግን ፡ ካሁን ፡ ወዲያ ፡ ጊዜ ፡ አላባክንም ፡ ብሎ ፡ በመቁረጥ ፡ ጋብቻው ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ እንዲሆን ፡ ወሰነ ። ልዑሉም ፡ በዚህ ፡ ሐሳብ ፡ እጅግ ፡ በመደሰት ፡ ወደእጮኛው ፡ ጋ ፡ ሄደ ። ደብዳቤዋ ፡ እንዳሳ ዘነውና ፡ በጊዜ ፡ ብዛትም ፡ ስሜቷን ፡ ለመማረክ ፡ ተስፋ ፡ እንዳለው ፤ እሷን ፡ የማግባትንም ፡ ሐሳብ ፡ ችሎ ፡ የማይቀበ ል ፡ መሆኑንና ፡ በራሱ ፡ ላይም ፡ የሞት ፡ ፍርድን ፡ ለመፍ ረድ ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ገለጸላት ። ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግ ሮም ፡ እጅዋን ፡ በትህትና ፡ ሳመና ፡ ወጥቶ ፡ ሄደ ። ስላባቷ ፡ ውሳኔ ፡ ግን ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ አልነገራትም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ልዑሉ ፡ ገና ፡ ካጥር ፡ ግቢው ፡ እንደወጣ ፡ አባቷ ፡ ወደክፍሏ ፡ ሄደና ፡ በሚቀጥለው ፡ ቀን ፡ ለጋብቻ ፡ እን ድትዘጋጅ ፡ በቀጥታ ፡ ነገራት ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ልዑሉ ፡ በተናገራት ፡ ቃል ፡ ተበሳጭታ ፡ ስለነበር ፡ ይህንን ፡ ስትሰ ማ ፡ ደግሞ ፡ እንባዋ ፡ ፈሰሰ ፤ አባቷ ፡ ጫማ ፡ ላይ ፡ ወድቃም ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ጮኸች ፤

« አባቴ ፡ ሆይ ፤ ውድ ፡ አባቴ ፡ ሆይ! አትግደለኝ ። ልዑ ሉን ፡ አልወደውም ፤ ሚስቱም ፡ አልሆንም ። »

« ምን ፡ ማለትሽ ፡ ነው? » አለና ፡ ጮኸባት ። « እስካ ሁን ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ በማለት ፡ መስማማትሽን ፡ አረጋግጠ ሽ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሐሳብሽን ፡ በመለወጥ ፡ እንደገና ፡ ቃ ልሽን ፡ ለማጠፍ ፡ ትፈልጊያለሽ! አትቀልጂ ፡ እባክሽ! እኔ ፡ እንደሆንኩ ፡ በዚህ ፡ አልታለልም! »

« አትግደለኝ! » አለች ፡ ደግማ ፡ ምስኪኗ ፡ ማሻ ። « ካንተ ፡ ነጥለህ ፡ ለማልወደው ፡ ሰው ፡ ለምን ፡ ትሰጠኛለህ? ስለቸሁህን? እንደዱሮው ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡ ለመቀመጥ ፡ እፈልጋለሁ ። እኔን ፡ ስታጣ ፡ ታዝናለህ ፡ አባቴ ፡ ሆይ! ይልቁንም ፡ እንደበደልሽኝ ፡ ስታውቅ ፡ ይበልጥ ፡ ይከፋሃል ። ለማግባት ፡ አልፈልግም ፤ አታስገድደኝ ። »

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ልቡ ፡ ተነካ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስሜቱን ፡ በመደበቅ ፡ ገፋትና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በጭካኔ ፡ ቃል ፡ ተናገራት ፤

« የተናገርሽው ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ። ትሰሚኛለሽ? አንቺን ፡ የሚያስደስትሽን ፡ እኔ ፡ ካንቺ ፡ ይበልጥ ፡ አውቀዋለሁ ። ያፈሰስሽው ፡ እንባ ፡ ለምንም ፡ አይረዳሽ ። ሰርግሽ ፡ ከነገወዲያ ፡ ይሆናል ። »

« ከነገወዲያ! » ብላ ፡ ጮኸች ፡ ማሻ ። « በእግዚአብሔር! የለም! የለም! አይሆንም ፤ አይቻልም! ስማኝ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፤ እኔን ፡ ለማጥፋት ፡ ቆርጠህ ፡ ከተነሳህ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ አንተ ፡ ያላሰብከው ፡ ሊያድነኝ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ አገኛለሁ ። የቱን ፡ ያህል ፡ እጭንቅና ፡ እመከራ ፡ ውስጥ ፡ እንደጣልከኝ ፡ ኋላ ፡ ትገነዘበውና ፡ ይጸጽትሃል ። »

« ምን? ምን? » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « ማስፈራራትሽ ፡ ነው! እኔን ፡ ደፍረሽ ፡ ማስፈራራትሽ ፡ ነው ፤ አንች ፡ ባለጌ! ከዚህ ፡ የባሰ ፡ ነገር ፡ ላደርግብሽ ፡ እንደምችል ፡ አታውቂም! ሌላ ፡ ሰው ፡ ያድነኛል ፡ ብለሽ ፡ የምታስፈራሪው ፡ እኔን ፡ ነው! እረ ፡ ለነገሩ ፡ የሚያድንሽ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው! »

« ቭላዲሚር ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ነው ፡ » ብላ ፡ ማሻ ፡ በመጨነቅ ፡ ተናገረች ።

ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ልጁ ፡ ያበደች ፡ መሰለው ።

« ማስፈያ ፡ ነዋ ፡ » አለ ፡ ቆይቶ ። « የሚያድንሽ ፡ ሰው ፡ ማንም ፡ ይሁን ፡ ጠብቂ ። ለጊዜው ፡ ግን ፡ እስተጋብቻሽ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከዚህ ፡ ክፍል ፡ አትወጭም ። » ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ ወጣ ፤ በሩንም ፡ ከውጭ ፡ ቆለፈው ።

ምስኪኗ ፡ ልጃገረድ ፡ ወደፊት ፡ የሚጠብቃትን ፡ በማሰብ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ አለቀሰች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የደረሰባት ፡ የጭንቅ ፡ ማዕበል ፡ ልቧን ፡ አጽናናው ፤ ስለወደፊት ፡ ዕድሏም ፡ በርጋታ ፡ እንድታስብና ፡ የምታመልጥበትንም ፡ መንገድ ፡ እንድታመዛዝን ፡ አደረጋት ። ዋናው ፡ ዓላማዋ ፡ ከአሰቃቂው ፡ ጋብቻ ፡ ለመዳን ፡ ነበር ። ወደፊት ፡ ከሚጠብቃት ፡ ዕድል ፡ ይልቅ ፡ የወንበዴ ፡ ሚስት ፡ ሆኖ ፡ መኖርን ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ኑሮ ፡ ቆጠረችው ። ዱብሮቭስኪይ ፡ የሰጣትን ፡ ቀለበት ፡ ተመለከተች ። የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ እሱን ፡ ለማየትና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ለመመካከርም ፡ አጥብቃ ፡ ፈለገች ። ያንኑ ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ በአትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ የወይን ፡ ሐረግ ፡ አጠገብ ፡ እንደምታገኘው ፡ ስሜቷ ፡ ነገራት ። ሲመሽ ፡ እዚያው ፡ ቦታ ፡ ሄዳ ፡ እሱን ፡ ለመጠበቅ ፡ ቆረጠች ። ጊዜው ፡ መሸ ፤ ማሻም ፡ ለመሄድ ፡ ተዘጋጀች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በሩ ፡ ተቆልፎ ፡ ነበር ። ገረዲም ፡ ከበሩ ፡ በስተጀርባ ፡ ሆና ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እንዳትወጣ ፡ ማዘዙን ፡ ነገረቻት ። ምስኪኗ ፡ ልጃገረድ ፡ በእስር ፡ ላይ ፡ ነበረች ፡ ማለት ፡ ነው ። ልቧ ፡ ክፉኛ ፡ በሐዘን ፡ ስለተሰበረ ፡ ልብሷን ፡ ሳታወልቅ ፡ በመስኮቱ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጣ ፡ ጥቁሩን ፡ ሰማይ ፡ ስትመለከት ፡ ሊነጋጋ ፡ ተቃረበ ። ሲነጋጋም ፡ እንቅልፍ ፡ ሸልብ ፡ አደረጋት ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህንኑ ፡ ትንሽ ፡ እንቅልፏን ፡ አሳዛኝ ፡ ሕልም ፡ በጠበጠው ። ወዲያውም ፡ የጸሐይዋ ፡ ጨረር ፡ አነቃት ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

እንደነቃችም ፡ ያለችበት ፡ አሰቃቂ ፡ ሁናቴ ፡ አዕምሮ ዋ ፡ ላይ ፡ ሠፈረ ። ደወል ፡ ደወለች ፤ ገረዲም ፡ መጣች ። ማ ሻ ፡ ላቀረበችላት ፡ ጥያቄ ፡ ስትመልስም ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ያን ፡ ዕለት ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ አርባቶቮ ፡ ሄዶ ፡ በጣም ፡ አምሽቶ ፡ እንደተመለሰና ፡ እሷ ፡ ከክፍሏ ፡ እንዳትወጣና ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እንዳያነጋግራትም ፡ ትዕዛዝ ፡ እንደሰጠ ፡ ነገረቻት ። ከዚህ ፡ በተረፈም ፡ ቄሱ ፡ ከመንደር ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይወጣ ፡ ከመታዘዙ ፡ በቀር ፡ ልዩ ፡ የሠርግ ፡ ድግሥ ፡ በመዘጋጀት ፡ ላይ ፡ አለመሆኑን ፡ ገለጸችላት ። ይህን ፡ ወሬ ፡ ካሰማቻት ፡ በኋላ ፡ ገረዲ ፡ ወጥታ ፡ ሄደች ፤ በሩንም ፡ ከውጭ ፡ በኩል ፡ ቆለፈችው ።

የሰማችው ፡ ነገር ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናን ፡ አበሳጫት ። ናላዋ ፡ ተበጠበጠ ፤ ደሟም ፡ ፈላ ። ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ለዱብ ሮቭስኪይ ፡ ለማስታወቅ ፡ ስለፈለገች ፡ ቀለበቱን ፡ ወደዋርካ ው ፡ ቀዳዳ ፡ ወስዳ ፡ የምትጥልበትን ፡ መንገድ ፡ ማሰብ ፡ ጀመረች ። በዚሁ ፡ ሰዓት ፡ መስኮትዋን ፡ ድንጋይ ፡ ሲመታ ው ፡ ሰማች ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ብቅ ፡ ባለች ፡ ጊዜም ፡ ት ንሹ ፡ ሳሻ ፡ እጇን ፡ በምሥጢር ፡ ሲያወዛውዝላት ፡ አየች ። እንደሚወዳት ፡ ስለምታውቅም ፡ ባየችው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አ ላት ። መስኮቱንም ፡ ወለል ፡ አድርጋ ፡ ከፈተችው ።

« እንዴት ፡ አደርክ ፡ ሳሻ ። ልታነጋግረኝ ፡ ትፈልጋለ ህ ፡ እንዴ? »

« እትዬ ፤ የምትፈልጊው ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ልጠይቅ ሽ ፡ ነው ፡ የመጣሁት ። አባባ ፡ በጣም ፡ ስለተቆጣ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ላንቺ ፡ እንዳይታዘዝ ፡ ብሏል ። እኔ ፡ ግን ፡ የፈለግ ሽውን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ። »

« እግዚአብሔር ፡ ይስጥልኝ ፡ ውድ ፡ ሳሻ ። ስማኝ ፤ በወ

ይን ፡ ሐረጉ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ያረጀና ፡ ቀዳዳ ፡ ያለው ፡ የዋርካ ፡ ዛፍ ፡ ታውቅ ፡ የለም? »

« አዎን ፡ አውቀዋለሁ ፡ እትዬ ። »

« እንግዲያውስ ፡ ትወደኝ ፡ እንደሆን ፡ በፍጥነት ፡ እ ሩጥና ፡ ይህችን ፡ ቀለበት ፡ እቀዳዳው ፡ ውስጥ ፡ ጣላት ። ማ ንም ፡ ሰው ፡ እንዳያይህም ፡ ተጠንቀቅ ። »

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግራ ፡ ቀለበቱን ፡ ጣለችለትና ፡ መስ ኮቱን ፡ ዘጋች ።

ልጁ ፡ ቀለበቷን ፡ ያዘና ፡ ሲሮጥ ፡ ሄደ ። ከሦስት ፡ ደ ቂቃ ፡ በኋላም ፡ እተባለው ፡ ዛፍ ፡ አጠገብ ፡ ደረሰ ። ትንፋ ሽ ፡ ስላጠረው ፡ ቆም ፡ አለና ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ተመልክቶ ፡ ቀለ በቷን ፡ እቀዳዳው ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠ ። መልዕክቱን ፡ መ ፈጸሙን ፡ ለማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ ለመንገር ፡ ተመልሶ ፡ ሊ ሮጥ ፡ ሲል ፡ አንድ ፡ ቡትቶ ፡ የለበሰና ፡ ጸጉረ ፡ ቀይ ፤ ዓይነ ፡ ጠንጋራ ፡ ልጅ ፡ ከወይኑ ፡ ሐረግ ፡ ሥር ፡ ድንገት ፡ ብቅ ፡ ብ ሎ ፡ ወደ ፡ ዋርካው ፡ ጋ ፡ ሮጠና ፡ እጁን ፡ ወደቀዳዳው ፡ አ ስገባ ። ሳሻም ፡ እንደነብር ፡ እመር ፡ ብሎ ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ያዘው ።

« ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ እዚህ ፡ » አለና ፡ በቁጣ ፡ ጠየቀው ።

« ምን ፡ አገባህ ፡ አንተን ፡ » ሲል ፡ ልጁ ፡ ለማምለጥ ፡ እየ ታገለ ፡ መለሰ ።

« ቀለበቱን ፡ አምጣ ፤ አንት ፡ ጠንጋራ ፡ ቀይ ፡ እራስ ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡ አሳይሃለሁ ። »

ለዚህ ፡ መልስ ፡ ልጁ ፡ ሳሻን ፡ እፊቱ ፡ ላይ ፡ በቡጢ ፡ መታው ፡ ሳሻ ፡ ግን ፡ ጥብቅ ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፤

« ኡኡ! ሌባ! ሌባ! » ብሎ ፡ በኃይል ፡ ጮኸ ።

ልጁ ፡ ለማምለጥ ፡ በተቻለው ፡ ሞከረ ። ዕድሜው ፡ ከ ሳሻ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ የሚበልጥና ፡ በጉልበትም ፡ ይበልጥ ፡ የሚጠነክር ፡ ይመስላል ፤ ሳሻ ፡ ግን ፡ ጠፍር ፡ ነበር ። ለጥቂ

ት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ከታገሉ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ባለቀይ ፡ ጸጉሩ ፡ ልጅ ፡ ስላየለ ፡ ሳሻን ፡ ገልብጦ ፡ እመሬት ፡ ላይ ፡ ጣለና ፡ ጉሮሮውን ፡ አንቆ ፡ ያዘው ። ያነየውኑ ፡ ግን ፡ አትክልተኛው ፡ ስቴፓን ፡ በጠንካራ ፡ እጁ ፡ የልጁን ፡ ቀይ ፡ ጸጉር ፡ ይዞ ፡ ከመሬት ፡ አንድ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አነሳው ።

« አንት ፡ ቀይ ፡ ራስ ፡ አውሬ ፡ » አለ ፡ አትክልተኛው ።
« እንዴት ፡ ብትደፍር ፡ ነው ፡ ታናሹን ፡ ጌታ ፡ የመታኸው? »

ሳሻ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ተነስቶ ፡ ቆመና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

« ያለደንቡ ፡ ታግለኸኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አትጥለኝም ፡ ነበር ። ቶሎ ፡ ቀለበቱን ፡ ስጠኝና ፡ ከዚህ ፡ ጥፋ ። »

« የለም ፡ » አለ ፡ ልጁ ። ድንገት ፡ ጠምዘዝ ፡ ብሎም ፡ ያጐፈረ ፡ ጸጉሩን ፡ ከስቴፓን ፡ እጅ ፡ አስለቀቀ ።

እሩጫም ፡ ጀመረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ሳሻ ፡ ደረሰበትና ፡ ጀርባውን ፡ ቢመታው ፡ በግንባሩ ፡ ተደፋ ። አትክልተኛው ፡ እንደገና ፡ ያዘውና ፡ በቀበቶው ፡ አሰረው ።

« ቀለበቱን ፡ ስጠኝ ፡ » ሲል ፡ ሳሻ ፡ ጮኸ ።

« ቆይ ፡ ጌታዬ ፡ » አለ ፡ ስቴፓን ። « ለጥያቄ ፡ ወደም ስለኔው ፡ ጋ ፡ እንወስደዋለን ። »

አትክልተኛው ፡ እስረኛውን ፡ ይዞ ፡ ከሳሻ ፡ ጋር ፡ አንድነት ፡ ወደቤት ፡ አመሩ ። ሳሻ ፡ የተቀደደና ፡ ሳር ፡ ያበላሸውን ፡ ሱሪውን ፡ በፍርሃት ፡ ተመለከተ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ የፈረስ ፡ ጋጣውን ፡ ለመመልከት ፡ ሲመጣ ፡ ሶስቱንም ፡ አገኛቸው ።

« ምንድነው ፡ ነገሩ? » ሲል ፡ ስቴፓንን ፡ ጠየቀው ።

ስቴፓንም ፡ ሁናቴውን ፡ ባጭሩ ፡ ገለጸ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ታሪኩን ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ ሰማ ።

« አንት ፡ መጋጣ ፤ እዚህ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ስትል ፡ ገባ
ህ ፡ ደግሞ? » ሲል ፡ ሳሻን ፡ ጠየቀው ።

« አባባ ፤ ቀለበቱን ፡ ከዛፉ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ ሰርቆ ፡ ወ
ስዱ.ልና ፡ እንዲመልስ ፡ አድርገው ። »

« የምን ፡ ቀለበት ፡ ነው? የምንስ ፡ ቀዳዳ ፡ ዛፍ ፡
ነው? »

« ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ የሰጠችን ፡ ቀለበት ፡ ... እ ... ፡ ቀ
ለበቱ ፡ ... »

ሳሻ ፡ የሚናገረው ፡ ጠፋው ። አንደበቱ ፡ ታሠረ ። ኪ
ሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ፊቱን ፡ ኰስትሮና ፡ እራሱን ፡ እየነቀነ
ቀ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

« ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ እዚህ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ አለ
ችበት? እንግዲያውስ ፡ ዕውነቱን ፡ አውጣ ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡
መልክህ ፡ ለገዛ ፡ እናትህ ፡ እስቲጠፋት ፡ ድረስ ፡ እገርፍሃ
ለሁ ። »

« አባባ ፡ ዕውነት ፡ እልሃለሁ ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ አ
ንድም ፡ ነገር ፡ እንዳደርግ ፡ አልጠየቀችም ። »

« ስቴፓን ፡ ሂድና ፡ ደህና ፡ ልምጭ ፡ ቀጥፈህ ፡ አምጣ
ልኝ ። »

« አባባ ፡ ቆይ! ሁሉንም ፡ እነግርሃለሁ ። ዛሬ ፡ በጓሮ ፡
በኩል ፡ ስሮጥ ፡ እትዬ ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ መስኰቷን ፡
ከፈተች ። እኔም ፡ ወደርሷ ፡ ጋ ፡ ስሄድ ፡ ቀለበቷን ፡ ጣለ
ችው ። አንስቼ ፡ ወደዛፉ ፡ ቀዳዳ ፡ ልሸሽገው ፡ ስል ፡ ... ይሄ ፡
ባለቀይ ፡ ጸጉር ፡ ልጅ ፡ ሊሰርቀው ፡ ሞከረ ። »

« እሷ ፡ ቀለበቷን ፡ ጣለች ፤ አንተም ፡ ልትሸሽግ ፡ ወ
ሰድከው ፤ ልምጩን ፡ አምጣልኝ ፡ ስቴፓን ። »

« ቆይ ፡ አባባ ፡ ሁሉንም ፡ ልንገርህ ። እትዬ ፡ ማሪያ ፡
ኪሪሎቭና ፡ ቀለበቱን ፡ ወስጄ ፡ እዛፉ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ እን

ዳስቀምጠው ፡ ጠየቀችኝ ። እኔም ፡ ወስጄ ፡ ሳስቀምጠው ፡ ይሄ ፡ መጥፎ ፡ ልጅ ፡ መጣና ፡ ... »

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ወደ ፡ መጥፎው ፡ ልጅ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ ጠየቀው ፤

« የማነህ ፡ ልጅ? »

« ከዱብሮቭስኪይ ፡ የቤት ፡ አሽከሮች ፡ አንዱ ፡ ነኝ ፡ » ሲል ፡ ጸጉረ ፡ ቀዩ ፡ ልጅ ፡ መለሰ ።

የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ፊት ፡ ጠቆረ ።

« ለካ ፡ እኔን ፡ እንደጌታህ ፡ አትቆጥረኝም ። ደግ ፡ ነዋ ። ባትክልቴ ፡ ውስጥስ ፡ ምን ፡ ታደርግ ፡ ኖርዋል? »

« ኰሽም ፡ ስለቅም ፡ ነበር ፡ » ሲል ፡ በግዴለሽነት ፡ መለሰ ።

« እህ! አሽከርም ፡ እንደጌታው ። ቄስ ፡ በተከታዮቹ ፡ ይታወቃል ፡ ይባላል ። ኰሽም ፡ በኔ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ በዋርካ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የሚበቅለው? »

ልጁ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ አልሰጠም ።

« ቀለበቱን ፡ እንዲመልስ ፡ ጠይቀው ፡ አባባ ፡ » አለ ፡ ሳሻ ።

« ዝም ፡ በል ፡ አሌክሳንደር! » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « ገና ፡ አንተንም ፡ አሳይሃለሁ ። ሂድ ፡ ወደክፍልህ ። አንተ ፡ ጠንጋራ ፤ ጮሌ ፡ ቢጤ ፡ ትመስላለህ ። ቀለበቱን ፡ ስጠኝና ፡ ሂድ ። »

ልጁ ፡ መዳፉን ፡ በመዘርጋት ፡ በእጁ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ አሳየ ።

« ዕውነቱን ፡ ብትናገር ፡ አልገርፍህም ፤ እንዲያውም ፡ ኖቾሊኒ ፡ የምትገዛበት ፡ አምስት ፡ ሳንቲም ፡ እሰጥሃለሁ ። አለበለዚያ ፡ ግን ፡ በሕይወትህ ፡ አይተኸው ፡ የማታውቀው ፡ ጉድ ፡ ይፈላብሃል ፤ ታዲያስ? »

ልጁ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ሳይመልስ ፡ እንደመንደር ፡ ቂል ፡ አንገቱን ፡ አቀርቅሮ ፡ ዝም ፡ አለ ።

« መልካም ፡ ነው ፡ » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ። « እን ዳያመልጥ ፡ ቆልፍበት ። ያመለጠ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ ነፍሳ ችሁ ፡ እንዳለ ፡ ቆዳችሁን ፡ አስገፍፈዋለሁ ። »

ስቴፓን ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ ርግቦች ፡ ቤት ፡ ወስዶ ፡ ቆ ለፈበትና ፡ ዶሮ ፡ አርቢዋን ፡ አሮጊት ፡ አጋፊያን ፡ እንድ ትጠብቀው ፡ ነገራት ።

« በተቻለ ፡ ፍጥነት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሄደህ ፡ ምስለኔውን ፡ ጥራ ፡ » ሲል ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ አንዱን ፡ አሽከሩን ፡ አዘዘ ።

በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተንጐራደደና ፡ « የድል ፡ ነጐድጓድ ፡ ይሰማ ፡ » የሚለውን ፡ ዜማ ፡ እያፏጨ ፡ « ካሁን ፡ ወዲያ ፡ ነገሩ ፡ አያጠራጥርም ፡ » ሲል ፡ አሰበ ። « ከዚያ ፡ ከተረገመ ፡ ከዱብሮቭስኪይ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ነ በራት ፡ ማለት ፡ ነው ። ዕውነት ፡ እንዲረዳት ፡ ጠርታው ፡ ይ ሆን? ምናልባት ፡ እኔ ፡ ፋናውን ፡ ተከትዬ ፡ እይዘው ፡ ይሆና ል ፤ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ሊያመልጥ ፡ አይችልም ። ይህን ፡ መል ካም ፡ አጋጣሚ ፡ እንሰራበታለን ። እሰይ! የልጓም ፡ ቃጭል ፡ ነው ፡ የምሰማው! ተመስገን ፡ አምላኬ ፡ ምስለኔው ፡ መጣ ። ያን ፡ የያዝነውን ፡ ልጅ ፡ አምጡት! »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ ወደ ፡ አጥር ፡ ግቢው ፡ ው ስጥ ፡ አመራ ። ምስለኔው ፡ አቧራ ፡ ለብሶ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ገባ ።

« የማሰማህ ፡ ቸር ፡ ወሬ ፡ አለኝ! » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮ ቪች ። « ዱብሮቭስኪይን ፡ ያዝኩት ። »

« ክቡር ፡ ሆይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ፡ » አለ ፡ በፍስሐ ፡ ስሜት ። « የት ፡ ነው ፡ ያለው? »

« ዱብሮቭስኪይ ፡ እንኳ ፡ አይደለም ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጭፍሮች ፡ አንደኛው ፡ ነው ። አሁን ፡ ይመጣል ። ዋናውን ፡ ቀንደኛ ፡ ለመያዝም ፡ ይረዳናል ። ይሂውልህ! »

ምስለኔው ፡ ያሰበው ፡ ግድንግድ ፡ ሽፍታ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ስለነበር ፡ አንድ ፡ ኰሳሳ ፡ ያስራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሲያይ ፡ ገረመው ። ወደኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ዞወር ፡ ብሎም ፡ በመደነቅ ፡ እየተመለከተ ፡ ታሪኩን ፡ ለመስማት ፡ ጠበቀ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪችም ፡ ጧት ፡ የሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዘርዝሮ ፡ ነገረው ። ሆኖም ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለችበት ፡ አላነሳም ፡ ነበር ።

ምስለኔውም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ትንሹን ፡ ወሮበላ ፡ እየተመለከተ ፡ ልብ ፡ ብሎ ፡ አዳመጠው ። ልጁ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ነገሩን ፡ ያልሰማ ፡ መስሎ ፡ እንደ ፡ ቂል ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

« ክቡር ፡ ሆይ ፡ ብቻዎን ፡ ላነጋግርዎት ፡ ይፈቀድልኛል? » ሲል ፡ ምስለኔው ፡ ጠየቀ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ወደሌላ ፡ ክፍል ፡ ወሰደውና ፡ በሩን ፡ ቆለፈ ።

ከግማሽ ፡ ሰዓት ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ፍርዱን ፡ ወደሚጠብቅበት ፡ ክፍል ፡ ተመልሰው ፡ መጡ ። ምስለኔውም ፡ ልጁን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፤

« ክቡርነታቸው ፡ ወደከተማ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ልከው ፡ በብረት ፡ አለንጋ ፡ ሊያስገርፉህና ፡ ከቤትህም ፡ ሊያባርሩህ ፡ አስበው ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በኔ ፡ አማላጅነት ፡ ምህረት ፡ ላስደርግልህ ፡ ቻልኩ ። ፍቱት ። »

ልጁ ፡ ተፈታ ።

« ክቡርነታቸውን ፡ አመስግን ፡ » አለው ፡ ምስለኔው ።

ልጁ ፡ ወደኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ሄደና ፡ እጁን ፡ ሳመ ።

« ወደቤትህ ፡ መሄድ ፡ ትችላለህ ፡ » አለው ፡ ኪሪላ ፡ ፔት ሮቪች ። « ዳግመኛ ፡ ግን ፡ ከዋርካው ፡ ዛፍ ፡ ቀዳዳ ፡ ውስጥ ፡ ኰሽም ፡ ስትሰርቅ ፡ እንዳላገኝህ ። »

ልጁ ፡ ከበረንዳው ፡ ላይ ፡ እየፈነጠዘ ፡ ወረደና ፡ ተገላ ምጦ ፡ ሳያይ ፡ በኪስቴኞቭካ ፡ ሜዳ ፡ እየሮጠ ፡ ሄደ ። ወደ ፡ መንደር ፡ ሲደርስም ፡ ከመንገድ ፡ ዳር ፡ ባለች ፡ የፈረሰች ፡ ጐጆ ፡ አጠገብ ፡ ቆመና ፡ መስኰቱን ፡ አንኳኳ ። መስኰቱም ፡ ተከፈተና ፡ አንድ ፡ አሮጊት ፡ ሴት ፡ ብቅ ፡ አለች ።

« አያቴ ፡ ዳቦ ፡ ስጭኝ ። ከጧት ፡ አንስቶ ፡ እህል ፡ አ ልቀመስኩም ፤ እርቦኛል ፡ » አለ ፡ ልጁ ።

« ሚትያ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንዴ! እስካሁን ፡ የት ፡ ጠፍተ ህ ፡ ዋልህ ፡ አንት ፡ ዘዋሪ ፡ » አሉ ፡ አሮጊቷ ።

« በኋላ ፡ እነግርሻለሁ ፡ አያቴ ። ስለእግዚአብሔር ፡ ብለሽ ፡ ዳቦ ፡ ስጭኝ ። »

« ግባ ፡ ወደ ፡ ቤት ። »

« ጊዜ ፡ የለኝም ፡ አያቴ ። ገና ፡ የምሄድበት ፡ ቦታ ፡ አ ለ ። ስለክርስቶስ ፡ ብለሽ ፡ ዳቦ ፡ ስጭኝ ። »

« ምን ፡ ያለ ፡ ቀዠቃዣ ፡ ነው ፡ » ብለው ፡ አሮጊቷ ፡ አጉ ረመረሙና ፡ « ያውልህ ፡ ውሰድ ፡ » ብለው ፡ በመስኰቱ ፡ ቁ ራሽ ፡ ጥቁር ፡ ዳቦ ፡ ጣሉለት ።

ልጁም ፡ በተራበ ፡ ሆዱ ፡ ዳቦውን ፡ እየገመጠና ፡ እያ ላመጠ ፡ መንገዱን ፡ ቀጠለ ።

መምሸት ፡ ጀመረ ። ልጁ ፡ በእህል ፡ ጐተራና ፡ በአትክ ልት ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ አልፎ ፡ ወደኪስቴኞቭካ ፡ ጫካ ፡ ገባ ። እንደዘበኛ ፡ ቆመው ፡ ጫካውን ፡ ከሚጠብቁት ፡ ሁለት ፡ የጥ ድ ፡ ዛፎች ፡ ጋ ፡ ሲደርስ ፡ ቆም ፡ አለና ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አካ ባቢውን ፡ ተመልክቶ ፡ አጭር ፡ ፉጨት ፡ አሰማ ፤ መልሱ ንም ፡ ይጠብቅ ፡ ጀመር ። ለመልስ ፡ ያህልም ፡ ለስለስ ፡ ያለ ፡

ረጅም ፡ ፉጨት ፡ ሰማ ። ወዲያውም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከጫካ ው ፡ ውስጥ ፡ ወጥቶ ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፰ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ያንኑ ፡ ዜማውን ፡ ከተለመደው ፡ በላይ ፡ በኃይል ፡ እያፏጨ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይንጐራደዳል ። የቤቱም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይተራመሳል ። አሽከሮቹ ፡ ይሯሯጣሉ ፤ ገረዶቹም ፡ ይጣደፋሉ ። ፈረስ ፡ ጫኝዎቹም ፡ የሠረገላ ፡ ፈረሶችን ፡ በጥላ ፡ ሥር ፡ ይጭናሉ ። አጥር ፡ ግቢውን ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ መልተውታል ። በሴት ፡ መልበሻ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ የከበቧት ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ በመስታዋቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ቆማ ፡ የጠወለገችውንና ፡ የማትላወሰውን ፡ ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናን ፡ ታለብሳለች ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭናም ፡ ያደረገችው ፡ አልማዝ ፡ ስለከበዳት ፡ ራሷን ፡ ደፍታ ፡ ፍዝዝ ፡ ብላለች ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አልባሺ ፡ ተሳስታ ፡ በመርፌ ፡ ስትወጋት ፡ ብቻ ፡ ትንሽ ፡ የመንቀሳቀስ ፡ ስሜት ፡ ታሳያለች ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቃል ፡ ሳትናገር ፡ መስታዋቱን ፡ ብቻ ፡ ፈዛ ፡ ትመለከታለች ።

« ታዲያስ ፡ ቶሎ ፡ ተዘጋጅተሽ ፡ ትጨርሻለሽ ፡ ወይ? » ሲል ፡ የኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ድምጽ ፡ ከበሩ ፡ በስተውጭ ፡ በኩል ፡ ተሰማ ።

« አዎን ፡ በአንድ ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ » ስትል ፡ አልባሺዋ ፡ ሴት ፡ ወይዘሮ ፡ መለሰችና ፡ « ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ እንግዲህ ፡ ተነሽና ፡ እራስሽን ፡ ተመልከቺ ፤ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ተስማምቶሻል? » አለቻት ።

ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ሳትናገር ፡ ተነሳች ፤ በሩም ፡ ተከፈተ ።

« ሙሽራዋ ፡ ተዘጋጅታለች ፤ እሰረገላው ፡ ላይ ፡ ለመውጣትም ፡ እንችላለን ፡ » አለች ፡ አልባኗ ።

« የእግዜር ፡ ፈቃዱ ፡ ይሁን ፡ » አለ ፡ ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ አንድ ፡ የሰማዕት ፡ ሥዕል ፡ ከጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ እያነሳ ። ቀጥሎም ፡ ከልብ ፡ በመመሰጥ ፡ « ልጄ ፡ ማሻ ፡ ነይ ፡ ወዲህ ። ልመርቅሽ ፡ እፈልጋለሁ … » አለ ።

ምስኪኗ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እሜማው ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ እንባዋን ፡ ታፈስ ፡ ጀመር ።

« አባባ … አባባ … » እያለች ፡ ተንቀሳቀሰች ፤ ድምጿም ፡ ጭልጥ ፡ ብሎ ፡ ጠፋ ።

ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ ምርቃቱን ፡ ለመስጠት ፡ ተጣደፈ ። ከተደፋችበት ፡ አንስተውና ፡ ተሸክመው ፡ ወደ ፡ ሰረገላው ፡ ላይ ፡ አወጧት ። ባጠገቧም ፡ ሞግዚቷና ፡ ደንገጡሯ ፡ ተቀመጡ ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስትያንም ፡ አመሩ ። ሙሽራው ፡ እዚያ ፡ ቀድሞ ፡ ሂዶ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ነበር ። ሊቀበላቸው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ በሙሽራዋ ፡ ሁኔታና ፡ በፊቷ ፡ መለወጥ ፡ ደነገጠ ። አንድነት ፡ ሆነውም ፡ ጭር ፡ ወዳለውና ፡ ወደባዶው ፡ ቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ። ቄሱ ፡ ከቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ወጣና ፡ ስርዓቱ ፡ ጋብቻውን ፡ ወዲያው ፡ ጀመረ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ የሚታያትና ፡ የሚሰማት ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። እሷ ፡ የምታስበው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ዱብሮቭስኪይን ፡ ከጧት ፡ ጀምራ ፡ ትጠብቀው ፡ ነበር ። ተስፋ ፡ የመቁረጥ ፡ ሐሳብም ፡ በአዕምሮዋ ፡ አንድም ፡ ጊዜ ፡ ሽው ፡ አላለም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ቄሱ ፡ ወደርሷ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ የተለመደውን ፡ የጋብቻ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንድትሰጥ ፡ ሲጠይቃት ፤ ትንቀጠቀጠች ፤ ሰውነቷም ፡ ደረቀ ። ነገሩን ፡ ለማዘግየት ፡ ሞከረች ፤ ተስፋም ፡ አደረገች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቄሱ ፡ የእሷን ፡

መልስ ፡ ሳይጠብቅ ፡ የማይሻረውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አጸና ።

ስርዓተ ፡ ጋብቻው ፡ ተፈጸመ ። ማሪያ ፡ ኪሪሎቭና ፡ የማትወደው ፡ ባሏ ፡ ሲስማት ፡ ተሰማት ። ባካባቢዋ ፡ ያሉ ትም ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ ያለሽ ፡ እያሉ ፡ ደስታቸውን ፡ ሲገል ጹላት ፡ ሰማች ። ሆኖም ፡ ሕይወቷ ፡ በዚህ ፡ እንዳለቀና ፡ ዱብ ሮቭስኪይም ፡ በርሮ ፡ መጥቶ ፡ ሳያድናት ፡ እንደቀረ ፡ ለማመ ን ፡ አልቻለችም ። ልዑሉ ፡ በፍቅር ፡ ስሜት ፡ ያነጋግራት ፡ ነበር ፤ እሷ ፡ ግን ፡ ምን ፡ እንደሚላት ፡ አይገባትም ፡ ነበር ። ከቤተ ፡ ክርስትያኑ ፡ ወጡ ፤ የፖክሮቭስኮዬም ፡ ነዋሪዎች ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ። ባይኗ ፡ ሁሉንም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተመለከተቻቸውና ፡ እንደገና ፡ ፈዘዘች ። አዲሶቹ ፡ ሙሽሮ ች ፡ በሠረገላ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ አርባቶቮ ፡ አመሩ ። ኪሪላ ፡ ፔትሮቪች ፡ እነሱን ፡ ለመቀበል ፡ ቀድሞ ፡ ሄዶ ፡ ነበር ። ል ዑሉ ፡ ከወጣቷ ፡ ሚስቱ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ብቻውን ፡ በሠረገ ላ ፡ ሲሄድ ፡ በርሷ ፡ ኩርፊያና ፡ ዝምታ ፡ ቅንጣትም ፡ አልተ በሳጨም ፡ ነበር ። በውዳሴ ፡ ከንቱና ፡ ማር ፡ በተቀባ ፡ ቃል ፡ አልነተረካትም ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አስር ፡ ቬርስታ ፡ ያህል ፡ ተጓዙ ፤ ፈረሶቹም ፡ በእባጣ ፡ ጐርባጣው ፡ የገጠር ፡ መን ገድ ፡ ላይ ፡ ገሠገሡ ፤ ሠረገላው ፡ ከሥሩ ፡ የእንግሊዝ ፡ ሽቦ ፡ የ ደለደለ ፡ በመሆኑ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ አይወዛወዝም ፡ ነበር ። ድንገት ፡ ያባራሪዎች ፡ ጩኸት ፡ ተሰማ ፤ ሠረገላውም ፡ ቆመ ፤ መሣሪያ ፡ የያዙ ፡ ሰዎችም ፡ ከበቡት ። ፊቱን ፡ የተሸፈነ ፡ ሰው ፡ በልዕልቲቱ ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ በር ፡ ከፈተና ፡ እንዲ ህ ፡ አለ ፤

« ነፃ ፡ ነሽ ፤ ውጪ ። »

« ምንድነው ፡ ነገሩ? አንተስ ፡ ማነህ? » ሲል ፡ ልዑሉ ፡ ጮኸ ።

« ዱብሮቭስኪይ ፡ ነው ፡ » አለች ፡ ልዕልቷ ።

ይህን ፡ ጊዜ ፡ ልዑሉ ፡ የመንገድ ፡ ሽጉጡን ፡ ከኪሱ ፡ መዘዘና ፡ ፊቱን ፡ ወደተሸፈነው ፡ ወንበዴ ፡ ተኰሰ ። ልዕልቲቱ ፡ በፍርሃት ፡ ፊቷን ፡ በእጆቿ ፡ ሸፍና ፡ ጮኸች ። ዱብሮቭስኪይ ፡ እትከሻው ፡ ላይ ፡ ቆሰለ ፤ ደሙም ፡ እየፈለቀ ፡ ወረደ ። ልዑሉም ፡ ጊዜ ፡ ሳያባክን ፡ ሌላ ፡ ሽጉጥ ፡ መዘዘ ። ነገር ፡ ግን ፡ ከመተኰሱ ፡ በፊት ፡ የሠረገላው ፡ በር ፡ ብርግድ ፡ ብሎ ፡ ተከፈተ ፤ ኃይለኛ ፡ እጆችም ፡ ጐትተው ፡ አወጡና ፡ ሽጉጡን ፡ ነጠቁት ። በራሱ ፡ ላይም ፡ ጩቤ ፡ መዝዘው ፡ አወዛወዙበት ።

« አትንኩት! » አለ ፡ ድብሮቭስኪይ ። ጨካኝ ፡ ጭፍሮቹም ፡ ዘርዘር ፡ ብለው ፡ ቆሙ ።

« ነፃ ፡ ነሽ ፡ » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ወደጠወለገችው ፡ ልዕልት ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ነገሩን ፡ ቀጠለ ።

« የለም ፤ ጊዜው ፡ ዘግይቷል ፤ አግብቻለሁ ፤ የልዑል ፡ ቬሬይስኪይ ፡ ሚስት ፡ ነኝ ፡ » ስትል ፡ መለሰች ።

« ምን! » አለ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በመጨነቅ ። « የለም ፡ የሱ ፡ ሚስት ፡ አይደለሽም ፤ ያገባሽውም ፡ ተገዶሽ ፡ ነው ፤ ሳትስማሚ ፡ ነው ። »

« ተስማምቻለሁ ፤ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ገብቻለሁ ፡ » ስትል ፡ በቀጥታ ፡ መለሰችለት ። « ልዑሉ ፡ ባሌ ፡ ነው ። እንዲለቁት ፡ ንገራቸው ፤ እኔንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተውኝ ። አላታለልኩህም ። እስከመጨረሻው ፡ ደቂቃ ፡ ድረስ ፡ ጠበቅሁህ ፤ አሁን ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ አልፏል ። ተውን ፡ እንሂድ ። »

ዱብሮቭስኪይ ፡ ቁስሉ ፡ ስላመመውና ፡ አዕምሮው ፡ ስለተበጠበጠ ፡ ቀጥሎ ፡ የተናገረችውን ፡ ቃል ፡ ሊሰማ ፡ አልቻለም ። በሠረገላው ፡ እግር ፡ ሥር ፡ ወደቀ ፤ ጭፍሮቹም ፡ ከበቡት ። እንደምንም ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ተነፈሰና ፡ እፈረሱ ፡ ላይ ፡ ተሸክመው ፡ አወጡት ፤ ሁለቱ ፡ ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ ደገ

ፉት ፤ ሦስተኛው ፡ ልጓሙን ፡ ያዘ ። የልዑሉ ፡ ሠረገላ ፡ እመ ኻከል ፡ መንገድ ፡ እንደቆመና ፡ አሽከሮቹም ፡ እንደታሰሩ ፤ ፈረሶቹም ፡ እንደተፈቱ ፡ ትተዋቸው ፡ ሁሉም ፡ ወደዳር ፡ አፈገፈጉ ። እንዳችም ፡ ነገር ፡ ሳይሰርቁና ፡ የጌታቸውንም ፡ ደም ፡ ለመበቀል ፡ አንድም ፡ ጠብታ ፡ ደም ፡ ሳያፈሱ ፡ ተመል ሰው ፡ ሄዱ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፱ ።

ጥቅጥቅ ፡ ባለው ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኝ ፡ ባንድ ፡ ጠ ባብ ፡ ገላጣ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ከጭቃ ፡ የተሠራ ፡ ካብና ፡ ለምሽ ግ ፡ የተማሰ ፡ ጉድጓድ ፡ አለ ። በዙሪያውም ፡ አያሌ ፡ ድንኳ ኖችና ፡ ከጭቃ ፡ የተሠሩ ፡ ጐጆዎች ፡ ይገኛሉ ።

በጐጆዎቹ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ ግልጥ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ እጅብ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ድስት ፡ ከበው ፡ እራታቸውን ፡ ይበላሉ ። በለበሱት ፡ የተጣጣፈ ፡ ልብስና ፡ በያዙት ፡ መሣ ሪያ ፡ ወንበዴዎች ፡ መሆናቸው ፡ ወዲያው ፡ ይታወቃል ። አ ንድ ፡ ዘበኛ ፡ በአንድ ፡ ትንሽ ፡ መድፍ ፡ አጠገብ ፡ እካቡ ፡ ላ ይ ፡ እግሩን ፡ አጣምሮ ፡ ተቀምጧል ። ዘበኛው ፡ ልብሱን ፡ ይጥፋል ፤ የመርፌ ፡ አያያዙና ፡ አሰፋፉም ፡ ከባለሙያ ፡ ል ብስ ፡ ሰፊ ፡ የሚያስንቅ ፡ ነው ። ልብሱን ፡ ሲጥፍም ፡ ገልመ ጥ ፡ እያለ ፡ አካባቢውን ፡ ይመለከታል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ሰዎቹ ፡ ካንድ ፡ ቀንጫ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየተቀባበሉ ፡ ቢጠጡም ፡ ሁሉም ፡ ያለወትሯቸው ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ነበር ። ከእራት ፡ በኋላም ፡ አጭር ፡ ጸሎት ፡ አድ ርሰው ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየተነሱ ፡ ሄዱ ። ግማሾቹ ፡ ወደ የድንኳናቸው ፤ ግማሾቹ ፡ ደግሞ ፡ ወደጫካው ፡ ውስጥ ፡ ተ

ሰማሩ ። አንዳንዶቹ ፡ ግን ፡ የበሉት ፡ እንዲንሸራሸርላቸው ፡ ጋደም ፡ አሉ ።

ዘበኛውም ፡ ልብሱን ፡ ጥፎ ፡ ሲጨርስ ፡ አራገፈና ፡ ለማድነቅ ፡ ያህል ፡ አየሩ ፡ ላይ ፡ አንጠልጥሎ ፡ ተመለከተው ። ኋላም ፡ መርፌውን ፡ እጅጌው ፡ ላይ ፡ ሰካና ፡ ወደመድፉ ፡ ጠጋ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ አሳዛኝ ፡ የዱሮ ፡ ዜማ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ያዜም ፡ ጀመር ፤

« ማጉረምረምሽ ፡ ይብቃ ፡
አንቺ ፡ ለምለም ፡ ጫካ ፡ አንቺ ፡ የኔ ፡ እናት ፡
ተይኝ ፡ አትከልክይኝ ፡
እንዳሻኝ ፡ ለማሰብ ፡ ስጭኝ ፡ ነፃነት ። »

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከሳር ፡ ጐጆዎቹ ፡ ያንደኛው ፡ በር ፡ ተከፈተ ፤ ነጭ ፡ ቆብ ፡ የደፋችና ፡ ንጹህ ፡ ልብስ ፡ የለበሰች ፡ አሮጊት ፡ ሴትዮ ፡ ብቅ ፡ ብላ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ተናገረች ፤

« ዝም ፡ በል ፡ ስቴፕካ ፤ ጌታችን ፡ እረፍት ፡ ሲያደርግ ፡ ያንተ ፡ መጮኸ ፡ ምን ፡ ይባላል! ሕሊናም ፡ እርኅራኄም ፡ የለህን? »

« ይቅርታ ፡ አድርጊልኝ ፡ የጐሮቭና ። እሺ ፡ ዝም ፡ እላለሁ ። ጌታችንም ፡ ተሽሎት ፡ እንዲነሳ ፡ እረፍት ፡ ያድርግ ፡ » ሲል ፡ ስቴፕካ ፡ መለሰ ።

አሮጊቷ ፡ ሴት ፡ ተመልሳ ፡ ገባች ፤ ስቴፕካም ፡ በካቡ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ መመላለስ ፡ ጀመረ ።

አሮጊቷ ፡ ሴትዮ ፡ ብቅ ፡ ካለችበት ፡ ጐጆ ፡ ውስጥ ፡ የቆሰለው ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በአንድ ፡ የመንገድ ፡ አልጋ ፡ ላይ ፡ እመጋረጃ ፡ ውስጥ ፡ ተጋድሟል ። ባጠገቡ ፡ ባለ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይም ፡ ሽጉጦቹ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ሰይፉም ፡ በራስጌው ፡ ተሰቅሏል ። በወለሉም ፡ ላይ ፡ የሚያማምሩ ፡ ስጋጃዎች ፡ ተነ

ጥፊዋል ፤ ግርግዳውም ፡ በተዋቡ ፡ ያበባ ፡ ምንጣፎች ፡ አጊጧል ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ባለ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ የሴት ፡ የመታጠቢያ ፡ ቤት ፡ ዕቃዎችና ፡ ሰፌ ፡ መስታዋት ፡ አለ ። ዱብሮቭስኪይ ፡ በእጁ ፡ መጽሐፍ ፡ ገልጦ ፡ ይዟል ። ነገር ፡ ግን ፡ ዓይኖቹ ፡ ተከድነዋል ። አሮጊቷ ፡ ሴትዮም ፡ በመጋረጃው ፡ አጥልጋ ፡ ስታይ ፡ ተኝቶ ፡ ይሁን ፡ ወይስ ፡ ሐሳብ ፡ ይዞት ፡ ይሁን ፡ ለማወቅ ፡ አልቻለችም ።

ድንገት ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ አፈፍ ፡ ብሎ ፡ ተነሳ ፤ ከውጭ ፡ በኩልም ፡ የማስጠንቀቂያ ፡ ድምጽ ፡ ሰማ ፤ ስቴፓካም ፡ በመስኮቱ ፡ እራሱን ፡ አስገብቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጮኸ ፤

« ጌታዬ ፡ ቭላዲሚር ፡ አንድሬዬቪች ፡ ሆይ! ይኸ ፡ የሚሰሙት ፡ የኛ ፡ ማስጠንቀቂያ ፡ ነው ፤ እኛን ፡ ፍለጋ ፡ መጥተዋል! »

ዱብሮቭስኪይ ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ዘሎ ፡ ወረደና ፡ መሣሪያውን ፡ ይዞ ፡ ከጐጆው ፡ ውስጥ ፡ ወጣ ። ሲንጫጩ ፡ የነበሩት ፡ ጭፍሮቹ ፡ እሱ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ጸጥ ፡ አሉ ።

« ሁላችሁም ፡ እዚህ ፡ ናችሁን? » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ጠየቀ ።

« ከፋኖዎቹ ፡ በስተቀር ፡ ሁላችንም ፡ እዚህ ፡ ነን ፡ » ሲል ፡ አንደኛው ፡ መለሰ ።

« ወደየቦታችሁ ፡ ተሰማሩ ፡ » ሲል ፡ አዘዛቸው ፤ ሽፍቶቹም ፡ ወደየተመደበላቸው ፡ ቦታ ፡ ሄዱ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ፋኖዎች ፡ እየሮጡ ፡ ወደበሩ ፡ መጡ ፤ ዱብሮቭስኪይ ፡ ሊቀበላቸው ፡ ሄደ ።

« ምንድነው? » ሲል ፡ ጠየቃቸው ።

« በጫካው ፡ ውስጥ ፡ ወታደሮች ፡ አሉ ፤ ተከበናል ፡ » ሲሉ ፡ መለሱለት ።

ዱብሮቭስኪይ ፡ በሮቹ ፡ እንዲዘጉ ፡ አዘዘና ፡ ትንሿን ፡ መድፍ ፡ ለመፈተሽ ፡ እሱ ፡ እራሱ ፡ ሄደ ። ከጫካው ፡ ውስጥ ፡ የሚሰማው ፡ ድምጽ ፡ እየተቃረበ ፡ ሄደ ። ሽፍቶቹ ፡ ጸጥ ፡ ብ ለው ፡ ጠበቁ ። ድንገት ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ወታደ ሮች ፡ ከጫካው ፡ ውስጥ ፡ ብቅ ፡ አሉና ፡ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ ተመልሰው ፡ በመሸሽ ፡ ለጓደኞቻቸው ፡ የተኩስ ፡ ምልክት ፡ ሰጡ ።

« ለጦርነት ፡ ተዘጋጁ! » ሲል ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ጮኸ ።

ሽፍቶቹም ፡ የመርሯሯጥ ፡ ድምጽ ፡ አሰሙና ፡ ወዲያው ፡ ጸጥ ፡ አሉ ።

ወታደሮች ፡ እየተቃረቡ ፡ ሲመጡ ፡ ተሰማ ፤ የጦር ፡ መሣሪያም ፡ በዛፎቹ ፡ ውስጥ ፡ ሲያብረቀርቅ ፡ ታየ ። አንድ ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ወታደሮች ፡ ከጫካው ፡ ውስጥ ፡ ዘ ለው ፡ ወጡና ፡ በጩኸት ፡ ወደ ፡ ካቡ ፡ አመሩ ። ዱብሮቭ ስኪይ ፡ የመድፉን ፡ ባሩድ ፡ አቀጣጠለና ፡ ተኰሰው ። ከወ ታደሮቹ ፡ አንደኛውን ፡ እራሱን ፡ ገንጥሎ ፡ ጣለው ፤ ሁለት ፡ ሌሎችም ፡ ቆሰሉ ። የቀሩት ፡ ተደናገጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መሪ ፡ መኰንናቸው ፡ ወደፊት ፡ እየገሠገሠ ፡ ስለሄደ ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ጉድጓድ ፡ ተከትለውት ፡ ሮጡ ። ሽፍቶቹም ፡ ጠበንጃና ፡ ሽጉጥ ፡ ተኰሱባቸው ፤ መጥረቢያ ፡ ይዘውም ፡ ወታደሮ ቹ ፡ እካቡ ፡ ላይ ፡ እንዳይወጡ ፡ መከላከል ፡ ጀመሩ ። ወታደ ሮቹ ፡ ግን ፡ ሃያ ፡ ያህል ፡ የቆሰሉ ፡ ሰዎች ፡ እጉድጓዱ ፡ ው ስጥ ፡ ትተው ፡ እካቡ ፡ ላይ ፡ ወጡ ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የጨበጣ ፡ ውጊያ ፡ ተጀመረ ። ወታደሮቹ ፡ አይለው ፡ ካቡን ፡ መጣስ ፡ ሲጀምሩና ፡ ሽፍቶቹም ፡ መልቀቅ ፡ ሲጀምሩ ፡ ዱብሮቭስኪ ይ ፡ ወደ ፡ መኰንኑ ፡ ሄደና ፡ አነጣጥሮ ፡ በሽጉጥ ፡ ደረቱን ፡ አለው ። መኰንኑ ፡ በጀርባው ፡ ወደቀ ፤ ብዙ ፡ ወታደሮችም ፡ ተሸክመውት ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ሸሹ ። የቀሩት ፡ መሪአቸው ፡ ስለጠፋባቸው ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። ሽፍቶቹ ፡ ወታደሮቹ ፡ እን

ደተደናገጡ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ገፍተው ፡ እጉድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ ጨመሯቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቹ ፡ ሽሽት ፡ ጀመሩ ፤ ሽፍቶቹም ፡ እየጮኹ ፡ አባረሯቸው ፤ ድልም ፡ አደረጓቸ ው ። ዱብሮቭስኪይ ፡ ጠላቶቹ ፡ እንደተበታተኑ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ጭፍሮቹን ፡ ሰበሰበና ፡ ምሽጉን ፡ ዘጋ ። የቆሰሉትም ፡ እንዲ ነሱ ፤ ዘበኞችም ፡ እጥፍ ፡ እንዲሆኑና ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከምሽጉ ፡ እንዳይወጣ ፡ አዘዘ ።

ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ የዱብሮቭስኪይ ፡ ጀብዱና ፡ ድ ፍረት ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ በነገሩ ፡ አጥብቀው ፡ እን ዲያስቡበት ፡ አደረጋቸው ። ያለበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ተጠይቆ ፡ በሕይወት ፡ ተይዞ ፡ ወይም ፡ አሬሳው ፡ እንዲመጣ ፡ ወታ ደሮች ፡ ተላኩ ። ከጭፍሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ስለተያዙ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ በመካከላቸው ፡ እንደሌለ ፡ ገለጹ ። ጦርነት ፡ ባደረገ ፡ ማግሥት ፡ ወይም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ጭፍሮቹ ን ፡ ሁሉ ፡ ጠርቶ ፡ ለዘላለሙ ፡ እንደሚለያቸው ፡ ነግሯቸው ፡ ነበር ፤ ኑሮዋቸውንም ፡ እንዲለውጡ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መከ ሯቸው ፡ ነበር ፤

« በእኔ ፡ መሪነት ፡ ለመበልጸግ ፡ ችላችኋል ፤ እያንዳንዳ ችሁ ፡ ወደሩቅ ፡ ግዛት ፡ ሄዳችሁ ፡ የቀረውን ፡ ዕድሜአችሁን ፡ በክብርና ፡ በጌትነት ፡ ለማሳለፍ ፡ ትችላላችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁላችሁም ፡ ወንበዴዎች ፡ ስለሆናችሁ ፡ ይህን ፡ ሙያችሁ ን ፡ ለመተው ፡ አትፈልጉ ፡ ይሆናል ። »

ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ሄደ ። ወዴት ፡ እንደሄደም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አያውቅም ። መጀመ ሪያ ፡ ይህ ፡ ወሬ ፡ ዕውነት ፡ ለመሆኑ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተጠራ ጥረው ፡ ነበር ። ሽፍቶቹ ፡ ጌታቸውን ፡ እጅግ ፡ እንደሚወዱ ት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ስለሚያውቅ ፡ እሱን ፡ ለመሸፈን ፡ ሲሉ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ መስሎ ፡ ነበር ። ኋላ ፡ ግን ፡ የተናገሩት ፡ ዕውነት ፡ ለመሆኑ ፡ እየተገለጸ ፡ ሄደ ። ዝርፊያና ፡ ንጥቂያ ፤

ተኩሰና ፡ ሽብር ፡ እየጠፉ ፡ ሄዱ ። መንገዶቹም ፡ ሰላም ፡ ሆኑ ። ከሌላ ፡ ምንጭ ፡ በተገኘው ፡ ወሬ ፡ ዱብሮቭስኪይ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ እንደሄደ ፡ ተገለጸ ።

## መግለጫ ።

ገጽ ፡ ፯

[1]ይህ ፡ ጥቅስ ፡ የተቀዳው ፡ እ . ኤ . አ . በ ፲፯፻፹፪ ዓ . ም . ከተጻፈው ፡ « ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ » ከተባለው ፡ ኰሜዲ ፡ ሲሆን ፤ ደራሲውም ፡ በአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ ታላቁ ፡ የሩሲያ ፡ የድራማ ፡ ደራሲና ፡ ፑብሊሲስት ፡ ዴኒስ ፡ ፎንቪዚን ፡ ነው ።

ተኩስ ።

ገጽ ፡ ፲፫

[2]የመጀመሪያ ፡ ጥቅስ ፡ ባለቅኔው ፡ የፑሽኪን ፡ ወዳጅ ፡ የቨጌኒይ ፡ ባራቲንስኪይ ፡ ከደረሰው ፡ « የዳንስ ፡ ጨዋታ ፡ » ከተባለው ፡ ግጥም ፡ የተቀዳ ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ ጥቅስ ፡ እ . ኤ . አ . በ ፲፰፻፳፫ ዓ . ም . በቄሣር ፡ ላይ ፡ አድመው ፡ ከተነሱት ፡ አድመኞች ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ የሆነው ፡ አሌክሳንደር ፡ ቤስቱዤቭ-ማርሊንስኪይ ፡ ከጻፈው ፡ « ምሽት ፡ በጦር ፡ ሠፈር ፡ » ከተባለው ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የተቀዳ ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፳፩

[3]« ... ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቡርትሶቭ ፡ ከተባለው ፡ የታወቀ ፡ ጠጪ ፡ ይበልጥ ፡ ጠጣሁ ። ስመ ፡ ጥሩው ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ ዴኒስ ፡ ዳቪዶቭ ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ዘለዓለማዊ ፡ የሆነ ፡ ግጥም ፡ ጽፏል ። »

የፑሽኪን ፡ ወዳጅ ፡ ዴኒስ ፡ ዳቪዶቭ ፡ ባለቅኔና ፡ የጦር ፡ ፑብሊሲስት ፡ ነበር ። እ . ኤ . አ . በ ፲፰፻፲፪ ዓ . ም . የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ክፍል ፡ አርበኞችና ፡ የባላገር ፡ አርበኞች ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ከፈረንሳይ ፡ ወራሪዎች ፡ ጋር ፡ በጅግንነት ፡ ተዋግቷል ።

ቡርትሶቭ ፡ እ . ኤ . አ . በ ፲፰፻፲፪ ዓ . ም . በተደረገው ፡ ታላቅ ፡ የሕዝብ ፡ ጦርነት ፡ ተካፋይ ፡ ነበር ። ዳቪዶቭም ፡ በ ብዙ ፡ ግጥሞቹ ፡ ላይ ፡ ጠቅሶታል ።

<u>ገጽ ፡ ፴፪</u>

[4]አሌክሳንደር ፡ ኢፕሲላንቲ — የሩሲያ ፡ የጦር ፡ ሠራ ዊት ፡ ጀኔራል ፡ ነበር ፤ እ . ኤ . አ . በ ፲፰፻፳ ዓ . ም . ከቱርክ ፡ ወራሪዎች ፡ ግሪክን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ የተቋቋመው ፡ ምሥጢ ራዊ ፡ የኤቴሪስቶች ፡ የሬቮሉሺን ፡ ማኅበር ፡ መሪ ፡ ሆነ ። እ . ኤ . አ . ሰኔ ፡ ፳፱ ቀን ፡ ፲፰፻፳፩ ዓ . ም . በስኩሊያኒ ፡ ከተማ ፡ አጠገብ ፡ በፕሩት ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ በበለጠ ፡ የቱርክ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ የኤቴሪስቶች ፡ ወገን ፡ ተሸነፈ ።

## <u>የበረዶ ፡ ውሽንፍር ።</u>

<u>ገጽ ፡ ፴፫</u>

[5]ይህ ፡ ጥቅስ ፤ ባለቅኔውና ፡ ተርጓሚው ፡ ቫሲሊይ ፡ ዡ ኮቭስኪይ ፡ ( እ . ኤ. አ . ከ ፲፯፻፹፫-፲፰፻፶፪ ዓ . ም . ) ከደረ ሰው ፡ « ስቬትላና ፡ » ከተባለው ፡ ግጥም ፡ የተቀዳ ፡ ነው ።

<u>ገጽ ፡ ፴፭</u>

[6]አርቴሚዛ ፡ የካሊካርኖስ ፡ ንጉሥ ፡ የሞሶል ፡ ሚስት ፡ ነበረች ። ባልዋ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አላገባም ፡ ብላ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በመግባት ፡ « ሞሶሊኤም ፡ » የተባለ ፡ ሐውልት ፡ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ አቆመችለት ።

## ገጽ ፡ ፵፮

[7]Vive Henri-Quatre— ሻርል ፡ ኰሊየ ፡ የተባለ ፡ የፈረንሳይ ፡ ደራሲ ፡ እ . ኤ . አ . በ ፲፯፻፷፩ ዓ . ም . ከጻፈው ፡ « አንሪ ፡ አራተኛው ፡ ወደ ፡ አደን ፡ ሲወጣ ፡ » ከተባለው ፡ ኰሜዲ ፡ የተቀዳ ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

[8]« … ከ« ላ-ዠኰንድ ፡ » የተቀዳ ፡ የኦፔራ ፡ ዜማ … » — ኒኰሎ ፡ ከደረሰው ፡ « ዠኰንድ ፡ ወይም ፡ አስቂኝ ፡ ሁኔታዎች ፡ ፈላጊ ፡ » ከተባለው ፡ የኰሚክ ፡ ኦፔራ ፡ የተቀዳ ፡ የዜማ ፡ ጥቅስ ፡ ሲሆን ፤ ኦፔራው ፡ እ . ኤ . አ . በ ፲፰፻፲፬ ዓ . ም . የሩሲያ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ በፓሪስ ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ የተወደደ ፡ ነበር ።

[9]« … ሻሻቸውን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወረወሩ ። » — የአሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ድራማ ፡ ደራሲና ፡ ዲፕሎማት ፡ አሌክሳንደር ፡ ግሪቦየዶቭ ፡ ከደረሰው ፡ « ብልህ ፡ መሆን ፡ ያመጣል ፡ ሐዘን ፡ » ከተባለው ፡ ኰሜዲ ፡ የተቀዳ ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

# የሬሳ ፡ ሣጥን ፡ ሠሪ ።

## ገጽ ፡ ፶፬

[10]የአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ የሩሲያ ፡ ባለቅኔ ፡ ጋቭሪላ ፡ ዴርዣቪን ፡ ከደረሰው ፡ « ፏፏቴ ፡ » ከተባለው ፡ ግጥም ፡ የተቀዳ ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

## ገጽ ፡ ፶፭

[11]« … ሼክስፒርና ፡ ሰር ፡ ወልተር ፡ ስኰት ፡ በአዕምሮአችን ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሜትን ፡ ለማሳደር ፡ ሲሉ ፡ መቃብር ፡ ቆፋሪዎችን ፡ በገራገርና ፡ በቀልደኛ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ ያቀርቡል

ናል ። » — ቹሽኪን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የተናገረው ፡ ሸክስፒር ፡ በጻፈው ፡ በ « ሐምሌት ፡ » ና ፡ ሰር ፡ ወልተር ፡ ስኮት ፡ በጻ ፈው ፡ « የላሜርሙር ፡ እጮኛ ፡ » በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የመቃብር ፡ ቆፋሪዎች ፡ ምስል ፡ በማ ሰብ ፡ ነው ፡ ( እ . ኤ . አ . ፲፰፻፲፱ ዓ. ም.) ።

ገጽ ፡ ፶፰

[12]« … የፖጐሬልስኪይ ፡ ፖስተኛ ፡ ሳያቋርጥ ፡ በታማኝነ ት ፡ ሥራውን ፡ ይፈጽም ፡ ነበር ። » — የአስራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሩሲያ ፡ ደራሲ ፡ ፖጐሬልስኪይ ፡ ከደረሰው ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ በታማኝነት ፡ የሚያገለ ግል ፡ አንድ ፡ ፖስተኛ ።

የማመላለሻ ፡ ጣቢያ ፡ ሹም ።

ገጽ ፡ ፰፮

[13]ይህ ፡ ጥቅስ ፡ የተቀዳው ፡ የአስራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሩሲያ ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ ፒዮትር ፡ ቪያዜምስኪይ ፡ ከደረ ሰው ፡ « የማመላለሻ ፡ ጣቢያ ፡ » ከተባለው ፡ ግጥም ፡ ነው ።

የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ አማካሪ ፡ ከሁሉ ፡ ዝቅተኛ ፡ የ ሆነ ፡ የሲቪል ፡ ማዕርግ ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፻፫

[14]« … ድሚትሪየቭ ፡ በጻፈው ፡ ግጥም ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገ ኘው ፡ እንደ ፡ ቴሬንቲች ፡ … » — ቴሬንቲች ፤ የአስራ ፡ ስ ምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሩሲያ ፡ የተረት ፡ ደራሲ ፡ ኢ ቫን ፡ ድሚትሪየቭ ፡ በደረሰው ፡ « የሰው ፡ ምስል ፡ » በተባለ ው ፡ ግጥም ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ ገባር ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፹፯

[15]ያስራስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሩሲያ ፡ ደራሲ ፡ ኢ. ፖሊት ፡ ቦግዳኖቪች ፡ ከደረሰው ፡ « ፍቅሬ ፡ » ከተባለው ፡ ግጥም ፡ የተቀዳ ፡ ጥቅስ ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፹፰

[16]« ... ነገር ፡ ግን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዘዬ ፡ ለመስኰብ ፡ ማሽላ ፡ አይስማማውም ፡ » — የሩሲያ ፡ ደራሲ ፡ አሌክሳንደር ፡ ሻኾቭስኮይ ፡ ከደረሰው ፡ « ውስጠ ፡ ወይራ ፡ ቅኔ ፡ » ከተባለው ፡ ግጥም ፡ የተቀዳ ፡ ነው ፡( እ . ኤ . አ . ከ ፲፯፻፵፯-፲፰፻፴፫ ዓ . ም . ) ።

ገጽ ፡ ፹፱

[17]« ... አሌክሴይ ፡ ለድንገትኛ ፡ ሁናቴ ፡ ዝግጁ ፡ ሆኖ ፡ ለመገኘት ፡ እሪዝ ፡ አበቀለና ... » — በዚያን ፡ ዘመን ፡ ወታደር ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ እሪዝ ፡ ማብቀል ፡ ነበረበት ።

ገጽ ፡ ፺፩

[18]ዣን ፡ ፖል — የጀርመን ፡ ደራሲ ፡ የዮሐን ፡ ፓውል ፡ ሪኽተር ፡ የድብቅ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ( እ . ኤ . አ . ከ ፲፯፻፶፭-፲፰፻፲፯ ዓ. ም. ) ።

ገጽ ፡ ፺፪

[19]« ... በስድስት ፡ በስድስት ፡ ወርም ፡ « ፖሚላ ፡ » የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከመጨረሻ ፡ ታነባለች ። »

« ፖሚላ ፡ » የእንግሊዝ ፡ ደራሲ ፡ ሪቻርድሶን ፡ የደረሰው ፡ ታሪክ ፡ ነው ፡ ( እ . ኤ . አ . በ ፲፯፻፵፩ ዓ . ም . ) ።

ገጽ ፡ ፪፻

[20]ማዳም ፡ ደ ፡ ፖምፓዱር ፡ የሉዊ ፡ አስራምስተኛው ፡ ወዳጅ ፡ ነበረች ።

ገጽ ፡ ፪፲፩

[21]የላንካስተር ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ በእንግሊዛዊው ፡ መምህር ፡ በላንካስተር ፡ ተመርምሮ ፡ የወጣ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ የማስተማር ፡ ዘዴ ፡ ሲሆን ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ ይሠራበት ፡ ነበር ፡ ( እ . ኤ . አ . ከ ፲፯፻፸፰-፲፰፻፴፰ ዓ . ም . ) ።

[22]« ናታሊያ ፤ የባላባቱ ፡ ልጅ ፡ » የሩሲያ ፡ ደራሲ ፡ ኒኮላይ ፡ ካራምዚን ፡ የደረሰው ፡ ታሪክ ፡ ነው ፡ ( እ . ኤ . አ . ፲፯፻፺፪ ዓ . ም . ) ።

ገጽ ፡ ፪፲፬

[23]« ... ታራስ ፡ ስኮቲኒን ፡ እንዳለው ... » — ታራስ ፡ ስኮቲኒን ፡ የአሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የሩሲያ ፡ የድራማ ፡ ደራሲ ፡ ፎንቪዚን ፡ ከደረሰው ፡ « ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ » የተባለው ፡ ኮሜዲ ፡ ዓይነተኛ ፡ ሰው ፡ ነው ።

## ዱብሮቭስኪይ ።

**ገጽ ፡ ፻፵፩**

[24]« በድግሥ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡
አስከሬን ፡ ተጋድሟል ። »
ዴርዣቪን ፡ የተባለ ፡ በአስራስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ ሥመ ፡ ጥሩ ፡ የሩሲያ ፡ ባለቅኔ ፡ ከደረሰው ፡ « ለልዑል ፡ ሜሼርስኪ ፡ መታሰቢያ ፡ » ከተባለው ፡ ግጥም ፡ የተቀዳ ፡ ቃል ።

**ገጽ ፡ ፻፵፪**

[25]« የድል ፡ ነጐድጓድ ፡ ይሰማ ፡ » የአንድ ፡ መዝሙር ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ።

**ገጽ ፡ ፻፶፫**

[26]« … በቱርክ ፡ ዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ » እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፰፻፸፯-፲፰፻፸፰ ዓ ፡ ም ፡ በቱርኮችና ፡ በመስኮቦች ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ ጦርነት ።

**ገጽ ፡ ፻፸፯**

[27]« … ቁርጥ ፡ ኩልኔቭን ፡ የሚመስል ፡ ሰው ፡ » ኩልኔቭ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ከ ፲፰፻፰-፲፰፻፱ ዓ ፡ ም ፡ በስዊድንና ፡ በሩሲያ ፡ መካከል ፡ በተደረገ ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ድል ፡ ያስገኘ ፡ የመስኮብ ፡ ጄኔራል ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፪፹፱

[28]ራድክሊፍ ( ከ ፲፯፻፷፬-፲፰፻፳፫ ) የሚያስፈራሩ ፡ ታሪኮች ፡ የምትጽፍ ፡ እንግሊዛዊት ፡ ደራሲ ፡ ነበረች ።

ገጽ ፡ ፫፻፮

[29]« ሪናልዶ-ሪናልዲኒ ፡ » የጀርመን ፡ ደራሲ ፡ ቡልፒውስ ፡ በደረሰው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ዋናውን ፡ ክፍል ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ጨዋ ፡ ሽፍታ ፡ ነው ።

ገጽ ፡ ፫፻፱

[30]«ኰንራድ ፡ » ታላቁ ፡ የፖላንድ ፡ ባለ ፡ ቅኔ ፡ አዳም ፡ ሚትስኬቪች ፡ ከደረሰው ፡ « ኰንራድ ፡ ቫሌንሮድ ፡ » የተባለው ፡ ጽሑፍ ፡ ጀግና ፡ ነው ። የዚህ ፡ ጀግና ፡ ሰው ፡ አፍቃሪ ፡ በሐሳብ ፡ በመመሰጧ ፡ ጽጌረዳ ፡ ስትነድፍ ፡ በአረንጓዴ ፡ ሐር ፡ ጽጌረዳውን ፡ ነድፋ ፡ ቅጠሎቹን ፡ በቀይ ፡ ሐር ፡ ሰፋች ።

## አንባቢ ፡ ሆይ!

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ ስለዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ትርጉም ፥ ዝግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡ አስተያየትና ፡ አሳባችሁን ፡ ብትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል ።

አድራሻው ፤ 17, Zubovsky Boulevard, Moscow, U.S.S.R.